አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

# ትምህርተ፡ አበ፡ ነፍስ።



« እግዚአብሔር ፡ እረኛዬ ፡ ነው ፡ የሚያሳጣኝም ፡ የለም ፡ በለመለመ ፡ መስክ ፡
ያሳድረኛል ። ከዕረፍትም ፡ ውሃ ፡ ዘንድ ፡ ይመራኛል » ።

(መዝ/ ፳፪፡፩—፪)

እኔ ፡ ነኝ ፡ ቸር ፡ ጠባቂ።
ቸር ፡ ጠባቂ ፡ ራሱን ፡ ስለ ፡
በጎቹ ፡ ይሰውጣል ።
(ዮሐ/ ፲ ፡ ፲፩) ፡

ከአባ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ወርቅነህ ።

www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ፡ አበ፡ ነፍስ።



«እግዚአብሔር ፡ እረኛዬ ፡ ነው ፡ የሚያሳጣኝም ፤ የለም ፡ በለመለመ ፡ መስክ ፡ ያሳድረኛል ። ከዕረፍትም ፡ ውሃ ፡ ዘንድ ፡ ይመራኛል » ።

(መዝ/ ፳፫፡፩—፪)

እኔ ፡ ነኝ ፡ ቸር ፡ ጠባቂ።
ቸር ፡ ጠባቂ ፡ ራሱን ፡ ስለ ፡
በጎቹ ፡ ይለውጣል ።
(ዮሐ/ ፲ ፡ ፲፩) ፡

ከአባ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ወርቅነህ ።

www.ethiopianorthodox.org

ይኸ ፡ ድርሰት ፡
ለማዕርገ ፡ ክህነት ፡ እድገት ፡
ለቤተ፡ ክርስቲያናችን፡ስፋት ፡

ሌት ፡ ከቀን ፡ ለደከሙት ፡ ለግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡
ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ፡

የተሰጠ ልዩ ፡
መታሰቢያ ፡
ነው ።

ያለ ፡ ደራሲው ፡ ፈቃድ ፡
በሙሉም ፡ በከፊልም ፡
ማሳተም ፡ ክልክል ፡
ነው ።

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ በሠላሳ ፡ አንደኛው ፡ ዓመተ ፡ መንግሥት ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ታተመ ።

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።



እግዚአ ፡ በኀይልከ ፡ ይትፌሣሕ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡
ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤ ወብዙኀ ፡ ይትሐሠይ ፡ በአድኀኖትከ ።
(መዝ/ ፳፩ ፡ ፩ )፡

www.ethiopianorthodox.org



ንግሥትነ ፡ ይብሉኪ ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ ደቂቀ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ኵሎሙ፡
ወወርኀ ፡ ግዕዛንኪ ፡ ያብዕሉ ።

www.ethiopianorthodox.org




የአንበሳው ፡ ልጅ ፡ አንበሳ ፡
ልዑል ፡ መርዕድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡
የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org



ተውህቦ ፡ መራኁት ፡ ለአቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡
ወፓትርያርክ ፡ ዘኢትዮጵያ ።

www.ethiopianorthodox.org



ደ ራ ሲ ው ፡

አባ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ወርቅነህ ።

www.ethiopianorthodox.org

# ለግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

## ግ ር ማ ዊ ፡ ሆ ይ ፤

ስለ ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ አርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡ ልማትና ፡ ስፋት ፡ ድርጅትም ፡ ያሰቡ ፤ የሠሩና ፡ የደከሙ ፡ ነገሥታት ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ፤ ስለዚህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በማኅበር ፡ ጸሎት ፡ ያለማቋረጥ ፡ ስታስታውሳቸው ፤ ጸሎት ፡ ስታደርግላቸው ፡ ትኖራለች ። እነዚህ፡ብዙ ፡ ነገሥታት ፡ ይድከሙ ፡ እንጂ ፤ ዋናውን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሸክም ፡ ሊያቀሉ ፤ ሕጉን ፡ ሊያሻሽሉ ፡ አልቻሉም ፤ ማለት ፡ አረፍተ ፡ ዘመን ፡ ገታቸው ፤ ዕድልም ፡ አልተሰጣቸውም ፡ ነበር። ፩ኛ/ ኢትዮጵያ፡ ሰፊ ፡ ሀገር ፡ ስትሆን ፤ በየጊዜው ፡ የሚወጣው ፡ ጳጳስ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፤ ያውም ፡ ከሰው ፡ አገር ፡ መጥቶ ፤ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ፈጅቶ ፤ ቋንቋውንና ፡ የሀገሯን፡ ባህል ፡ ባለማወቁ ፡ ከምእመናን ፡ አንድነት፡ርቆ ፤ ከብዙ፡መንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ ተለይቶ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። ፪ኛ/ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ራሷን ፡ ባለመቻሏ ፤ ለአስተዳደሯም፡ ልክ፡ መልክ፡ ባለመኖሩ፡ የተወሰነ፡ ሕግ ፡ የወጣ ፡ ደንብ ፡ አልነበራትም ፤ እንዲሁ ፡ በልማድ ፡ እየተሠራ ፡ የጠፋው ፡ ከልማቱ ፡ የበለጠ ፡ ነው ። በየጊዜው ፡ የተነሡ ፡ ነገሥታት ፡ ለዚህ፡መሻሻያ ፡ ያሰቡና ፡ የደከሙ ፡ ብዙ ፡ ሲሆኑ ፤ ከላይ ፡ እንደተናገርኩት ፡ እንዲሁ ፡ በናፍቆትና ፡ በምኞት ፡ ብቻ ፡ ጊዜያቸውን ፡ አሳለፉ ፤ «ብዙዎች፡ ነቢያት፡ጻድቃን ፡ እላንት ፡ ያያችሁትን ፡ ያዩ ፡ ዘንድ ፡ ተመኙ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አላዩም ፤ እላንትም ፡ የሰማችሁትን ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ፡ተመኙ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልሰሙም ፡ » (ማቴ/ ፲፫ ፡ ፲፯ ) ፤ ብሎ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፤ የማሰብም ፤ የመሥራትም ፤ የመፈጸምም ፡ ዕድል፡ ለግርማዊ

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ነትዎ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ተሰጠ ፡ ተመኝተው ፡ ያልጀመሩት ፤ ጀምረውም ፡ ያልፈጸሙት ፡ አንድም ፡ ሥራ ፡ አይገኝም ።

ከላይ ፡ እንደተናገርኩት ፡ በባዕድ ፡ መሪነት ፡ ከመገኘቱት፡ የበለጠ፡ ሸክም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ አልነበረባትም ፤ ይህንም፡ ለማስወገድ፡ ዐሰበ ፡ ሥሩም ፡ ከፍጻሜም ፡ አደረሱ ፡ ማለት ፡ ከጳጳስነት ፡ እስከ፡ ሊቀ፡ ጳጳስነትና ፡ እስከ ፡ ፓትሪያርክነት ፡ አድርሰው ፡ ራሷን ፡ አስቻሉ ። ይህ ፡ የሥራዎ ፡ መጀመሪያ ፡ አድርገው ፡ ያሰቡለትና ፡ የደከሙለት ፤ መልካም ፡ ውጤትም ፡ ያስገኙለት ፡ ማዕርገ ፡ ክህነት ፡ መልክ ፡ አግኝቶ ፤ እግር ፡ አውጥቶ፡በፈቃዱ ፡ እንዲራመድ ፡ መሪ ፡ ትሆነው ፡ ዘንድ፡ "ትም ህርተ ፡ አበ ፡ ነፍስ ፡" ብዬ ፡ የሰየምኳት ፡ መጽሐፍ ፡ ስለ ፡ ማዕርገ ፡ ክህነት ፡ ለደከሙት ፡ ድካምዎ ፡ መታሰቢያ ፡ እንድትሆን ፡ ሳበረክት ፡ ከዙፋንዎ ፡ ሥር ፡ ወድቄ ፡ ነው ።

ትሑት ፡ አገልጋይዎ ፡

አባ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ወርቅነህ ።

# መቅድም ።

ሀይማኖት ፡ መያዝና ፡ ሀይማኖተኛ ፡ መሆን ፡ ለሰው ፡ ከልቡናው ፡ የተተከለ ፤ ለዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፤ በጥንተ ፡ ፍጥረት ፡ የተሰጠ ፡ ታላቅ ፡ ሀብት ፡ ነው ። ይህንም ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ተባብረው፡ደግ ፈውታል ፤(የሐ/ ሥራ፡፲፯፡፳፬—፳፰፡ ሮሜ፡፩፡፲፱—፳)። ብዙዎችም ፡ ዓለ ማውያን ፡ ሊቃውንት ፡ ተስማምተው ፡ አጽድቀውታል፤ለምሳሌ፡ካንድ ፡ የተባለ ፡ ጀርመናዊ ፡ ፈላስፋ ፡ « ውሳጣዊ ፡ አእምሮዬን ፡ በማድነቅና ፡ በማክበር ፡ ኹለት ፡ ነገሮች ፡ ይሞሉታል ፤ እነዚህም፡ ከከብን፡የተሞላው፡ ሰማይና ፡ በልቡናዬ ፡ ያለው ፡ ሕግ ፡ ጠባዕያዊ ፡ ናቸው ፡ » ብሎ ፡ አስረ ድቷል።ሀይማኖት ፡ ወይም ፡ መንፈሳዊነት ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ወይም ፡ ብቸኝነት ፡ ወስኖ ፡ የሚኖር ፡ ታላቅ ፡ ልጓም ፡ ነው ፤ እን ዲሁም ፡ ሰውን ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ሰውሮ ፡ ከመጥፎም፡ መንገድ፡ገትቶ፡ወደ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፤ ወደ ፡ ደግነት ፡ ማዕርግ ፡ የሚያደርስ ፡ ሐብል ፡ ነው ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ሀይማኖ ትን ፡ ያከብራል ፤ መንፈሳዊነትን ፡ አጥብቆ ፡ ይይዛል ። የመንግሥት፡ባለ ሥልጣኖች፡ ኹሉ ፡ የሃይማኖት ፡ መሪ ፡ እየሆኑ ፡ የጠበቁበት ፡ ጊዜ፡ብዙ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ የይሀማኖት ፡ ኀይል ፡ ከሰው ፡ ሠራሽ ፡ ሕግና፡ ከመን ግሥት ፡ ሥልጣን ፡ የበረታ ፡ ነውና፤ ፍጹም ፡ ላልሆነና ፡ እውነተኝነቱ ፡ ላልተረዳ ፡ ሀይማኖት ፡ ብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ አምነውበት ፡ ብዙም ፡ የተ ሥራ ፡ ሠርተውበት ፡ ከኖሩ ፡ ክርስቶስ ፡ የሠራው ፤ እውነተኝነቱ ፡ የተ መሰከረለት ፡ የክርስቲያን ፡ ሀይማኖትማ ፡ ምንኛ ፡ የበለጠ ፡ የተከበረ ፡ ይሆን ? እውነተኛነቱ ፡ የተረዳ ፡ ሀይማኖት ፡ የክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ ሳያቋ ርጥ ፡ የሚገለጥበት ፡ የክርስትና ፡ ሀይማኖት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ቅዱስ ፡ ጳው ሎስ ፡ አስረድቷል፤(፪፡ ቆሮ፡ ፭—፲፬)።ነገር ፡ ግን ፡የክርስትና ፡ ሀይማኖት፡ ከታሰበው ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ ለሕዝብም ፡ የተረዳ ፡ የድኅነት ፡ ጎዳና ፡ ለመሆን ፡ የታሰበ ፡ እንደኾነ ፤ በተለዩ፡ ሰዎች ፡ ከእግዚአብሔር፡ ወይም፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለዚህ ፡ ነገር ፡ በተመረጡ ፡ መሰበክና ፡ መነገር ፡ ያስፈልጋል ፤ ምክንያቱም ፡ ማመን ፡ ማምለክም ፡ የወል፡ ሲሆን ፤ ለዚህ፡ እምነትና ፡ አምልኮት ፡ መሪ ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በማንኛውም ፡ ሀይማ

www.ethiopianorthodox.org

ኖት ፤ መቼውንም ፡ ጊዜ ፡ በኑሮዋቸውና ፡ በሥራቸው ፡ በጠቅላላውም ፡
ስሜታቸው ፡ ኹሉ ፡ ከሌላው ፡ ሰው ፡ ተለይተው ፡ የታወቁ ፡ ናቸው ።
በክርስትና ፡ ሀይማኖት ፡ ለዚህ ፡ አገልግሎት፡ የተመረጡ ፡ ካህናት፡
ተብለው ፡ የሚጠሩ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እንደራሴዎች ፡ የሐዋርያት ፡ተከ
ታዮች ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ ሰዎች ፡ የሚሠሩት ፡ ሰው ፡ ኹሉ፡ በክርስ
ቶስ ፡ አምኖ ፡ እንዲጠመቅ ፡ መምከር ፤ ማስተማርና ፡ ክርስቶስ፡ በደሙ፡
የገዛቸውን ፡ የሰዎችን ፡ ነፍስ ፡ ተግቶ ፡ ነቅቶ ፡ በልዩ፡ ጥበቃ፡መጠበቅ፡
ነው ፤ «አሁንም ፡ ለራሳችሁ ፡ ተጠንቀቁ ፡ ለመንጋውም ፡ ኹሉ ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ጠባቆች ፡ አድርጎ ፡ የሾማችሁ ፡ የእግዚአብ
ሔርን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትጠብቁ ፡ ዘንድ፡እርሱ ፡ በደሙ ፡ የዋጃትን»
(የሐ/ሥራ፡ ፳፡ ፳፰)፡ብሎ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዳስተማረ ። የእነዚህም፡
ሰዎች ፡ አመራረጥና ፡ ተልእኮ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሲሆን ፤ ሥራቸው ፡ ደግሞ ፡
የበለጠ ፡ ከባድ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ ያመኑትን ፡ ማጽናት ፡ በመንፈ
ሳዊ ፡ ጐዳናም ፡ መምራት ፤ እንዲሁም፡በምግባር ፡ በሀይማኖት፡ ጸንተው፡
እንዲኖሩ ፡ ቀን ፡ ከሌት ፡ መሥራትና ፡ ከሀይማኖት ፡ ውጭ ፡ የሆኑትን ፡
ደግሞ ፡ ወደ ፡ ክርስትና ፡ ሀይማኖት ፡ መግባት ፡ የሚችሉበትን፡ መንገድ፡
ጥርጊያ ፡ አድርጎ ፡ ማሳየት ፤ የሕዝብም ፡ ጠቅላላ፡ ኑሮ ፡ ሰላምንና ፡ ፍቅር፡
አንድነትን ፡ የተመላ ፡ ኹኖ ፡ እንዲኖር ፤ በምድር ፡ ያለች ፡ የእግዚአ
ብሔር ፡ መንግሥት ፡ እንድትስፋ ፤ ምእመናን ፡ እንዲበዙ ፡ መድከም ፡
የካህናትን ፡ ኀላፊነት ፡ የሚጠይቅ ፡ ነው ። የመንፈሳውያን ፡ መሪዎች ፡
ሥራቸው ፡ ብዙ ፡ ኀላፊነታቸው ፡ ከባድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ወይም ፡ ከቤተ ፡ ክርስታያን ፡ ጥሪና ፡ ስጦታም ፡ ሊኖራቸው ፡ ይገባል ፤
ሥራውንም ፡ በፍጹም ፡ ልቡናቸው ፡ የወደዱት ፡ ራሳቸውን ፡ ንጹሕ ፡
መሥዋዕት ፡ አድርገው ፡ ለመስጠት ፡ ፈቃደኛ ፡ መሆን ፡ ያስፈልጋቸ
ዋል ። ማንኛውም ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ጥበብ ፡ ከታሰበው ፡ ግብ ፡ ለመድ
ረስና ፡ መልካም ፡ ውጤትን ፡ እንዲያገኝ ፡ የታሰበ ፡ እንደ፡ ኾነ ፤ ለዚህ ፡
የሚመደቡት ፡ ሰዎች ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ እንዲኖራቸው ፤ ሥራውንም ፡
በፍጹም ፡ ልቡናቸው ፡ እንዲያፈቅሩት ፡ ወደው ፡ ለምደው ፡ ራሳቸውን፡
መሥዋዕት ፡ ለማድረግ ፡ ቈርጠው ፡ መግባት ፡ አለባቸው ።

ለሌላው ፡ ሥጋዊ ፡ አስተዳደር ፤ ሰው ፡ በዕድሜው ፤ በስጦታው ፤
በጠባዩና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ የሚመረጥ ፡ ከሆነ ፡ ለሰው ፡ የሥጋና ፡



የነፍስ ፡ ጠባቂ ፤ ለበጎ ፡ ነገርም ፡ አብነት፡ ሁነው ፡ መንፈሳዊውን፡ነገር፡
እንዲፈጽሙ ፡ ለሚታሰቡት ፡ ሰዎችማ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ጥንቃ
ቄና ፡ ደንበኛ ፡ ምርጫ ፡ ሊኖር ፡ ይገባል ፤ በተለየም ፡ ለዘመናችን ፡ ሕገ
ብና ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ተስማሚ ፡ የኾኑ ፡ በምግባር ፤ ያጌጡ ፡ ለበጎ ፡
ነገር ፡ አብነት ፡ የሚሆኑ ፤ ራሳቸውን ፡ መሥዋዕት ፡ ለማድረግ፡ የቈረጡ፡
ካህናትን፡ መምረጥ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ተቀዳሚ ፡ ተግባሯ ፡ ነው ፤ ምክን
ያቱም ፡ ምንም፡ ሀይማኖት ፡ በሰው ፡ ልቡና ፡ የተተከለ ፤ ሊጠፋም ፡ የማ
ይችል ፡ ከጥንት ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ጊዜ ፡ የተሰጠ ፤ መቼውንም ፡ ጊዜ ፡
በሰው ፡ ባሕርይ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ከሰው ፡ ስሜት ፡ ፈጽሞ ፡ ሊወጣ ፡
የማይችል ፡ ቢሆን ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ሥጋዊ ፡ ፈቃድ ፡ የሠለጠነበት ፡
ሕዝብ፡ከእግዚአብሔር ፡ የራቀበት ፤ የመንፈሳዊ ፡ ተግባር ፡ የተጓደለበት፤
ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ የተሰነካከለበት ፤ በጠቅላላም ፡ የክርስትና ፡ ዓላማ፡ የተ
ለወጠበት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ይህን ፡ ወደ ፡ ቀደመ ፡ ዓላማው ፡ ለመመለስ ፡
ብዙ ፡ ድካምና ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ስለሚጠይቅ ፡ ለዚህ ፡ የሚበቁና ፡ ራሳቸ
ውን ፡ መሥዋዕት ፡ አድርገው ፡ የሚሰጡ፡ካህናት ፡ የግድ ፡ ያስፈልጋል።
ይህንም ፡ ለመሥራት ፡ ስብከት ፡ ብቻ ፡ ስለማይጠቅም ፤ የሕዝብ መን
ፈስ ፡ ተባባሪ ፡ ኾኖ ፡ ለበጎ፡ነገር ፡ አብነት ፡ የሚኾንበትን ፡ ነገር፡በሥራ ፡
ለመግለጥና ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ሕቅታ ፡ ራስን ፡ አሳልፎ ፡ እስከ ፡
መስጠት ፡ ያህል ፡ የቈረጡ ፡ መሆናቸውን ፡ እየገለጡ ፡ ማስተማርና፡ማሳ
የት ፡ ያስፈልጋል ።

የዘመኑ ፡ ሊቃውንት ፡ በሥጋዊ ፡ ጥበባቸው ፡ ጸንተው ፡ ከመሥራ
ታቸው ፡ የተነሣ ፤ ስለ፡ዓለም ፡ ሥልጣኔና ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ኑሮ ፡ መሻ
ሻል ፡ መልካም ፡ ውጤትን ፡ አስገኝተው ፤ የራቀውን ፡ አቅርበውና፡የረቀ
ቀውን ፡ አጕልተው ፡ ለአዲሱ ፡ ዓለም ፡ አንድ ፡ መልክ ፡ ሲያወጡለት፤
መንፈሳውያን ፡ ሊቃውንትማ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ሥራቸው ፡ ጸንተው፡የዓ
ለም ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥልጣኔ ፤ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ መሻሻል ፤ የእግዚአብ
ሔር ፡ መንግሥት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንድትስፋፋ ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ በፍቅ
ርና ፡ በሀይማኖት ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ በጠቅላላም ፡ ዓለም ፡ በመንፈሳዊ፡
መልክ ፡ አንድ ፡ ቅርጽ ፡ እንዲኖራት ፡ ማድረግ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡
እንዴት ፡ ይሳናቸዋል ? ስለዚህ ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምሮ ፡ በሥራው፡ የታወቀ፤
ከሕዝቡ፡ ጋራ፡አንድነትና ፡ ኅብረት ፡ ያለው ፤ ታሪኩ ፡ በዓለም ፡ ጐልቶ፡



www.ethiopianorthodox.org

የሚታየው ፡ የሀገሬ ፡ ካህን ፤ ሽማግሌው ፡ በማንበብ ፤ ወጣቱም ፡ በመማር ፡ ኀላፊነታችን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐውቀን ፤ ከዓለም ፡ ትእዛብት ፡ ሳንወድቅ ፡ ከክርስቶስ ፡ በታች ፡ ራሳችንን ፡ ለሀገራችን ፡ ለወገናችን ፡ መሥዋዕት ፡ አድርገን ፡ እንድንሰጥ ፡ መሪ ፡ ትሆነን ፡ ዘንድ ፤ በተለይም ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለሚደክሙላት ፡ ማዕርገ ፡ ክህነት ፡ መታሰቢያና ፡ መምሪያ ፡ እንድትሆን ፡ «ትምህርተ ፡ አበ ፡ ነፍስ » ብዬ ፡ የሰየምኋትን ፡ ይህችን ፡ ጽሑፍ ፡ ሳበረክት ፡ አባቶች ፡ የማያውቁት፤ለኔ፡ የተገለጠ ፡ ሳይሆን ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ተናገርኩት ፡ ትንሽ ፡ ትልቅ፡ ሳንል፡ ኀይላችንን ፡ አንድ ፡ አድርገን ፡ ለመነሣት ፡ ኹላችንም ፡ እንደ፡ ስጦታችንና ፡ እንደ ፡ ችሎታችን ፡ መሥራት ፡ ግዴታ ፡ መሆኑን ፡ ለመግለጥ ፡ ብቻ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ እንዲሁም ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ወደ፡ልዩ፡ ልዩ፡ ጥበባት ፡ ወጣቶችን ፡ ማስማራታቸው ፡ እንደየስጦታቸው ፡ ሀገርንና ፡ ወገንን ፡ የሚጠቅመውን ፡ ለማበርከት ፡ እንደ፡ኾነ ፡ በመገንዘብ፡ጠቃሚ፡ መስሎ ፡ ስለ ፡ ታየኝ ፤ ለመጻፍ ፡ መንፈሴ ፡ አነሣሣኝ ። ይህንም፡ ጽሑፍ ፡ ሳቀርብ ፡ ስሕተቱን ፡ አርማችሁ ፡ ጕድለቱን ፡ መልታችሁ ፡ በቀና ፡ መንፈስ ፡ እንድታነቡልኝ ፡ አሳስባለሁ ።

የካህን ፡ ሥራው ፡ ከሌላው ፡ ከማንኛውም ፡ ሥራ ፡ የተለየ ፡ ዕጥፍ ፤ ከባድም ፡ ስለ፡ ኾነ ፤ የሚያሰጠውም ፡ ዋጋ ፡ ይህንኑ ፡ ያህል ፡ ነው ፤ ስለ ዚህ ፡ የሠራ ፡ ዋጋውን ፡ ያልሠራ ፡ ፍዳውን ፡ በዕጥፍ ፡ ስለሚያገኝ ፡ ተግ ተን ፡ ነቅተን ፡ በመሥራት ፡ ዋጋችንን ፡ እንድናገኝ ፤ የኔም ፡ የናንተም ፡ መልካም፡ምኞትና፡ጸሎት፡ ይሁን።ዘመኑ ፡ እየተሻሻለ፡ በመሄዱ ፡ ዓለም፡ለሰላምም ፡ ኾነ ፡ ለጦርነት ፡ የሚጠቀምባቸው ፡ መሣሪያዎች፡ዘመኑን ፡ ተከትለው ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው ፤ ስለዚህ ፡ ሰዎች ፡ ለዘመናዊ ፡ መሣሪያ፡ መሣሪያውም ፡ ለዘመናውያን ፡ ሰዎች ፡ ተባባሪ ፡ በመሆናቸው ፤ እነሆ ፡ ብዙዎች ፡ እንደየዓላማቸው ፡ ሲፈጽሙ ፡ እናያለን ፤ ለዓለም ፡ የሰላምና ፡ የሕይወት ፡ መሣሪያ ፡ የሆነው ፡ ካህንም ፡ ለዘመናዊ ፡ ሕዝብ ፡ ተስማሚና ፡ ተባባሪ ፡ የኾነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ብዙ ፡ ጥቅምን ፡ ስለሚሰጥ ፤ ዘመናዊው ፡ ካህን ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ኾነና ፡ ምን ፡ መሥራት ፡ እንደሚገባው ፡ በዚሁ ፡ አስረዳለሁ ።

በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ልዩ ፡ ካቢኔ ፡ የመንፈሳዊ ፡ ክፍል ፡ ሹምና ፡ የመንበረ ፡ ጸባዖት ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ገዳም ፡ ተጠባባቂ ፡ አባ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ወርቅነህ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ሰኔ ፡ ፩ ፡ ፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡

## መ ግ ቢ ያ ።

«ትምህርተ ፡ አበ ፡ ነፍስ ፡ » ማለት ፡ የንስሐ ፡ አባት ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ የሚማሩት ፡ ትምህርት ፡ ነው ፤ የጠባቂነት ፡ ትምህርትም ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ፤ ምክንያቱም ፡ የሰው፡ የነፍሱም ፡ የሥጋውም ፡ ጠባቂ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ ካህኑ ፡ ነውና ። በቀድሞ ፡ ዘመን፡የበግ፡ ሀብት፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ በመሆኑ ፤ ደግሞም ፡ የበጎች ፡ ጠባቂዎች ፡ ንቁዎች ፡ የታመኑና ፡ ለበጎቻቸው ፡ የሚያስቡ ፡ ደጋግ ፡ በመሆናቸው ፤ የሥጋዊም ፡ የመንፈሳዊም ፡ መሪዎች ፡ ሲነሡ ፡ ጠባቂዎች ፡ ይሏቸው ፡ ነበር፤ «አንተ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በእስራኤል ፡ ጠባቆች ፡ ላይ ፡ ትንቢት ፡ ተናገር ፤ ለጠባቆችም ፡ እንዲህ ፡ በል ፤ እንዲህ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ እስራኤል ፡ ጠባቆች ፡ ወዮላቸው ፡ ራሳቸውን ፡ ለሚያሳምሩ ፤ ጠባቆች ፡ በጎችን፡ የሚያሰማሩ፡ አይደሉምን ? - -»(ሕዝቅ/ ፴፬፡ ፪—፳፯)፡ እያለ፡ልዑል፡ እግዚአብሔር ፡ ጠባቂዎችን ፡ በሚወቅስበት ፡ ምዕራፍ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ። «እግዚአብሔር ፡ እረኛዬ ፡ ነው ፡ የሚያሳጣኝም ፡ የለም ፤ በለመለመ ፡ መስክ ፡ ያሳድረኛል፡ በዕረፍትም ፡ ውሀ ፡ ዘንድ ፡ ይመራኛል፤» (መዝ/፳፫፡፩—፪)፡ደግሞም ፡ « ኖላዊሆሙ ፡ ለእስራኤል ፡ አጽምዕ - - - » (መዝ/፹ ፡ ፩) ፡ እያለ ፡ ነቢዩ ፡ ዳዊት ፡ ጌታን ፡ እረኛ ፡ ይለዋል ። ይህም ፡ ማለት ፡ እግዚአብሔር ፡ ቸር፡እረኛ ፡ ሕዝቡን ፡ የሚጠብቅ ፡ የሚከባከብ ፡ ወደ ፡ ደግ ፡ ነገር ፡ የሚመራ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህ ፡ የብሉይ ፡ ኪዳን፡መንፈስ ፡ ወደ ፡ ሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ስለ ፡ ተላለፈ ፡ ክርስቶስ ፡ እውነተኛ፡ ጠባቂ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ራሱ ፡ በሰፊው ፡ « እኔ ፡ ነኝ ፡ ቸር ፡ ጠባቂ ፤ ቸር ፡ ጠባቂ ፡ ራሱን ፡ ስለ ፡ በጎቹ ፡ ይለውጣል ፡ - - - » (ዮሐ/ ፲ ፡ ፲—፲፰)፡ እያለ፡መስክሯል ፤ ይህን ፡ የመሰለ ፡ በሐዲስ ፡ ኪዳንና ፡ በሊቃውንት ፡ ጽሑፍ ፡ እናገኛለን ።

እንዲሁም ፡ የቀደሙ ፡ ሠዓሊዎችና ፡ አናጺዎች ፡ ክርስቶስን ፡ እንደ ፡ በግ ፡ ጠባቂ ፡ እያደረጉ ፡ በግ ፡ አሸክመው ፡ ይሥሉና ፡ ይቀርጹ ፡ ነበረ ፤ ይህም ፡ ማለት ፡ እውነተኛ ፡ ጠባቂ ፡ መንጋዎቹን ፡ እንዲወድና ፡ እንዲከባከብ ፤ የጠፉትውንም ፡ ፈልጎ ፡ እንደሚያመጣ ፤ ክርስቶስም ፡ መልካም ፡ እረኛ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መንጋውን ፡ ምእመናንን ፡ እንዴት ፥

www.ethiopianorthodox.org

እንደሚወድና ፡ እንደሚከባከባቸው ፤ የጠባቂዎችም ፡ አለቃ ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የሚያስረዳ ፡ ነበር ። ክርስቶስም ፡ የርሱን ፡ መንጋ ፡ ለሚጠብቁ ፡ ለሐዋርያት ፡ የመጠበቅን ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቶ ፡ ሹሞዋቸዋል ፤ (ዮሐ/ ፳፩ ፡ ፲፭—፲፯ ፤ የሐ/ ሥራ ፡ ፳ ፡ ፳፰) ፤ ስለዚህም ፡ ጠባቂዎች ፡ ይባላሉ ። የሐዋርያት ፡ ተከታዮችም ፡ እንዲሁ ፡ ጠባቂዎች ፡ ይባላሉ ፤ የነርሱን ፡ ሥልጣን ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ስለ ፡ ወረሱ ፤ አንድ ፡ ጠባቂ ፡ ምንደኛ ፡ ሳይኾን ፡ እውነተኛ ፡ ለበጎቹ ፡ የሚያስቢ ፡ በፊት ፡ በፊታቸው ፡ እየሄደ ፡ ከጠራ ፡ ውሃና ፡ ከለመለመ ፡ ሣር ፡ ሲደርስ ፡ ዘንጉን ፡ ተክሎላቸው ፡ እንዲመግባቸው ፡ አውሬ ፡ እንዳይነጥቃቸውና ፡ ሌባም ፡ እንዳይሰርቃቸው ፡ ተግቶ ፡ ነቅቶ ፡ እንዲጠብቅ ፤ ካህናትም ፡ ነቢብ ፡ አእምሮ ፡ ያላቸውን ፡ መንጋዎች ፡ ተግተው ፡ ነቅተው ፡ ስለሚጠብቁ ፤ ደዌ ፡ ሥጋ ፡ ደዌ ፡ ነፍስም ፡ እንዳያገኛቸው ፡ አስፈላጊውን ፡ መድኀኒት ፡ ስለሚያደርጉላቸው ፡ ከምግባር ፡ ከሀይማኖት ፡ እንዳይናወጡ ፤ ከቀናው ፡ ጎዳና ፡ እንዳይወጡ ፡ ስለሚጠብቁ ፡ የንስሓ ፡ አባቶች ፡ ኹሉ ፡ ጠባቂዎች ፡ ይባላሉ ።

ስለዚህ ፡ የሚነገረው ፡ ትምህርትም ፡ «ትምህርተ ፡ አበ ፡ ነፍስ ፡ » ተባለ ፤ ምክንያቱም ፡ እንዴት ፡ መጠበቅ ፡ እንዴት ፡ መከባከብ ፡ እንደሚገባ ፡ ዐቅዱንና ፡ ዘዴውን ፡ ስለሚገልጥ ፡ ነው። ካህን ፡ የሚሆን ፡ ኹሉ ፡ የካህን ፡ ሥራው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ኀላፊነቱም ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ማወቅና ፡ የካህናትን ፡ ታሪክ ፡ ትምህርቱንም ፡ ማወቅ ፡ የግድ ፡ ያስፈልገዋል ። የዚህም ፡ መጽሐፍ ፡ ዋናው ፡ ዓላማ ፤ የንስሓ ፡ አባት ፡ የሚኾኑ ፡ ሰዎች ፡ ሥራቸው ፡ ብዙ ፤ በሕዝቡም ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ ኀላፊነት ፡ ከባድ ፡ መኾኑንና ፡ ይህን ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ዘዴ ፡ ለመሥራትና ፡ ከኀላፊነታቸውም ፡ ለመዳን ፡ የሚችሉበትን ፡ መንገድ ፡ የሚገልጥ ፡ ነው ። ይህም ፡ ትምህርት ፡ ፕራክቲካል ፡ ቲዎሎጂ ፡ ከተባለው ፡ አንደኛው ፡ ክፍል ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ለካህናት ፡ ለዕለት ፡ ተግባራቸው ፡ የሚረዳ ፤ መንገዱን ፡ የሚመራ ፤ ሐሳቡን ፡ የሚያብራራ ፡ ነው ። አለዕውቀት ፡ ማጥፋቱን ፡ ዐውቆ ፡



መሥራት ፤ ማልማቱን ፡ ዐውቀን ፡ የልማቱን ፡ ሥራ ፡ እንድንሠራ ፤ የንስሓ ፡ አባት ፡ ለሆኑና ፡ ለሚኾኑ ፡ ካህናት ፡ ትልቅ ፡ ጥቅምን ፡ እንደሚሰጥ ፡ በማመን ፤ ደግሞም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የክህነት ፡ ማዕርግ ፡ ያላቸው ፡ ወደፊትም ፡ ለዚህ ፡ ማዕርግ ፡ የታጩ ፡ ቢኖሩ ፤ የማዕርጉን ፡ ታላቅነት ፡ የሥራውን ፡ ብዛት ፡ የኀላፊነቱን ፡ ከባድነት ፡ አስቀድመው ፡ ዐውቀውና ፡ ወደው ፡ ራሳቸውን ፡ መሥዋዕት ፡ አድርገው ፡ እንዲገቡ ፡ ለማስገንዘብ ፤ በታላላቅ ፡ አምስት ፡ ክፍል ፡ ከፍዬ ፡ ጽፌዋለሁ ። ለዚሁም ፡ ድርሰት ፡ ምንጭ ፡ ኾነው ፡ የረዱኝ ፡ መጻሕፍት ፡

፩ኛ ፤ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡
፪ኛ ፤ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡
፫ኛ ፤ ሲኖዶስ ፡
፬ኛ ፤ ዲድስቅልያ ፤
፭ኛ ፤ ተግሣጽ ፡ ዘዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፤
፮ኛ ፤ ቀኖና ፡ አቡሊዲስ ፡ ናቸው ።

አባ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ወርቅነህ ።

www.ethiopianorthodox.org

# ክፍል ፤ ፩ ፤
# የቤተ ፡ ክርስቲያን ፣ ፍች ፤

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

ክህነትም ፡ ኾነ ፡ ማንኛውም ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎትና ፡ መንፈሳዊ ፡ ምስጢር ፡ የሚጀመረው ፤ የሚፈጸመውም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ከኹሉ ፡ አስቀድመን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ፍችና ፡ ዓላማ ፡ ማወቅ ፡ አስፈላጊያችን ፡ ነው ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማለት ፡ ከኹለት ፡ ቃላት ፡ የተገናኘ ፡ ቤተ ፡ አደረ ፡ ካለውና ፡ በክርስቶስ ፡ ክርስቲያን፡መሢሐውያን ፡ ከተባለው ፡ «ክርስቲያን ፡ » ካለው ፡ ቃል ፡ የተገናኘ ፡ ነው ፤ ዋና ፡ ፍችው ፡ የክርስቲያን ፡ መሰብሰቢያ ፤ መከማቻ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከማንኛውም ፡ ቤት ፡ ለመለየት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይላል ፤ ምክንያቱም ፡ ቤተ ፡ ዕገሌ ፤ ያለ ፡ እንደኾን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የሚያዝበት ፡ የተለየ፡ ሀብቱ ፡ ይሆንና ፡ ያለ ፡ እርሱ ፡ ፈቃድ ፡ ማንም ፡ ሊገባ ፡ ስለማይችል ፡ በግድ ፡ ፈቃድ ፡ ያስፈልገዋል ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ በዘር ፤ በሀገር ፤ በቀለም ፤ በቋንቋ ፤ በዜግነትና ፡ ይህንም ፡ በመሰለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አኳኋን፡ ቢለያይ ፡ በክርስቶስ ፡ ያመነ ፤ የቀና ፡ እምነትና ፡ ሥርዐት ፡ ያለው ፡ በአንድነት ፡ ተሰብስቦ ፡ የሚጸልይበት ፤ አምልኮቱን ፡ የሚገልጥበት ፤ ፍላጎቱን ፡ የሚነግርበት ፤ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎቱን ፡ ኹሉ ፡ የሚፈጽምበት ፡ የክርስቲያን ፡ መሰብሰቢያና ፡ መወያያ ፡ ታላቅ ፡ አዳራሽ ፡ ማለት፡ነው።

ይህን ፡ የመሰለ ፤ በኦሪቱ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የተባለ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አምልኮት ፡ የሚገለጥበት ፤ መሥዋዕት ፡ የሚሠዋበት ፤ በጠቅላላም ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ ኹሉ ፡ የሚፈጸምበት ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ የወል ፡ አምላክ ፡ ሲኾን ፤ ኹሉም ፡ ሊያመሰግነው ፡ ሲገባ ፤ በዚያ ፡ ቦታ ፡ አምልኮታቸውን ፡ ለመግለጥ ፡ የሚችሉና ፡ ቦታውን ፡ በተለይ ፡ ገንዘብ ፡ አድርገው ፡ ይዘውት ፡ የነበር ፡ እስራኤል ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ የተለየች ፡ የትንሹም ፡ የትልቁም ፤ የስ

www.ethiopianorthodox.org

ደተኛውም ፡ የባለሀገሩም ፤ የድኻውም ፡ የባለጸጋውም ፤ ቤት፡ሁና፡ ኹሉ፡ ሐሳቡን ፡ የሚገልጥባት ፡ ናት ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስንልም ፡ በልማድ፡ ወይም ፡ በማደሪያው ፡ የተጠራ ፡ ኹኖ ፡ ግንቡን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እን ላለን ፡ እንጂ ፡ ግንቡ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚባለው ፡ የካህናቱና ፡ የሕዝቡ ፡ አንድነት ፤ እንደ ፡ አንድ ፡ ልብ ፡ መካሪ ፤ እንደ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ተናጋሪ ፡ ሁነው ፡ አንድ ፡ እምነት ፡ አንድ ፡ ሥርዐትና ፡ አስተያየት ፡ ያላቸው ፤ በክርስቶስ ፡ አምነው ፡ ክርስቲያን፡ የተባሉ፡ኹሉ፡ ናቸው ። ይህንም ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለው ፡ የክርስቶስ ፡ ንግግርና ፡ ሌላ ውም ፡ አገላለጥ ፡ ያስረዳናል ፡ « - - እርሳቸውንም ፡ ባይሰማ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን፡ንገራት ፤ ደግሞም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ባይሰማት ፡ ከአረማ ዊና ፡ ካጣሪ ፡ ቍጠረው ፡ »(ማቴ/ ፲፰፡ ፲፯፤ ሮሜ፡ ፲፮፡፳፤ የሐ/ ሥራ፡ ፱፡ ፲፯ ፤ ፲፭ ፡ ፳፱—፳፯) ።

## ፩ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሠረት ።

ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ የመሠረተ ፡ ጌታችን ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየ ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሲሆን ፤ መሠረቷ ፡ ደግሞ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡ ነው ፤ እርሷም ፡ የተመሠረተችው ፡ የጰንጠቆስጤ ፡ ዕለት ፡ ነው ። በቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ ውስጥ ፡ እውነተኛው ፡ ሃይማኖት ፤ የቀናው ፡ ሥርዐት ፡ ሰውን ፡ ለማዳንና ፡ ለማንጻት ፡ ያለ ፡ ማቋረጥ ፡ የሚሰጡ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምስጢራት ፤ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፤ ጌታ ፡ የሠራው ፤ ሐዋርያት ፡ ያስተ ማሩት ፡ ትምህርት ፡ ይገኝበታል ፤ ይህም ፡ ማለት ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውጭ ፡ ከቶ ፡ ሕይወት ፡ እንደሌለ ፡ ደግሞም ፡ እንደማይሰጥ ፡ የሚያረጋ ግጥ ፡ ነው ።

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ራስ ፡ ወይም ፡ ጉልላት ፡ በደሙ፡ ያነጻት፡ መድ ኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፤ (ኤፌ/ ፩ ፡ ፳፪ ፤ ፪ ፡ ፳)፤ኀይልን፡ የሚሰጥ ፤ የሚያጸናት ፡ ግን ፡ ለምእመናን ፡ ከተሰጠ ፡ የማይለየው ፡ የባሕ ርይ ፡ ሕይወቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ።



## ፪ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባሎች ።

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባሎች ፡ አማንያኑ ፡ ኹሉ ፡ ትንሽ ፡ ትልቅ ፤ ሴት ፡ ወንድ ፤ ካህን ፡ ሕዝባዊ ፡ ሳይል ፡ ያመነ ፤ የተጠመቀ ፡ ኹሉ፡ ነው፡ ማለት ፡ በአንድ ፡ አካል ፡ ብዙ ፡ ሕዋሳት ፡ መሰብሰቢያው ፡ ግን፡ አናት፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ አማንያኑን ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ የምታደርግ ፡ የምታዛምድና ፡ የምታስተሳስብ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ናት ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የማትለ ወጥ ፡ አንዲት ፡ ስትሆን ፡ አባሎቿ ፡ በኹለት ፡ ይከፈላሉ ፡ አንደኛዋ ፡ ዕልፈኛ ፡ ተዋጊ ፡ ተጋዳይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትባላለች ፡ ወይም ፡ በዐ ጸደ ፡ ሥጋ ፡ ያሉ ፡ ምእመናን ፡ ይባላሉ ። በምድር ፡ ያሉ ፡ ሁልጊዜ ፡ ከአ ጋንንት ፡ ጋራ ፡ ሲሰለፉ ፡ ሲዋጉ ፡ የሚኖሩ ፡ ምእመናን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፤ «የእግዚአብሔርን ፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡ ኹሉ ፡ ልበሱ ፤ የሰይጣንን ፡ ተንኰል ፡ ትቋቋሙ ፡ ዘንድ ፡ እንዲቻላችሁ ፤ መታገላችን ፡ ከሥጋና ፡ ከደም ፡ ጋራ ፡ አይደለምና ፤ ከገዢዎችና ፡ ከሥልጣናት ፡ ጋራ ፡ እንጂ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ጨለማ ፡ ላይ ፡ ከሚገዙ ፡ ጋራ ፡ እንጂ ፤ በሰማይም ፡ ታች ፡ ከምትኖር ፡ ከመንፈሳዊት ፡ ዓመፃ ፡ ጋራ ፤ ስለዚህም ፡ የእግዚአብሔርን፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡ ኹሉ ፡ ልበሱ ፤ በክፉ ፡ ቀን ፡ መቋቋም ፡ ሥራውንም ፡ ኹሉ፡ በፈጸማችሁ፡ ጊዜ ፡ እንድትችሉ ። አሁንም ፡ ቁሙ ፤ ወገባችሁንም፡ በእውነት፡ታጠቁ፡ የጽድቅንም ፡ ጥሩር ፡ ልበሱ ፤ እግራችሁም ፡ የተጫመተ ፡ ይሁን ፡ በሰላም ፡ ወንጌል ፡ መዘጋጀት ። ከዚህም ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ የሀይማኖትን ፡ ጋሻ፡ውሰዱ ፤ እሳት ፡ የምታቃጥለውን ፡ የክፉውን ፡ ፍላፃ ፡ ኹሉ ፡ ታጠፉ፡ ዘንድ ፡ የምትችሉበት ፤ በራሳችሁም ፡ የመድኀኒት ፡ ራስ ፡ ቁር ፡ ጫኑ ፤ የመንፈስንም ፡ ሰይፍ ፡ ውሰዱ ፤ እርሱም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው፤ በጸሎትና ፡ በልመናም ፡ ኹሉ ፡ ሁልጊዜ ፡ በመንፈስ ፡ ጸልዩ ፡ ለዚህም ፡ ትጉ ፤ አዘውትራችሁ ፡ ስታፀምዱ ፡ ስለ፡ ቅዱሳን ፡ ኹሉ፡ »(ኤፌ/ ፮፡ ፲፩፡ ፲፰) ፡ እያለ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በሰፊው ፡ ያስረዳናል ።

ኹለተኛዋ ፡ ደግሞ ፡ ድል ፡ አድራጊዋ ፡ አቸናፊዋ ፡ የድል ፡አድራ ጊነትን ፤ ዘውድ ፡ የተቀዳጀችዋ ፡ የቅዱሳን ፡ አንድነት ፡ ወይም ፡ በዐጸደ፡ ነፍስ ፡ ያሉ ፡ ምእመናን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፤ «በሀይማኖት ፡ መንግሥታትን፡ ያስገዙ ፡ ጽድቅ ፡ አደረጉ ፤ ተስፋ ፡ የተሰጣቸውን ፡ ተቀበሉ ፤ የአናብስ

www.ethiopianorthodox.org

ትን ፡ አፍ ፡ ዘጉ ፤ የእሳቱን ፡ ኀይል ፡ አጠፉ ፤ ከሰይፍ ፡ ስለት ፡ዳኑ ፤ ከድካም ፡ በረቱ ፤ በመጋደል ፡ ኀየለሙ ፤ የእሕዛብን ፡ ጭፍራ ፡ አስሸሹ ፡ » (ዕብራ/፲፩፡ ፴፫—፴፬) ፡ እያለ ፡ በሰፊው፡ የሚያስረዳላቸው ፡ ናቸው።እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ «መልካሙን ፡ ገድል ፡ ተጋደልኩ ፤ ሩጫዬንም፡ ጨረስኩ፤ ሀይማኖትም ፡ ጠበቅሁ ፡ እንግዲህ ፡ የጽድቅ ፡ አክሊል ፡ ተዘጋጅቶልኛል ፤ እግዚአብሔር ፡ የሚሰጠኝ ፡ በዚያች ፡ ቀን ፤ ያ ፡ ጻድቅ ፡ ፈራጅ ፡ ለኔም ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ መገለጡን ፡ ለሚወዱ ፡ ኹሉ ፡ እንጂ ፤ » (፪ ፡ ጢሞ/ ፬፡ ፯—፰)፡እያለ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ስለ፡ኹለቱም ፡ ይናገራል። በዐጸደ ፡ ሥጋ ፡ ያሉት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባሎችም ፡ እንዲሁ ፡ በኹለት ፡ ይከፈላሉ ፡ አንደኛው ፡ የካህን ፡ ወገን ፤ ዲያቆን ፤ ቄስ ፤ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ የተባሉት ፡ ሦስቱ ፡ መዓርጋት ፡ ናቸው ። ሥራቸው ፡ መስበክ ፤ ማስተማር ፡ ሕዝቡም ፡ ከኀጢአታቸው ፡ የሚነጹበትን ፤ የነፍሳቸውም ፡ የሥጋቸውም ፡ ድኅነት፡ የሚገኝበትን ፤ የክርስቶስ ፡ መንግሥት ፡ የሚስፋፋበትን ፤ ምእመናን ፡ የሚበዙበትን ፡ ሥራ ፡ ተግተውና ፡ ነቅተው ፡ መሥራት ፤ ነጋ ፡ ለጸሎት ፡ መሸ ፡ ለመሥዋዕት ፡ ማለት ፡ ነው ። ኹለተኛው ፤ ወንድ፡ሴት ፤ ትንሽ፡ትልቅ ፡ ሳይለይ ፡ ሕዝባዊ ፡ የተባለው፡ነው ። የነርሱም ፡ ሥራ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምትደረጅበትን ፤ የምትገለገልበትን ፤ ካህናት ፡ የሚደገፉበትን ፡ ማንኛውም ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚከናወንበትን ፤ ዐሥራቱን ፡ በኵራቱን ፡ በማውጣት ፡ የሚያስቡና፡ በገንዘብ ፡ የሚረዱ ፡ ናቸው ። ኹለቱም ፡ ወገን ፡ አስፈላጊ ፡ ስለ፡ ኾኑ ፤ እንደ ፡ ሥራቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ማገልገል ፡ አለባቸው፤ያለ ፡ ካህናቱ ፡ ሕዝቡ፡ ብቻቸውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊባሉ ፡ ወይም ፡ የሚያሰኛቸውን ፡ ሥራ ፡ ሊሠሩ ፡ አይችሉም ፤ ካህናትም ፡ ያለ ፡ ሕዝቡ ፡ እንዲሁ ፡ ስለ ኾኑ ፤ የኹለቱ ፡ አንድነት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መባልንና ፡ የሥራ ፡ ክንውንን ፡ የኃላፊነትን ፡ ማቅለል ፡ ሊያስገኝ ፡ ይችላል ።

## ፫ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዓላማ ።

ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ በምድር ፡ ያለች ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት፡ ስለ ፡ ሆነች ፡ ለሕዝቡ ፡ ብዛትን ፡ ለሀገሩ ፡ ስፋትን ፡ ለአገዛዙ፡ በረከትን ፡ ለአስተዳደሩ ፡ ጸጥታን ፡ በጠቅላላው ፡ ለዓለም ፡ ሰላምን ፡ ፍቅር ፡ አንድነትን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲሰጥ ፡ መጸለይ ፤ እንዲሁም ፡ በኀጢ



አቱ ፡ ርቆ ፡ የነበረውን ፡ ሰው ፡ ማቅረብ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ማስታረቅ ፤ በምእመናንና ፡ በእግዚአብሔር ፡ መካከል ፡ መገናኛ ፡ ድልድይ ፡ መሆን ፤ ምስጢራትን ፡ ለሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ ማደል ፤ ጸጋን ፡ ልጅነትን፡ ሀብትን ፡ ረድኤትን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ማሰጠት ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የእግዚአብሔር ፡ የጸጋ ፡ መዝገብ ፡ ትባላለች፡ ምክንያቱም፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመናፍቃን ፡ ጋራ ፡ እየተዋጋች ፤ እውነተኛውን፡እምነት ፡ እየጠበቀች ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ እያጸናች ፤ ጸጋን ፡ ሰላምን ፡ ይቅርታን ፡ የኀጢአት ፡ ሥርየትን ፡ የነፍስ ፡ ድኅነትን ፡ ለምእመናን ፡ ታድላለችና ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መንፈሳዊ ፡ ዓላማ ፡ ያላት ፡ እንደ ፡ መሆኗ ፤ የርሷም ፡ መሪዎች ፡ ፍጹም ፡ መንፈሳውያን ፡ መሆን ፡ የምትመራበትም ፡ ሕግ ፡ ፍጹም ፡ መንፈሳዊ ፡ መሆን ፡ የግድ ፡ ያስፈልገዋል ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## መ ን ግ ሥ ት ።

ሰው ፡ ኹሉ ፡ የአዳምና ፡ የሔዋን ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ዘር ፡ በመሆኑ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ አብሮ ፡ መኖርን ፡ መረዳዳትን ፡ ገንዘብ፡ አድርጎ፡ከባሕርዩ ፡ እንደ፡ተገኘ ፡ አድርጎ ፡ ይዞ ፡ ይኖራል። ይህም ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ በየጊዜው ፡ ከቤተ ፡ ሰብ ፡ ጀምሮ ፡ አብሮ ፡ መኖር ፡ ይለምዳል ፡ አብሮ ፡ ከኖረም ፡ ዘንድ ፡ ኹሉን ፡ የሚያገናኝ ፡ የሚያስማማና ፡ የሚያስተዳድር፡ እርምጃን ፡ የሚሰጥ ፡ ሕግ ፡ ስለሚያስፈልግ ፡ ኹሉም ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ ያወጣሉ ። በአንድ ፡ ሕግ ፡ የሚያድር ፡ በተወሰነ ፡ ሀገር ፡ የሚኖርና ፡ አንድ ፡ ሥርዐት ፡ ያለው ፡ አንድነት ፡ ያለውም ፡ ሕዝብ፡መንግሥት ፡ ይባላል ፤ የዚህም ፡ መንግሥት ፡ ኀይሉና፡ ስሜቱ፡ የሚገለጠው፡ በመሪውና ፡ በአስተዳዳሪው ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ ወይም ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

## ፩ ፤ የመንግሥቱ ፡ ዓላማ ።

የመንግሥት ፡ ዋና ፡ ዓላማው ፡ የሕዝቡ ፡ ኑሮ ፡ ዋስትና ፡ ያለው ፡ ሰላምን ፡ የተመረከዘ ፡ እንዲሆን ፤ በስም፡ በመልክና ፡ በባሕርይ ፡ የተለያየውን ፡ በአንድ ፡ አቅድ ፡ ለማስተዳደር ፤ አንድ ፡ ኅብረት፡እንዲኖረው፡ ማድረግ ፡ ነው ፤ ይህንም ፡ ለማድረግ ፡ እንዲመቸው ፡ ሕግ ፡ አውጥቶ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ሥርዐት ፡ ሠርቶ ፤ አጥፊውን ፡ ቀጥቶ ፤ አልሚውን ፡ ሹሞ፤በሕግ፡ዘንድ ፤ ትንሹ ፡ ከትልቁ ፤ ድኻው ፡ ከባለጸጋው ፤ ደካማው፡ከኀይለኛው ፤ ያልተማረው ፡ ከሊቁ ፤ ልዩነት፡ሳይኖራቸው ፡ በትክክል፡በሕግ ፡ መንግሥቱ፡ መሠረት ፡ ኹሉም ፡ መብቱን ፡ ዐውቆ ፡ እንዲኖር ፡ ያደርጋል ። የሕዝብ፡ አንድነት ፡ ወይም ፡ ኅብረት ፡ ታላቅ ፡ ኀይልን ፤ መልካም ፡ ድርጅትን ፤ ያማረ፡ ውጤትን ፡ ይሰጣል ። የሕዝብ ፡ አንድነት ፡ የመንግሥት ፡ አቅዋም ፡ በተፈጥሮ ፡ ሊኖር ፡ የሚገባ ፡ ፍላጎትን ፡ የሚያረካ ፤ መፍቅድን ፡ የሚፈጽም ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ፡ የተቋቋመ ፡ እንደ፡ ኾነ ፤ ለዚህም፡ መሪና፡ አስተዳዳሪ፡ ሆኖ፡ የሚሾመው፡ ንጉሡ፡ ነገሥት፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ፡ የሚሾም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ለማወቅ ፡ «ሰው ፡ ኹሉ ፡ ይገዛ ፡ ለተሾመው ፡ መኰንን ፤ ሹመት ፡ አይሆንምና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በቀር ፡ » (ሮሜ/፲፫ ፡ ፩—፲፭ ፤ ቲቶ ፡ ፫ ፡ ፩ ፡ ፩ ጴጥ/፪፡፫—፲፫)ሲሉ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ተስማምተዋል ።

፪ ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ።

መንግሥት ፡ በአንድ ፡ በኩል ፤ ሕዝቡ ፡ በግብረ ፡ ገብነትና ፡ በቀናው ፡ ሥርዐት ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖርና ፡ በተፈጥሮ ፡ የተሰጠውን ፡ ጸጋ፡ አክብሮ ፡ እንዲጠብቅ ፡ ያደርጋል ፤ በአንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ጸጥታው፡ የተረጋገጠ ፤ ኑሮው ፡ የተሻሻለ ፤ በእርምጃው ፡ ከፍ፡ያለ፡ደረጃን ፡ እንዲይዝ፡ ተግቶና ፡ ነቅቶ ፡ መሥራት ፡ በተለይም ፡ በአስተዳደርና ፡ በፍርድ ፡ በኩል ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ያለ፡አድልዎና ፡ ያለ ግብዝነት ፡ ጥብቅ ፡ የኾነ ፡ መቈጣጠር ፡ እያደረገ ፤ ሀብቱ ፡ እንዲደረጅ ፤ በቍጥርም ፡ እንዲበዛ ፤ ሰላምና ፡ ደስታን ፡ የተመላ ፡ እንዲሆን ፤ እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ ይሠራል ። በዚህ ፡ መንፈስ ፡ የሚተዳደሩ ፡ የክርስቲያን ፡ መንግሥታት ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ፤ ስለዚህ ፡ በየዕለቱ ፡ የሚያሳዩት ፡ የሥራ ፡ እርምጃና ፡ የኑሮ ፡ መሻሻል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ፤ ለምሳሌ ፡ የኛን ፡ የንጉሡ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ብንመለከት ፡ በቂ ፡ አስረጂ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፤ ማለት ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምሮ ፡ የተነሡ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ለሀገሪቷ ፡ ስፋት ፡ ለሕዝቡ ፡ ብዛት ፤ ለሀይማኖቷ ፡ ጽናት ፤ ለታሪኳ ፡ ገናናነት ፤ ስለሚያስቡና ፡ በትጋት ፡ ስለሚሠሩ ፡ ከአፍሪካ ፡ ለይ



ተው፡ ለአገሪቷ ፡ ነጻነትን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኗ ፡ ሀይማኖትን ፡ ጠብቀው፡ አቈዩዋት ። በተለይ ፡ ግን ፡ በኛ ፡ ጊዜ ፡ የተነሡ ፡ ደገኛው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዐፄ ፡ ወራሽና፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ከነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምረው ፡ በትጋትና ፡ ራሳቸውን ፡ ለሕዝብ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርገው ፡ ዕረፍትን ፡ ሳይሹ ፡ ከመሥራቸው ፡ የተነሣ ፡ ሥልጣኔ ፡ በርሳቸው ፡ ጊዜ ፡ መጀመሩን ፡ ስናውቅ ፡ እርምጃውን ፡ ስናይ ፡ ደግሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የተፈጥሮ ፡ ባሕሪዋ ፤ ወይም ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምሮ፡የነበር ፡ መስሎ ፡ ይገኛል ። ይህን ፡ አደራውን ፡ የሚጠብቅ ፡ ዓላማውን ፡ የሚከተል ፤ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራና ፡ የሚያመልክ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችንን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲጠብቅ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እጆቿን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘርግታ ፡ ትለምናለች ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

የቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ የመንግሥት ፡ ግንኙነት ።

፩ ፡ መሠረታቸው ።

ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ መንግሥት ፡ በጣም ፡ ቅርብ ፡ የኾነ ፡ ግንኙነትና ፡ አንድነት ፡ አላቸው ፤ ምክንያቱም ፡ የኹለቱም ፡ ድርጅት ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ። ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ክርስቶስ ፡ ራሱ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ ሥጋ ፡ ለብሶ ፡ በምድር ፡ ተመላልሶ ፡ ፍጹም ፡ መንፈሳዊ ፡ አቅዋምና ፡ መንፈሳዊ ፡ አስተዳደር ፡ ያላት፡ አድርጎ ፡ መሠረታት፡ ስለዚህ ፡ በራሷ ፡ መራጭነት ፡ በሚመረጡ ፡ መንፈሳውያን ፡ ገዢዎች ፡ ትመራለች ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በምድር ፡ ያለች ፡ የእግዚአብሔር፡መንግሥት ፡ ስትሆን ፡ አቅዋሟ ፡ በምድር ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ዓላማዋ ፡ ሰማያዊ ፡ ስለ ፡ ኾነና ፡ ለሰማያዊ ፡ ማዕርግ ፡ ስለሚያበቃ ፡ ከዓለም ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ የላትም « ኢየሱስም ፡ መለሰ ፡ አለም ፡ መንግሥቴ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ አይደለችም ፤ መንግሥቴስ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም፡ ብትኾን ፡ ሎሌዎቼ፡ ይዋጉልኝ ፡ ነበሩ ፤ ወደ ፡ አይሁድ ፡ እንዳልሰጥ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ መንግ

ሥቱ ፡ ከዚህ ፡ አይደለችም » (ዮሐ/ ፲፰ ፡ ፴፮ ) እያለ ፡ ክርስቶስ ፡ ራሱ፡
መስክሯል ።

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥልጣን ፡ ምንም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሁኖ ፡ የማሠ
ርና ፡ የመፍታትም ፡ መብት ፡ ቢኖራት ፡ ከሥጋዊ ፡ አስተዳደር ፡ ጋራ ፡
ተቃራኒ ፡ በሚሆን ፡ ነገር ፡ አትገባም ። መንግሥትንም ፡ ደግሞ ፡ ያቋ
ቋመ፡ እንዲሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲሆን ፡ በግልጥ ፡ ሳይሆን ፡ በምስጢር ፡
በረቂቅ ፡ አቋቋመ ፡ ማለት ፡ ሕዝብ ፡ በምድር ፡ እንዲበዛ ፡ ቅዱስ፡ ፈቃዱ፡
ስለ ፡ ኾነ ፡ «እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ ፈጠረ፡ በመልኩ ፡ በእግዚአብሔር፡
መልክ ፡ ፈጠረው ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አድርጎ ፡ ፈጠራቸው ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ባረካቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ አላቸው ፡ ብዙ ፡ ተባዙም ፡ ምድር
ንም ፡ ምሏት ፡ግዟትም » (ዘፍ/ ፩፡ ፳፯—፳፰ ) እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ባረካ
ቸው።ሰውም፡ ከበዛ ፡ ዘንድ ፡ አንድነት ፡ ለመኖር ፡ ኀይልን ፡ አንድ፡ለማ
ድረግ ፡ ሰላምን ፡ ለማግኘት ፡ የግድ ፡ መንግሥትን ፡ አቋቋመ ፡ በሕግ ፡
ጠባዕይ ፡ የተረዳ ፡ በመሆኑ ፡ የቀደሙ ፡ ሰዎች፡ ማንም ፡ ሳይነግራቸውና፡
ሳይመክራቸው ፡ መንግሥት ፡ አቁመው ፡ ይተዳደሩ ፡ ነበር ፡ ይህንንም ፡
ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ የዓለም ፡ ታሪክ ፡ በሰፊው ፡ ያስረዳናል። ማንኛውም፡
ድርጅት ፡ ማንኛውም ፡ አቀዋም ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ከቶ ፡
ሊሆን ፡ አይችልም ፡ ስለዚህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ በርሱም ፡ መሥ
ራችነት ፡ ነገሥታት ፡ ይነግሣሉ ፡ ሹማምንትም ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፈቃድ ፡ ይሾማሉ ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ከትንሽ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡
ትልቁ ፡ ያለው ፡ ማዕርግ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ይሆናል ።
«ነገሥታት ፡ በኔ ፡ ይነግሣሉ ፡ ሹማምንት ፡ የቀናውን ፡ ፍርድ ፡ በኔ ፡ ያደር
ጋሉ ፡ አለቆችም ፡ በኔ፡ያዛሉ ፡ ክቡራንና ፡ የምድር ፡ ፈራጆች ፡ ኹሉ፡ - -»
(መጽ/ ምሳ/፰፡ ፲፭—፲፮) እንዲሁም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ « ሰው ፡ ኹሉ ፡
ይገዛ ፡ ለተሾመው ፡ መኰንን ፡ ሹመት ፡ አይሆንምና ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ዘንድ ፡ በቀር » (ሮሜ/ ፲፫፡፩—፲፭ ፡ ቲቶ፡፫፡ ፩)። ቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፡ የመ
ንግሥት ፡ መሥራች ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ፡ ኾነ ፡ « አሁንም ፡ ለሰው ፡
ሥርዐት ፡ ኹሉ፡ተገዙ ፡ ስለ፡ እግዚአብሔር ፡ ለንጉሥም ፡ ቢሆን፡በኹሉ፡
ላይ ፡ ሁኗልና ፡ ለመኳንንትም ፡ ቢሆን ፡ ከርሱ ፡ ተልከዋልና ፡ በክፉ ፡
አድራጎች ፡ ላይ ፡ መቅሠፍትን ፡ ሊያመጡ ፡ በበጎ ፡ አድራጎች ፡ ግን፡ምስ



ጋናን ፡ ይህች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ናት - - » (፩ ፡ ጴጥ/ ፪ ፡ ፲፫ ፡
፲፬) ። ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ በቃልም ፡ በምስጢርም ፡ ሳይለዩ ፡ ተባ
ብረው ፡ የተናገሩት ፡ በእርግጥ ፡ መንግሥት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተ
ገኘ ፡ መሠረቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሆኑን ፡ በማስረዳት ፡ ነው ። እንዲያ
ውም ፡ «ሥርዐተ ፡ ሰማይ ፡ ተሠርዓ ፡ በዲበ ፡ ምድር ፡ » እንዲል ፡ በም
ድር ፡ ያለውን ፡ ሥርዐት ፡ አክብረን ፡ ካልተገዛን ፡ ለሰማያዊውም ፡ እን
ዲሁ ፡ እናምጻለን ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህ ፡ ኹሉ ፡ ነገር ፡ ከእግዚአብሔር ፡
የተገኘ ፡ መንግሥትን ፡ የመሠረተ ፡ አሁንም ፡ የሚጠብቃት ፡ የሚያጸ
ናት ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይህን፡ ይዛ፡ ነገ
ሥታት ፡ ሲነግሡ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዐት ፡ በጸሎት፡ በቅብዐት፡
ታነግሣለች ፡ ነገሥታትም ፡ ምንም ፡ ኀይለኞች ፡ ቢሆኑ ፡ በኀይላችን ፡
ተነሣን ፡ በሥልጣናችን ፡ ነገሥን ፡ አይሉም ። « ሥዩመ ፡ እግዚአብ
ሔር፡ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እገሌ ፡ -- - - » እያሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡
መንግሣቸውን ፡ ያጸድቃሉ ።

## ፪ ፡ ግንኙነታቸው ።

መሠረታቸው ፡ ወይም ፡ መሥራቻቸው ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡
መጠን ፡ ዓላማቸው ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ይገናኛሉ፡ ለም
ሳሌ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምታስተምረው ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ግብረ ፡ ገብ
ነቱን ፡ እንዲጠብቅ ፡ በሥርዐቱ ፡ በሀይማኖቱ ፡ እንዲጸና ፡ ኑሮው ፡ ሰላ
ምን ፡ የተመላ ፡ እንዲሆን ፡ ኅብረት ፡ አንድነት ፡ እንዲኖረው ፡ መረዳ
ዳት ፡ መግባባት ፡ በመካከላቸው ፡ እንዲኖር ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሌላም ፡
ሲሆን ፡ መንግሥትም ፡ ይህን ፡ ያጸድቃል፡ እንጂ ፡ ሊያፈርስ፡አይችልም፡
ማለት ፡ የክርስቲያን ፡ መንግሥት ፡ ሕግ ፡ ኹሉ ፡ ሥሩ ፡ መሠረቱ ፡ ዐሠ
ርቱ ፡ ቃላት ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምታስተምረው ፡ ሕግ፡
ለራሱ ፡ ደጋፊ፡ከመሆን ፡ በቀር፡ ሊያፈርስበት ፡ አይችልም። መንግሥቱ ፡
ያልተረጋገጠ ፡ ደንበኛ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የሌለው ፡ ዲክቴተር ፡
በፈቀደው ፡ ለመምራት ፡ ኀይሉን ፡ ለማሳየት ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ ቤተ ፡
ክርስትያንንና ፡ መንግሥትን፡ የሚለያቸው ፡ ሕግ ፡ የለም። የመንግሥቱ፡
ዜጋ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባሎች ፡ ናቸው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባ

www.ethiopianorthodox.org

ሎችም ፡ የመንግሥቱ ፡ ዜጋ ፡ ስለ፡ኾኑ ፡ የቤተ፡ ክርስቲያንንም ፡ የመንግሥትንም ፡ ልማት ፡ ስፋት ፡ ያስባሉ ፤ ሕጋቸውም ፡ እንዲከበር ፡ ያደርጋሉ።ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመንግሥቱ ፡ የምታደርገው፡ ርዳታ ፤ የሕዝቡ፡ ኑሮ ፡ ሰላምን ፤ ጤንነትን ፤ በረከትን ፤ ረድኤትን ፡ የተመላ ፡ እንዲሆን ፤ የመንግሥቱ ፡ አስተዳደር ፡ ጸጥታ ፡ ያለው ፤ የመንግሥቱ ፡ ጠላት ፡ እንዲደክም ፡ ያለማቋረጥ ፡ ትጸልያለች ፤ መሥዋዕት ፡ ትሠዋለች ፤ ቡራኬዋን ፡ ታድላለች ፡ ማለት ፡ የተወለደው ፡ እንዲያድግ ፤ የተዘራው ፡ እንዲበቅል ፤ የበቀለውም፡ ለምግብ፡ እንዲደርስ፤ ከዚህም ፡ በቀር ፡ ሕዝቡ፡አንድነት ፡ እንዲኖረው ፡ በመሪውና ፡ በአስተዳዳሪው ፡ ልቡና፡እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ እንዲያድርበት ፤ ዕድሜው ፡ እንዲረዝም ፤ ግብረ ፡ ገብነቱንና ፡ ነጻነቱን ፡ ጠብቆ ፡ እንዲኖር ፡ ትመክራለች ፤ ታስተምራለች ። መንግሥት ፡ ደግሞ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰፊ ፡ ቸሮታውን ፡ ያደርግላታል ፤ እንድትሰብክና ፡ እንድታስተምር ፡ ሙሉ ፡ ነጻነትን ፡ ይሰጣታል ፤ በችግሯ ፡ ይረዳታል ፤ ሕግ ፡ አፍራሽን ፡ ይቀጣላታል ። ኹለቱ ፡ በዚህ ፡ መልክ ፡ ተግባብተውና ፡ ተረዳድተው ፡ በመሥራታቸው ፡ እርምጃቸውና ፡ ኀይላቸው ፡ ተሰብስቦ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ በመሆን ፡ መልካም ፡ ውጤትን ፡ ያስገኛሉ ።

ይህ ፡ አስተዳደር ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ በኢትዮጵያችን ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ከአካባቢዋ ፡ ተለይታ ፡ ሀገሯ ፡ በነጻነቷ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኗም ፡ በሀይማኖቷ ፡ ጸንተው ፡ ለመኖር ፡ ቻሉ ። ወደፊትም ፡ እንዲሁ ፡ ጸንተው ፡ እንዲኖሩ ፡ የሁላችን ፡ ምኞትና ፡ ጸሎት ፡ የሥራም ፡ ትጋት ፡ መሆን ፡ አለበት ።

ለማስታወስ ፡ ያህል ፡ በዘመናችን ፡ የተሠራውን ፡ እናንሣለን ፤ ደጉ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የመንግሥቱ ፡ መሪ ፤ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የበላይ ፡ ጠባቂ፡ ሁነው ፡ ኹለቱንም፡ አስማምተው፡ በሚያስተዳድሩበት ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎትም ፡ በሚፈጽሙበት፡ ጊዜ፡ ለምቀኝነት ፡ የሚያርፈው ፡ ግፈኛው ፡ ጠላት፡ በዓለም ፡ መንግሥት፡ሕግ፡



በተከለከለው ፡ መርዝ ፡ አገራችንን ፡ ለማጥፋት ፡ በአጥቂነት ፡ በተነሣ ፡ ጊዜና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጊዜም ፡ ቢኾን ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥታችን ፡ ድል ፡ ለማድረግ ፡ የረዳቸው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጸሎት ፡ የርሳቸውም ፡ ብርታት፡ የሕዝቡም ፡ ኅብረት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ማንም ፡ አይስተውም ።

አሁንም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ ለቤተ፡ ክርስቲያናችንና፡ ለመንግሥታችን ፡ ስፋት ፡ እንሥራ ፡ ሀይማኖትና ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ «ኹሉ ፡ አገሬ ፡ » የሚል ፡ ነው ፡ ሕዝባዊ ፡ ሁኖ ፡ ለመንግሥትና ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎት ፡ የሚቸገረው ፡ ነገር ፡ የለም ፤ ካህንም ፡ ኹኖ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ለመንግሥት ፡ ያገለግላል ፤ የሚገደው ፡ ወይም ፡ የሚቸግረው ፡ ነገር ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ ሕዝቡና፡ ካህናቱ፡ አንድ ፡ ሲሆኑ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደተባሉ ፡ ካህናትም ፡ ሕዝብም ፡ በአንድ ፡ ሁነው ፡ ተባብረው ፡ የሠሩ ፡ እንደ፡ኾነ ፤ መንግሥት ፡ ይባላሉ፤ መንግሥታቸውንና ፡ ሀገራቸውን ፡ ለመርዳት ፡ ይችላሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

# ክፍል ፡ ፪ ።

## አበ ፡ ነፍስ፡ (የቤተ ፡ ክርስቲያን፡ ጠባቂ) ፡ ወደ፡ ክህነት፡ ከመግባት፡ በፊት።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### የክህነት ፡ ፍች ።

ካህን ፡ ማለት ፡ « ተክህነ ፡ አገለገለ ፡ » ካለው ፡ ከግእዝ ፡ የወጣ ፡ ቃል፡ ነው፤ ፍቺውም ፡ አገልጋይ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ ሲሆን፡ አንድ፡ ሰው ፡ ሥልጣነ ፡ ክህነትን ፡ ከተቀበለ ፡ ጀምሮ ፡ ራሱን ፡ ለሕዝብ ፡ የሚያስገዛ ፡ የሚያገለግል ፡ ማለት ፡ ነው ። የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥራዋ ፡ ምእመናንን ፡ ማንጻትና ፡ ማጽናት ፡ ነው ፡ ይህንም ፡ ቅዱስ ፡ ሥራዋን ፡ በተለዩ ፡ መሣሪያዎቿ ፡ በካህናት ፡ ትፈጽማለች ፡ እነርሱም ፡ ሥልጣንን ፡ መብትን ፡ ከካህናት ፡ አለቃ ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተቀበሉ ፡ ናቸው። ለዚህም ፡ አስረጂ ፡ «እርሱም ፡ ሰጠ ፡ እኩሌቶቹ ፡ ሐዋርያት፡ እኩሌቶቹ፡ ነቢያት ፡ ሌሎችም ፡ ሰባኪዎች ፡ ሌሎችም ፡ ጠባቂዎችና ፡ አስተማሪዎች» (ኤፌ/፬፡፲፩—፲፪)እያለ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ መስክሯል።እነዚህም ፡ የቤተ፡ ክርስቲያን ፡ አገልጋዮች ፡ የተባሉት ፡ ካህናት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መራጭነት ፡ ተመርጠው ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ተሹመው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀብለው ፡ ከሕዝብነት ፡ ተራ ፡ ወጥተው ፡ ለዚህ ፡ ግብር ፡ ብቻ ፡ የተወሰኑ ፡ ናቸው ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ የካህናት ፡ ማዕርግ ፡ በኹለት ፡ ይከፈላል፡ ማለት፡ ከፍተኛ፡ ማዕርግና፡ ዝቅተኛ፡ ማዕርግ፡ ናቸው ፡ በከፍተኛ ፡ ማዕርግ፡ የሚገቡ፡ ዲያቆን፤ ቄስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ናቸው።እነዚህም፡ከላይ፡ እንደ ፡ ተናገርነው ፡ ኹሉ ፡ በደንበኛው ፡ ምርጫ ፡ ተመርጠው ፡ በደንበኛው ፡ ሹመት ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ተሹመው ፡ የመስበክን ፡ የማስተማርን ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ የመፈተት ፡ ማንኛውንም ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ የመፈጸም ፡ ሥልጣንን ፡ ገንዘብ ፡ ያደረጉ ፡ ሦስቱ፡ ማዕርገ፡ ክህነት ፡ የሚባሉት ፡ ናቸው ። ዝቅተኛ ፡ ማዕርገ ፡ ክህነት ፡ የሚባሉት ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ሳይሾሙ ፡ በልዩ ፡ ጸሎትና ፡ ቡራኬ ፡ ኤጲስ፡ ቆጶስ፡

www.ethiopianorthodox.org

የሚባርኳቸው ፤ ከላይ ፡ ለዘረዘርናቸው ፡ ለሦስቱ ፡ ከፍተኞች፡ ማዕርጋት፡ አገልጋዮች ፡ የሚሆኑ ፡ ንፍቅ ፡ ዲያቆን ፤ አንባቢ ፤ አናጕንስጢስ ፡ ዘማሪ ፤ አጻዌ ፡ ኆኅት ፡ ናቸው (ፍት/ ነገ/ አንቀጽ፡፫) ሥልጣነ ፡ ክህነት፡ ጌታ ፡ ለሐዋርያት ፡ የሰጣቸው ፡ እንዲያሥሩና ፡ እንዲፈቱ ፤ ድውይ ፡ እን ዲፈውሱ ፤ ሙት ፡ እንዲያነሡ ፤ በጠቅላላም ፡ የነፍስና ፡ የሥጋ፡ድኅነት፡ የሚገኝበትን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ከፍተኛ፡ ሥልጣን፡ ነው ። ሐዋርያትም ፤ እንዲሁ ፡ ለተከታዮቻቸው ፡ በአንብሮተ ፡ እድ፡ እየ ሾሙ ፡ አስተላልፈዋል ፤ እንዲሁም ፡ እስከኛ ፡ ደርሷል፤ ከእኛም ፡ እስከ፡ ምጽአት ፡ ያለ ፡ ማቋረጥ ፡ የሚሰጥ ፡ ታላቅ ፡ ጸጋ ፡ ነው ።

## ፩ ፤ የክህነት ፡ ጅማሬ ።

በአንድ ፡ ነገር ፡ ማመን ፡ እርሱንም ፡ ማምለክ ፡ የሰው ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባዕይ ፡ ሲሆን ፤ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ለሚያምኑትና ፡ ለሚያመልኩት፡አም ላክ ፡ የተለዩ ፡ አገልጋዮች ፡ መምረጥም ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የተለመደ ፡ ነው ፤ ማለት ፡ እውነተኛውን ፡ አምላክ ፡ የሚያመልኩም ፡ ቢሆኑ ፤ በሐ ሰትና ፡ በጣዖትም ፡ የሚያመልኩ ፡ ቢሆኑ ፤ ለዚህ ፡ አገልግሎት ፡ ካህና ትን ፡ ወይም ፡ ካህናተ ፡ ጣዖታቱን ፡ ለይተው ፡ የሚሰጡ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ በዓለም ፡ ታሪክም ፡ የታወቀ ፡ ነው ፤ ለምሳሌ፡ በግብጽ ፡ የጣዖቱ ፡ ስም ፡ አሞን ፤ ራዕ ፡ ሲሆን ፡ እርሱን ፡ የሚያገለግሉ፡ ደግሞ ፡ ካህናት ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩ ፡ ሥራቸውም ፡ ኑሮዋቸውም ፡ የተ ለዩ ፡ ነበሩ፤በግሪክም ፡ ማንዴስ ፤ የሮፋንዴ ፡ ኢኦኖስኮፒ ፡ ይባሉ፡ ነበር፤ በእስራኤልም ፡ ቀድሞ ፡ ሌዋውያን ፡ የተባሉ ፡ የተለዩ ፡ ነገዶች ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ በሰፊው ፡ ያስረዳናል (ዘፀ/ ፳፰ ፡ ፩ ) ዛሬም ፡ ረቢ ፡ የተባሉ ፡ ይገኛሉ ። አሪት ፡ ለወንጌል ፡ አምሳል፡ መርገፍ፡ እንደ ፡ መሆኗ ፡ እውነተኛዪቱ ፡ ሕገ ፡ ወንጌል ፡ በተተካች ፡ ጊዜ ፡ የወን ጌል ፡ ሰባኪዎች ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልጋዮች ፡ የተለየ ፡ ስም ፡ የተ ለየ ፡ ማዕርግ ፡ የተለየ ፡ ሥራ ፡ ተሰጣቸው ። ይህም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ ራሱ፡ ጌታችን፡ዐሥራ፡ ኹለቱን፡ ሐዋርያት፡ ሥልጣነ ፡ክህነት ፡ ሰጣቸው፡ የካህናት ፡ አለቃ ፡ የሐዲስ ፡ ሕግ ፡ መሥራች ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኾነ ፡ ( ማቴ/ ፲ ፡ ፩—፵፪ ፤ ፳፰ ፡ ፲፱—፳ ) ማር/ ፯ ፡ ፯—፲፫ ፤ ሉቃስ ፡ ፱ ፡



፩—፯ ፤ ዮሐ/ ፳፡ ፳፩—፳፫) ፤ እንዲሁም ፡ በኀምሳኛው ፡ ቀን ፡ መንፈስ፡ ቅዱስን ፡ ላከላቸውና ፡ በአእምሮ ፡ እንዲጎለምሱ ፡ በዕውቀት ፡ እንዲታ ደሱ ፡ ምስጢር ፡ እንዲተረጕሙ ፡ በብዙ ፡ ቋንቋ ፡ እንዲናገሩ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ እንዲያገለግሉ ፡ አደረጋቸው (የሐ / ሥራ ፡ ፪ ፡ ፩—፵፯) ስለዚህ ፡ የክህነት ፡ ጀማሪ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኾነ ።

## ፪ ፤ ክህነት ፡ ቅዱስ ፡ አገልግሎት ፡ እንደ፡ኾነ።

ክህነት ፡ ታላቅ ፡ ምስጢር ፡ ቅዱስ ፡ አገልግሎት ፤ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ የሚሰጥ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ አንደኛ ፡ መሥራቹ ፡ ራሱ ፡ ክርስቶስ ፡ ቅዱስ ፤ ክቡርና ፡ ልዑል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው።እርሱ ፡ እንደ ፡ መሠረተው ፡ እርሱም ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ እንደ፡ ኾነ፡ «እግዚአብሔርም ፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ እንደ፡ ተባለ ፡ እንደ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ሹመት »(ዕብ/ ፯፡ ፲) እያለ ፡ ቅዱስ፡ ጳውሎስ ፡ ይመሰክራል ። ራሱ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ሆኖ ፡ ራሱን፡ መሥዋ ዕት ፡ አድርጎ ፡ ለዓለም ፡ ኀጢአት ፡ ማስተስረያ ፡ ሰጥቷልና ፤ ቀጥሎም ፡ ለርሱ ፡ ተከታዮች ፡ ለቅዱሳን ፡ ሐዋርያት ፡ አስተላልፏልና ። ኹለተኛ ፡ ሰውን ፡ ለማዳን ፡ ከኀጢአቱም ፡ ለማንጻት ፡ ታላቅ ፡ ኀይል ፡ አለውና ፤ የኀጢአት ፡ ሥርየት ፡ ለማንኛውም ፡ አማኒ ፡ በካህኑ ፡ አማካይነት ፡ ይሰ ጣልና ፤ የክህነትን ፡ ከፍተኝነት ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ፡ «ካህን፡ በምድር ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፤ በሰማይ ፡ ከሚኖሩ ፡ ከመላእክት፡ ነገድ፡ይቆ ጠራል» ፡ ሲል ፡ በድርሳኑ ፡ መስክሯል። ቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፡ «እናንተ፡ ግን ፡ የተመረጠ ፡ የመንግሥትና ፡ የክህነት ፡ ወገን፡ ናችሁ ፤ የተቀደሰች፡ ዘር ፤ ለርስት ፡ የተለየ ፡ ሕዝብ ፤ ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ማይነገር ፡ ብርሃን፡የጸ ራችሁን ፡ ሥራ ፡ ትገልጹ ፡ ዘንድ ፡ » (፩፡ጴጥ/ ፪፡፲) እያለ ፡ ከፍተኛነቱን፡ ገልጧል ። ካህናት ፤ የመፍታት ፡ የማሠር ፡ ሥልጣን ፡ ስለ ፡ ተሰጣቸው፡ የተከበሩ ፡ የተቀደሱ ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ አገልግሎታቸውም ፡ ማዕርገ ፡ ክህነት ፡ ቅዱስ ፡ አገልግሎት ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፫ ፡ ክህነት ፡ ከፍተኛ ፡ ማዕርግ ፡ እንደ፡ ኾነ ።

የክህነት ፡ ምስጢር ፡ ገላጭ ፡ የሥራው ፡ መሥራች ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ መላልሰን ፡ ተናግረናል ። ስለዚህ ፡ እርሱ ፡ የሠራው፡ እርሱ፡ ያከበረው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ማዕርግ ፡ ነው።ይህ፡ማዕርግ ፡ ለማንም፡ ሊ.ናኝ ፡ ማንም፡ ገንዘብ ፡ ሊያደርገው ፡ የማይችል ፤ ማንም ፡ በኀይል፡የማ ይዘርፈው ፡ በገንዘብ ፡ የማይገዛው ፡ ጸጋ ፡ ነው (የሐ / ሥራ፡ ፰፡ ፲—፳፬) ። ቅዱስ ፡ ዮሐንስም ፡ የክህነትን ፡ ማዕርግ ፡ ከፍተኛነት ፡ ሲመሰክር ፡ «ዘኢ.ተገብረ ፡ ለመላእክት ፡ ተገብረ ፡ ለካህናት ፡» ብሏል።ክህነት ፡ እግዚ አብሔር ፡ የሠራው ፡ ምስጢር ፡ ከመሆኑ ፡ ጋራ ፡ ሌላዎች ፡ ምስጢራት ፡ ያለርሱ ፡ የማይሠሩ ፡ የማይቀደሱ ፡ ጸጋም ፡ የማይሰጡ ፡ በመሆናቸው ፤ ከፍተኛነቱንና ፡ ቅዱስነቱን ፡ ይገልጣሉ ። ከዚህም ፡ ጋር ፡ ሰውን ፡ ከእግ ዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ የሚያስተያይ ፡ መንጥር ፡ ሕዝብን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ የሚያገናኝ ፡ ድልድይና ፡ መሰላል ፡ ነው ፤ ማለት ፡ ቄሱ፡ ኀጢአ ቱን ፡ ያስተሰረየለት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ዕንቅፋት ፡ ሳይመታው፡ ማዕበል፡ ሳያንገላታው ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ስለሚገባ ፤ እግዚአብሔርም፡ በክብር፡ ስለሚቀበለው፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ወርቅ ፡ የክህነትን ፡ ከፍተኛነት ፡ የካህናትን ፡ ሥልጣን ፡ ሲገልጥ ፤ «ካህ ናት ፡ በምድር ፡ የፈጸሙትን ፡ ጌታ ፡ በሰማይ ፡ ያጸናዋል ። የባሮችን ፤ ሐሳብ ፡ ጌታ ፡ ይቀበለዋል ፡ »ብሏል። ከማንኛውም ፡ ምድራዊ ፡ ሥራና ፡ ምድራዊ ፡ ሀብት ፡ እንዲሁም ፡ ምድራዊ ፡ ማዕርግ ፡ ክህነት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የተቀደሰ ፡ ማዕርግ ፡ ነው ፡ ምክንያቱም ፡ ማንኛውም ፡ ማዕርግ፡ ሥጋዊ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ ከሰውዬው ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ይጠፋል ፤ ክህነት ፡ ግን ፡ ሰውን ፡ ኹሉ ፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡ በወዲያኛውም ፡ ዓለም ፡ ለመንግ ሥት ፡ ተስማሚ ፡ አድርጋ ፡ ሳታልፍ ፡ የምትኖር ፡ ናትና ።

## ፬ ፡ የክህነት ፡ ችግር ።

ክህነት ፡ ከማንኛውም ፡ ሥራ ፡ የበለጠ ፤ ከማንኛውም ፡ ማዕርግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቅዱስ ፡ ማዕርግ ፡ እንደ፡ ኾነ ፡ አንበናል ፤ ይህን ፡ ማዕርግ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ ይፈታተኑታል ፤ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክን ያቶች ፡ ያሰናክሉታል ፤ ካህን ፡ የሚሆኑ ፡ ኹሉ ፤ የማዕርጉን፡ ከፍተኛነት፡



ብቻ ፡ መመልከት ፡ የለባቸውም ፤ ችግርና ፡ ፈተና ፡ እንዳለበት ፡ አው ቀው ፡ ወደው ፡ ለምደው ፡ መግባትና ፡ እንደ፡ክህነት ፡ ዓላማ ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ። አስቀድመውም ፡ የሚያመዛዝኑት ፡ አንደኛ ፡ በየጊዜው ፡ የሚመጣው ፡ ችግር ፡ ስሙም ፡ ዐይነቱም ፡ ብዙ ፡ መሆኑን ፡ ዐውቀው ፡ በዚህ ፡ ቢመጣ ፡ በዚህ ፡ ድል ፡ ይነሣል ፡ ብለው ፡ ዐቅማቸውን ፡ መሣሪያ ቸውን ፡ መመዘን ፤ ኹለተኛ፡ ዐቅምም ፡ ቢኖራቸው ፡ ድል ፡ የሚያደርጉ በትም ፡ መሣሪያ ፡ በእርግጥ ፡ ቢኖራቸው ፤ ተግተውና ፡ ነቅተው ፡ ተሰል ፈውም ፡ ለመኖር ፡ መቻላቸውን ፡ ማወቅ ፡ አለባቸው ። «ካህን ፡ ከመሆ ንህ ፡ በፊት ፡ የሚገጥምህን ፡ ችግር ፡ አጥና ፤ ለማዕርጉ ፡ ከፍተኛነት ፡ ብለህ ፡ ካህን፡ብትሆን ፡ ከክፉ ፡ ወጥመድ ፡ ትገባለህ ፡ » እያለ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ፡ወርቅ ፡ ይመክራል ። በቤተ፡ ክርስቲያን፡ላይ፡ ያለውን፡ ኀላፊነት ፡ አፓ ፍቶ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት፡መቆም ፡ ኹለተኛ፡ ሞት ፡ ነው፤ ይህን ፡ ከባድ፡ ኀላፊነት፡ ለመወጣት፡የጋለ፡ መንፈስ፡ የበረታ፡ ምኞት፡ መንፈሳዊ፡ ቅናት፡ ኖሮት ፡ ተግቶና ፡ ነቅቶ ፡ መሥራት ፡ አለበት ፤ «አቅምን፡ጠብቁ ፤ ትጉም፤ ሰይጣን ፡ ጠላታችሁ ፡ እንደሚጮህ ፡ አንበሳ ፡ ይዞራልና ፤ የሚውጠ ውን ፡ ሰው ፡ ሽቶ » (፩፡ጴጥ/ ፭፡፰፤ ሉቃ/፳፩፡፴፬፤ ፩፡ተሰሎ/፭፡፮) ። እያለ፡ ካህናትን ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ያስጠነቅቃል ። ታጥቆ ፡ ተሰልፎ ፡ መሣሪ ያን ፡ አሰናድቶ ፡ መኖር ፡ ለካህን ፡ ቀርቶ ፡ ለክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ የግድ ፡ እንዲገባ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ፡ ለኤፌሶን ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ በሰፊው ፡ ያስረዳል (ኤፌ/፯፡፲፩—፲፰) ካህኑ ፡ ሰንፎ ፡ ከመንጋው ፡ አን ደኛውን ፡ ቢያስነጥቅ ፤ ከመንጋው ፡ ባለቤት ፡ ይቅርታ ፡ የለውም ፤ ምክ ንያቱም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ሙቶለታል ፤ በንጹሕ ፡ ደሙም ፡ ገዝቶታልና ። (ዮሐ/፳፡፳፫) ምዕመናን ፡ በኀጢአት ፡ በሽታ ፡ በወደቁ፡ጊዜ ፡ እውነተኛ፡ ሐኪም ፡ ሁኖ ፡ ሳይውል ፡ ሳያድር ፡ በሽታውን ፡ ለማስወገድ ፡ መጣ ጣር ፡ አለበት ።

### የክህነት ፡ ችግሮች ፡ ኹለት ፡ ዐይነቶች ፡ ናቸው ፤

(ሀ)ውሳጣዊ፡ችግር፡ ይባላል፤እነዚህም፡ ችግሮች፡ ከካህኑ፡ ባሕርይ፡ የሚ መነጩ፡ናቸው ፤ ለምሳሌ ፡ መፍቀሬ ፡ ንዋይ ፡ መሆን ፤ ውዳሴ ፡ ከንቱን ፡ መውደድ፤ ስንፍናንና፡ ቸልተኝነትን፡ መውደድ፤ በሥጋዊ፡ ነገር፡ መታለል፤ ቍጡና ፡ ብስጩ ፡ መሆን ፤ ፈሪና ፡ አፋራም ፡ መሆን ፤ በቀላሉ ፡ ነገር ፡ ተስፋ ፡ መቍረጥ ፤ በጠቅላላው ፡ ከአሮጌው ፡ ውሳጣዊ ፡ ሰውነት፡የሚመ

www.ethiopianorthodox.org

ነጩ ፡ ሥጋውያን ፡ ፈቃዶች ፡ ናቸው ። እነርሱም ፡ ረቂቅ ፡ ወጥመድ ፡ ኹነው፡ ካህኑን ፡ አስረው ፡ ተብትበው፡ የሚይዙ፡ ናቸው ፡ ስለዚህ፡ ካህኑ ፡ እነዚህን ፡ እርግፍ ፡ አድርጎ ፡ ጥሎ ፡ በሐዲስ ፡ መንፈስ ፡ ተቃኝቶ፡ ከዚህ፡ ወጥመድ ፡ ማምለጥና ፡ መዳን ፡ አለበት ። « አታውቁምን ? ሩጫ ፡ ወዳለበት ፡ ስፍራ ፡ የሚቀድሙ ፡ ኹሉ ፡ እንዲሮጡ ፡ ይመወዙን ፡ ሽል ማቱን ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ከነርሱ ፡ ይወስዳል ። እላንትም ፡ እንዲሁ፡ ሩጡ፡ እንድታገኙ ፡ የሚጋደል ፡ ኹሉ ፡ ነገርን ፡ ኹሉ ፡ ይተዋል ። እሊህም ፡ የሚጠፋውን ፡ አክሊል ፡ ይወስዱ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እኛ፡ ግን፡ የማይጠፋ ውን ፡ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ እንዲሁ ፡ ሮጣለሁ ። ሳልታወቀ ፡ ነገር ፡ እንደሚ ሮጥ ፡ እንዳልሆን ። ነገር ፡ ግን ፡ ሥጋዬን ፡ አጥብቄ ፡ እቀጣለሁ ፡ አስገዛ ውም ፡ አለሁ ። ሌሎችን ፡ አስተምሬ ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ የተጣልሁ ፡ እንዳል ሆን» (፩/ቆሮ፡፱፡፳፬—፳፯ ፡ ሮሜ ፡ ፰፡ ፲፫ ፡ ፲፰፡ ፲፬) እያለ ፡ ካህን ፡ የሆነ ፡ ኹሉ፡ ከፈቃደ፡ ሥጋው ፡ ርቆ ፡ ፈቃደ ፡ ነፍስን ፡ እንዲከተል ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ያስተምራል።እንዲሁም ፡ «በመንፈስ ፡ ተመላለሱ ፡ የሥጋን ፡ ምኞት ፡ አትፈጽሙ ። ሥጋ ፡ መንፈስ ፡ የሚጠላውን ፡ ይወዳልና ፡ መን ፈስም ፡ ሥጋ ፡ የሚጠላውን ፡ እሊህም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይጣላሉ።እላ ንት ፡ የምትወዱትን ፡ ነገር ፡ እንዳታደርጉ ፡ በመንፈስ ፡ ግን ፡ ብትሄዱ ፡ ከኦሪት ፡ በታች ፡ አይደላችሁም » (ገላ / ፭ ፡ ፲፯—፳፯) እያለ ፡ እንኳን ፡ ካህን ፡ ማንም ፡ ክርስቲያን ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋውን ፡ መከተል ፡ እንደማይገ ባው ፡ በሰፊው ፡ አስረድቷል ።

(ለ) አፍአዊ ፡ ችግር ፡ ይህም ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ የሚመነጭ ፡ ካህኑን ፡ ዘወትር ፡ የሚዋጋ ፡ ነው ፡ ለምሳሌ ፡ የካህን ፡ ሥራ፡ሁሉ ፡ በሰው፡ዘንድ ፡ ይመረመራል ፡ ይገመታል ፡ ስለዚህ ፡ የካህኑ ፡ ትንሽ ፡ ጥፋት ፡ በሕ ዝቡ ፡ ዘንድ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ስለሚገመት ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ ካህኑን ፡ ያገኝ ዋል ፡ ይህንም ፡ ለማለፍ ፡ ካህኑ ፡ ያለበት ፡ ጥንቃቄ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። «ማንም ፡ ሕፃንነትህን ፡ አይናቀው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለምእመናን ፡ ምሳሌ ፡ ሁን ፡ በነገር ፡ በአካሄድ ፡ በፍቅር ፡ በመንፈስ ፡ በሀይማኖት፡ በንጽሕና » (፩፡ ጢሞ/ ፬፡ ፲፪—፲፯) እያለ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ጢሞቴዎስን ፡ እንደ ፡ መከረ ፡ ካህን ፡ በአካሄዱ ፡ በኑሮው ፡ በጠቅላላው ፡ ስሜቱ፡ ስለሚገመት፡ በዚህ ፡ ኹሉ ፡ መጠንቀቅ ፡ አለበት ። አንድ ፡ ሕዝባዊ ፡ ሰው ፡ ቢያጠፋ ፡ ጥፋቱ ፡ ለራሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የካህኑ ፡ ጥፋትና ፡ ነቀፌታ ፡ ግን ፡ ለኹሉ ፡



ስለሚደርስ ፡ ካህኑ ፡ ያለበት ፡ ችግር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ይህንም ፡ በአ ጭር ፡ ታጥቆ ፡ ተስልፎ ፡ የኖረ ፡ እንደ ፡ ኾን ፡ በቀላሉ ፡ ሊያልፈው ፡ ይችላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ለክህነት ፡ መጠራት ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ለአንድ ፡ ሥራ ፡ ጥሪ ፡ ወይም ፡ስጦታ፡ አለው፡ ይህም ፡ ስጦታ ፡ የተፈጥሮ፡ (የባሕርይ)፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ ወይም ፡ በት ምህርትና ፡ በልማድም ፡ ይገኛል ። ይህም ፡ ነገር ፡ እርግጠኛ ፡ መሆኑን ፡ የሚያስረዳ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ነገርን ፡ ይወዳል ፡ አንደኛውን ፡ይጠ ላል ፡ አንደኛውን ፡ አዘውትሮ ፡ ይሠራል ፡ ስለርሱም ፡ ይናገራል ፡ አን ደኛውን ፡ ግን ፡ ሊያየው ፡ ቀርቶ ፡ ሊሰማው ፡ አይወድም ። ይህ ፡ የመው ደድና ፡ የመጥላት ፡ ስሜት ፡ ኀይል ፡ «ጥሪ ፡ ወይም ፡ ስጦታ ፡ » ይባላል። የተፈጥሮ ፡ ስጦታ ፡ ወይም ፡ ጥሪ ፡ የተባለው ፡ በሳይኮሎጂ ፡ መንገድ ፡ የማይናወጥ ፡ ልባዊ ፡ ስሜት ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። የተፈጥሮ ፡ ስጦታ ፡ ወይም ፡ ጥሪ ፡ በትምህርት ፡ ምክንያት ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ እየ ተሻሻለና ፡ እያደገ ፡ እየተስፋፋም ፡ የሚሄድ ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ሕፃንን ፡ ከልጅነቱ ፡ ጀምሮ ፡ በዚህ ፡ ስጦታው ፡ ሊመሩትና ፡ ሊያሳድ ጉት ፡ ይገባል ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ የሆኑ ፡ ዕውቀትና ጥበባት ፡ ይገኛሉ ፡ የሰውም ፡ ስጦታው ፡ እንዲሁ ፡ የተለያየ ፡ በመሆኑ ፡ አንዱ ፡ የሚወደውንና ፡ የሚያዘወትረውን ፡ አንደኛው ፡ አይወደውም ፡ ስለ ፡ ርሱም ፡ ፍላጎት ፡ ከቶ ፡ የለውም ፡ ይህን ፡ ይዘው ፡ የቀደሙ ፡ አቱና ውያን ፡ ሕፃናት ፡ በመረጡት ፡ እንዲያድጉ ፡ በማለት ፡ ከሕፃንነታቸው ፡ ጀምሮ ፡ የሚሠሩትንና ፡ የሚናገሩትን ፡ ጠንቅቀው ፡ ይከታተሏቸው ፡ በዚያውም ፡ ያሳድጓቸው ፡ ነበር ፡ ይባላል። ካህንም ፡ የሚሆን ፡ ሰው፡ እን ዲሁ ፡ የተፈጥሮ ፡ ስጦታና ፡ ጥሪ ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል፤ ምክንያቱም ፡ የሕ ዝቡ ፡ መሪ፡የነፍሳቸውም ፡ ጠባቂ፡ የትሩፋት፡ አበጋዝ ፡ የመልካም፡ ሥራ፡ አብነት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከጀመረ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሊመለስ ፡ የማ ይችል ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡ « ኢየሱስም ፡ አለ ፡ ማንም ፡ የለም ፡ ማረሻ ፡ በእጁ ፡ ይዞ፡ወደ ፡ ኋላው ፡ የሚመለከት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ይሆን ፡ ዘንድ » (ሉቃ/ ፱፡ ፷፪) እያለ ፡ ያስተምር ፡ ነበር። ይህን፡ ለማለፍ
ለሥራውም ፡ መልካም ፡ ውጤትን ፡ ለማግኘት ፡ የሚችለው ፡ ቀድሞ
ውን ፡ ጥሪ ፡ ሲኖረው ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ሲታዘዝ ፡ ነውና ።

ይህ ፡ ጥሪ ፡ ሰማያዊ ፡ የኾነ ፤ ሰማያዊ ፡ አገልግሎት ፡ ያለው ፤ በሚ
ገባም ፡ ቢፈጽሙት ፡ ሰማያዊ ፡ ዋጋን ፡ የሚያሰጥ ፡ ስለ፡ኾነ ፤ ብዙዎች ፡
አክብረው ፡ ይቀበሉታል ፤ እንደ ፡ ጥሪያቸውም ፡ ለመፈጸም ፡ ታላቅ ፡
ተጋድሎን ፡ ያደርጋሉ ፤ ይህ ፡ ጥሪ ፡ ወይም ፡ ስጦታ ፡ የተባለው፡ ሀብት፡
ከእግዚአብሔር ፡ የሚሰጥ ፡ ወይም ፡ የሚጠራ ፡ ማለት ፡ ነው ። በብሉይ፡
ኪዳን ፡ አርእስተ ፡ አበው ፡ የተባሉት ፡ እነ፡ አብርሃም ፡ እነ፡ ሙሴ ፡ በመ
ላም ፡ ነቢያት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ እየተጠሩ ፤ ሀብተ ፡ ትንቢት ፡
እየተሰጣቸው ፤ ተልእኮዋቸውን ፡ ፈጽመዋል ። በሐዲስ ፡ ኪዳንም ፡ በክ
ርስቶስ ፡ የተጠሩ ፡ በመላ ፡ ሐዋርያት ፡ እነጳውሎስ ፤ ሰብዓ ፡ አርድእት ፡
ይህንም ፡ የመሰሉ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። ይህም ፡ ጥሪ ፡ በኹለት ፡ ይከፈ
ላል ፤ አንደኛው ፡ ውሳጣዊ ፤ ኹለተኛው ፡ አፍአዊ ፡ ጥሪ ፡ ይባላል ።

(ሀ) ውሳጣዊ ፡ ጥሪ ፡ ውሳጣዊ ፡ ጥሪ ፡ የተባለው ፡ በገጽ፡ ፴፱ ፡ እንደ
ገለጽነው ፡ በተፈጥሮ ፡ የሚሰጥና ፡ የሚጠራው ፡ አሳቡ ፡ የሚያዘነብል
በት ፡ በዚያውም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖርበት ፡ ከትምህርትም ፡ ጋራ ፡ የተከታተ
ለው ፡ እንደ፡ኾን ፡ መልካም ፡ ውጤትን ፡ የሚሰጥ ፡ ጥሪ ፡ ወይም ፡ ስጦታ፡
ነው ። ይህ ፡ ጥሪ ፡ ወይም ፡ ስጦታ ፡ ለማንኛውም ፡ ሥራ ፡ ለማንኛ
ውም ፡ ጥበብ ፡ የሚሰጥ ፡ ነው ፤ በተለይ ፡ ግን ፡ ሊጠነቀቁለት ፡ የሚገባ ፡
ለክህነት ፡ ማዕርግ ፡ ነው፤ ምክንያቱም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ስጦታ፡ወይም፡
ጥሪ ፡ ያለው ፤ ራሱም ፡ ወዶ ፡ ለምዶ ፡ የገባው ፡ ካህን ፡ ምንም ፡ ጊዜ ፡
ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጸዋትወ ፡ መከራ ፡ ቢጸናበት ፡ አይሠቀቅም ፤ አይመረርም ፡
እንዲያውም ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ በመከራ ፡ ላይ ፡ መከራ ፡ ቢጨመርለት ፡
ጸጋ ፡ እንዲበዛለት ፡ አምኖ ፡ ይሠራል» (ቆሮ/፲፫፡ ፱—፲፡ የሐ ፤ ሥራ ፡ ፭ ፡
፵—፵፪) ። ጥሪ ፡ ሳይኖረው፡ ራሱም ፡ ሳይወደው፡ የገባ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ በየጊ
ዜው ፡ ሲመረር ፡ ሲበሳጭ ፡ ለራሱ ፡ ቀርቶ ፡ ለሌሎችም ፡ የመሰናክል ፡
ድንጋይ ፡ ይኾናል ። ስለዚህ ፡ ካህን ፡ የሚኾን ፡ ሰው ፡ ሰውነቱን ፡ ይመር
ምር ፤ ጥሪውን ፡ ያክብር ፡ የኀላፊነቱን ፡ ከባድነት ፡ የሥራውን ፡ ብዛት ፡
አጥብቆ ፡ ያጥና።ጥሪ ፡ ወይም ፡ ስጦታ ፡ እንዲኖረው ፡ የፈለገ፡ እንደ፡ኾነ፤
አንደኛ ፡ ልባዊ ፡ ጸሎት ፡ ያድርግ ፤ ለማንኛውም ፡ ሥራ ፡ ተስማሚ፡ እን



ዲሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲፈቅድለት ፡ «ወይኩን ፡ ፈቃድከ፡ » እያለ፡
ይጸልይ ፤ ጸሎት ፡ የበር ፡ ኹሉ ፡ መክፈቻ ፡ የማትሰበር ፡ ቍልፍ ፡ ናት ።
ስለዚህ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ይጸልይ ፡ ክርስቶስ ፡ እንኳን ፡ ሐዋርያትን ፡ ለዚህ፡
ሥራ ፡ ሲመርጥ ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ወጥቶ ፡ ጸሎት ፡ ጸልዮ ፡
ነው።«ሆነም ፡ በዚያች፡ ወራት ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ወጥቶ ፡ ጸሎት ፡ ይጸልይ፡
ዘንድ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ጸሎትም ፡ ተግቶ ፡ ነበር » ሌሊቱን፡ ኹሉ ፡
ቀንም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ጠራ፡ከእርሳቸውም ፡ ዐሥራ፡
ኹለት ፡ መረጠ ፡ ሐዋርያት ፡ ያላቸውን » (ሉቃ / ፮ ፡ ፲፪—፲፫) ። ይህ ፡
የሚያስረዳን ፡ ለሺሚም ፡ ለተሺሚም ፡ አስቀድሞ ፡ ጸሎት ፡ ማድረግና ፡
ጥሪውን ፡ ወይም ፡ ስጦታውን ፡ ለማግኘት ፡ እንዲችል ፡ የሚረዳው ፡
መሆኑን ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ሥራው ፡
ጸሎት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንዲረዳው ፡ ነው (፩ ፡ ጢሞ / ፪ ፡ ፩—፫ ) ።

ኹለተኛ ፡ ይናዘዝ ፡ ኑዛዜ ፡ ያለፈውን ፡ የሠራውን ፡ ብቻ ፡ አይደ
ለም ፤ ወደፊትም ፡ ሊሠራው ፡ ያሰበው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ከእግዚአብሔር፡
ፈቃድ ፡ ጋራ ፡ እንዲተባበርለት ፡ ወይም ፡ ሰይጣናዊ ፡ ዐሳብ ፡ እንደሆን፡
እንዲተወው ፡ ማንኛውም ፡ ለመምህረ ፡ ንስሓው ፡ ይነግረዋል ፡ ደግ ፡
ዐሳብ ፡ እንደ፡ኾን ፡ «ወይኩን ፡ ፈቃድከ» ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር፡
ይጸልይለታል ፡ ሰይጣናዊ ፡ ዐሳብ፡ እንደ፡ ኾን ፡ በቶሎ ፡ ከመጥፎ፡ ዐሳቡ፡
እንዲመለስ ፡ ይመክረዋል ። ዐሳቡ ፡ ያልተብራራ ፡ እንደ ፡ ኾን ፡
እግዚአብሔር ፡ እንዲገልጥላቸው ፡ ኹለቱም ፡ ጸሎት ፡ ያደርጋሉ ፤ በመ
ጨረሻውም ፡ መልካም ፡ ውጤትን ፡ ያገኛሉ ፡ ስለዚህ ፡ ዐሳቡን ፡ለአበ፡
ነፍስ ፡ ቀርቶ ፡ ለሚወዱት ፡ ባልንጀራና ፡ ለሚያምኑት ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡
መንገርም ፡ መልካም ፡ ውጤትን ፡ ያስገኛል። እንደ ፡ ልቡ ፡ የመጣለትን፡
የሚናገርና ፡ የሚሠራ ፡ ኹሉ ፡ መሠረቱ ፡ ድቡሽት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ቤት፡
በቶሎ ፡ ይወድቃል ፤ አወዳደቁም ፡ ከባድ ፡ ይኾናል። «ይህንም ፡ ነገሬን፡
ሰምቶ ፡ የማያደርገው ፡ ሰው ፡ ሰነፍ ፡ ሰውን ፡ ይመስላል ፡ ቤቱን ፡ በአ
ሸዋ ፡ ላይ ፡ የሠራ፡ዝናምም ፡ ዘነመ ፤ ጐርፍም ፡ ጐረፈ ፡ ነፋስም ፡ ነፈሰ ፤
ያንንም ፡ ቤት ፡ መቱት ፤ ወደቀም ፤ አወዳደቁም ፡ ታላቅ ፡ ኾነ » (ማቴ/
፯፡፳፬—፳፯) እያለ ፡ በምክረ ፡ ካህን ፡ በፈቃደ ፡ ካህን ፡ ጸንቶ ፡ የኖረው፡
ዋጋውን ፡ ሲያገኝ ፡ ብቻውን ፡ ዐስቦ ፡ እንደ ፡ ልቡ ፡ የሚሠራ ፡ እንደዚህ፡
ወድቆ ፡ እንደሚቀር ፡ ክርስቶስ ፡ ያስተምረናል ።

www.ethiopianorthodox.org

ሦስተኛ ፡ መጽሐፍ፡ቅዱስን ፡ ማንበብ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ፡ማጥናት፡ ለተጠራበት ፡ ሥራ ፡ የበቃ ፡ ያደርገዋል ፤ ወይም ፡ በመንፈስ ፡ እንዲጠራ፡ ያደርገዋል ፤ « ከሕፃንነትህ ፡ ጀምረህ ፡ የተቀደሱትውን ፡ መጽሐፍ ፡ ተምረኻልና ፤ ለድኅነት ፡ ታስተምርህ ፡ ዘንድ ፡ የምትችል ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሀይማኖት ። መጽሐፍ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ተጻፈች ፤ ለትምህርትም ፡ ትረባለች ፤ ለዘለፋም ፡ ለተግሣጽም ፡ ለማስተ ማርም ፡ በጽድቅ» (፪፡ ጢሞ/ ፫፡ ፲፭—፲፯) እያለ ፡ ቅዱስ፡ ጳውሎስ፡ ተወ ዳጅ ፡ ልጁን ፡ ጢሞቴዎስን ፡ መክሮታል ። ከመጻሕፍትም ፡ ውስጥ ፡ በተ ለይ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ የጻፋቸውን ፡ ኹለቱን ፡ ወደ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ የተላኩትንና፡ ወደ፡ቲቶ ፡ የተላከውን ፡ የክህነት ፡ መልእክ ቶች ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩትን ፡ ማንበብ ፡ አለበት ። እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ የካ ህኑን ፡ ጥሪ ፡ የኀላፊነቱን ፡ ሥራ ፡ በዝርዝር ፡ ስለሚገልጡ ፤ ካህኑ ፡ አዘ ውትሮ ፡ ማንበብ ፡ ይገባዋል።ይህንም ፡ የመሰለ ፡ የአባቶችን ፡ ተግሣጽና፡ ድርሳናት ፡ ማንበብ ፡ ይጠቅማል ፤ ምክንያቱም ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ ይረ ዳል ፡ ብለው ፡ አውጥተው ፡ አውርደው ፤ ቅዱስ ፡ መጽሐፍን ፡ ምንጭ ፡ አድርገው ፡ ጽፈውታልና ።

አራተኛ፡ልከኛ ፡ ዕድሜ ፡ ይኑረው ፤ ጥሪውን፡ ወይም ፡ ስጦታውን፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሊያውቀው ፡ የሚችል ፡ ልከኛ ፡ ዕድሜ ፡ ሲኖረው ፡ ነው ፤ ሕፃንነት ፡ እንኳን ፡ ለክህነት ፡ ለማንኛውም ፡ ሥራ ፡ በቂ ፡ አለመሆኑን፡ አባቶች ፡ ተረድተው ፡ « ልጅ ፡ ያቦካው ፡ ለራት ፡ አይበቃም » ፡ እያሉ ፡ ይመስላሉ ። ምንም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሁነው ፡ የማያስቡና ፡ አላዋቂዎ ችም ፡ ቢኖሩ ፡ ሕፃንነት ፡ ብዙ ፡ ተከታይ ፡ ስላለው ፡ በበለጠ ፡ ያሠጋል ፤ ስለዚህ ፡ ከኻያ ፡ አምስት ፡ በታች ፡ ዕድሜ ፡ ያለው ፡ ለምንም ፡ ሥራ ፡ እንደማይጠቅም ፡ ተገንዝቦ ፡ ቸል ፡ ቢሉት ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ዕድሜ ፡ ከዲቁና ፡ ጀምሮ ፡ ሊታሰብበት ፡ ይገባል ።

(ለ) አፍአዊ ፡ ጥሪ ፤ አፍአዊ ፡ ጥሪ ፡ ማለት ፡ እንዲሁ ፡ ከውጭ ፡ የሚሰማ ፡ ድምፅ ፡ ነው ። ይህ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በኹለት ፡ ይከፈላል ፤ ቀጥ ተኛ ፡ አፍአዊ ፡ ጥሪና ፡ በገሆን ፡ የሚሆን ፡ አፍአዊ ፡ ጥሪ ፡ ነው ።

ቀጥተኛ ፡ ጥሪ ፡ ማለት ፤ በቀጥታ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚጠሩት ፡ ጥሪ ፡ የሚሰሙት ፡ ድምጽ ፡ ማለት ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ ያለ ፡ ጠባቂ ፡ ከቶ ፡ ትቶት ፡ አያውቅም ፤ ስለዚህ ፡ የርሱ ፡ እንደራሴ ፡ ሁነው ፡ በታማኝነት ፡ የሚጠብቁለትን ፡ ሲጠራና ፡ ሲመርጥ፡ድምፅ፡ ሲያ ሰማ ፡ ይኖራል ፤ ለምሳሌ ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ አብርሃምን ፡ ሙሴን፡ ኤል ያስን ፡ እንዲሁም ፡ በመላ ፡ ነቢያትን ፡ ሕጉን ፡ የሚያስተምሩለትን ፡ ትንቢት ፡ የሚናገሩለትን ፡ ሕዝቡን ፡ የሚያስተዳድሩለትን ፡ አስነሣ ። (ኦሪት፡ዘፀአ/ ፫፡፬—፳፪) ። በሐዲስ፡ኪዳንም ፡ በመላ ፡ ሐዋርያትንና፡ ሰብዓ፡ አርድዕትን ፡ ራሱ ፡ ጠራቸው (የሐ/ ሥራ፡ ፲፫፡ ፩—፫) «እርሳቸውም ፡ ለእ ግዚአብሔር ፡ ሲያገለግሉ ፡ ሲጾሙም ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አለ ፤ በርናባስ ንና ፡ ሳውልን ፡ ለዩልኝ ፤ ለጸራኋቸው ፡ ሥራ ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ጾሙ ፡ ጸለዩም ፤ እጃቸውንም ፡ በጫኑባቸው ፡ ጊዜ ፡ ሰደዱዋቸው» (የሐ/ ሥራ፡ ፲፫፡ ፪—፫) በመላ፡ ሐዋርያት፡ እንደ፡ ተመረጡ ፡ የሚያስረዳ ፤ «እናንተ፡ አልመረጣችሁኝም ፡ እኔ ፡ እላንትን ፡ መረጥኋችሁ ፡ እንጂ ፡ አስነሣኋ ችሁ ፡ ትሄዱ ፡ ዘንድ ፡ ፍሬም ፡ ታፈሩ ፡ ዘንድ ፡ ፍሬያችሁም ፡ ይኖር ፡ ዘንድ » ( ዮሐ/ ፲፭ ፡ ፲፮ ፤ የሐ/ ሥራ ፡ ፩ ፡ ፪—፳፬) ።

እንደዚህ ፡ እያደረገ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኀላፊ ፡ ጠባቂ ፡ አበ ፡ ነፍስ ፡ የሚሆኑትን ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲጠራቸው ፡ እናገኛለን ፤ ይህም ፡ ቀጥተኛ ፡ ጥሪ ፡ ይባላል ። ቀጥተኛ ፡ ያልኾነ ፡ አፍአዊ ፡ ጥሪ ፡ ማለት፡ደግሞ ፡ ከራሱ፡ከእግዚአብሔር ፡ ቀጥታ፡እንደዘረዘርነው ፡ ሳይሆን፡ በገሆን ፡ በሕልም ፡ በሰው ፡ ወይም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አማካይነት ፡ የሚጠሩት ፡ ጥሪ ፡ ነው ። በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚጠሩት ፡ ጥሪ ፡ ለም ሳሌ ፡ በርናባስንና ፡ ማትያስን፡ በምግባር፡ በሀይማኖት ፡ ፍጹም ፡ ሁነው፡ ቢያገኟቸው ፡ ሐዋርያት ፡ መረጡዋቸው « ኹለትም ፡ አቆሙ ፡ በፊታ ቸው ፡ ዮሴፍን ፡ በርናባስ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራውን ፡ ዮስጦስ ፡ ተብሎ ፡ የሚ ጠራውንም ፡ ማትያስን ። በጸለዩም ፡ ጊዜ ፡ አሉ ፤ አንተ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ የኹሉን ፡ ልብ ፡ የምታውቅ ፡ ከነዚህ ፡ ከኹለቱ ፡ አንዱን ፡ ግለጥ ፤ የመረ ጥኸውን ፡ የዚህችን ፡ ማገልገል ፡ የመልእክቲቱን ፡ ስፍራ ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ ይሁዳ ፡ የተዋትን ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፤ ዕጣም ፡ ተጣጣሉ ፤ ዕጣውም ፡ በማትያስ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፤ ከ፲፩ሥራ ፡ አንዱ ፡ ሐዋር ያት ፡ ጋራም ፡ ተቆጠረ» (የሐ / ሥራ ፡ ፩ ፡ ፳፫—፳፮) ። ይህንም ፡ የመ ሰለ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚደረግ ፡ ጥሪ ፡ እስጢፋኖስንና ፡ ሌሎቹን ፡ ስድስቱን ፡ ዲያቆናት ፡ እናገኛለን (የሐ / ሥራ፡ ፮ ፡ ፫—፯) ። ቀጥተኛ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ከእግዚአብሔር ፡ ያልሆነ ፡ እፍአዊ ፡ ጥሪ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጥሪ ፡ ምርጫ ፡ ለካህናት ፡ የኖራቸው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የሥራቸው ፡ እርምጃ ፡ ከዕለት ፡ ወደ ፡ ዕለት ፡ እየጐላ ፡ ይሄዳል ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## የካህን ፡ ትውልድ ።

በኦሪት ፡ ዘመን ፡ ለክህነት ፡ ሥራ ፡ የሚመረጠው ፡ ከሌዊ ፡ ዘር ፡ ብቻ ፡ ነበር ፡ ምንም ፡ ከዚያው ፡ በአካሉ ፡ ሙሉነት ፡ በግብረ ፡ ገብነቱ ፡ ፍጹምነት ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ብዙ ፡ ነገርም ፡ አስተያየትና ፡ ምርጫ ፡ ማድረጋቸውም ፡ ባይቀር ፡ ምርጫው ፡ የሚደረገው ፡ ከዚያው ፡ ከሌዊ ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ ነበር ፡ (ዘጸአ / ፵ ፡ ፲፪—፲፭) ። በሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ ቀርቶ ፡ ኹሉም ፡ ቅዱስ ፡ ሕዝብ ፡ ልዩ ፡ ወገን ፡ ኹኖ ፡ የመቀደስ ፤ የመወደስ ፤ የምስጢራት ፡ ኹሉ ፡ ተካፋይነት ፡ መብት፡ ለኹሁም ፡ እንዲኖረው ፡ በመካከል ፡ የነበረውን ፡ ልዩነት ፡ክርስቶስ፡ አጥፍቷል ፤ ስለዚህ ፡ ከማንኛውም ፡ ትውልድ ፡ መካከል ፡ ከማንኛውም፡ ዜጋ፡ ለዚህ ፡ የበቃውን ፡ መመረጥ ፡ ይቻላል ። ይቻላልም ፡ ስላልን ፡ ትልቅ ፡ ጥንቃቄ ፡ ሊደረግበት ፡ የሚገባው ፡ አንደኛ ፡ ከአዲስ ፡ አማኒ ፡ ወገን ፡ ባይኾን ፡ ደግ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ ስለ ፡ ሀይማኖት ፡ ስለ ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ ያለው ፡ አስተያየት ፡ ያነሰ ፡ ይሆንና ፡ እርሱም ፡ ሥራውንና፡ሥልጣኑን ፡ ያቀልዋል ፡ ሌሎችም ፡ በርሱ ፡ መንገድ ፡ ይሄዱና ፡ ከመልካሙ ፡ ጐዳና ፡ እንዳይወጡ ፡ ወይም ፡ ሰው ፡ እንጂ ፡ ቢያጡ ፡ ነው፤ እኔን ፡ የመረጡ ፡ እያለ ፡ እንዳይታበይ ፤ «አዲስ ፡ ተክልም ፡ በሀይማኖት፡ አይሁን ፡ ልቡ፡እንዳይታበይ ፡ ወደ፡ዲያብሎስም ፡ ፍርድ ፡ እንዳይወድቅ፡ » (፩ ፡ ጢሞ / ፫ ፡ ፮) ። ኹለተኛ ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ ከሌላቸው ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ እንዳይሆን ፡ ማለት ፡ በስም ፡ ክርስቲያን ፡ ሁነው ፡ በሥራ፡ ግን፡ ከአረማዊያን ፡ የበለጠ ፡ የሚሠሩ ፡ ይኖራሉና ፡ ከነዚህ ፡ የተወለዱ ፡ በልጅነታቸው ፡ የንጽሕናቸው ፡ ጠባይ ፡ ሳያድግ ፡ ለመልካም ፡ ነገር ፡ ቀናተኞች ፡ ሁነው ፡ በክህነት ፡ ሥራ ፡ ቆይተው ፡ የአሳደጓቸውና ፡ የወለዷቸው ፡ ሰዎች ፡ ልምድና ፡ ጠባይዕ ፡ ትዝ ፡ እያላቸው ፤ እንደ ፡ ሥዕልም ፡ ከፊታቸው ፡ ተቀርጾ ፡ ስለሚታያቸው ፡ በእሾኽ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡



ተዘራ ፡ አዝመራ ፤ ፍሬም ፡ እንደማይሰጥ ፡ መጥፎው ፡ ልማድ ፡ አስጨንቆና ፡ አስጠብቦ ፡ ወደ ፡ ወገኖቻቸው ፡ ሥራ ፡ ስለሚመልሳቸው ፤ በዘር መልካምነት ፡ በግብረ ፡ ገብነት ፡ አስተዳደግ ፡ ካላቸው ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ መምረጥ ፡ ታላቅ ፡ ጥቅምን ፡ ይሰጣል ። ከመልካም ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ የተወለደ ፡ በትሩፋትና ፡ በመልካም ፡ ምግባር ፡ እየተመራ ፡ ደግነትን ፡ ቅንነትን ፡ እየተመገበ ፡ ያደግና ፡ በዕድሜ ፡ ከፍ ፡ ሲል ፡ ደጋግ ፡ ሥራዎቹ ፡ ኹሉ ፡ አብረው ፡ ሲያድጉ ፡ በሥራም ፡ ሲገለጡ ፤ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ መልካም ፡ አብነት ፡ ሆኖ ፡ ሥራው ፡ ኹሉ ፡ ይከናወንለታል ። ከቤተ ፡ ሰብም ፡ በተለይ ፡ የእናት ፡ ግብረ ፡ ገብነትና ፡ መንፈሳዊነት፡ ሕፃናትን፡ ይስባቸዋል ፤ ማለት ፡ በጡዋት ፡ በማታ ፡ በቀንም ፡ ቢሆን ፡ የሚያዩና ፡ የማይለዩ ፡ እናታቸውን ፡ ስለ፡ኾነ ፤ ደግም፡ ቢሆን ፡ ክፉ፡ ነገር ፡ በበለጠ፡ ሊማሩት ፡ የሚችሉ ፡ ከእናታቸው ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ነገር ፡ በዓለም ፡ ታሪክም ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ የተረዳ ፡ ነው ። በታሪክም ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ ጐልቶ ፡ የሚታየው ፡ የሙሴ ፡ አስተዳደግ ፡ ነው። እናቱ ፡ ዮካብድ ፡ ብትከባከበውና ፡ ትንቢት ፡ ተስፋ ፡ የተነገረላቸው ፡ ሱባዔ ፡ የተቈጠረላቸው ፡ የእስራኤል ፡ ልጅ ፡ ነህ ፡ እያለች ፡ ብትመክረውና ፡ በዚህም ፡ መንፈስ ፡ ብታሳድገው ፡ በኋላ ፡ የፈርዖን ፡ ልጅነቱን ፡ ካደ ፤ «በሀይማኖትም ፡ ሙሴ ፡ ባአደገ ፡ ጊዜ ፡ ካደ ፤ የፈርዖን ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ እንዳይባል ። በመከራም ፡ ጊዜ ፡ መከራውን ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ወገን ፡ ጋራ፡ ወደደ ፤ በኀጢአት ፡ ጥቂት ፡ ዘመን፡ ደስ፡ ኪለው ፡ ይልቅ ፤ የክርስቶስን ፡ ስድብ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ፡የሚበልጥ ፡ ባለጠግነት፡ አድርጓልና ፡ ከምሥር ፡ ከብት ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ የዋጋውን ፡ መልካምነት ፡ ተመልክቶ ፡ ነበርና ። በሀይማኖት ፡ የምሥርን ፡ አገር ፡ ተወ ፤ የንጉሥንም ፡ ቁጣ ፡ አልፈራም ፤ የሚያየውም፡ እንደማያየው ፡ ስለሆነ በት ፡ ታገሠ ፤ «ዕብ / ፲፩ ፡ ፳፫—፳፯፤ ዘፀአ ፡ ፩ ፡ ፳፪፤ የሐ/ ሥራ ፡ ፯ ፡ ፳ ፡ ፴፯) እንዲሁም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ጢሞቴዎስን ፡ ሲመርጥና፡ ሲሾም፡ የራሱን ፡ እምነትና ፡ የቤተ ፡ ሰቡን ፡ መልካምነት ፡ መርምሮ ፡ እንደ ኾን፡ «ተንኰል ፡ የሌለበት ፡ ሀይማኖትህን ፡ አስባለሁና ፡ አስቀድሞ፡ በአሚታህ፡ በሎድያ፡ ያደረች ፤ በእናትህም ፡ በኤውንቄያ ፡ እኔም ፡ ደግሞ፡ አምናለሁ፡ ባንተ ፡ እንዳለች» (፪ ፡ ጢሞ / ፩ ፡ ፭ ፤ የሐ/ ሥራ ፡ ፲፮ ፡ ፩)

www.ethiopianorthodox.org

እያለ ፡ ያስረዳናል ። ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ዘቂሳርያም ፡ «የመጀመሪያውን፡ እግዚአብሔርን ፡ የማወቅ ፡ ትምህርት ፡ ያገኘሁት ፡ ከቡርክቲቱ ፡ እናቴ ፡ ነው » ሲል ፡ መስክሯዋል ። ጐርጐርዮስ ፡ በናቱ ፡ በኖና ፤ ዮሐንስ ፡ አፈርቅ ፡ በእናቱ ፡ በአንቱሳ ፡ ሌሎችም ፡ እንዲሁ ፡ በእናታቸው ፡ ደግ ነትና ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ ተመርተው ፡ አድገው ፡ ከፍጹምነት ፡ ማዕርግ ፡ የደረሱ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። ይህም ፡ የሚሆንበት ፡ የሕፃናት ፡ ልቡና ፡ እንዳ ልተጻፈበት ፡ ሰሌዳ ፡ ንጹሕ ፡ በመሆኑ ፡ ወይም ፡ እንደ፡መልካም፡ፊልም፡ ማንኛውም ፡ የሰሙትንና ፡ ያዩትን፤ ለማንሣት ፡ ዝግጁ ፡ ስለ፡ ኾነ ፡ ከቀ ናው፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ የሚወለዱትና ፡ የሚያድጉት ፡ የቀና ፡ መንፈስ ፡ የቀና፡ አስተያየት ፡ ሲቀስሙ ፡ አድገው ፤ በኋላ ፡ በሥራ ፡ ይገልጡታል ። ከመ ጥፎ ፡ ቤተ ፡ ሰብም ፡ የሚገኙ ፡ እንዲሁ ፡ የጠመመውን ፡ ዐሳብ፡ የጠመ መውን ፡ ሥራ ፡ ሲያዩና ፡ ሲሠሩ፡ ያድጉና ፡ ዘመናቸው ፡ ኹሉ፡ እንዲሁ፡ እንደተጣመመ ፡ ያልፋል ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## ክህነትን ፡ ከመቀበሉ ፡ በፊት ፡ ሊኖሩት ፡ የሚገባው ።

ለማንኛውም ፡ ሥራ ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ ሊኖረው ፡ እንደሚገባ ፡ ለመ ንፈሳዊም ፡ እንዲሁ ፡ አስፈላጊነቱን ፡ በሰፊው፡አትተናል ፤ ይሁን፡እንጂ፡ የተፈጥሮ ፡ ስጦታ ፡ ብቻ ፡ በቂው ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሌላም ፡ እርሱን ፡ የሚረዱና ፡ የሚያጸኑ ፡ ነገሮች ፡ ከውጭ ፡ የሚገኙ ፡ አሉ ።

### ሀ/ በመንፈሳዊነት ፡ ( በሃይማኖት ) ፡ በኩል ፤ የካህን ፡ ሥራው ፡

የእግዚአብሔርን ፡ ጐዳና ፡ ለመጥረግ ፡ ሰውን ፡ ኹሉ ፡ የእግዚአብ ሔር ፡ ማደሪያ ፡ መንፈሳዊ ፡ ዓለም ፡ ለማድረግ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ አስ ቀድሞ ፡ እርሱ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ የበረታ ፡ በሃይማኖት ፡ የጸና ፤ በበጎ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ያጌጠ ፡ መሆን ፡ አለበት።መንፈሳዊነትም ፡ ማለት ፡ በረቂቅነት ፡ የጠለቀ ፡ ከግዙፍ ፡ ዓለም ፡ ስሜትና ፡ ዐሳብ፡የራቀ ፡ ሥጋዊ፡ ፈቃድን ፡ ሥጋዊ ፡ ሥራን ፡ የሸሸ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስን ፡ እጅ ፡ ያደ ረገ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከሥጋ ፡ ብቻ ፡ የተወለደ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፤ ዐሳቡም ፡ ሥራውም ፡ ሥጋዊ ፡ ብቻ ፡ ይሆናል ። ክርስቲያን ፡ ግን ፡ በመንፈስ ፡



ከእግዚአብሔር ፡ የተወለደ ፡ መንፈሳዊ ፡ ኾኖ ፡ መንፈሳዊነትን ፡ ገን ዘብ ፡ ያደርጋል ፤ መንፈሳዊ ፡ ሥራንም ፡ ይሠራል ፤ «ከሥጋ ፡ የተወለደ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፤ ከመንፈስም ፡ የተወለደው ፡ መንፈስ ፡ ነው» (ዮሐ/ ፫፡ ፮)። መንፈሳዊነትን ፡ የሚገልጡ ፡ አራት ፡ ነገሮች ፡ አሉ ።

### ፩ኛ/ የጸና ፡ ሀይማኖት ፤ ሀይማኖት ፡ ማለት ፡ ያልታየውን ፡

እንደታየ ፤ ያልተደረገውን ፡ ነገር ፡ እንደተደረገ ፡ አድርጎ ፡ መቀበል ፡ ማለት ፡ ነው « ሃይማኖትም ፡ ማመን ፡ ነው ፤ ተስፋ ፡ በተደረገችው ፡ ነገር ፡ የማትታየውንም ፡ ነገር ፡ ማየት ፤ ...በሃይማኖት፡ እናውቃለን፤ ዓለ ማት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንደ፡ተዘጋጁ ፡ ከማይታየውም ፡ ነገር ፡ የሚታየው ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ኾነ» (ዕብራ / ፲፩ ፡ ፩—፫)። ሀይማኖት ፡ የል ቡና ፡ ማረፊያ ፡ ወደብ ፡ ነው ። ሀይማኖት ፡ ከሌለ ፡ ልባችን ፡ በዐሳብና ፡ በጥርጥር ፡ ማዕበልነት ፡ ሲናወጽ ፡ ይኖራል።ሀይማኖት ፡ የሥራው፡ኹሉ፡ መጀመሪያና ፡ መጨረሻ ፡ ነው ፤ ማንኛው ፡ ነገር ፡ ውጤት ፡ እንዳለው ፡ ካለመነ ፡ ሊጀመር ፡ አይችልም ፤ ካልጀመረም ፡ ሊጨርስ ፡ አይችልምና፤ ሀይማኖትም ፡ የጸና ፡ መኾን ፡ አለበት ፤ ዘመን ፡ መከራ ፡ የማይለው ጠው ፤ ጥርጥር ፡ የሌለበት፤ ፍጹም ፡ ሀይማኖት፡ ከሌለው ፡ ለማን ፡ ብሎ፡ ይሠራዋል ? ተግቶስ ፡ ካልሠራ ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ ያገኛል ? ፍጹም ፡ ሀይማኖት ፡ ለኹሉ ፡ ሲገባ ፤ አብነት ፡ ለሚኾነው ፡ ለካህኑ ፡ በተለይ ፡ የበለጠ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

### ፪ኛ/ ፡ ፍጹም ፡ ፍቅር ፡ በክርስቶስ ፤ ፍጹም ፡ ፍቅር ፡ ማለት ፡

እንከን ፡ ጥርጥር ፡ የሌለበት ፡ እውነተኛ ፡ ፍቅር ፡ ማለት ፡ ነው ። በክርስ ቶስ ፡ ያለን ፡ ፍቅር ፡ ምንም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ የቀዘቀዘ ፡ ሊሆንና ፡ አንድ፡ ምክንያት ፡ ሊኖርበት ፡ አይገባም ። ምክንያቱም ፡ አስቀድሞ ፡ እርሱ ፡ በፍጹም ፡ ፍቅር ፡ ወደደን ፤ ስለኛም ፡ ራሱን ፡ አሳልፎ ፡ ለሞት ፡ ሰጥቶ ታልና ፡ እርሱም ፡ ከሕግጋቱ ፡ ኹሉ ፡ ፍጹም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍቅር፡ እንደምትበልጥ « ኢየሱስም ፡ አለው ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክህን ፡ ትወድ ፡ ዘንድ ፤ በፍጹም ፡ ነፍስህ ፡ በፍጹም ፡ ልብህ ፡ በፍጹም፡ ዐሳብህ ፡ ይህች ፡ መጀመሪያዪቱ ፡ ትእዛዝ ፡ የምትበልጥ ፡ ናት ። ኹለተኛ ዪቱም ፡ የምትመስላት ፡ ባልጀራህን ፡ ትወድ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ነፍስህ ፤ በሊህ ፡ በኹለቱ ፡ ትእዛዛት ፡ አሪት ፡ ኹሉ ፡ ነቢያትም ፡ ተሰቅለዋል። »



www.ethiopianorthodox.org

(ማቴ/ ፳፪ ፡ ፴፯—፵) እያለ ፡ አስተማረን ። ቀጥሎም ፡ « አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ከኔ ፡ ይልቅ ፡ የወደደ ፡ ለኔ ፡ ሊሆን ፡ አይገባውም » ( ማቴ/ ፲ ፡ ፫ ) እያለ ፡ እንዲሁ ፡ መስክሯል ። ጴጥሮስን ፡ ወደ ፡ ቀደመው ፡ ሐዋርያነት ፡ ማዕርጉ ፡ ወደ ፡ ቀደመ ፡ ብፅዕናው ፡ የመለሰው ፤ የፍቅርን ፡ መማለጃ ፡ ከተቀበለው ፡ በኋላ ፡ ነው (ዮሐ/ ፳፩ ፡ ፲፰—፲፱) ። ካህን ፡ የሚኾነው ፡ አስቀድሞ ፡ ከኹሉ ፡ በፊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማፍቀርና ፡ ፍቅሩንም ፡ በሥራ ፡ መግለጥ ፡ አለበት ። የክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ ለክርስቲያኖች ፡ ኹሉ ፡ ይገባል ፤ ምክንያቱም ፡ አስቀድሞ ፡ የወደደን ፡ እርሱ ፤ ከሞትም ፡ ያዳነን ፡ እርሱ ፡ ነውና «እኛ ፡ እንወድዋለን ፤ አስቀድሞ ፡ እርሱ ፡ ወዶናልና » (፩ ፡ ዮሐ / ፬ ፡ ፲፱ ) እያለ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ፍቁረ ፡ እግዚእ ፡ ያስተምረናል ። ለካህን ፡ የክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ ፍቅር ፡ በልቡናው ፡ ሰፍሮ፡ የኖረ ፡ እንደ ፡ ኾነ፡ ማንኛቸውም ፡ መከራ ፤ ማንኛቸውም ፡ ፈተና ፡ ከቶ ፡ አይለውጠውም ፡ እንደ፡ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ «ማነው ፡ ከክርስቶስ ፡ ፍቅር፡ የሚለየን ፤ ሐዘንን ፡ ጭንቀትን ፡ ስደትን ፡ ራብን ፡ መራቈትን ፤ ፍርሃትን ፡ ሰይፍን ፡ . . . . . እኔ ፡ በልቤ፡ አምናለሁ፡ ሞትም ፡ ቢሆን፡ ሕይወትም ፡ መላእክትም ፡ አለቆችም ፡ ኀይላትም ፡ የኾነውም ፡ የሚኾነውም፡ ከፍታም ፡ ዝቅታም ፡ ሌላም ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ሊለየኝ ፡ አይችልም ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ በጌታችን » (ሮሜ / ፰ ፡ ፴፭—፴፱) እያለ ፡ ይመሰክራል ። የክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ ፍቅር ፡ የሌለው ፡ ካህን ፡ የክርስቶስ ፡ መንጋን ፡ ተግቶ ፡ ነቅቶ ፡ ሊጠብቅ ፡ አይችልም ፤ ስለዚህ ፡ መጀመሪያ ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በልቡ ፡ እንደ ፡ ዘሩን ፡ እንዲዘረጋ ፡ ያስፈልገዋል ።

፫ኛ/ ፤ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፤ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ መጠበቅ ፡ እርሱን ፡ ማምለክ ፤ የሚገባ ፡ ክብሩን ፡ መስጠት ፡ አምላኤ ፡ ዓለማትነቱን ፡ ፈጣሪ ፡ ፍጥረትነቱን ፡ ታላቅነቱን ፡ ልዑልነቱን ፡ እያሰቡ ፡ መፍራት ፡ ነው ። የራስን ፡ ኀጢአት ፡ እያሰቡ ፤ ይቀስፈኛል ፡ ያጠፋኛል ፡ የሚለው ፡ ዐሳብ ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር፡ አይባልም ፤ ቅዱስ ፡ ፍርሃት ፡ የሚባለው ፡ ፍጹም ፡ ፍቅሩን ፡ አውቆ ፡ ልዑልነቱን ፡ መጋቢነቱን ፡ የዓለም ፡ ገዥ ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፤ ከርሱ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ መሄድ ፡ አለመቻሉን ፡ ዐውቆ ፡ መፍራት ፡ ነው ፤



ይህም ፡ ለካህኑ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ የሚገባ ፡ ነገር ፡ ነው ።

፬ኛ/ ፤ መንፈሳዊ ፡ ቅናት ፤ ለካህን ፡ መንፈሳዊነትና ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅናት ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ፤ ይህም ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅናት፡ ከፍጹም፡ ፍቅር ፡ የሚመነጭ ፡ ነው ፤ ማለት ፡ ክርስቶስን ፡ ከመውደዱ ፡ የተነሣ ፡ ለመንግሥቱ ፡ ስፋት ፡ ለህይማኖቱ ፡ ጽናት ፡ ለወገኖቹ ፡ ብዛት ፤ ቀንቶ ፡ ሕወቱን ፡ በመላ ፡ ለዚህ ፡ ቅዱስ ፡ ምግባር ፡ ያውለዋልና ። ይህን ፡ የመሰለ ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅናት ፡ በቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ መልቶ ፡ ሰፍቶ ፡ ይገኝ ፡ ስለ፡ነበር ፤ «ነገር ፡ ግን ፡ እኔ፡ ከሰው ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ አርነት ፡ የወጣሁ፡ ስሆን ፡ ራሴን ፡ ለኹሉ ፡ አስገዛሁ ፤ ኹሉን ፡ ዕረባ ፡ ዘንድ ፡ ከአይሁዳዊም ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ አይሁዳዊ ፡ ሆንኩ ፡ አይሁድን ፡ ዕረባ ፡ ዘንድ ፡ ከኦሪት ፡ በታች ፡ ካሉት ፡ ጋራ ፡ ከኦሪት ፡ በታች ፡ እንዳለሁ ፡ ሆንኩ ፡ ከኦሪት ፡ በታች ፡ ያሉትን ፡ እረባ ፡ ዘንድ፡ ሕግ ፡ ከሌላቸው ፡ ጋራ ፡ ሕግ፡ እንደሌላቸው ፡ ሆንኩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያለ፡ሕግ፡አይደለሁም፡ በክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ አለሁ ፡ እንጂ ፤ ሕግ ፡ የሌላቸውን ፡ እረባ ፡ ዘንድ ፤ ከደካሞች ፡ ጋራ ፡ እንደደካሞች ፡ ሆንኩ ፤ ደካሞችን ፡ እረባ ፡ ዘንድ ፤ ከኹሉ፡ጋር፡ እንደርሳቸው ፡ ሆንኩ ፤ ከርሳቸው ፡ ሰዎች ፡ ፈጽሜ ፡ አድን፡ ዘንድ » — (፩ ፡ ቆሮ / ፱ ፡ ፲፱—፳፺) እያለ ፡ ጮሆ ፡ አሰምቶ፡ ተናገረ ። «ለምትበልጥ፡ ጸጋ ፡ ቅኑ፡ »(፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፴፩)፡ እያለም ፡ ይመክራል ። ይህን ፡ የመሰለ፡ የመንፈሳዊ፡ ቅናት ፡ የሌለው ፡ ካህን ፡ ምንም ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ። ክርስቶስ ፡ ለአባቱ ፡ ሕግ፡ ለአባቱ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ቀናተኛ ፡ ሆኖ ፤ በቤተ ፡ መቅደስ፡ የሚሸጡትን፡ የሚለውጡትን፡ ካስወጣ፡ በኋላ ፡ የጸሎቱን ፡ ቤት ፤ የአባቱን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የሌባ ፡ ዋሻ ፤ የወንበዴ ፡ ጋሻ ፡ አደረጋችኋት ፡ « የቤትህ ፡ ቅናት ፡ በላችኝ ፡ » (መዝ / ፷፱ ፡ ፲)፡ ብሎ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ከምድራውያን ፡ ነገሥታት ፡ ከሌዋውንያን ፡ ካህናት ፡ ውስጥ ፡ አይደለ ፡ ይህን ፡ የሚሠራው ፡ በማን ፡ ሥልጣን ፡ ነው? እያሉ ፡ ሲያጕረመርሙ «ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ዐሰቡ ፡ ተጽፎ ፡ እንዳለ ፤ የቤትህ ፡ ቅናት ፡ በላችኝ ፡ የሚል ፡ »ስለዚህ ፡ በሚገባ ፡ እንዲሠራ ፡ አረጋገጡ ። ይህም ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅናት ፡ ቅዱስ ፡ ቅናት ፡ ይባላል ፤ ምክን-

www.ethiopianorthodox.org

ቱም ፡ ርኩስ ፡ ቅናት ፡ አለና ፡ ከዚያ ፡ ለመለየት ።ርኩስ ፡ ቅናት ፡ የተባ
ለውም ፡ በኹለት ፡ ይከፈላል ፤

አንደኛው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ በተንኰል ፡ በባልጀራው፡ በሀብቱ ፤ በቤቱ ፤
በጤናው ፡ በጠቅላላውም ፡ በኑሮው ፡ የሚቀናው ፡ ቅናት ፡ ነው ። ሁለተ
ኛው ፡ ያለ ፡ እውቀት ፡ በሞኝነት ፡ ወይም ፡ በድንቁርና ፡ የሚቀኑት ፡
ቅናት ፡ ነው ፡ ለምሳሌ ፡ መጥፎ ፡ ሥራ ፡ ደግ ፡ መስሏቸው ፡ በዚህ ፡ አንገ
ታችንን ፡ እንሰጥበታለን ፡ ሕይወታችንን ፡ እናሳልፍበታለን ፤ የሚሉት ፡
ነው ፤ «እኔ ፡ እመሰክርላቸዋለሁ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ቅናት ፡ እንዳላቸው ፡
ነገር ፡ ግን ፡ በዕውቀት ፡ አይደለም ። የእግዚአብሔርን ፡ ጽድቅ ፡ አላወቁ
ምና ፡ ለራሳቸውም ፡ የሠሩትን ፡ ያጸኑ ፡ ዘንድ ፡ ሽተዋልና ፤ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ጽድቅ ፡ አልተገዙም» (ሮሜ ፡ ፲ ፡ ፪—፫) ፡ እያለ ፡ ቅዱስ ፡ ጳው
ሎስ ፡ እንደ ፡ መሰከረባቸው ። መንፈሳዊ ፡ ቅናት ፡ የተባለው ፡ ደጉን ፡
ከክፉ ፡ ለይቶ ፡ ዐውቆ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ቀናተኛ ፡ መሆን ፡
ነው ።

ለ/ ፡ በፍጹም ፡ ምግባር ፡ (ሞራል) ፡ በኩል ፤ ካህን ፡ የሚሆን፡ ኹሉ፡
ፍጹም ፡ ምግባራዊ ፡ አስረጂ ፡ ኑሮት ፤ በአፋኣዊ ፡ ሥራ ፡ ተመስክሮለት ፡
ካልተሾመ ፡ እንዲሁ ፡ የገባ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የሕዝብ ፡ መጥፎ ፡ ግምት ፡
ሊወድቅበት ፤ ከሰይጣን፡ ወጥመድ፡ ሊገባ ፡ ይችላል «ደግሞ ፡ ደኅና ፡ ምስ
ክር ፡ በሜዳ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ የሚሆንለት ፡ ይሁን ፡ ወደ ፡ ስድብ ፡ እንዳ
ይወድቅ ፡ ወደዲያብሎስም፡ ወጥመድ» (፩ ፡ ጢሞ /፫ ፡ ፯) ፡ እያለ፡ ቅዱስ፡
ጳውሎስ ፡ ያስጠነቅቃል ። የምግባራትም ፡ ስልቶች ፡ ስማቸው ፤ ዐይነታ
ቸው ፡ ብዙ ፡ ሲሆኑ ፡ ለካህኑ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ መስለው ፡ የታዩት ፡
እነዚህ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

፩ኛ/ ቅድስና ፤ ይህም ፡ ማለት ፡ ከማንኛውም ፡ ጥርጥር ፡ ትእዝ
ብት ፡ ያልገባ ፤ በምንም ፡ የማያሙት ፡ ማለት ፡ ነው ። ካህን፡ በእርግጥ፡
ቅዱስ ፡ ካልሆነና፡ የሚያሰኘውንም ፡ ሥራ፡ ካልሠራ፡ ከሕዝቡም ፡ በዚህ፡
ካልተለየ ፤ የሚታማ ፡ የሚጠረጠር ፡ በመጥፎ ፡ ግምት ፡ የሚገባ ፡ እንደ
ሆን ፡ ከቶ ፡ ከኀላፊነቱ ፡ ሥራ ፡ አንደኛውን ፡ እንኳን ፡ ሊያከናውን ፡
አይችልም። ስለዚህ ፡ በማንኛውም ፡ ነገር፡ ተጠንቅቆ፡ መልካም፡ አብነት ፡



የሚሆንበቅን ፡ ብቻ ፡ እየሠራ ፡ ኑሮው ፡ ኹሉ ፡ የተቀደሰ ፡ በንጽሕና ፤
በቅድስና ፡ ያጌጠ ፡ መኾን ፡ አለበት ፤ ምክንያቱም ፡ ከካህኑ ፤ አንድ ፡
ጥፋት ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ኾነ፡ ፍጹም ፡ ኀጢአት ፡ የሠራው ፡ ኹሉ ፡ የራ
ሱን ፡ እየተወ ፡ የካህኑን ፡ አስፋፍቶ ፡ ስለሚናገርና ፡ ለሕዝብም ፡ ዕንቅ
ፋት ፡ ስለሚኾን ፡ ነው ። በሕዝብ ፡ ግምት ፡ ሚዛን ፡ ገብቶ ፡ ቀሎ ፤ ጎድሎ ፡
የተገኘ ፡ ካህን ፡ ወዮለት ! ሕዝብ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መጥፎ ፡ ግምትን ፡
ከጣለ ፤ መጥፎም ፡ ስምን፡ ካወጣለት፡ መቸም፡ ቢሆን ፡ ሊለወጥና ፡ ሊታ
ደስ ፡ አይችልም ። ሕዝቡም ፡ የርሱን ፡ አብነትነት ፡ እየተከተለ ፡ ስለ
ሚበድል ፡ ለመጥፎው ፡ ሥራ ፡ አብነት ፡ ሆኖ ፡ ሕዝብን፡ የሚያሰናክል ፡
ወዮለት ! « ከነዚህም ፡ ከታናናሾቹ ፡ በኔ ፡ ከሚያምኑት ፡ አንዱን ፡ ያሰ
ነካከለ ፡ የወፍጮ ፡ ድንጋይ ፡ በአንገቱ ፡ ታስሮ ፡ ወደ ፡ ጥልቅ ፡ ባሕር ፡
በሰጠመ ፡ ይሻለዋል ፡ » (ማቴ/ ፲፰ ፡ ፮) ፡ እያለ ፡ ክርስቶስ ፡ አስቀድሞ ፡
ያስጠነቅቃል ። አብነት ፡ ከሚሆንበት ፡ ሥራ ፡ በቀር ፡ ለካህን ፡ ከመጥፎ ፡
ሥራ ፡ መራቅ ፡ አለበት ፤ ቅዱስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሥራም ፡ መሥራት ፡ የቀ
ደመ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ። መጥፎ ፡ ሥራ ፡ በስውር ፡ እየሠራ ፡ ሕዝብ ፡ አያ
ውቅብኝም ፡ ሊል ፡ አይችልም ፤ ምክንያቱም ፡ ልቡናን ፡ ያህል ፡ ታዛ
ቢና ፡ ገማች ፤ ከካሽም ፡ ባላንጋራም፡ ሳለ ፡ ከቶ፡ ሰው፡ ተሠውሮ ፡ ሊቀር፡
አይችልም ። ሰው ፡ በተመለከተው ፡ ጊዜ ፡ ኀጢአቴን ፡ አወቀብኝ ፡
ማን ፡ ነገረብኝ ፡ ይሆን ፡ እያለ ፡ በኃፍረትና ፡ በፍርሀት ፡ መጋረጃ ፡ ተሰ
ውሮ ፡ ይኖራል። ከዚህ፡ ኹሉ፡ ለመዳን ፡ ካህን ፡ አስቀድሞ ፡ በምግባርና፡
በሀይማኖት ፡ የከበረ ፡ ቅድስናን ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

፪ኛ/ አስተዋይነት ፤ አስተዋይ ፡ ማለት ፡ የአእምሮ ፡ ዐይን ፡
ያለው ፤ ክፉውን ፡ ከደግ ፡ ለይቶ ፡ የሚያውቅ ፤ የአእምሮ ፡ ጤንነትና ፡
የአእምሮ ፡ ሚዛን ፡ ያለው ፤ ኹሉን ፡ የሚገምት ፤ በአእምሮው ፡ የሚያዝ
በት ፡ ማለት ፡ ነው ። ከቶ ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ አስቦ ፡ በሠራው ፡ ተጸጽቶ
አያውቅም ። እንዲያውም ፡ ሥራው ፡ መልካም ፡ ውጤትን ፡ ስለሚሰ
ጠው ፡ ኹልጊዜ ፡ ሲደሰት ፡ ይኖራል ። አስተዋይነት ፡ ከምግባር ፡
ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ያላት ፤ በሠሩት ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ፡ የምታሰጥ ፡ ሥራ ፡
ናት ። እርስዋን ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገ ፡ ኹሉ ፡ ደስታን ፤ መታደስን ፤
ረፍም ፡ ዕድሜንም ፡ ክብር ፡ ያለው ፡ ሽምግልናንም ፡ ገንዘብ ፡ አድርጎ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ይኖራል ። አስተዋይነት : ከሌለ : ዕድሜ : ሊረዝም : አይችልም ፤ ቢረ
ዝምም : በሽምግልናቸው : ሲያፍሩበትና : ሲጸጸቱበት : ይኖራሉና ።
ኹሉም : ያልፋል : አስተዋይነት : ግን : እስከ : መጨረሻው : ሕቅታ :
ቆይታ : ለሰው : መልካም : ዝናንና : ክብር : ያለው : ታሪክን : ታሰጣ
ለች : አስተዋይነት : ለሰው፡ልጅ : ኹሉ : የግድ፡አስፈላጊ : ሲሆን : ካህኑ፡
ግን : በበለጠ : አስፋፍቶ : ሊይዘው : ይገባዋል ። ያለ : አስተዋይነት ፤
ያለ : ዕውቀት : የሚሠሩት : ሥራ : ኹሉ : ከንቱ : ዋጋ : ቢስ : ስለ :
ኾነ ፤ የሮሜን፡ ሰዎች : «እኔ : ግን : እለምናችኋለሁኝ : ወንድሞቼ : ሆይ፡
በእግዚአብሔር : ምሕረት : ሥጋችሁን : ታቀርቡ : ዘንድ : ሕያው : መሥ
ዋዕት : አድርጋችሁ : የተቀደሰች : እግዚአብሔርን : ደስ : የምታሰኝ :
እርስዋም : በአእምሮ : ማገልገላችሁ : ናት » ( ሮሜ : ፲፪ : ፩ ) : እያለ :
ቅዱስ : ጳውሎስ : ይመክራል ።

፫ኛ/ በቂ : እውቀት ፤ ካህን : የሚሆን : ሁሉ : በቂ : እውቀት፡
ያለው : ሊኾን : ይገባል : የዕውቀቱም : ዐይነት : ከሌሎች : የበለጠ :
ሊኾን : ያስፈልጋል ። ዕውቀት : በሁለት : ይከፈላል : ይኸውም : አንደ
ኛው : የተፈጥሮ : ዕውቀት ፤ ኹለተኛው : ደግሞ : የትምህርት :
ወይም : የልምድ : ዕውቀት : ነው ።

ሀ/ የተፈጥሮ : ዕውቀት : እግዚአብሔር : በጥንተ : ተፈጥሮ :
ሰውን : ዐዋቂ : አድርጎ : ፈጥሮታል : የዚያ : ጸጋ : በአንዳንዱ : ሰው :
የበዛ : ሲሆን : ሳይማር : ዐዋቂ : ይሆናል ፤ ይህም : የተፈጥሮ : ዕውቀት፡
ይባላል ። ደግሞም : እንዲሁ : ጥበቡን : ትምህርቱን : ኹሉ : ሲሮጥ :
ይይዘዋል : ማለት : የተፈጥሮ : ዕውቀቱ : ከፍ : ያለ : ሆኖ :
ሲነገር . . . ሲወራ : የሰማውን : በቶሎ : ይይዘዋል ፤ በሥራም : ይገልጠዋል።
ስለዚህ : ካህን : የሚሆን : ኹሉ : ይህ : የተፈጥሮ : የእውቀት : ጸጋና :
የመረዳት : ኀይል : በበለጠ : ሊኖረው : ይገባዋል ። ከኹሉም : ይልቅ :
የተፈጥሮ : ዕውቀት : የኖረው : እንደሆን፡ ኹሉን : ማስተዋልና፡ አርቆ፡
ማሰብን : ገንዘብ፡ ያደርጋል ። ሲነግሩትና : ሲያስተምሩት : ቀን : ይፍጅ
እንጂ : የማይገባው : የለም ፤ የተፈጥሮ : ዕውቀት : ያለው : ግን : እን
ኳን : ነግረውት : እንዲሁ : በመላ : ሊያውቅ ፤ በቀላሉም : ሊረዳ : ይች



ላል ፤ ቢሆንም : ከተፈጥሮ : እውቀት፡ ጋራ፡ የትምህርት : ዕውቀት፡ ካል
ተጨመረበት : ከንቱ : ነው ።

ለ/ የትምህርት : ዕውቀት ፤ የትምህርት : ዕውቀት : ለካህን : የበ
ለጠ : አስፈላጊው : ነው፤ ማለት : ለተጠየቀው፡ ጥያቄ : ኹሉ : ደምበኛ፡
መልስ : ለመመለስ ፤ ወይም : እርሱ : በሚያደርገው : ትምርህርት : ደን
በኛ : አስረጂ : ለመስጠት : እንዲችል ፤ ወይም፡ በሕዝቡ : ደረጃ : ከፍ፡
ብሎ : ተገምቶ : የሚናገረው : እንዲሰማ፤ እርሱም፡ እንዲከበር : ከሕዝቡ
ከፍ : ያለ : የበለጠ : ዕውቀትና : ጥናት፡ ሊኖረው፡ ይገባል ። የትምህርት፡
ዕውቀትም : እንዲሁ : በኹለት : ይከፈላል፤ አንደኛው : ልዩ : ዕውቀት :
ኹለተኛው : ደግሞ : ጠቅላላ : ዕውቀት : ይባላል ።

፩ኛ/ ልዩ : ዕውቀት ፤ ልዩ : ዕውቀት : የተባለው : ለካህን፡የተለየ :
ጥናት : ሊሆን : የሚገባው፡ መንፈሳዊ፡ ወይም : የቤተ፡ ክርስቲያን : ትም
ህርት : ነው ። መንፈሳዊ : ትምህርት፡ ወይም፡ የቤተ : ክርስቲያን : ትም
ህርትም : በአራት : ታላላቅ : ክፍል : ይከፈላል ።

አንደኛው፤ ቲዎሬቲካል፡ ቴዎሎጂ፤ ምራምራዊ : መንፈሳዊ : ትምህ
ርት ፤ ይባላል ፤ እርሱም : ብዙ : ጊዜ : በምርምርና : በእምነት : ብቻ
የሚቀበሉት : እንጂ ፤ ጐልቶ : የማይታይ ፤ ምስጢረ : ሥላሴን ፤ የመለ
ኮትና : የሥጋ : ተዋህዶን : የመሰለ ፤ በጠቅላላም : የሃይማኖት : ትምህ
ርት : የተባለው : ነው ። ሁለተኛው : ፕራክቲካል : ቴዎሎጂ ፤ ምግባራዊ :
ቴዎሎጂ : የሚባል : ዕልቱን : ከሥራ : የሚውል : ወይም : ትምህርቱ :
በሥራ : የሚገልጥ : ነው ፤ ለምሳሌ : ይህ : ትምህርተ : አበ : ነፍስ :
ከዚሁ፡ ክፍል፡ ውስጥ፡ ነው ። ሦስተኛ፡ ትርጉም : ነው ፤ ትርጉም : ማለት፡
መጽሐፍ : ቅዱስና : በጠቅላላው : ሌላም : የቤተ : ክርስቲያን : መጻ
ሐፍ : ሁሉ : እንደ : ቤተ : ክርስቲያን : ትምህርት : ሕዝቡ : እንዲ
ረዳው : በየጊዜው : የሚተረጐምና : የጠመመው : እንዲቀና : ማድረግ
ነው ። አራተኛ : ታሪክ : ነው ፤ የቤተ : ክርስቲያን : ታሪክ ፤ የሀይማ
ኖት : ታሪክ ፤ ይህንም : የመሰሉ፡ ቤተ : ክርስቲያንን : ነክ : የኾኑ : ታሪ
ኮችን : የሚመለከት : ትምህርት : ነው ፤ ከዚህ : በላይ : የተዘረዘሩት :
አራት : ታላላቅ : መንፈሳውያን : የትምህርት : ቅርንጫፎች : እያንዳን

www.ethiopianorthodox.org

ዳቸው ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ በበለጠ ፡ ክፍል ፡ ይከፈላሉ ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፤ ካህን ፡ እነዚህን ፡ ኹሉ ፡ አጠናቆ ፡ ማወቅ ፡ ግዴታው ፡ ነው ። አንድ ፡ ሐኪም ፡ የሚሆን ፡ የሕክምናን ፡ ትምህርት ፡ አጠቃሎና ፡ አጠናቆ ፡ ካላወቀ፡ ሐኪም ፡ ሊሆን ፡ አይችልም፤በሰው ፡ ላይ ፡ አደጋን ፡ ያመጣልና ። ካህንም፡ የክህነትን ፡ ሥራና ፡ የክህነትን ፡ ትምህርት ፡ ጠንቅቆና ፡ አጠቃልሎ ፡ ካላወቀ ፡ ፡ በሰው ፡ በሥጋውም ፡ በነፍሱም ፡ አደጋና ፡ ጉዳት ፡ ያመጣል «ወይኢይኩን ፡ አሐዱ ፡ ቀሲስ ፡ ዘኢየአምር ፡ ነገረ ፡ መጻሕፍት ፡ አምላካውያት ፡ ሠናያት ፡ ፊድፋደሰ ፡ አርባዕተ ፡ ወንጌላተ » (ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አንቀጽ ፡ ሳድስ) ፡ እያሉ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባቶች ፡ አጽድቀውታል ።

፪ኛ/ ጠቅላላ ፡ ዕውቀት ። ካህን ፡ በመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ብቻ ፡ መወሰን ፡ የለበትም ፡ ኹሉን ፡ መሰለል ፡ ኹሉን ፡ ማወቅ ፡ ይገባዋል ፡ እንጂ፡ ለምሳሌ ፡ ብዙ ፡ ቋንቋ ፡ ማወቅ ፡ በዚያም፡ ማስተማር ፤ በዚያም፡ የተጻፉትን ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት፡ መመልከት፡ ታላቅ ፡ እርምጃን ፡ ይሰጡታል፤በዚያም ፡ ድርሰት ፡ ሊደርስ ፤ ስብከትም ፡ ሊሰብክ፡ ይችላልና። ብዙ ፡ ቋንቋ ፡ ማወቅ ፡ ምእመናንን ፡ ከማነጹና ፡ የራሱን ፡ ዕውቀት ፡ ከማስፋፋቱ ፡ ሌላ፡ መናፍቃን ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፡ በቋንቋቸው ፡ መልሱን፡ አስተካክሎ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል። ቀጥሎም ፡ ፊሎዞፊ ፡ ሳይንስ ፡ በመጠኑ፡ ማወቅ ፡ ተገቢ፡ ነው ፤ ምክንያቱም፡ ዛሬ፡ ጊዜው ፡ ማቴሪያሊስም፡ ሁኖ፡ ሣይንስ፡ ሠልጥኖ፡ ዓለሙ፡ ኹሉ፡ እንደ፡ ፈጣሪ፡ አድርጎ፡ ሳይንስን ፡ በሚያመልክበት፡ ጊዜ ፡ ከሳይንስ፡ የተገኙ፡ መልሶችን ፡ ለመስጠትና ፡ቲዎሪውን ፡ በቲዎሪ ፡ ለማፍረስ፡ የሚችለው፡ የሳይንስ፡ ልምድ ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ኾነ፡ ነው።ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ከሳይንስ ፡ የተገኙ ፡ አንዳንድ ፡ ቲዎሪዎች ፡ የሀይማኖትን ፡ መሠረትና ፡ ሕንጻ ፡ ስለሚንዱት ፡ ካህኑ ፡ ከሳይንስ፡ ጋራ ፡ በሚገባ ፡ መለማመድ ፡ አለበት ። ይህንም ፡ የመሰለ ፡ ኤቲክስና ፡ ሶሺያል ፡ ማጥናት ፡ ያስፈልገዋል . . . . . ምክንያቱም ፡ ዛሬ ፡ ኹሉ ፡ ግብረ ፡ ገብነቱን ፡ የዘነጋበት ፤ ማኅበራዊ፡ ኑሮም ፡ የተሰነካከለበት . . . . ሰው ፡ ተፈጥሮውን፡ የረሳበት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መኖርና ፡ የነፍስን ፡ ተፈጥሮ ፡ የካደበት፡ጊዜ ስለ ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በሽታና ፡ ሁከት ፡ እየበዛ ፤ ፍቅር ፡ እየተቀነሰ ፡ ጸጋው ፡ በረከቱ ፡ እያጸጸ ፡ ስለ፡ ሄደ ፡ ካህኑ ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፡ አንድ



ነት ፡ እየተገኘ ፡ ይህ ፡ አኳኋን፡ የሚሻሻልበትን ፡ መግለጥና ፡ ማስረዳት፡ እንዲቻል፤ የነዚህ ፡ ትምህርቶች፡ ዕውቀት ፡ በሰፊው፡ ሊኖረው፡ ይገባል ። ምክንያቱም ፡ ኹሉ ፡ በዕውቀት ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የንግግር ፡ ፈሊጥና ፡ የማስረዳት ፡ ስልት ፡ ሲኖረው . . ካህኑ ፡ ከነርሱ ፡ በለጥ ፡ ብሎ ፡ በማንኛውም ፡ ካልተገመተ ፤ ትምህርቱን ፡ መቀበላቸው ፡ ቀርቶ ፡ በእርሱ ፡ ይቀልዳሉ ፤ እርሱንም፡ መዘበቻ ፡ ያደርጉታል።ይህንም ፡ በመፍራት ፡ ከሕዝብ፡የራቀ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ከክህነት ፡ ዓላማ ፡ ይወጣል ፡ ከዓላማውም ፡ ከወጣ ፡ «አንተ ፡ ክፉ ፡ ባሪያ ፡ ተግባረ ፡ ፈትም ፡ ዐወቅህ ፡ ያልዘራሁትን ፡ እንዳጭድ ፤ ያልበተንሁትንም ፡ እንድሰበስብ ፡ ወርቄን ፡ ለሸራፎች ፡ ጥለኸው ፡ እንደ ፡ ሆንህ፡ ይገባህ ፡ ነበር ፤ እኔም ፡ መጥቼ ፡ ከብቴን ፡ ከትርፉ፡ ጋራ ፡ እወስደው ፡ ነበርሁ ። ስለዚህም ፡ ያን ፡ አንድ ፡ መክሊት ፡ ውሰዱበት ፡ ዐሥር ፡ መክሊትም ፡ ላለው ፡ ስጡት » (ማቴ/ ፳፭ ፡ ፳፮—፳፰) ፡ ተብሎ ፡ ይፈረድበታል ። ስለዚህ ፡ ካህን ፡ ሁል፡ ጊዜ ፡ ከማጥናት ፤ ሁል ጊዜ ፡ መጽሐፍ፡ ከመመልከት፡ ቸል ፡ ማለት ፡ የለበትም።ሁል፡ጊዜ ፡ ለጠየቁት፡ መልስ፡ ለመስጠት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ መኖር ፡ አለበት (፩ ፡ ጴጥ/፫ ፡ ፲፭) ።

ሐ/ በሰብአዊ ፡ ሁናቴ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ መድን ፤ በሰውነቱ ፡ ላይ ፡ ሙሉ ፡ ጤንነትና ፡ ሙሉ ፡ አካል ፤ ልከኛ ፡ ዕድሜ ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ፤ እነዚህ ፡ ግን ፡ ከጐደሉ ፡ ከቶ ፡ ሥራውን ፡ ሊያከናውንና ፡ ኀላፊነቱን ፡ ሊያስወግድ ፡ አይችልም ።

፩ኛ/ ሙሉ ፡ አካል ፡ የኾነ። ሙሉ፡ አካል ፡ ማለት ፡ ነውር ፡ ነቀፋ፡ የሌለበት፤ የሥራውን፡ ጉድለት ፡ የሚያስከትል ፡ በሕዝብም ፡ ፊት ፡ ስሜቱን ፡ የሚቀንስ ፡ እንዳይሆን ፡ ያስፈልጋል ። አካለ ፡ ጐደሎ ፡ በኦሪቱ ፡ እንኳን ፡ ካህኑን ፡ ለመሥዋዕት ፡ የሚሆነውን ፡ ከብት ፡ አይቀበሉትም ፡ ነበር (ዘሌዋ/ ፳፩ ፡ ፲፰) ። በኦሪቱ ፡ ይህ፡ አካለ፡ ጐደሎ ፡ እንደ ፡ ኀጢአት፡ ስለሚቆጠር፡ ከቅዱሱ ፡ ነገር፡ ኹሉ ፡ ያርቁት ፡ ነበር። በሐዲስ ፡ ኪዳን፡ ግን፡ ይህ ፡ የአካል ፡ ጉድለት ፡ ኀጢአት ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ የሥራን ፡ ጉድለት ፡ ብቻ ፡ የሚያመጣ ፡ ሲሆን ፡ ይከለከላል «ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዘጋኔን ፡ - - - - ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዕውር ፡ ወኢጽሙም ፤ ወኢዝንጉዕ ፡ አኮ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ነውር ፡ አላ ፡ እስመ፡ ውእቱ፡ ኢይክል ፡ በእንተ ፡ ፈጽሞቱ ፡ ለዝ ፡ ውእቱ ፡ ይትፈቀድ ፡ እምግብራተ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ » ፍት/ ነገ/ አንቀጽ ፡ ሐምስ ፡ ረስጠጅ ፡ ፶፪) ። ካህን፡ የሚሆን ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ የአካል ፡ ጕድለት ፡ ሊኖርበት ፡ አይገባውም ፤ ምክንያቱም ፡ ሥጋ ፡ ለነፍስ ፡ ምሳሌ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በሥጋው ፡ ጕድለት ፡ ያለው ፡ በነፍስም ፡ እንዲሁ ፡ ጐደሎ ፡ ይሆናልና ።

፪ኛ/ ሙሉ ፡ ጤንነት ። ሙሉ ፡ ጤንነት ፡ እንዲሁ፡ አስፈላጊ ፡ ነው፤ ምክንያቱም ፡ ጤነኛ ፡ ሰው ፡ ፀሳቡ ፡ የቀና ፡ አንደበቱ ፡ የረታ ፡ ሀይማኖቱ ፡ የጸና ፡ በመላ፡ ኑሮው ፡ የተቃና ፡ ኹኖ፡ መልካም ፡ ውጤትን ፡ ለመስጠት ፤ ኀላፊነቱን ፡ ለመወጣት ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ ለመሥራት ፡ ይችላልና ። ክህነት ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ሥራ ፡ ሰዓት ፡ የማይሰጥ ፤ ቀጠሮ ፡ የማይደረግበት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ለክህነት ፡ ሥራ ፡ በበሽታቸውና ፡ በአካላቸው ፡ ምክንያት ፡ የሌላቸው ፤ ፍጹም ፡ ጤነኛ ፡ የኾኑ ፡ ሰዎች ፡ ያስፈልጋል ። የክህነት ፡ ሥራ ፡ ከባድ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ እንኳን ፡ በሽተኞች ፡ ጤናማዎቹም ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ በመሥራታቸው ፡ ከመታመም ፡ ይደርሳሉ ፤ ስለዚህ በመጀመሪያ ፡ የጤንነት ፡ ምልክት ፡ ያላቸውን ፡ መርጦ ፡ መሾም ፡ ይገባል ።

፫ኛ ፡ ልከኛ ፡ ዕድሜ ። ልከኛ ፡ ዕድሜ ፡ ሳይኖረው ፡ ሥልጣነ ፡ ክህነትን ፡ የሚቀበለው፡ ከበሽተኛውና ፡ ከአካለ፡ ጐደሎው ፡ የተሻለው፡ ነገር፡ የለም ፤ ምክንያቱም ፡ አንደኛ ፡ በልጅነቱ ፡ የሥራው ፡ ጕድለት ፤ የትምህርትና ፡ የዐቅም ፡ ማነስ ፡ ብዙ ፡ ጕድለትን ፡ ያስከትላልና ፤ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ክፉውን ፡ ከደግ ፡ ለይቶ ፡ ስለ ፡ ማያውቅ ፡ ጥፋቱንም ፡ ለይቶ ፡ ስለ ማይሠራ ፡ ከልማቱ፡ ይልቅ ፡ ጥፋቱ ፡ የበለጠ፡ ይሆናል።ይህንም ፡ ይዘው ፡ የቀደሙ ፡ አባቶች ፡ ከ፳፫ ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ለሥልጣነ ፡ ክህነት ፡ ቀርቶ ፡ ለማንኛውም ፡ ሥራ ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ አያገቡትም ፡ ነበር። ብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ በልጅነታቸው ፡ ቄስ ፡ ዲያቆን ፡ የነበሩ ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ አመንዝራዎች ፡ ሁነው ፡ ለሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ዕንቅፋት ፡ የኾኑ ፡ ይገኛሉ ፤ «የተቀደሰውን ፡ ለውሾች ፡ አትስጡ ፤ ዕንቁዎቻችሁንም ፡ አትጣሉ ፤ በዕሪያዎች ፡ ፊት ፤ በእግሮቻቸው ፡ እንዳይረግጡት ፤ ተመልሰውም ፡ እንዳይነክሷችሁ »(ማቴ/ ፯ ፡ ፯) ፡ ብሎ ፡ ክርስቶስም ፡ አስቀድሞ ፡ ተናግሯል ። የተቀደሰውን ፡ ሥልጣነ ፡ ክህነት ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ አፍርሰው ፡ አመ



ንዝራ ፡ የሚሆኑት ፡ ከውሾች ፡ የባሱ ፡ ናቸው ፤ አመንዝራነትም ፡ ከአምስቱ ፡ ውሾች ፡ አንደኛው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ «በሜዳ ፡ ግን ፡ ናቸው፤ አምስቱ፡ ውሾች ፡ አስማተኞችም ፡ አመንዝሮችም ፡ ነፍስ ፡ ገዳዮችም ፡ ጣኦት ፡ የሚያመልኩም ፤ ሐሰትም ፡ የሚወዱ ፡ የሚያደርጉም » (ዮሐ/ ራዕ/ ፲፰ ፡ ፲፫)፡ ሲል ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ አስረድቷል። ስለዚህ ፡ የተቀደሰውን ፡ ሌላውንም ፡ ሊቀድስና ፡ ሊያነጻ ፡ የሚችለውን ፡ ሥልጣነ፡ ክህነት ፡ ላልበቁ፡ ውሾችን ፡ ለሚመስሉ ፡ የሚሰጥ ፡ ጳጳስ፡ ወዮለት ! ማንኛውም ፡ ሥጋዊ፡ ሥልጣንና ፡ ሹመት ፡ እንኳን ፡ ዕድሜው ፡ ሲከለክለው ፡ በሞግዚት ፡ ሲያስተዳድር ፡ መንፈሳዊ ፡ ሹመትማ ፡ በዕድሜ ፡ ከፍ ፡ ላሉ ፡ የማስተዋልም ፡ ችሎታ ፡ ላላቸው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሊሰጥ ፡ አይገባም ።

www.ethiopianorthodox.org

# ክፍል ፣ ፫ ።

## የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጠባቂ ፡ (አበ ፡ ነፍስ ፡ ) ወደ ፡ ክህነት ፡ በገባ ፡ ጊዜ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ክህነታዊ ፡ ዝግጅት ።

ካህን ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፤ ትልቅ ፡ ኀላፊነት ፡ ያለበት ፡ ዐዋቂ ፡ ጠን ቃቃ ፡ መሆን ፡ እንዲገባ ፤ ምን ፡ ፀይነትም ፡ ችሎታና ፡ ስጦታ ፡ እንዳ ለው ፤ ኀላፊነቱንም፡ እንዴት፡ አድርጎ ፡ እንደሚወጣው፡ በመጀመሪያው፡ ክፍል ፡ ተናግረናል፤ አሁን ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ፈተና ፤ አልፎ፤ አመክ ሮውን ፡ ፈጽሞ ፡ ለክህነት፡ የሚሆነውን ፡ ዝግጅት፡ እንናገራለን።ከኹሉ፡ በፊት ፡ ንስሐ ፡ መግባት ፤ በሕዝባዊነት ፡ ሳለ ፡ ሲታወቀው ፡ በድፍ ረት ፤ ሳይታወቀውም ፡ በስሕተት ፡ የሠራውን ፡ ኀጢአት ፡ ኹሉ ፡ ዘር ዝሮ ፡ ለአበ ፡ ንስሐው፡ መንገር ፡ ሲሠራው፡ ያላፈረውን ፤ ለመናገር ፡ ሳያ ፍር ፤ ወይም ፡ ኹሉን ፡ የተናገርኩ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ክህነቴ ፡ ይቀርብኛል ፡ ሳይል ፡ ሳይፈራ ፡ ሊናገር ፡ ይገባዋል። በሕይወቱ ፡ ውስጥ ፡ ሲታወቀው፡ የሠራውን ፡ ኹሉ ፡ ተናዝዞ ፡ ሲፈጽም ፤ ክህነትን፡ የሚያስነቅፍ ፡ ሥራ፡ ሠርቶ ፡ የቀረበ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ክህነቱ ፡ ይቀርበታል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ቀላል ፡ ኀጢአቱ ፡ ጾም ፡ ጸሎትና ፡ ሌላም ፡ ቀኖና ፡ ይሰጠዋል ፤ ለጊዜው፡ መንፈሳዊ ፡ ቅጣት ፡ ይሆናል ፤ ዋና ፡ ነገሩ ፡ ግን ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ፡ ጻዋሚ ፤ ተሐራሚ ፡ መሆኑን ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ ነው ። የተወሰ ነው ፡ ቀን ፡ ተፈጽሞ ፡ ማዕርገ ፡ ክህነትን ፡ በሚቀበልበት ፡ ጊዜ ፡ መሥ ዋዕት ፡ ይሠዋል ፤ ጳጳሱም ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ይሾመዋል ፤ ከሐዋር ያት ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣውን ፡ ሥልጣነ ፡ ክህነት ፡ ያስተላልፍ ለታል።በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ተሹሞ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀብሎ ፡ ሥል ጣነ ፡ ክህነትን ፡ እጅ ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፤ ቀድሞ ፡ ከነበረበት ፡ ከሕዝባዊ ነት ፡ ተራ ፡ ይወጣል ፤ ከሰማያዊና ፡ ከመንፈሳዊ ፡ ነገድ ፡ ገብቶ፡ ይቆጠ ራል።አሮጌው ፡ ስሜቱ ፤ አሮጌው፡ ዐሳቡ ፡ ተለውጦ ፡ በዕውቀት ፡ ታድሶ፡

www.ethiopianorthodox.org

በመንፈስ ፡ ጐልምሶ ፡ እውነተኛ ፡ የክርስቶስ ፡ አገልጋይ ፡ ለመሆን ፡
«ሳውልና ፡ በርናባስን ፡ እኔ ፡ ለመረጥኋቸው ፡ ሥራ ፡ ለዩልኝ ፡ » (የሐ/
ሥራ ፡ ፲፫ ፡ ፪) እንዳለው ፡ ያለ ፡ ድምፅ ፡ ይሰማል ። እስከዚህ ፡ ቀን ፡
ድረስ ፡ ካህኑ ፡ በራሱ፡ ኀጢአት ፡ ብቻ ፡ ይፈረድበት ፡ ነበር፤ከዚህ ፡ ቀን፡
ጀምሮ ፡ ግን ፡ በሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ደም ፡ ተጠያቂ ፡ ስለ ፡ ኾነ፤ ራሱን ፡ ለሕ
ዝብ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ ይሰጣል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ሥልጣነ ፡ ክህነት ፡ ምሥጢር ፡ እንደ፡ ኾነ ።

ምሥጢር፡ ማለት ፡ አንደኛ፡ ለባለቍርጥ ፡ ዘመድና፡ ወዳጅ ፡ ብቻ ፡
የሚነገር ፤ በምሥጢርም ፡ የሚቀር፡ ለማንም ፡ የማይናኝ ፡ ነገር፡ ማለት፡
ነው ። ይህም ፡ የክህነት ፡ ሥራ፡ ምሥጢር ፡ የተባለበት ፡ ለተለዩ ፡ ለተ
መረጡ ፡ ሰዎች ፡ እንጂ ፤ ለማንም ፡ የማይናኝ ፡ ታላቅ ፡ ጸጋን ፡ ረቂቅ ፡
ሀብትን ፡ የሚሰጥ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ። ኹለተኛ ፤ በእጅ ፡ የማይጨበጥና፡
በዐይን ፡ የማይታይ ፡ በልብ ፡ ብቻ ፡ የሚመረመር ፡ ተመርምሮም፡ የማ
ይደረስበት ፡ በእምነት ፡ ብቻ ፡ የሚታይ ፡ በእምነት ፡ የሚጨበጥ ፤ ገንዘ
ብም ፡ የሚሆን ፡ ነውና ፤ ይህም ፡ የክህነት ፡ ሥራ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጸጋን ፡
የሚሰጥ ፡ ሲሆን ፡ እንዴት ፡ እንደሚሰጥ ፡ ስለማይታወቅ ፡ ምሥጢር ፡
ተብሏል ። ይህንም ፡ የመሰሉ ፡ ሌሎች ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምሥጢ
ራት ፡ አሉ ፤ እነዚህም ፡ ምሥጢራት ፡ በክርስቶስ ፡ መሥራችነት ፡ የተ
መሠረቱ ፤ በነርሱም ፡ አማካይነት ፤ ጸጋውን ፡ ጽድቁንም ፡ የሚሰጥባ
ቸው ፡ ናቸው ፤ «ከምላቱም ፡ እኛ ፡ ሁላችን ፡ ወሰድን ፡ ጸጋም ፡ በጸጋ ፡
ፈንታ ፤ አሪት ፡ በሙሴ ፡ ተሰጥቷልና፡ ጸጋ ፡ ግን ፡ እውነትም፡ በኢየሱስ ፡
ክርስቶስ፡ ኾነ ፡ » (ዮሐ/ ፩ ፡ ፲፯—፲፯)። እነዚህም፡ ምሥጢራት፡ በክርስቶስ፡
መሥራችነት ፡ የተመሠረቱ ፤ ክርስቶስ ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ ካደረገው ፡
የማዳን ፡ ሥራ ፡ የመነጩ ፤ የማዳን ፡ ሥራውም ፡ ያለ ፡ ማቋረጥ ፡ እየቀ
ጠለ ፡ የሚሄድባቸው፤ ኃይሉ ፡ የሚታወቅባቸው ፤ ሥልጣኑ ፡ የሚገለጥባ
ቸው ፤ የማንጻትና ፡ የማጽናት ፡ ሥራው ፡ የሚቀጥልባቸው ፡ ታላላቅ ፡
ምሥጢሮች ፡ ናቸው።ለምሥጢራተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም፡ የሚታይ፡ አገ
ልግሎት ፡ የማይታይ ፡ ሀብት ፡ አለው ፤ የክህነት፡ ምሥጢር ፡ የሚታየው፡



አገልግሎት ፤ ጳጳሱ ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ሲሾም ፤ የተለየ ፡ ጸሎት ፡ ሲጸ
ልይ ፤ ክህነት ፡ የሚቀበለውም ፡ በሰቂለ ፡ ሕሊና ፤ በሰፊሐ ፡ እድ ፤ በአ
ንቃዕድዎ ፡ አዕይንት ፤ በአድንኖ ፡ በተመስጦ ፡ ሲጸልይ ፡ ይታያልና ፡
ይኽ ፡ የሚታይ ፡ አገልግሎት ፡ ይባላል ። እንዲሁም ፡ ሥልጣነ፡ ክህነት ፡
ሥልጣን ፡ ሲሰጥ ፡ አይታይም ፤ ይህም ፡ የማይታይ ፡ ሀብት ፡ ይባላል ።
ጋ ፤ ሀብት ፤ የማሠር ፤ የመፍታት ፤ የማንጻትና ፤ የማጽናት ፤ የማዳን ፡
እነዚህን፡ ምሥጢራት ፤ ክርስቲያን ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ በሚገባ ፡ መፈጸም ፡
አለበት ፤ ያለዚያ ፡ ግን ፡ ከተስፋው ፡ ከመድኀኒቱ ፡ ወጣ ፡ ተለየ ፡ ማለት ፡
ነው። ደግሞም ፡ የግድ ፡ ያስፈልጋሉ ፤ በተለይም ፤ ጥምቀት ፤ ሜሮን ፡
ቍርባን ፤ ንስሓ፤እነዚህ፡ አራቱ ፡ የግድ ፡ ለክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ ያስፈል
ጋሉ።ቀንዲል ፡ ተክሊል፡ ክህነት ፡ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ግን ፡ ለተለዩ ፡ አስ
ፈላጊነታቸው ፡ ለታወቁ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ናቸው ፤ ምክንያ
ቱም ፡ ኹሉ ፡ ሰው ፡ ታማሚ ፡ አይደለም ፤ ስለዚህ ፡ ምስጢረ ፡ ቀንዲል፡
ኹልጊዜ ፡ ለኹሉ ፡ አስፈላጊ ፡ አይኾንም ፤ ኹሉ ፡ ሰው ፡ አያገባም፤ ስለ
ዚህ ፡ ተክሊል ፡ ለኹሉ ፡ አያስፈልግም ፤ ለሚያገቡት ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፤
ኹሉ ፡ ካህን ፡ አይሆንም ፡ ከተመረጡት ፡ በቀር፡ ስለዚህ ፡ ለኹሉ ፡ ምሥ
ጢረ ፡ ክህነት ፡ አይፈጸምለትም ።

## ፩ኛ | የምሥጢራት ፡ አገልግሎት ፤

ምሥጢራተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሀብትን ፡ ያሰጣሉ ፤ የማሠርን ፡
የመፍታትን ፡ ሥልጣን፡ ያስገኛሉ ፡ ስንል ፡ አንደኛ ፡ አገልግሎታቸው ፡
ፍጹም ፡ መሆን ፡ አለበት፤ ማለት፡ አፍአዊ፡ ነገር ፡ ኹሉ፡ ንጹሕ ፡ መሆን፤
ሥራውም ፡ ከልብ ፡ እንዲሠራ ፡ ጸሎቱም ፡ ከልብ ፡ እንዲጸለይ ፡ ያስፈል
ጋል ። ኹለተኛ ፡ የሚፈጽማቸው ፡ ሰው ፡ ደንበኛ ፡ ካህን ፡ በእውነት ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የመረጠችው ፡ በሚገባም ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ የተ
ሾመ ፡ ካህን ፡ መሆን፡ አለበት ። ሦስተኛ ፤ ምሥጢሩ ፡ የሚፈጸምለትም፡
ሰው፡ ከልቡ ፡ የተዘጋጀ ፤ ልቡን ፡ ከሕዝባዊነት ፡ ተራ ፡ የለወጠና ፡ ወደ ፡
መንፈሳዊ ፡ ዓለም ፡ የዞረ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ፡ ከልቡ ፡ የፈለገ ፡
መሆን ፡ አለበት ፤ እነዚህ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ነገሮች ፡ በሚገባ፡ የተፈጸሙ፡
እንደ ፡ ኾነ ፤ ከታሰበው ፡ ዓላማ ፡ ይደርሳል ፤ የተፈለገውም ፡ ዋጋ ፡ ይገ
ኛል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፩ኛ / ሀብተ ፡ ክህነት ፡ እንዴት ፡ እንደሚሰጥ ።

የክህነትን ፡ ጸጋ፡ ክርስቶስ ፡ በመጀመሪያ ፡ እንደ ፡ ተነሣ፡ ለቅዱሳን፡
ሐዋርያት ፡ አደላቸው ፡ «ይህንም ፡ ብሎ ፡ እፍ ፡ አለባቸው ፤ አላቸውም፡
መንፈስ፡ ቅዱስን፡ ተቀበሉ፡ ኀጢአቱን፡ የተዋችሁለት፡ ቀረችለት፤ የያዛች
ሁበትም፡ ሰው፡ ተያዘችበት» (ዮሐ/፳ ፡ ፳፫ ፡ ማቴ/፲ ፡ ፩-፵፪ ፡ ማር/፮ ፡ ፯-፲፫፡
ሉቃ/፱፡ ፩-፫)«እርሱም፡ሰጠ፡ እኩሌቶችም፡ ነቢያት፡ ሌሎችም፡ ሰባኪዎች፡
ሌሎችም ፡ ጠባቂዎችና ፡ ሰባኪዎች ፡ . . . »(ኤፌ/ ፬፲፡ ፩—፲ ) እያለ ፡ ቅዱስ፡
ጳውሎስም ፡ ይመሰክራል ። « አሁንም ፡ ለራሳችሁ ፡ ተጠንቀቁ ፡ ለመ
ንጋውም ፡ ኹሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ጠባቆች ፡ አድርጎ ፡
የሾማችሁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትጠብቁ ፡ ዘንድ ፤ እርሱ፡
በደሙ ፡ የዋጃትን ፡ » (የሐ / ሥራ ፡ ፳ ፡ ፳፰ ) ብሎ ፡ እንዲሁ ፡ ቅዱስ ፡
ጳውሎስ ፡ ያስረዳል። ክርስቶስ ፡ ለሐዋርያት ፡ የሰጣቸው ፡ በነርሱ ፡ ብቻ፡
እንዲወሰን ፡ አይደለም ፡ ለነርሱ ፡ ብቻ ፡ ቢሆን ፡ « - - - እኔ ፡ እነሆ ፡ ከላ
ንት ፡ ጋራ ፡ ነኝ ፡ በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜው ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ »
(ማቴ/፳፰ ፡ ፳ ) ብሎ ፡ ባልመሰከረም፡ ነበር ፡ ምክንያቱም ፡ ኹሉም ፡ ሐዋ
ርያት ፡ በአንደኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የሞቱ ፡ ሲሆን ፤ እስከ ፡ ዓለም ፡
ፍጻሜ ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝ ፡ ባላለም ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሐዋርያት ፡
ለተከታዮቻቸው ፡ እንዲያወርሱ ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ እንዲሾሙ ፤ ይህ ፡
ማዕርገ ፡ ክህነት ፡ ሳያቋርጥ ፡ የሚሰጥ ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ቃል ፡
ነው ። ስለዚህ ፡ ሐዋርያት ፡ ወዲያውኑ ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ሰባቱን፡ዲያ
ቆናት፡ ሾሙ ፡ (የሐ / ሥራ ፡ ፮ ፡ ፫ - ፱)ቀጥለውም ፡ ኹሉም ፡ በየሄዱበት፡
ዲያቆን ፡ ቄስ ፡ (ጳጳስ) ፡ ኤጲስ፡ ቆጶስ ፡ ሾሙ ፡ (የሐ/ ሥራ ፡ ፲፬ ፡ ፳፫) ። ለም
ሳሌ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ጢሞቴዎስን ፡ ለኤፌሶን ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ አድ
ርጎ ፡ እንደ ፡ ሾመው ( ፩ ፡ ጢሞ / ፩—፫ ) እናገኛለን። የኤጲስ ፡ ቆጶስነቱም፡
ምልክት ፡ እርሱ ፡ እንዲሾም ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቶት ፡ ነበር ፤ « በተሰጠ
ችህ ፡ ጸጋ ፡ በትንቢት ፡ በቀሳውስትም ፡ እጅ ፡ በመጫን ፡ ቸል፡ አትበል»
(፩ ፡ ጢሞ/ ፬ ፡ ፲፬) ። እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ የሚመክረው ፡ ጢሞቴዎስን ፡
መጀመሪያ ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ከሾመው ፡ በኋላ ፡ ነው «ስለዚህም ፡ አሳ
ስብሃለሁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የጸጋውን ፡ ሕይወት ፡ ለማደስ ፡ ያደረችብህ፤
በተሰጠኸው ፡ እጄን ፡ በላይህ ፡ በጫንኩብህ ፡ ጊዜ ፡ » (፪ ፡ ጢሞ/ ፩-፮) ።



እንዲሁም ፡ በቀርጤስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ አድርጎ ፡ ቲቶን ፡ ሹሟል « ስለ
ዚህ ፡ በቀርጤስ፡ ተውኩህ ፤ የጐደለውን ፡ ኹሉ ፡ ታቆም ፡ ዘንድ፤ ቀሳ
ውስትንም፡ትሾም፡ ዘንድ ፤ በየሀገሩ ፡ እንዳዘዝኩህ ፡ » (ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፭)።ይህን፡
የመሰለ ፡ ኹሉም ፡ በየሄዱበት ፡ በአንብሮተ፡ እድ ፡ እየሾሙ ፡ ከዲቁና ፡
እስከ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ያለውን ፡ ማዕርግ ፡ ሰጥተዋል ። ከዚያም ፡
ጀምሮ ፡ ያለ ፡ ማቋረጥ ፡ እስካሁን ፡ ይተላለፋል ፤ እስከ ፡ ምጽአትም ፡
ይህ ፡ ጸጋ ፡ ሳይጓደል ፡ ይሰጣል ።

### ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ካህኑ ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በሹመት፡ ቦታው ፡ ሲታይ ።

በጠቅላላው ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመረመረውና ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ተገ
ኝቶ ፡ ከተሾመ ፡ በኋላ ፤ ለተሾመበት ፡ ቦታ ፡ ያለው ፡ ኀላፊነት ፡ ኹሉ ፡
እርሱን ፡ ስለሚመለከት ፤ ተግቶ ፡ ነቅቶ ፡ ምእመናንን ፡ መጠበቅ ፤ የሚ
ያነጻበትንና ፡ የሚያጽናናበትን ፡ ሥራ ፡ በትጋት ፡ መሥራት ፡ የራሱ፡ኀላ
ፊነትና ፡ ፈንታ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ መጀመሪያ ፡ ወደ ፡ ተሾመበት ፡ ቦታ ፡
እንደ ፡ ገባ ፡ ዕረፍትን ፡ ሳይሻ ፤ ይህን ፡ ይሉኛል ፡ ሳይል ፤ ሳይ
ፈራ ፡ ኀላፊነቱን ፡ የሚመለከቱትን ፡ ጉዳዮች ፡ ኹሉ ፡ በሚገባ ፡
መፈጸም ፡ አለበት ፤ አጀማመሩ ፡ የመጨረሻው ፡ እኩሌታ ፡ መኾኑን ፡
ዐውቆ ፡ በአጀማመሩ ፡ ያለውን ፡ ስሜት ፡ መግለጥ ፡ አለበት ፡ ምክን
ያቱም ፤ ለማንኛውም ፡ ነገር ፡ ስም ፡ የሚወጣ ፡ በመጀመሪያው ፡
ነውና ፤ «አንድ ፡ ጊዜ ፡ ስም ፡ ከወጣ ፡ አይመለስም ፡ » እንደ ፡ ተባለው ፡
አንድ ፡ ጊዜ ፡ በመጥፎ ፡ ግምት ፡ እንዳይወድቅና ፡ ያልሆነ ፡ ስም ፡ እንዳ
ይወጣበት ፤ ትልቅ ፡ ጥንቃቄ ፡ ያስፈልገዋል።ስለዚህ ፡ በከባዱ ፡ ሥራው፡
ያለውን ፡ ኀላፊነትንና ፡ በምእመናን ፡ ያለውን ፡ ፍቅር ፡ በሰፊው ፡ መግ
ለጥ ፡ የመጀመሪያ ፡ ሥራው ፡ ነው ። ይህንም ፡ ከዚህ ፡ በሚከተሉት ፡
ነገሮች ፡ ሊገልጠው ፡ ይችላል ፤ ማለት ፡ መጀመሪያ ፡ ሲገባ ፡ በሚያደር
ገው ፡ የንግግር ፡ አገላለጥ ፤ በአረማመዱ ፡ በአስተያየቱ ፡ ሊያስረዳ፡ ይች
ላል ። ምክንያቱም ፡ አዲስ ፡ በተሾመው ፡ ካህን ፡ ላይ ፡ የሕዝቡ ፡ ዐይን ፡
ስለሚያርፍበት ፤ የሚሠራውና ፡ የሚናገረው ፤ በጠቅላላም ፡ ስሜቱ ፡ የሕ



www.ethiopianorthodox.org

ይወት ፡ ታሪኩን ፡ ስለሚገልጥ ፤ ሕዝቡ ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ ሊያጠናው ፡
ይችላልና ። ለዘለዓለምም ፡ መታሰቢያ ፡ ሁነው ፡ የሚቀሩት ፡ አስረጂዎች ፡
የመጀመሪያው ፡ ንግግር ፤ ሥራውና ፡ ስሜቱ ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ አጀ
ማመሩ ፡ የሕይወቱ ፡ ግማሽ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

ይህም ፡ ነገር ፡ ለጊዜው ፡ ለያዝነው ፡ ለክህነት ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ ሰጠ
ነው ፡ እንጂ ፤ በሥጋዊም ፡ ሹመት ፡ ቢሆን ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ለተሾመበት ፡
ሥራ ፤ ተሹሞም ፡ ለሄደበት ፡ አገር ፡ የሚጠብቀው ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡
ነው ። ካህኑ ፡ ከዚህ ፡ ኹሉ ፡ ትእዝብት ፡ ለመዳን ፡ የመጀመሪያ ፡ ንግግሩ ፡
እውነትን ፡ የተመረኰዘና ፡ ዕድሜ ፡ ልኩን ፡ ሊሠራው ፡ ከሚገባውና ፡
ከሚችለው ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ መሆን ፡ አለበት ። እንዲሁም ፡ መጣ
ልን ፡ ብለው ፡ ከሚጠብቁት ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ እንዲኖረው ፤ በን
ግግሩና ፡ በአስተያየቱ ፡ ፍጹም ፡ ፍቅሩን ፡ መግለጥ ፤ ቀጥሎም ፡ አረማ
መዱ ፡ አነጋገሩ ፡ የተወሰነ ፡ እንዲሆን ፤ በጠቅላላውም ፡ ለሥራው ፡
ኹሉ ፡ ልክ ፡ መልክ ፡ እንዲኖረው ፡ ያስፈልጋል ። ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡
ለማድረግ ፡ የሚችለው ፡ በመጀመሪያ ፡ ንግግሩ ፡ ነው ፤ ማለት ፡ በኀጢ
አት ፡ በሽታ ፡ የታመሙትን ፡ እንደ ፡ መልካም ፡ ሐኪም ፡ የሚያክም ፤
መንገድ ፡ የጠፋባቸውንና ፡ የተሰነካከሉትን ፡ እንደ ፡ ታመነ ፡ መሪ ፤ ለደጋ
ግና ፡ ለመልካም ፡ ሰዎች ፡ የትሩፋት ፡ አበጋዝና ፡ ምሳሌ ፤ ለሕፃናት ፡ ሞግ
ዚት ፤ ለሽማግሌዎች ፡ ደጋፊ ፡ ምርኵዝ ፤ በጠቅላላም ፡ ለኹሉ ፡ መካሪ ፡
አስተማሪ ፡ ሁኖ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መሰጠቱን ፡ መግለጥ ፡ አለበት ።

እንዲሁም ፤ እርሱ ፡ ለምእመናን ፡ ሊያደርገው ፡ የሚገባውን ፡ ግዴ
ታና ፡ ኀላፊነቱን ፤ ምእመናንም ፡ ሊያደርጉት ፡ የሚገባቸውን ፡ ከአስረዳ ፡
በኋላ ፤ ኹላችንም ፡ ከባዱን ፡ ኀላፊነታችንን ፡ የምንወጣበትን ፡ ተባብ
ረን ፡ የሠራን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ነው ፤ ተባብረውና ፡ ተግባብተው ፡ የሚሠሩ
ትን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወዳቸዋል ፤ ስለዚህም ፡ ይረዳቸዋል ፤ እያለ ፡
ምሳሌ ፡ የርሱንና ፡ የምእመናንን ፡ አንድነት ፡ በሰፊው ፡ መግለጥ ፡ አለበት ፡
ይህንም ፡ ለመፈጸም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርዳን ፡ ብሎ ፡ ተስፋን ፡ በተ
መላ ፡ ቃል ፡ ጸሎት ፡ አድርጎ ፡ ይፈጽማል ።



## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## የካህኑ ፡ ሥራ ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በመዘርዘር ፡ በአስረዳነው ፡ ሁናቴ ፡ ካህኑ ፡ ሥል
ጣነ ፡ ክህነትን ፡ እጅ ፡ ካደረገና ፡ ከምእመናንም ፡ ጋራ ፡ ተገናኝቶ ፡ የሹ
መት ፡ ቦታውን ፡ ከወረሰ ፡ በኋላ ፤ መልካም ፡ እረኛ ፡ መንጋውን ፡ እንዲ
ጠብቅ ፤ መልካም ፡ አባትም ፡ የወለደውን ፡ ልጁን ፡ እንዲወድና ፡ በሚ
ገባ ፡ እንዲከባከብ ፤ ካህኑም ፡ የሕዝቡ ፡ መንፈሳዊ ፡ አባት ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡
መጠን ፡ በሚገባ ፡ ማሰብና ፡ እንደ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ መከባከብ ፡ አለበት ።
እነርሱንም ፡ ለመከባከብ ፡ እንዲመቸው ፡ በአቅራቢያቸው ፡ መኖር ፡
አለበት ፤ ይህም ፡ ማለት ፡ በማንኛውም ፡ ችግራቸው ፡ ተካፋይ ፡ ኾኖ ፡
ለመምከርና ፡ ልቡናቸውን ፡ ለማነጽ ፤ ለማጽናናትም ፤ ለማንጻትም ፤ ለመ
ባረክ ፤ ቅዱስ ፡ ምሥጢርንም ፡ በየጊዜው ፡ እንደ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ ለመ
ስጠት ፡ እንዲመቸው ፡ ነው ። በመካከላቸው ፡ መገኘቱ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ፡
የምንለው ፤ ለመምከርና ፡ ለማስተማር ፡ እንዲመቸው ፤ ለበጎ ፡ ነገርም ፡
ምሳሌ ፡ ሆኖ ፡ እንዲታያቸው ፤ በጧት ፡ በማታ ፡ እንዲከባከባቸው ፡ ነው ፤
ነገር ፡ ግን ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ እየኖረ ፡ ሥጋዊ ፡ ጥቅሙን ፡ ብቻ ፡ የሚመ
ለከት ፡ ከኾነ ፤ ቢርቅ ፡ የተሻለ ፡ ይሆናል ፤ ምክንያቱም ፡ እርሱን ፡ የጥ
ሩት ፡ አብነት ፡ አድርገው ፡ ሲከተሉ ፤ ከጥቅሙ ፡ ይልቅ ፡ ጕዳቱ ፡ ይበል
ጣልና ። እንደዚህ ፡ በስንፍና ፡ ራስን ፡ በመውደድ ፡ ሥጋዊ ፡ ጥቅምን ፡
በመፈለግ ፡ ዓላማቸውን ፡ ሳይከተሉ ፡ መንጋቸውን ፡ የሚበትኑትን ፡
ጠባቂዎች ፤ የጠባቂዎቹ ፡ አለቃ ፡ በጣም ፡ ይወቅሳቸዋል ፤ ደሙንም ፡
ከነርሱ ፡ ይከፈላል ፡ (ሕዝ/ ፴፬ ፡ ፪ ) ።

የካህኑ ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ የሚቀለው ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ በመ
ኖር ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ጠባቂ ፡ የበጎችን ፡ ስም ፡
ከመልክ ፡ ለይቶ ፡ እንደሚያውቅ ፤ መንፈሳዊው ፡ ጠባቂ ፡ ካህኑም ፡ የምእ
መናኑን ፡ ቍጥር ፤ መልክ ፡ ከስምና ፡ ከምግባር ፡ ለይቶ ፡ ማወቅና ፡ እንደ ፡
ጠባዩ ፡ መምከር ፡ በጣም ፡ አስፈላጊው ፡ ነው ። የርሱም ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዲሁ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ «እኔ ፡ ነኝ ፡ ቸር ፡ ጠባቂ ፡
በጎቼንም ፡ ዐውቃለሁ ፤ በጎቼም ፡ ያውቁኛል » (ዮሐ/ ፲ ፡ ፲፬ ፡)ሲል ፡ አስ

www.ethiopianorthodox.org

ረድቷል ። በዚህም ፡ መሠረት ፡ ለመፈጸም ፡ ጳጳስ ፡ የኾነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ በአጭር ፡ ታጥቆ ፡ ፕሮግራም ፡ አውጥቶ ፡ ሀገረ ፡ ስብከቱን ፡ በመላ ፡ መዞር፤ የቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ቍጥር ፡ ማወቅ ፤ በያንዳንዱም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ የምእመናንን ፡ ብዛት ፤ የምእመናንንም ፡ ስምና ፡ መልክ ፡ ሥራ ፡ ማወቅ፤ ቄስም ፡ የኾነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እርሱ ፡ ባለበት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ ወይም ፡ የራሱ ፡ የንስሓ ፡ ልጆች ፡ የሚሆኑትን ፤ በተወሰነ ፡ ዕለትና ፡ ሰዓት ፡ እየዞረ ፡ መጐብኘት ፤ እርምጃ ፡ ቸውንም ፡ መከተል ፤ በእርግጥ ፡ ለማወቅ ፡ ይረዳዋል ፤ ከዐወቃቸውም ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ዓላማው ፡ ለመፈጸም ፡ ይጠቅመዋል። ሀገረ ፡ ስብከቱንና፡ ምእመናንን ፡ እየዞሩ ፡ መጐብኘት ፡ አዲስ፡ ነገር ፡ አይደለም ፤ ከክርስቶስና ፡ ከሐዋርያት ፡ የመጣ ፡ ነው፡ እንኳ ፤ ማለት ፡ አስተምረው ፡ አይተ ዋቸውም ፡ ነበር ፤ እንዲሁ ፡ በእግር ፡ እየተመላለሱ ፡ በመጐብኘት ፡ በጽ ሑፍም ፡ በማጽናናት ፡ ይጠይቋቸው ፡ ነበር ። (የሐ ፤ ሥራ፡ ፲፫ ፡ ፵፩) ። ማንም ሰው ፡ ዘሩን ፡ ዘርቶ ፡ እንዲሁ ፡ አይተውም ፡ በጕልጓሎው ፤ በዐረሙ፡ እን ዲሁም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጊዜ ፡ ጕብኝት ፡ ያደርግለታል ፡ እንኳ ፤ እንዲ ሁም ፡ እንደ፡ ዘርዕ ፡ የተዘራውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ ጊዜ፡ ተናገርኩ ፡ ብሎ ፡ መተው ፤ ዘርቶ ፡ እንደ ፡ መተው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ዕለት ፡ ለይቶ ፤ ፕሮግራም ፡ አውጥቶ ፤ ተራ ፡ ሰጥቶ ፡ ኹሉን ፡ መጐብኘት ፡ በጣም ፡ ያስፈልጋል ። በዚህ ፡ ጕብኝት ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ ለመተዋወቅ ፡ ይችላሉ ፤ ቀጥሎም ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ በቅርብ ፡ ሁኖ ፡ ከማጥናቱ ፡ የተነሣ ፡ ጕድለቱን ፡ ለመሙላት ፡ ጥፋቱን ፡ ለማረም ፡ ይረዳዋል ። በተ ለይ ፡ ግን ፡ በታመሙ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አደጋ፡ ወይም ፡ ኀዘን ፡ በገጠማቸው፡ ጊዜ ፡ ከነርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ መለየት ፡ የለበትም ። በአንድ ፡ በኩል ፡ ቤተ ፡ ሰብነቱን ፡ ይገልጣል ፤ ማለት ፡ ከአባል ፡ አንደኛው ፡ ሲታመም ፡ በመላ፡ አካሉ ፡ ኹሉ ፡ ይታመማል ፤ ከአባል ፡ አንደኛው ፡ ሲደክም ፡ በመላ ፡ አካሉ ፡ ሁሉ ፡ ይደክማልና ፤ «የዚህም ፡ ፍጻሜ ፡ አንድ ፡ ልብ ፡ ትሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤ ከሚያዝንም፡ ጋራ፡ የምታዝኑ፤ እንደ ፡ ወንድማማች ፡ እን ድትዋደዱ - - -» (፩ ፡ ጴጥ/ ፫ ፡ ፰) እያለ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ እንዳስተማረ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ «ደስ ፡ ካላቸው ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፤ ከሚያለ ቅሱ ፡ ጋራም ፡ አልቅሱ ፡ » (ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፲፭) እያለ ፡ ይመክረናል ።



ከቤተ ፡ ሰብ ፡ አንዱ ፡ ሲደሰት ፡ አብሮ ፡ ይደሰታል ፤ አንዱ ፡ ሺሾም ፡ ሲሸለም ፡ ኹሉ ፡ ይደሰታል ፤ በኀዘንም ፡ ጊዜ ፡ እንዲሁ ፡ ነውና ። ኹለተ ኛም ፡ ተስፋ ፡ እንዳይቈርጡ ፡ ለማጽናናት፡ ምክርና፡ እዝናት ፡ ለመስጠት፡ ነው ፤ የክርስቲያን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ሆኖ ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ሌላቸው እንደ ፡ አሕዛብ ፡ መራራ ፡ ኀዘን ፡ ሊያዝንና ፡ ተስፋ ፡ ሊቈርጥ ፡ አይገባውም ፡ «ነገር ፡ ግን ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ፡ እወዳለሁ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ! ስላንቀላፉ፡ ሰዎች ፡ እንዳታዝኑ ፤ እንደ ፡ ሌሎች ፡ ተስፋ ፡ እንደሌላቸው ፤ ኢየሱስ ፡ ሙቶ ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ ካመነ ፤ እንዲሁም ፡ በኢየሱስ ፡ ያንቀላፉትን ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ፡ ያመጣቸዋልና ፤» (፩ ፡ ተሰ/ ፬ ፡ ፲፫) እያሉ ፡ መም ክር ፡ ማስተማር ፡ የካህኑ ፡ ተግባር ፡ ነው ። በደስታ ፡ ጊዜም ፡ እንዲሁ ፡ በተለይ ፤ በክርስትና ፡ በተክሊል ፡ ጊዜ ፡ እየተገኙ ፡ የደስታው ፡ ተካፋይ፡ የምሥጢሩ ፡ ፈጻሚ ፡ መሆን ፡ የካህኑ ፡ ዋና ፡ ተግባር ፡ ነው።ካህኑ ፡ ከሰው፡ ቤት ፡ መለየት ፡ የለበትም ፡ ስንል ፤ የባለጸጋዎችንም ፡ የድኾችንም ፡ የበሽተኞችንም ፡ የጤነኞችንም ፡ የደጎችንም ፡ የክፎችንም ፡ ቤት ፡ እየ ዞሩ ፡ መጐብኘት ፡ በማንኛውም ፡ ነገር ፡ መሳተፍና ፡ ቡራኬውን ፡ ምክ ሩን ፡ መስጠት ፡ አለበት ። ክፎች ፡ ከክፋታቸው ፡ እንዲመለሱ ፤ ደጎችም ፡ በያዙት ፡ ጐዳና ፡ እንዲራመዱ ፡ መምከርና ፡ ማስተማር ፡ የካህኑ ፡ ተግባር ፡ ነው ። ካህኑ ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ የሚተዳደሩትን ፡ ስም ፡ ከመልክ፡ ዐውቆ ፡ የሚውሉበትን ፡ የሚያድሩበትን ፡ የሚሠሩበትን ፡ ሥራ ፡ ፈቱን፡ ክፉውን ፡ ደጉን ፡ ኀጢአተኛውን ፡ ጻድቁን ፡ ሰነፉን፡ ልባሙን ፡ የተማ ረውን ፡ ያልተማረውን ፡ ደኻውን ፡ ባለጸጋውን ፡ ደኻ ፡ አደጉን ፡ ባልቴ ቷን ፡ በሽተኛውን ፤ በጠቅላላም ፡ በሥላሴ ፡ አርአያ ፡ ተፈጥሮ ፡ የኑሮ ፡ እር ምጃ ፡ የተሰነካከለበትን ፡ ተከባካቢ ፡ ያጣውን ፡ የተቸገረውን ፡ ጠባቂ ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ መንጋ ፡ እንዳይሆን ፡ ሰዓት ፡ ሳይወስን ፤ ተግቶና ፡ ነቅቶ፡ መሥራት ፡ አለበት ። በተለይ ፡ ግን ፡ ከባለጸጎች ፡ ለድኾች ፤ ከጤነኞች ፡ ይልቅ ፡ ለበሽተኞች ፤ ከጻድቁ ፡ ይልቅ ፡ ለኀጢአተኛው ፡ በበለጠ ፡ ማሰ ብና ፡ መሥራት ፡ አለበት ፤ ምክንያቱም ፡ እግዚአብሔር ፡ ራሱ ፡ ምሕረቱ፡ የበዛ ፤ መዓቱ ፡ የራቀ ፤ የነዳያንና ፡ ተስፋ ፡ የቈረጡ ፡ አምላክ ፡ ነውና ። ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ የመጣውም ፡ በኀጢአት ፡ ማሰሪያ ፡ የታሰሩትን ፡ ሊፈታ ፤ የተጋዙትን ፡ ነጻ ፡ ሊያወጣ ፤ በዕዳ ፡ የተያዙትን ፡ ራሱ ፡ ከፍሎ፡ ሊያስለቅቅ ፡ ነውና ፤ «ነገሪቱም ፡ እውነተኛ ፡ ናት ፡ እርሷንም ፡ መቀበል፡

www.ethiopianorthodox.org

የሚገባ ፡ ነው ፡ በፍጹም ፡ መቀበል ፤ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡
እንደ ፡ መጣ ፤ ኀጢአተኞችን ፡ ሊያድን ፤ እኔ ፡ መጀመሪያቸው ፡ የምሆን»
(፩ ጢሞ/ ፩ ፡ ፲፫ ፤ ማቴ/ ፲፰ ፡ ፲፩) ።

ከዚህ ፡ ሌላ ፡ የማዕርግ ፡ የዕውቀት ፤ የሀብት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥልጣ
ንና ፡ መብት ፡ ያላቸውን ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ ሰዓት ፡ ወስኖ ፡ እንደ ፡ ባሕሪ
ያቸው ፡ ተስማሚ ፡ የኾነውን ፡ መንፈሳዊ ፡ ምክር ፡ መመገብ ፤ ልክ ፡ እነ
ርሱን ፡ መስሎ ፡ ለክርስቶስ ፡ ማደሪያ ፡ እጅ ፡ ማድረግ ፤ «ከደካሞች ፡ ጋራ
ደካማ ፡ ኾንኩ ፤ ደካሞችን ፡ እረዳ ፡ ዘንድ ፡ ከኹሉ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ርሳ
ቸው ፡ ኾንኩ ፤ ከርሳቸው ፡ ሰዎች ፡ ፈጽሜ ፡ አድን ፡ ዘንድ» (፩ ፡ ቆሮ/ ፱ ፡ ፳፪)።
ብሎ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዳስተማረ ፤ በማንኛውም ፡ መንገድ ፡ ቢሆን ፡
ተራምዶ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ማዳን ፤ በበጎ ፡ ነገር ፡ ጸንቶ ፡ የቀናውን ፡ መን
ገድ ፡ መምራት ፡ የካህኑ ፡ ዋና ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ በዘረዘር
ነው ፡ ብቻ ፡ ሊወሰን ፡ አይገባውም ። እርሱም ፡ ከጊዜ ፡ ሥራው ፡ በአገ
ኘው ፡ ልምድና ፡ ሁናቴ ፡ አስፋፍቶ ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል።ከዚህ ፡ በላይ ፡ የዘ
ረዘርናቸው ፡ ኹሉ ፡ በትክክል ፡ ለመፈጸም ፡ የርሱም ፡ የምእመናንም ፡
ግዴታ ፡ ሁኖ ፡ አንዳንድ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ (ማኀበር) ፡ ማቋ
ቋም ፡ ይጠቅማል ፤ ምክንያቱም ፡ እርሱ ፡ ያስተማረው ፡ ትምህርት ፡
ፍሬ ፡ ማፍራቱንና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋሉን ፡ ይረዳዋል ፤ ምዕመናንም ፡
የተማሩት ፡ ትምህርት ፡ በልቡናቸው ፡ እንዳደረ ፡ በሥራ ፡ ሲገልጡት ፡
ኹለቱም ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ዳኑና ፡ ከኀላፊነታቸው ፡ እንደ ፡ ወጡ ፡ ያጠይ
ቃል ። በቃል ፡ ብቻ ፡ መናገርና ፡ መስማት ፡ ለክርስቲያን ፡ ከቶ ፡ ጠቃሚ
ነገር ፡ የለውም ፤ በሀገር ፡ ላይ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ተቋቁሞ ፡ ድኾች ፡ ልጆች ፡
በደንብ ፡ ሲያድጉ ፤ በሽተኞች ፡ ሲታከሙ ፤ ሽማግሌዎችና ፡ ባልቴቶች ፡
ሲጦሩ ፤ በጠቅላላውም ፡ የሕዝቡ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ኑሮ ፡ ትክክልና ፡ ሰላ
ማዊ ፡ ሲሆን ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ምሕረትና ፡ በረከት ፡ ይገኛልና።

ደግሞም ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ ከተከናወነ ፡ በኋላ ፤ ሥራ ፡ ፈት ፡ ከቶ ፡ አይ
ገኝም ፤ ሕዝብም ፡ ሥራ ፡ ካበዛ ፡ ኀጢአት ፡ ሊሠራና ፡ እግዚአብሔርን ፡
ሊበድል ፡ አይችልም ፤ የኀጢአት ፡ መሠረቱ ፡ ሥራ ፡ መፍታት ፡ ነውና።
ይህን ፡ ቅዱስ ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ እንዲቻል ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ የሆነ ፡
እንደ ፡ ኾነ ፤ በመንፈሳዊነታቸው ፡ በግብረ ፡ ገብነታቸውና ፡ በትምህር



ታቸው ፡ ከታወቁት ፡ ካህናት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ መያዝ ፡ አለበት ፤ እንዲ
ሁም ፡ ከምእመናን ፡ ውስጥ ፡ መርጦ ፡ ደጋግ ፡ ሰዎችን ፡ ማማከር ፡ ያስፈል
ጋል ፤ ምክንያቱም ፡ የሕዝቡን ፡ ጠባይ ፡ በቀደምትነት ፡ ሕዝቡ ፡ ያውቁ
ታል ። ደግሞም ፡ ለማናቸውም ፡ ሥራ ፡ ተሳታፊዎች ፡ ስለሚሆኑ ፤ ከነ
ርሱ ፡ የተወሰረ ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ፤ ስለዚህ ፡ ልማቱንም ፡ ጥፋቱንም ፡
በፍጥነት ፡ ይረዱታልና ። ቄስ ፡ የኾነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ከዲያቆናትና ፡ ከም
እመናንም ፡ እንዲሁ ፡ ደጋጎችን ፡ መርጦ ፡ ረዳት ፡ መያዝና ፡ በቤቱም ፡
ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ እንዲሁ ፡ ቅድስናና ፡ ንጽሕና ፡ የተሰማ
ቸው ፡ ሰዎች ፡ መኾን ፡ ያስፈልጋል ፤ ምክንያቱም ፡ ከነርሱ ፡ አብነት ፡ ሊወ
ሰድ ፡ ይቻላልና ። « የገዛ ፡ ቤቱን ፡ ሥርዐት ፡ ያሳመረ ፤ የታዘዙለትም ፡
ልጆች ፡ ያሉት ፤ በክብድና ፡ ኹሉ ፤ ሰው ፡ ግን ፡ የርሱን ፡ ቤት ፡ ለመግዛት ፡
ሳያውቅ ፡ እንዴት ፡ ይቻለዋል ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ይጠብቅ ፡ ዘንድ»፡ ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፬፭ ፡ ሲል ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ለካህናት ፡
መሪ ፡ ቃል ፡ ሰጥቷል ።

www.ethiopianorthodox.org

# ክፍል ፡ ፬ ፡፡

## የካህኑ ፡ ጠባይና ፡ ትሩፋት ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ፤

### የካህኑ ፡ ጠባይ ።

ጠባይ ፡ ማለት ፡ ለሰው ፡ በተፈጥሮ ፡ የሚጠሰው ፤ በአደገም ፡ ጊዜ ፡ የሚያዘነብልበት፡ በዚያውም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖርበት፤ በልቡናው ፡ ተተክሎ፡ የሚኖር ፡ ስሜት ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ በዘመን ፡ ክፋት ፤ በችግር ፡ ብዛት ፤ አካባቢውንም ፡ በመመልከት ፡ ደጎናው ፡ ሰው ፡ መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ ሊይዝ ፡ ይችላል ። እንዲሁም፡ መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ የነበረው ፡ ሰው፡ በምቾትና፡ በትምህርት፡ ብዛት ፤ አካባቢውንም፡ በመምሰል፡ ደግ፡ ጠባይ ፡ ሊይዝ ፡ ይችላል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የሰው ፡ ዋናው ፡ ሀብቱ ፡ ሌባ ፡ የማይሰርቀው ፤ ብዕልና ፡ ነቀዝ ፡ የማያጠፋው ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ ነው ።

ምእመናንን፡ የሚጠብቅ፡ካህን ፡ አስቀድሞ ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ፤ ምክንያቱም፡ የሚመክር ፡ የሚያስተምር ፡ ማንኛውንም፡ እውነት ፡ ነገር ፡ ለሕዝቡ ፡ የሚያስተላልፍ፡ አብነትነትም ፡ የሚወሰድበት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ መጀመሪያ ፡ እርሱ ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ። ከስብከቱና ፡ ከትምህርቱ ፡ ይልቅ ፡ ለሕዝቡ ፡ ጉልቶ፡ የሚታየው፡ የካህኑ ፡ የኑሮው ፡ ጸጥተኝነት ፤ የጠባዩ ፡ ትክክለኝነት ፡ ነው ። ጠባይ ፡ የሌለው ፡ ካህን ፡ እጁ ፡ እግሩ ፡ ሽባ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ምንም ፡ ለመሥራት ፡ እንደማይችል ፡ ሰው ፡ ነው ፤ እሠራለሁም ፡ ቢል ፡ የጠራውን ፡ ሥራ ፡ ያደፈርሰዋል ፤ ምክንያቱም ፡ ለሰው ፡ የሚያስተምረውን ፡ መጀመሪያ ፡ ራሱ ፡ ካልሠራውና ፡ ሠርቶም ፡ ካላሳየ ፤ እርሱ ፡ የማይፈጽመው ፡ የማይቻል ፤ ወይም ፡ የማይገባ ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ በማለት፡ ሕዝቡ ፡ ቸል ፡ ሊለው፡ ይችላል ። እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ጠባይ ፡ ሳይኖረው ፡ በሥራ ፡ የሚደክም ፡ ካህን ፡ በከንቱ ፡ ይደክማል ፡ ማለት ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

«ለሰነፎች ፡ ገሣጺ ፡ ለሕፃናት ፡ አስተማሪ ፤ የዕውቀትና ፡ የሰውነትም ፡ መልክ ፡ በኦሪት ፡ ላንተ ፡ የሆነ ፤ አንተ ፡ ኾይ ፡ ሌላውን ፡ የምታስተምር ፣ በውኑ ፡ ራስህን ፡ አታስተምርምን ? አትሥረቁ ፡ ትላለህ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ትሠርቃለህ ፤ አታመንዝሩ ፡ ትላለህ ፡ አንተም ፡ ታመነዝራለህ ፤ ጣዖትን ፡ ትጸየፋለህ ፡ አንተም ፡ የቤተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ዕቃ ፡ ትሠርቃለህ ፤ በኦሪትም፡ ትጓደዳለህ ፡ አንተም ፡ ኦሪትን ፡ በመተላለፍህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትንቃለህ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ስላንተ ፡ ይሰደባልና ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ » (ሮሜ፣ ፪፡ ፳—፳፬፡) እያለ ፡ ሳይሠራ ፡ የሚያስተምረውን ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ወቅሶታል ። ማንም ፡ ቢሆን ፡ ምግባሩ ፡ የቀና ፡ ሃይማኖቱ ፣ የጸና ፡ ካልኾነ ፤ ሥራ ፡ ሊሠራና ፡ እንደ ፡ ዓላማው ፡ ሊፈጽም ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ መንግሥት ፡ ሊወርስ ፡ አይችልም ፤ «አቤቱ ፡ አቤቱ፡ የሚለኝ ፡ ኹሉ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚገባ ፡ አይደለም ፤ በሰማይ ፡ ያለውን ፡ የአባቴን ፡ ፈቃድ ፡ የሚያደርግ ፡ እንጂ» (ማቴ/ ፯ ፡ ፳፩ ፤ ሮሜ ፡ ፪፡ ፲፫ ፤ ያዕ/ ፩፡፳፪—፳፯) ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚሠራውን ፡ የሚያስተምር፤ የሚያስተምረውንም ፡ የሚሠራ ፡ የተመሰገነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ « - - - እያደረገ ፡ ግን ፡ የሚያስተምር ፡ ይህ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ታላቅ ፡ ይባላል» (ማቴ/ ፳፡ ፲፱ ፤ ያዕ/ ፪ ፡ ፲ ፤) ሲል ፡ ክርስቶስ ፡ አስረድቷል ። የካህኑ፡ ጠባይ ፡ የታረመ ፡ ሥራው ፡ እውነተኛ ፡ ትክክለኛ ፡ ከኾነ ፤ ለሕዝቡም ፡ መልካም ፡ አርአያን ፡ ሰጥቶ ፡ በፍቅር ፡ ይስባቸውና ፡ እጅ ፡ ያደርጋቸዋል ፤ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ እርሱም ፡ የሰሙትም ፡ ይድናሉ ። «ለራስህ ፡ ተጠንቀቅ ፤ ለትምህርትህም ፡ በርስዋም ፡ ጽና ፤ ይህንም ፡ ያደረግህ ፡ እንደ፡ ኾነ፡ራስህን ፡ ታድናለህ ፤ የሚሰማህንም ፡ ደግሞ» ፡ (፩ ፡ ጢሞ/ ፬ ፡ ፲፮) ።

መልካም ፡ አርአያን ፡ ሰጥቶ ፡ ለበጎ ፡ ነገር ፡ አብነት፡ ኹኖ ፡ ማስተማር ፡ ለካህን ፡ አስፈላጊው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ክርስቶስ ፡ የዓለም ፡ ብርሃን፡እናንተ ፡ ናችሁ ፡ ብሎ ፡ በነርሱ ፡ ብርሃንነት ፡ ዓለም ፡ እንዲጠቀም ፤ ዓለም ወታእነርሱ ፡ በሄዱበት ፡ ጐዳና ፡ እንዲራመድ ፡ አስረድቶ ፡ ተናግሯል ። ወታደር ፡ ኹሉ ፡ የሚመስለው ፡ የሚከተለውም ፡ አለቃውን ፡ ነው «ተከተል ፡ አለቃህን ፡ ተመልከት ፡ ዓላማህን ፡ » እንደ ፡ ተባለ ። ሕዝቡም ፡ አለቃውን ፡ መሪውን ፡ ካህኑን ፡ ተከትሎ ፡ ስለሚጓዝ ፤ እርሱንም ፡ መስሎ ፡ ስለሚሠራ ፡ ካህኑ ፡ ከቶ ፡ እውነተኛ ፡ ብርሃን ፡ መሆንና ፡ ብርሃን ፡ የሚያ



ሰኘውን ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ አለበት ። «እንዲሁ ፡ ብርሃናችሁ ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ይብራ ፤ መልካሙን ፡ ሥራችሁን ፡ አይተው ፡ የሰማዩ ፡ አባታችሁን ፡ ያመሰግኑት ፡ ዘንድ » (ማቴ/ ፭፡ ፲፬—፲፯) ፡ ብሎ ፡ ክርስቶስ ፡ ለሐዋርያቱ ፡ እንዳስተማረ ። የካህኑ ፡ ትንሽ ፡ ጥፋት ፡ በሕዝቡ ፡ ጐልቶና ፡ በዝቶ ፡ ይታያል ፤ እርሱም ፡ ከሥራው ፡ በማለት ፡ ሕዝቡ ፡ ሠርቶ፡ ለክፉ ፤ አብነት ፡ የኾነ ፡ ካህን ፡ ወዮለት ! ስለዚህ ፡ ካህኑ ፡ በኑሮው ፡ በሥራው ፡ በአነጋገሩ ፡ ከኹሉ ፡ የተለየ ፡ የተወሰነ ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ ስሜቱ ፡ ኹሉ፡ አብነትነት ፡ ያለው ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልጋል፤ምክንያቱም ፡ ሕዝቡ ፡ የሚመለከተው ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ቅዱስ ፡ ነገር ፡ ነውና ።

በተቻለም ፡ መጠን ፡ ክርሱ ፡ አብነትነት ፡ ለመንሣት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ንቅናቄው ፡ አስተያየቱ ፡ አነጋገሩ፡ ኹሉ፡ ትምህርት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ትልቅ ፡ ጥንቃቄ ፡ ያስፈልገዋል። በካህኑ፡ ልብ ፡ ወይም ፡ ሐሳብ ፡ ሥጋዊ፡ ስሜት ፡ እንዳለ ፡ የግድ ፡ አስተያየቱም ፡ አነጋገሩም ፡ ሥራውም ፡ ሥጋዊ ፡ እንደሚሆን ፡ በሳይኮሎጂ ፡ የተረዳ ፡ ነው ፤ ክርስቶስም ፡ « ልብ ፡ የመላውን ፡ አፍ ፡ ይናገረዋል ፡ » (ሜቴ/፲፪ ፡ ፴፬) ፡ ሲል ፡ አስረድቷል ፡ ማለት፡ መልካም ፡ ሰው ፡ ከመልካም ፡ ልቡ ፡ መዝገብ ፡ መልካም ፡ ያወጣል ፤ ክፉም ፡ ሰው ፡ ከክፉ ፡ ልቡ፡ መዝገብ ፡ መልካም ፡ አያወጣም ፡ ክፉ ፡ እንጂ (ማቴ/ ፲፪ ፡ ፴፭ ) ። ካህኑ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ክርስቶስ ፡ ቅዱስ ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ «ነገር ፡ ግን ፡ እንደጸራችሁ ፡ እንደ፡ ቅዱሱ ፡ እላንትም ፡ ደግሞ ፡ ቅዱሳን ፡ ኹኑ ፤ በአካሄዳችሁ ፡ ኹሉ ፤ ተጽፏልና ፡ ቅዱሳን ፡ ኹኑ ፡ እኔ ፡ ቅዱስ ፡ ነኝና ፡ » ( ፩ ፡ ጴጥ/ ፩ ፡ ፲፭ ፤ ዘሌዋ/ ፲፩ ፡ ፵፬ ፤ መዝ / ፸፪ ፡ ፳፪) ።

፩ኛ ፡ ማዕርጉን ፡ መጠበቅ ፤ ማዕርጉን ፡ ክብሩን ፡ መጠበቅ ፡ ለካህን፡ አንደኛው ፡ ጠባይ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፤ ማለት ፡ ክህነት ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ሥራ ፤ ካህኑም ፡ እንደ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ አይደለምና ። በአንብሮተ ፡ እድ ፡ እንደ ፡ ተሾመ ፡ ዕለቱን ፡ ከቀድሞ ፡ ኑሮው ፤ ከሕዝባዊነት ፡ ደረጃው ፡ ተለይቶ፤ ሰማያዊ፡ ሀብትን ፡ ሰማያዊ ፡ በረከትን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጎ፣ ምንም ፡ ኑሮው፡ በምድር ፡ ቢሆን፡ ቍጥሩ፡ ከሰማያውያን ፡ ነገድ ፤ ኑሮው፡ በምድር ፡ ሳለ ፡ ሐሳቡ፡ በሰማያዊና፡ በረቂቅ፡ ዓለም፡ የተዋጠ፡ ነው ። ማዕርጉን ፡ በመጠበቁ ፤ ከማንኛው፡ ክስ ፡ ከማንኛው ፡ ትዝብት ፡ ይድናል ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ኛ፡ የመውጫውና፡ የመግቢያው፡ ጊዜ፡ እንዲወሰን። ይህም፡ ማለት፡ ካህኑ ፡ አደባባይ ፡ የሚወጣበት ፤ አገር ፡ ላገር ፡ የሚዞርበት ፡ ጊዜያቶችና ፡ ምክንያቶች ፡ የተወሰኑ ፡ እንዲኾኑ ፡ ያስፈልጋል ፤ ማለት ፡ የሚሄድበት ፡ ቦታና ፡ ምክንያት ፡ ከዓላማው ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ መኾን ፡ አለበት ፤ ለማስተማር ፤ ለማጥመቅ ፤ ለመባረክ ፡ ወይም ፡ ከሕዝብ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ለመገኘትና ፡ እርሱ ፡ ተባባሪ ፡ ለመሆን ፡ ሊሄድ ፡ ይገባዋል። ከዓላማው ፡ ውጭ ፡ ለኾነ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በዐደባባይ ፡ መገኘት ፡ ተዋርዶው ፡ ነው ፤ ምክንያቱም፡ በብዙ፡ ሕዝብ ፡ ዐይን ፡ ይገባል ፤ ምን ፡ አስገድዶት ፡ ወርቅ ፡ የሆነ ፡ ጊዜውን ፡ በማባከን ፡ በዚህ ፡ ተገኘ ፤ ወይስ ፡ ዓላማውን ፡ ዘንግቶ ፡ ሥራ ፡ ፈትቶ ፡ ከዚህ ፡ ተቀምጧል ፡ ተብሎ ፡ በመጥፎ፡ ግምት ፡ ማማረያነት ፡ እንዳይተበተብ ።

፫ኛ/ ንግግሩ ፡ የተወሰነ፡ እንዲሆን ፤ ማለት ፡ ካህን ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ በማይረባና ፡ በማይጠቅም ፡ ነገር ፡ መከራከር ፡ የለበትም ። አንደኛ/ ጊዜውን ፡ በከንቱ ፡ ያጠፋል ፤ ኹለተኛም ፡ ደረጃውን ፡ ማዕርጉን ፡ ያዋርዳል ፤ ሦስተኛም ፡ ነገር ፡ ሲበዛ ፡ ካህን ፡ ሊናገረው ፡ ቀርቶ ፡ ሊሰማው ፡ የማይገባውን ፡ ኹሉ ፡ ከመናገር ፡ ይደርሳልና ። መክረውት ፡ ከማይሰማ ፡ ዋዛ ፡ ፈዛዛ ፡ ቀልድ ፡ ጨዋታ ፡ ከሚወድ ፡ ሰው ፡ መራቅ ፡ ይገባዋል (፪ ጢሞ/ ፬ ፡ ፪) ።

፬ኛ/ ልብሱ ፡ የተለየ ፡ እንዲሆን ፤ የካህን ፡ ልብሱ ፡ የተለየ ፡ ከዓላማው ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ካህን ፡ ያገኘውን ፡ መልበስ ፡ የለበትም ፤ «ኢትልበሱ ፡ ልብሰ ፡ ሐራ ፡ » ሲል ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግ ፡ ይወስንብናል ። ከዚህም ፡ ጋራ ፡ ያረጀ ፤ የተቀደደ ፤ የቆሸሸ ፤ መልበስ ፡ የለበትም ፤ ማለት ፡ ያኑ ፡ እያጠበ ፤ እየሰፋ ፤ መልክም ፡ እየሰጠ ፡ መልበስ ፡ አለበት ። ካህኑ ፡ ለሥጋም ፡ ለነፍስም፡ አብነት ፡ የሚሆን፡ ስለ፡ ኾነ ፡ ንጽሕናና ፡ ጽዳት ፡ ከርሱ ፡ መጀመር ፡ አለበት ። ክርስቶስም ፡ በምሳሌ ፡ ሲያስተምር ፡ «ኢየሱስም ፡ አለ ፡ ወዳጄ፡ ሆይ ፡ እንዴት ፡ ወደዚህ፡ ገባህ ፤ የሠርግ ፡ ልብስ ፡ ሳትለብስ ፡ እርሱ፡ ግን ፡ ዝም ፡ አለ» (ማቴ/ ፳፪ ፡ ፲፪) ፡ ለዓላማው ፡ ያልተስማማ ፡ ልብስ ፡ በመልበሱ ፡ እንደ፡ ተወቀሰ ፡ ያስረዳናል ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ የዐደባባይ ፤ የሥራ ፤ የቅዳሴ ፡ ልብስ ፡ የተለየ ፡ እንዲሆንና ፡ እርሱም ፡ በንጽሕና ፡ ሊያዝ ፡ ይገባዋል ።



## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## የካህኑ ፡ ትሩፋት ።

ትሩፋት ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከተወሰነለት ፡ አልፎ ፤ አትርፎ ፤ አብዝቶ ፡ በፈቃዱ ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ ካህን ፡ ከተወሰነውና ፡ ከታዘዘው ፡ አልፎ ፡ አብዝቶ ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ክብሩን ፡ ማዕርጉን ፡ ከፍ ፡ የሚያደርግ ፤ ከሕዝብም ፡ ልዩነቱን ፡ የሚገልጥ ፤ ሊሠራው ፡ የሚገባው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ሥራውን ፡ ከዘረዘርን ፡ በኋላ ፡ ትሩፋቱንም ፡ እንዲሁ ፡ እንገልጣለን ። የትሩፋት ፡ ዓይነታቸው ፡ ስልታቸው ፡ ስማቸው ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፤ ማለት ፡ ባል ፡ ለሚስቱ ፤ ሚስት፡ ለባልዋ ፤ ቤተ፡ ሰብም ፡ ለአስተዳዳሪው ፤ አስተዳዳሪውም ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ እንዲሁም ፡ ሌሎች ፡ ለመሰላቸው ፡ ሊያደርጉት ፡ ሊፈጽሙት ፡ የሚገባቸው ፡ ይኖራል ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፤ የያዝነው ፡ ስለ ፡ ካህን ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ካህንኑ ፡ በጥብቅ ፡ የሚመለከቱትን ፡ ከዚህ ፡ እናትታለን ።

### ፩ኛ ፤ ንቃት ።

ንቃት ፡ ማለት ፡ ከንዋመ ፡ ሐኬት ፤ ከንዋመ ፡ ኃጢአት ፡ መንቃት ፤ ከመጥፎ ፡ ዐሳብና ፡ ሥራ ፡ መመለስ ፤ ከስንፍና ፡ ከድንቍርና ፡ ከነዝኅላልነት ፡ ይህንም ፡ ከመሰሉት ፡ ከሥጋና ፡ ከነፍስ ፡ ዕንቅልፍም ፡ መንቃት፡ ነው ። አዳም ፡ ከበደለ ፡ ወዲህ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ለሥጋዊ ፡ ፈቃዱ ፡ ብቻ ፡ እየተገዛ ፡ በኀጢአት ፡ እንቅልፍ ፡ ተደብቶ ፡ የማይሰማ ፡ የማይለማ ፡ ሁኖ ፡ ይኖር ፡ ነበር። የእንቅልፍ ፡ ሱስ ፡ (ልምድ ፡ በሽታ) ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ለመንቃት ፡ እንደማይችል ፤ ለማስወገድም ፡ ሲፈልግ ፡ ብዙ ፡ ሕክምና ፡ እንደሚያደርግ ፤ ብዙ ፡ ገንዘብም ፡ ወጪ ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ ብዙዎች ፡ የነፍስ ፡ ሐኪሞች ፡ አስረድተዋል ። እንዲሁም ፡ በኀጢአት ፡ እንቅልፍ ፡ ተደብተው ፡ አንቀላፍተው ፡ የነበሩት ፡ ለመንቃት ፡ አቅቷቸው ፡ ተቸግረው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር፤ የዓለሙን ፡ ኀጢአት ፡ ይቅ ር፡ ብሎ ፡ «የተኛህ፡ ንቃ ፡ ከሙታንም ፡ ተነሥ ፤ ክርስቶስ ፡ ያበራልሃልና» (ኤፌ/ ፭ ፡ ፲፬ ፤ ኢሳ፡ ፷ ፡ ፩)፡ ብሎ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ክርስቶስ ፡ የንቃት ፡ መድኀኒትን ፡ ሰጠን ።

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሚተኛ ፡ የክርስቶስን ፡ ዐዋጅ ፡ ያልሰማ ፡ ወይም ፡
በኀጢአት ፡ አረቄ ፡ የሰከረ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፤ በቀን ፡ የሚተኛ ፡ የለም «ይህ
ንም ፡ ዘመን ፡ ዕወቁ ፡ ከመኝታችን ፡ የምንነሣበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤
ዛሬ ፡ መድኀኒት ፡ ወደኛ ፡ የቀረበ ፡ ነውና ፡ ካመንበት ፡ ጊዜ፡ ይልቅ ፡ ሌሊ
ቱም ፡ ሂዶ ፡ ቀኑም ፡ ቀርቧልና ፤ ስለዚህ ፡ የጨለማን ፡ ሥራ ፡ ከኛ ፡ እና
ርቅ ፡ የብርሃንንም ፡ ጋሻ ፡ ጦር ፡ እንልበስ ፤ በቀኑም ፡ እንሂድ ፤ በቅን ፡
ነገር ፤ በዘፈንና ፡ በስካርም ፡ አይደለም ፤ በዝሙትም ፡ አይደለም ፤ በሴሰ
ኝነትም ፡ አይደለም ፤ በጸብም ፡ በቅናትም ፡ - - » (ሮሜ፡ ፲፫ ፡ ፲፬) ፡ እያለ ፡
ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ኹሉ ፡ መንቃት ፡ እንደሚገባው ፡ ያስተምረናል ።
ኹሉም ፡ በሚነቃበት ፡ ጊዜ፡ ካህኑማ፡ እንደ፡ ምን፡ የበለጠ፡ ተግቶ፡ ነቅቶ ፤
መኖር ፡ ይገባው ፤ ከኹሉም ፡ ይልቅ ፡ ካህኑ ፡ የነቃ ፡ የተጋ ፡ ኹኖ ፡ ሌላ
ውን ፡ መምከር ፡ ማስተማር ፡ እንደሚገባው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ « በታ
መነ ፡ ነገር ፡ የነቃ ፡ ይሁን ፡ እንደ ፡ ትምህርቱ ፡ ሌሎችን ፡ ደግሞ ፡ በእው
ነተኛ፡ ትምህርት ፡ ለማጽናት ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ የሚተላለፉትንም ፡ ለመ
ገሠጽ» (ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፱) ፡ ሲል ፡ ያስረዳናል ።

ዓመፅን ፡ ሐኬትን ፡ ስንፍናን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጎ ፡ ዋዛ ፡ ፈዛዛነትን ፡
አብዝቶ ፡ መንጋውን ፡ የሚያስነጥቅ ፡ ሰው ፡ ወዮለት ! ለእንቅልፋም ፡
ሰው ፡ ሌሊቱም ፡ ቀኑም ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ማለት ፡ በቀኑ ፡ ይጨልመዋል ፤
ለንቁ ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ ቀኑም ፡ ሌሊቱም ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ማለት ፡ ሌሊቱ
ይበራለታል ። ስለዚህ ፡ አኹን ፡ የብርሃን ፡ ጊዜ ፡ ኹኖ ፡ የማይሠሩ ፡ የቁም
እንቅልፍ ፡ የያዛቸው ፡ መቼውንም ፡ ቢኾን ፡ ሊነቁ ፡ የማይችሉ ፡ ስለ
ኾነ ፤ ካህኑ፡ በመጀመሪያ፡ እርሱ ፡ የነቃ ፡ የተጋ ፡ ሁኖ ፡ ጊዜ ፡ ሳይወስን
ኹሉን ፡ መጐትጐት ፡ ማንቃት ፡ ዋና ፡ ተግባሩ ፡ ነው ።

## የንቃት ፡ ዋጋው ፤

የነቃ ፡ የተጋ ፡ ሰው ፡ ቤቱን ፡ ከመበርበር ፡ ንብረቱን ፡ ከመዘረፍ ፡
ራሱን፡ ከአደጋ፡ ያድናል፡ ምክንያቱም ፡ ሌባ ፡ ኹል ፡ ጊዜ፡ የሚመጣው ፡
ባልቀጠሩት ፡ ዕለት ፡ ባልጠረጠሩት ፡ ሰዓት ፡ ባለቤቱ ፡ ተኝቶ ፡ ሥራ ፡
ፈትቶ ፡ ሰንፎ ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡ ክርስቶስ ፡ ሲያስተምር፡
«እንግዲህ ፡ ትጉ ፡ አታውቁምና፡ በምን ፡ ጊዜ ፡ ጌታችሁ ፡ እንደሚመጣ፡



ይህን ፡ ግን ፡ ዕወቁ ፡ ባለቤት፡ ቢያውቅ ፡ በምን ፡ ጊዜያት ፡ ሌባ ፡ እንዲ
መጣ ፡ በተጋ ፤ ቤቱም ፡ ሊቈፈር ፡ ባልተወም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ እና
ንተ ፡ ደግሞ ፡ ተዘጋጅታችሁ ፡ ኑሩ ፡ ባላሰባችሁት ፡ ጊዜ ፡ የሰው ፡ ልጅ፡
ይመጣልና» (ማቴ/ ፳፬ ፡ ፵፪—፵፬) ፡ ብሏል። እንዲሁም ፡ የነቃ ፡ የተጋ ፡
በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ባለቤት ፡ እንደሚሆን ፡ እንቅልፋም ፡ ግን ፡
እንዲሁ ፡ ወድቆ ፡ እንደሚቀር ፡ በ፭ ፡ ልባሞችና፡ በ፭ ፡ ሰነፎች ፡ ደናግል፡
መስሎ ፡ እንደሚከተለው ፡ ተናግሮዋል «የዚያን ፡ ጊዜ ፡ መንግሥተ ፡
ሰማያት ፡ ዐሥር ፡ ቈነጃጅትን ፡ ትመስላለች ፡ መብራታቸውን ፡ ይዘው ፡
የወጡ ፤ ሙሽራውን ፡ ለመቀበል ፤ አምስቱ ፡ ግን ፡ ከርሳቸው ፡ ብልሃተ
ኞች ፡ ነበሩ፤ አምስቱም፡ ሰነፎች፤ ሰነፎችም፡ መብራታቸውን ፡ ወስደው፡
ቅባኑግ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ አልወሰዱም ። ብልሃተኞች ፡ ግን ፡ ቅባኑግ ፡
ወሰዱ ፡ በማሰሮዋቸው ፡ ከመብራታቸው ፡ ጋራ ፤ ሙሽራውም ፡ በዘገየ ፡
ጊዜ ፡ ኹሉ ፡ አንቀላፉ ፡ ተኙም ። እኩለ ፡ ሌሊትም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡
ጩኸት ፡ ኾነ ፤ እነሆ ፡ ሙሽራ ፡ ደረሰ ፡ ውጡ ፡ ትቀበሉት ፡ ዘንድ ፤ የዚ
ያን ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ ቈነጃጅቶች ፡ ኹሉ ፡ ተነሡ ፤ መብራታቼውንም ፡
አበጁ ። ሰነፎችም ፡ ብልሃተኞችን ፡ አሉዋቸው ፤ ከቅባኑጋችሁ ፡ ስጡን፡
መብራታችን ፡ ይጠፋልና ፤ ብልሃተኞችም ፡ መለሱ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ባይ
በቃንስ ፡ ለኛም ፡ ለናንተም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሻጮች ፡ ሂዱ፤ለናንተም፡
ግዙ ። ሊገዙም ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ ሙሽራው ፡ መጣ ፡ የተዘጋጁትም ፡ ከርሱ ፡
ጋራ ፡ ወደ፡ ሠርግ ፡ ገቡ ። ደጅም ፡ ተዘጋ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የቀሩት ፡ ቆነጃ
ጅት ፡ መጡ ፤ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ አቤቱ ፡ አቤቱ ፡ ክፈትልን ፡ እርሱ ፡ ግን ፡
መለሰ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ እንዳላውቃችሁ ፤ እንግ
ዲህ ፡ ትጉ ፡ ቀኒቱን ፡ አታውቁምና ፤ ሰዓቲቱንም ፡ የሰው፡ ልጅ፡ የሚመጣ
በትን ፡ » (ማቴ/ ፳፭ ፡ ፩—፲፫) ። የሰነፍና ፡ የእንቅልፋም ፡ ውጤት ፡ ጊዜው ፡
ከአለፈ ፤ ምሕረት ፡ ከተከለከለ ፤ የምሕረትም ፡ በር ፡ ከተዘጋ ፡ በኋላ ፡
መጮህ ፡ ሲኾን ፤ የንቁዎች ፡ ግን ፡ ዋጋ ፡ ማግኘት ፤ የደስታው ፡ ተካፋይ
ነት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ በሰፊው ፡ ተረድተናል ። የንቃት ፡ ተቃራኒው ፡ እንቅ
ልፋምነት ፤ ሞኝነት ፤ ቸልተኝነት ፤ ስንፍና ፡ ናቸው ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡
የሰው ፡ የጥቅሙ ፡ በር ፡ ዘጊዎች ፡ ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፪ኛ ፡ ተጋድሎ ፤

ተጋድሎ ፡ ማለት ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ነጻነቱ ፡ ስለ ፡ መብቱ ፡ ስለ ሀብቱ ፡ የሚያደርገው ፡ ትግል ፡ ነው ፤ ማለት ፡ አጥቂ ፡ ተነሥቶበት፡ ሊነጥቀው ፡ ሲል ፡ አልሰጥም ፡ በማለት ፤ ወይም ፡ አንድ ፡ አደጋ ፡ መከራ ፡ ችግር ፡ በደረሰበት፡ ጊዜ ፤ እንዲያልፍ ፡ ዐውቆ ፡ የሚታገልና ፡ ሳይሠቀቅ ፡ ሳይመረር ፡ በትዕግሥት ፡ ማሳለፍ ፡ ነው ።

የሰው ፡ ሕይወት ፤ በተለየ ፡ የክርስቲያን ፡ ሕይወት ፡ መከራን፡ የተመላ ፡ ችግርንና ፡ ፈተናን ፡ የተጐናጸፈ ፡ ነው ፤ ኹል ፡ ጊዜ ፡ አሸክላው ፡ እንደ ፡ ተጠመደ ፤ መሰናክሉ ፡ ደንጋይ ፡ እንደ ፡ ተዘጋጀ ፡ ነው ። ይኽንም ፡ ክርስቶስ ፡ «ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ አለ ፤ መሰናከያ ፡ ሳይመጣ ፡ አይቀርም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ወዮለት ፡ መሰናከያ፡ በርሱ፡ ምክንያት ፡ ለሚመጣው፡ ሰው ፡ »(ሉቃ/፲፯ ፡ ፩ ፤ ማቴ/፲፰ ፡ ፯ ፤ ማር/፱ ፡ ፵፪)፡ ሲል ፡ አስረድቷል። ፈተናውም ፡ በብዙ፡ አኳኋን፡ ሊመጣ ፡ ይችላል ፡ ማለት ፡ ፩ኛው ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ከብዙ ፡ ባሕርያት ፡ የተፈጠረ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ባሕርያቱ ፡ ሳይስማሙ፡ ቀርተው ፤ አንደኛው ፡ ይሠለጥንና ፡ ሕገ ፡ ጠባዕይ፡ የሚከለክለውን ፡ እንዲሠራ ፡ ያነሣሣዋል ፤ ያስመኘዋል፤ ያስጐመጀዋል ። እውነተኛው ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፤ በተለየም ፡ ካህኑ ፡ ከዚህ ፡ ለማምለጥ፡ ሲል ፡ በልቡናው፡ ታላቅ ፡ ውጊያ ፡ ታላቅ ፡ ተጋድሎ ፡ ያደርጋል ። «እንግዲህ ፡ እኔ ፡ ሕግን አገኛለሁ ፡ መልካም ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡ በወደድኩ ፡ ጊዜ ፡ ክፉ ፡ እንዳለብኝ ። እኔ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ በውስጡ ፡ ሰውነቴ፡ በሕዋሳቴ ፡ ግን ፡ ያለው ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ የልቤን ፡ ሕግ፡ ሲጣላ፡ አየዋለሁ፤ በሕዋሳቴ ፡ ወዳለውም ፡ ወደ ፡ ኀጢአት ፡ ሕግ ፡ ይማርከኛል ። እኔ ፡ ጐስቋላ ፡ ሰው ፡ ማን፡ ባዳነኝ፡ ከዚህ ፡ ከሞተ፡ ሥጋ ፡ » (ሮሜ ፡ ፯፡ ፳፩—፳፬) ።

፪ኛውም ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ በማየትና ፡ በመስማት ፤ አካባቢውን ፡ በመምሰል ፡ ያየውን ፡ የሰማውን ፡ ለመሥራት ፡ ልቡናው ፡ ያነሣሣዋል ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አልሠራም ፡ የሥጋዬንም ፡ ፈቃድ ፡ አልፈጽምም ፡ የነፍሴን ፡ እንጂ ፡ በማለት ፡ ትልቅ፡ ተጋድሎ ፡ ያደርጋል፡ «እላለሁ ፡ በመንፈስ ፡ ተመላለሱ ፡ የሥጋንም ፡ መመኘት ፡ አትፈጽሙ ፤ ሥጋ፡ መንፈስ፡ የሚጠላውን ፡ ይወዳልና ፡ መንፈስም ፡ ሥጋ ፡ የሚጠላውን ፤ እሊህም ፡



እርስ ፡ በራሳቸው ፡ ይጣላሉ ። እናንት ፡ የምትወዱትን ፡ ነገር ፡ እንዳታደርጉት ፡ . . . . » (ገላ/፭ ፡ ፲፮—፲፯)፡ እያለ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ፡ እንዳስተማረ። ይኽንም ፡ ለመፈጸም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እየተገዙ ፡ ሰይጣንን ፡ ከነፈቃዱ ፡ መሸሽ፡ እንቢ ፡ ማለት ፡ ነው «አሁንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተገዙ ፡ ሰይጣንን ፡ ትቋቋሙት ፡ ዘንድ ፡ ከላንተም ፡ ይሸሻል » (ያዕቆ/፬ ፡ ፯) ፡ ሲል ፡ ቅዱስ ፡ ያዕቆብ ፡ ይመክረናል ።

ከዚህም ፡ ሌላ ፡ በሥጋም፡ ቢሆን፡ ብዙ፡ ፈተና፡ መከራ፡ አለ፤ ማለት፡ ሰው ፡ ያጣል ፡ ይነጣል ፤ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ እንደሚያገኝ ፡ ተስፋ ፡ አድርጎ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ የመጣው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ያርቅልኛል ፡ ብሎ ፡ አምኖ ፡ የሚጋደለው ፡ ተጋድሎ ፡ ነው ። ቅዱስ፡ያዕቆብ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ «ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፈተና ፡ በደረሰባችሁ ፡ ጊዜ ፡ ከደስታ ፡ ቍጠሩት ፡ ወንድሞቼ፡ ሆይ፡ ዐውቃችሁ ፡ የሀይማኖታችሁ ፡ መፈተን ፡ ትዕግሥትን ፡ እንዳደረገላችሁ፡ » (ያዕ/፩ ፡ ፪—፲) ሲል ፡ ይመክራቸዋል ። ቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፡ «ዛሬ ፡ በርሱ ፡ ደስ ፡ የሚላችሁ ፡ ጥቂትም፡ ልባችሁ ፡ በኀዘን ፡ በተላለፈ ፡ መከራ ፡ ስትፈተኑ ፡ ለላንት ፡ የሚገባ ፡ ሲሆን ፤ የሀይማኖታችሁ ፡ መፈተን ፡ ከሚጠፋ ፡ ወርቅ ፡ የሚከበር ፤ ምንስ፡ በእሳት ፡ ቢጸራ ፡ ይገኝ ፡ ዘንድ ፡ ለትምክህት ፡ ለምስጋናም ፡ ለክብርም ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መገለጥ ፡ »(፩ኛ፡ጴጥ/፩፡ ፮—፯ ፤ ምዕ/፬ ፡ ፲፬—፲፰) ፡ እያለ ፡ የክርስቲያን ፡ መከራ ፡ ለክብርና ፣ ለምስጋና ፡ መሆኑን ፡ በደስታም ፡ መቀበል ፡ እንደሚገባ ፡ ያስረዳል። ራሱ ፡ ክርስቶስ ፡ ለኛ ፡ ሲል ፡ ራሱን ፡ ወደ ፡ ፈተና ፡ አስገባ ፤ ተጋደለም ፤ በመጨረሻም ፡ ድል ፡ ነሣ ። (ማቴ/ ፬፡ ፩—፲፩) ። ከዚህም ፡ ሌላ፡ ራሱ ፡ ሲያስተምር ፡ እላንት ፡ የተመሰገናችሁ ፡ ናችሁ ፤ በሰደቧችሁ ፤ ባሳደዷችሁ ፡ ጊዜ ፤ በላያችሁም፡ ክፉውን፡ ኹሉ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ በሐሰት ፡ ስለኔ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፤ ሐሴትም ፡ አድርጉ፡ ዋጋችሁ ፡ በሰማያት ፡ ታላቅ ፡ ነውና ። እንዲሁ ፡ ነቢያትን ፡ ከላንት ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡ አሳደዋልና» (ማቴ/፭፡ ፲፩—፲፪)፡ እያለ፡ አመስግኗልና። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ራሳቸውን ፡ በፈቃዳቸው ፤ በደዌም ፡ በሰጊድ ፡ በትህርምት ፡ ይኽንም ፡ በመሳሰለ ፡ ትሩፋት ፡ የሚቀጡ ፤ ከሥጋቸው ፡ ጋራ ፡ የሚጋደሉ ፡ መንፈሳውያን ፡ አርበኞች ፡ አሉ ፤ እነርሱም ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

## የተጋድሎ ፡ ዋጋ ፤

አንድ ፡ ተጋዳይ ፡ ከጠላት ፡ ወረራ ፡ ተጋድሎ ፡ የሀገሩን ፡ ነጻነትና ፡ ሀብት ፡ እንዲጠብቅ ፤ በነጻነቱ ፡ እንዲኮራ ፡ በሀብቱም ፡ እንዲደሰት ፡ አንድ ፡ ክርስቲያንም ፡ በመንፈሳዊ ፡ ተጋድሎው ፡ በየጊዜው ፡ ከሚመጣ በት ፡ ፈተና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጾዋትወ ፡ መከራና ፡ ፈተና ፡ ተጋድሎ፡ ነፍሱን፡ ከሰይጣን ፡ ባርነት ፡ ያዳነ ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ሲደሰት ፡ ይኖራልና ። በተለየ ፡ ካህኑ ፡ ግን ፡ ራሱንም ፡ ምእመናንንም ፡ ለማዳን ፡ በሚያደርገው ፡ ተጋ ድሎ ፡ እንደ ፡ ማራኪ ፡ ጐበዝ ፡ በጌታው ፡ ፊትም ፡ ግዳይ ፡ እንደሚጥል፡ ምርኮ ፡ እንደሚያስረክብ ፤ ካህኑም ፡ በጌታው ፡ ፊት ፡ «አንተ ፡ መልካም፡ ባሪያ ፡ የታመንክም ፤ በጥቂት ፡ የታመንክ ፡ እኔ ፡ በብዙ ፡ እሾምሀለሁና ፡ ግባ ፡ ወደ፡ ጌታህ ፡ ደስታ . . . ፤ » (ማቴ/ ፳፭፡ ፳፩—፳፫) ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ይሰማልና ። የተጋድሎ ፡ ተቃራኒው ፡ ራስን ፡ ለመጣው ፡ ኹሉ ፡ ማስገዛት ፤ ፈቃድን ፡ አለመግታት ፤ ለኹሉ ፡ መሳሳት ፤ መጓጓት ፡ ነው ። ይህም ፡ ኹሉ ፡ ከክርስትና ፡ ጠባይ ፡ ውጭ ፡ የኾነ ፡ ነው ።

## ፫ኛ/ ትህርምት ።

ትህርምት ፡ ማለት ፡ መጥፎውን ፡ ነገር ፡ ከማየት ፤ ከመስማት ፤ ከማ ሰብ ፡ መራቅ ፡ መከልከል ፡ መተው ፡ ነው ። ደግሞም ፡ እንዳገኙ ፡ ከበሉ፤ እንዳገኙ ፡ ከጠጡ ፤ ሰውነትን ፡ ከኀጢአት ፡ ገትቶ ፡ መኖር ፡ እንዴ ፡ ምን ፡ ይቻላል ፡ ብሎ ፤ ሲርበው ፡ ሲጠማው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ከብዙ ፡ ምግብ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ መጠጥ ፡ መከላከል ፡ ነው።ማንም ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ልቡ ፡ ከበላና ፡ ከጠጣ ፡ ልቡ ፡ ይደነድናል ፤ አእምሮው ፡ ይፈዛል፤ አካሉ ፡ ይደነዝዛል ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ያለበትን ፡ ኀላፊነት ፡ ኹሉ ፡ ይረ ሳና ፡ ምናለብኝ ፡ ይላል ፤ «በነፍሳችሁ ፡ ግን ፡ ተጠንቀቁ ፡ ልባችሁ ፡በስ ስት ፡ በስካርም ፡ እንዳይደነድን ፤ ስለ ፡ አዳርም ፡ በማሰብ ፡ ያም ፡ ቀን ፡ ድንገት ፡ እንዳይደርስባችሁ ፡ » (ሉቃ/፳፩፡ ፴፬) ሲል ፡ ሰውነታቸውን ፡ የሚያደነድኑትን ፡ ክርስቶስ ፡ ያስጠነቅቃቸዋል ። የሰውነት ፡ ልጓሙ ፤ ሰውም ፡ ራሱን ፡ ለመግታት ፡ የሚችለው ፡ ትህርምትን ፡ አዘውትሮ ፡ የያዘ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ነው።ማንኛውም ፡ የሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ መጥፎ፡ ምኞት፡



ኹሉ ፡ የሚመነጨው ፡ ከምግብና ፡ ከመጠጥ ፡ ብዛት ፡ ነው። አጋንንትም፡ ሰውን ፡ የሚቈራኙት ፡ በሰውነቱም ፡ የሚሰራጩት ፡ በምግብና ፡ በመ ጠጥ፡ ብዛት ፡ ነው። እንዲህ ፡ ያለውም ፡ ርኩስ ፡ መንፈስ ፡ ካልጾሙበት ፡ ካልጸለዩበት ፡ ሊወጣ ፡ እንደ ፡ ማይችል ፡ «እንዲህ ፡ ያለ ፡ ዐይነት፡ ግን ፡ አይወጣም ፡ በጾምና ፡ በጸሎት ፡ እንጂ ፤ »(ማቴ/፲፯፡ ፳፩፤ ማር/፱፡፳፱፤ሉቃ/ ፱፡፴፫) ሲል ፡ ክርስቶስ ፡ አስረድቷል።ይህም ፡ ሲሆን ፡ የትህርምት ፡ መድ ኀኒትነት ፡ ለነፍስ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በበለጠ ፡ ለሥጋም ፡ ይጠቅማል ፡ ማለት ፡ ደሙ ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ በሕዋሳቱ ፡ ሲዘወዋርና ፡ ልም ላሜ ፡ ሲሰጥ ፤ ለሰውነቱ ፡ ጤንነት ፡ ለልቡ ፡ ደስታ ፡ ይሰማዋልና ፤ መብል፡ መጠጥ ፡ ሲበዛ ፡ ግን ፡ ደሙ ፡ በኀይል ፡ ከመምታቱ ፡ የተነሣ ፡ ልቡ ፡ ይደክማል ፤ የደም ፡ ሥሩ ፡ ይጎዳል ፤ አእምሮው ፡ ይጠፋል ፤ ወይም ፡ የደ ሙን ፡ መዘዋወሪያ ፡ ቧምቧ ፡ እየመላው ፡ ትክክለኛ ፡ ካለመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ የደም ፡ በሽታ ፡ የተባለትን ፡ ያስከትላል ። ስለዚህ ፡ በዕውቀት ከፍ ፡ ተብለው ፡ የሚገመቱት ፡ ዶክተሮች ፡ እንደ ፡ መልካም ፡ መድኃ ኒት፡ ቈጥረው ፡ ለአንዳንድ ፡ በሽተኛ ፡ ጾምን ፡ ያዛሉ ። እንዲሁም ፡ አባ ቶች ፡ «ካልጠገቡ ፡ አይዘሉ ፡ ካልዘለሉም ፡ አይሰበሩ ፡ » እያሉ ፡ እንደሚ መሰክሩት ፡ ኹሉ ፤ ብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ አገኙ ፡ ከመብላታቸውና ፡ ከመጠጣታቸው ፡ የተነሣ ፡ ገደሉ ፡ ሜዳ ፡ እየመሰላቸው ፡ እየዘለሉ ፡ የተ ሰበሩ ፡ ብዙዎች፡ ናቸው፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ «ከተራብ ፡ ለጠገበ ፡ አዝ ናለሁ ፡ አለ ፤ ምነው ፡ ቢለው ፡ ወድቆ ፡ ይሰበራል ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ » አለው፡ ይባላል ። ለሥጋ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ጥቅም ፡ ሲሰጥ ፡ ለነፍስ ፡ የበለጠ ፡ እንደሚሰጥ ፡ ክርስቶስ ፡ «ስለ ፡ ጽድቅ ፡ የሚራቡ ፡ የሚጠሙ ፡ ሰዎች ፡ የተመሰገኑ፡ ናቸው፤እርሳቸው ፡ይጠግባሉና ፡ » (ማቴ/ ፭፡ ፮፤ መዝ/፻፯፡፱፤ ኢሳ/ ፶፭ ፡ ፲፯ ፤ ምዕ/ ፶፭ ፡ ፩ ፤ ምሳሌ ፡ ፳፩ ፡ ፳፩) ፡ ሲል ፡ አስረድቷል።

የሚጠግቡ ፡ የሚሰከሩ ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ፡ አላለም ፤ የሚራቡ ፡ የሚጠሙ ፡ አለ ፡ እንጂ ፤ ይህም ፡ ሲሆን ፡ ክርስቶስ ፡ የሰውን ፡ ጥቅሙን ፡ እንጂ ፡ ጉዳቱን ፤ ደስታውን፡ እንጂ ፡ መከራውን ፡ የማይወድ ፡ የታመነ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነውና ፡ ለነፍስም፤ ለሥጋም ፡ ጥቅም ፡ የሚሆነውን ፡ በሰፊው ፡ ተናገረ ። ትህርምትም ፡ ሲባል ፡ ከመጀመሪያው ፡ እንደ ፡ ተና ገርነው ፡ ከምግብና ፡ ከመጠጥ ፡ መራቅ ፡ በተለይም ፡ ቅባት ፡ የኾኑ ፡ ነገ ሮችን ፡ መከልከል ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ክፉውን ፡ ነገር፡ኹሉ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከማሰብ ፡ ከመናገር ፡ ከማየት ፡ ከመስማት ፡ ከመሥራት ፡ መራቅ ፡ ነው።
ቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ «ይጹም ፡ ዓይን ፡ ይጹም ፡ ልሳን ፡ እዝንኒ ፡ ይጹም ፡ እም
ሰሚዐ ፡ ሕሱም ፡ በተፋቅሮ ፡ » እያለ ፡ አስረድቷል ። ቅዱስ ፡ ያዕቆብም፡
«በመካከላችሁ ፡ ማንም ፡ አምልኮኛ ፡ ሁኖ ፡ ቢመስለው ፡ ልሳኑን ፡ የማ
ይለጉም ፡ ልቡን ፡ ያስታል ፡ እንጂ ፡ የርሱ ፡ አምልኮ ፡ ከንቱ ፡ ናት ። የነ
ጻች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያላደፈች፡ አምልኮ ፡ ይህች ፡ ናት ፤ ሰው ፡
አባትና ፡ እናት ፡ የሌላቸውን ፡ ባልቴቶችንም ፡ በመከራቸው ፡ ይጐበኛ
ቸው ፡ ዘንድ፡ ራሱንም፡ ከዓለም ፡ ርኩሰት ፡ ይጠብቅ፡ ዘንድ» (ያዕቆብ ፡
፩፡ ፳፮—፳፯) ፡ ሲል፡ ያስረዳናል። ትህርምት ፡ ከፍ፡ ያለ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡
ሊሠራ ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ፡ ስንዘረዝር ፡ ክርስቲያኖች ፡ ኹሉ ፡ ማዘው
ተር ፡ አለባቸው ። ካህኑ ፡ ግን ፡ ሕይወቱን ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ ቅዱስ ፡ ተግ
ባር ፡ አድርጎ ፡ መያዝና ፡ ሌላውንም ፡ ማስተማር ፡ አለበት ።

## የትህርምትም ፡ ዋጋው ፤

ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ፡ ዘረዘርነው ፡ በሥጋ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንዳ
ገኘ ፡ ከመናገር ፡ ተከልክሎ ፡ ከመንግሥት ፡ ፖለቲካ ፤ ከጥለኛ ፡ ሰው ፡
ይድናል ፤ ለሰውነቱ፡ ሚዛን፡ ይሆንለትና፡ የሚናገረው ፡ የሚሠራው፡ ኹሉ ፡
የተለካ ፡ ሁኖለት ፡ ውጤቱ ፡ ያማረ ፡ ይሆናል ፤ በነፍስ ፡ የኾነ ፡ እንደ ፡
ኾነ ፡ ዐሠርቱ ፡ ቃላት ፡ አሪትንና ፡ ስድስቱ ፡ ቃላተ ፡ ወንጌልን ፡ ለመጠ
በቅ ፡ የሚቻለው ፡ ከመብልና ፡ ከመጠጥ ፡ የታገሠ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ነው ፤
በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ የተመሰገኑ ፡ ስለ ፡ ጽድቅ ፡ ብለው ፡ የሚ
ራቡና ፡ የሚጠሙ ፡ በጠቅላላውም ፡ ጾምን ፡ ትህርምትን ፡ ቅዱስ ፡ ተግ
ባር ፡ አድርገው ፡ የያዙ ፡ ናቸውና ፤ (ማቴ / ፭ ፡ ፮) ። የትህርምት ፡ ተቃራ
ኒው ፡ እንዳገኙ፡ መብላትና ፡ መጠጣት ፤ ከዐሳብ፡ ከመጥፎ ፡ ነገር ፡ ኹሉ፡
አለ ፤ መጠበቅ ፡ ነው ።

## ፬ኛ ፡ ገንዘብ ፡ አለ ፡ መውደድ ።

ገንዘብ ፡ የማይወድ ፡ ማለት ፡ ገንዘቡን ፡ በሚገባ ፡ ይዞ ፡ ለደኻ፡ የሚ
መጸውተውን ፤ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚሰጠውን ፡ ዐሥራቱን ፡ በኵራ
ቱን ፡ በሚገባ ፡ እያወጣ ፡ የቀረውን ፡ ደግሞ ፡ በሚገባ ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡
የሚያውል ፡ ማለት ፡ ነው ። ብዙ ፡ ሀብት ፡ ብዙ ፡ ንብረት ፡ እያላቸው ፤



ብንበላው ፡ ብንጠጣው ፤ ለበጎ ፡ ተግባር ፡ ብናውለውስ ፡ ቢጐልብንስ ፤
ለድኻና ፡ ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ ብናውለውስ፡ ቢያልቅብንስ ፤ እያሉ ፡ ራሳ
ቸውም ፡ ሌላውም ፡ በችግር ፡ አለንጋ ፡ ሲገረፍ ፡ ዝም፡ ብለው ፡ የሚያዩ፡
ናቸው ። ይህንም ፡ የመሰሉ ፡ ሌሎች ፡ ገንዘብ ፡ ሀብት ፡ ካለን ፡ እያሉ፡ለማ
ይረባና ፡ ለማይጠቅም ፡ ሥራ ፡ የሚያውሉ ፤ የዕለት ፡ ጉርስ፡ የዓመት ፡
ልብስ ፡ ካገኘን ፡ የቀረውን ፡ ለዘመድ፡ ለወዳጅ ፡ ለድኻ ፡ እናካፍል ፡ የማ
ይሉ ፡ የገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ ተብትቦ ፡ የያዛቸው ፡ ናቸው ። ማነኛውም ፡ ክር
ስቲያን ፡ በተለይ ፡ ግን ፡ ካህኑ ፡ የዕለት ፡ ጉርስ ፡ የዓመት ፡ ልብስ ፡ ካገኘ፤
የቀረው ፡ ትርፉ ፡ መጠበቁ ፤ መሰብሰቡ ፡ ድካምና ፡ ኀጢአት ፡ እንደ፡ኾነ፤
ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ተባብረውበታል ።

«ስለዚህም፡ መብልና፡ ልብስ፡ ካገኘን፡ ይበቃናል» ፡ (፩ኛ፡ ጢሞ/፮:፰፤
ዘፍ/፳፰: ፳ ፤ምሳሌ ፡ ፴፡ ፰) ክርስቶስ፡ ሲያስተምር፡ ኹል፡ ጊዜ፡ እንድንለም
ነውም ፡ የሚመክረን ፡ «እንጀራችንን ፡ የሚበቃንን ፡ ስጠነ ፡ ለዛሬ ፡ »
(ማቴ / ፮፡ ፲፩) ፡ የሚለውን ፡ ነው ። ከኹሉ ፡ የበለጠ፡ በምንም፡ መሣሪያ ፡
ሊቈርጡት ፡ የማይቻል ፡ የኀጢአት ፡ ሥር ፡ ገንዘብ ፡ መውደድ ፡ እንደ ፡
ኾነ «የክፉ ፡ ኹሉ፡ ሥር ፡ ከብት፡ መውደድ ፡ ነውና፡ ይህነንም ፡ ሰዎች ፡
ሲወዱ ፡ ከሀይማኖትም ፡ ጠፉ ፡ ራሳቸውንም ፡ ወደ ፡ ብዙ ፡ ኀዘን ፡
አገቡ ፡ » (፩ኛ / ጢሞ:፮:፲) ሲል ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ተናግሮዋል ። ምክን
ያቱም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ማንኛውንም ፡ ኀጢአት ፡ ከመሥራት ፤ በተለይም፡
እግዚአብሔርን ፡ ከመካድ ፡ የሚያደርስ ፡ የገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤
በይሁዳ ፡ እንረዳው «ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ አንዱ ፡ አለ ፡ እርሱም ፡ ይሁዳ፡
ያስቆሮቱ ፡ የሴሞን ፡ ልጅ ፡ ያሲዘው ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፤ ምነው ፡ አይሸጥ ፡
ይህ ፡ ኹሉ ፡ ሽቱ ፡ በሦስት ፡ መቶ ፡ ድሪም ፡ ለድኾችም ፡ አይሰጥ ፤
ይህንም ፡ ያለው ፡ ለድሆች ፡ አዝኖ ፡ አይደለም ። ሌባ ፡ ነበርና ፡ እንጂ ፤
ከረጢቱም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበር ፤ በርሱም ፡ የተገኘውን ፡ ኹሉ ፡ ይይዝ ፡
ነበር ፡ » (ዮሐ / ፲፪ ፡ ፬—፮) ።

ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በፍቅረ ፡ ንዋይ፡ ፍላፃ ፡ ከተነደፈ ፤ በፍቅረ፡
ንዋይ ፡ ጦር ፡ ከተወጋ ፡ አለሁ ፡ አለሁ ፡ ሲል ፡ የሞተ፡ነው ፤ ስንት ፡ ሰዎች፡
ናቸው ፤ ገንዘብ ፡ ከመውደዳቸው ፡ የተነሣ ፡ ከባለሟልነታቸው ፡ የራቁ፡
ከማዕረጋቸው ፡ የወደቁ ! ከክብራቸው ፡ የተዋረዱ ! ከእምነታቸው ፡
የጐደሉ ! ሰይጣን ፡ ሰውን ፡ የሚያሸንፍበት ፡ ምክንያት ፤ የሚገባበት ፡

ክፍት ፡ በር ፡ ገንዘብ ፡ በመውደድ ፡ ነው ። እንኳን ፡ ሰውን ፡ ክርስቶስን ፡
ሰይጣን ፡ የተፈታተነው ፡ በገንዘብ ፡ ነው ፤ ክርስቶስ ፡ ግን ፡ በጸሊአ ፡ ን
ዋይ ፡ ድል ፡ ነሥቶታል ፡ (ማቴ / ፬ ፡ ፳—፲፩)።ገንዘብ ፡ አለመውደድ ፡
ለክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ ዋና ፡ ጥቅም ፡ ነው ፤ በተለይ ፡ ግን ፡ ካህኑ ፡ ይህ ፡
ነገር ፡ ሊታይበት ፡ ቀርቶ ፡ ሊሰማበት ፡ አይገባውም ፤ እንዲያውም ፡
በዚህ ፡ ነገር ፡ ሊጠረጠር ፡ አይገባውም ፤ ፍጹም ፡ ተዋርዶው ፡ ነው ።

## የገንዘብ ፡ መጥላት ፡ ዋጋው ።

ገንዘብን ፡ መጥላት ፡ ራስን ፡ ከሰይጣን ፡ አሽክላ ፡ ማዳን ፡ ይሆናል ፤
እንዲያውም ፡ የተቸገሩ ፡ ሰዎችን ፡ ክርስቶስ ፡ ያመሰግናቸዋል ፤ « በነፍ
ሳቸው ፡ የተቸገሩ ፡ ሰዎች ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ፤ መንግሥት ፡ ሰማያት፡
የርሳቸው ፡ ናትና ፡ » ሲል ፡ ያመሰግናል ፡ እንጂ ፤ የከበሩ ፡ ገንዘብ ፡ የወ
ደዱ ፡ አይልም። (ማቴ / ፭ ፡ ፫) ገንዘብ ፡ በመጥላት ፡ ነፍሳቸውን ፡ ያዳኑ ፡
ብዙዎች ፡ ናቸው ። የገንዘብ ፡ መጥላት ፡ ተቃራኒው ፡ ያለመጠን ፡ ገን
ዘብ ፡ መውደድ ፤ ገንዘብን ፡ ማምለክ ፤ ከአይደለም ፡ ቦታ ፡ ማዋል ፡
ነው ፤ ይህም ፡ የኀጢአት ፡ ሥር ፡ ነው ።

## ፫ኛ ፤ ምጽዋት ።

ምጽዋት ፡ ማለት ፡ በማንኛውም ፡ ነገር ፡ ከርሱ ፡ ላነሱት ፡ ሰዎች ፡
የሚያደርገው ፡ ርዳታ ፡ የሚሰጠው ፡ ስጦታ ፡ በጠቅላላም ፡ ከልቡናው ፡
የሚመነጩ ፡ ኀዘኔታዎችና ፡ ልግሥና ፡ ናቸው ። ይህም ፡ በማሰብ ፤ በመ
ናገር ፤ በመሥራት ፡ ሊፈጸም ፡ ይቻላል ፤ ማለት ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡
ሰጠው ፡ ስጦታና ፡ ችሎታ ፡ የርኅራኄውን ፡ ሥራ ፡ ሊሠራለት ፡ ይችላል፤
ግን ፡ ሀብት ፡ ንብረት ፡ እያለው ፡ በቃል ፡ ብቻ ፡ ረዳዋለሁ ፡ ማለት ፡ ሐሰ
ትን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ መናገር ፡ ይቆጠራል ። ስለዚህም ፡
በሥ
ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ «ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ አንዋደድ ፡ በቃል ፡ በምላስም ፤ በሥ
ራና ፡ በእውነት ፡ እንጂ ፡ » (፩ኛ፡ዮሐ/ ፫፡፲፰) እያለ ፡ ይመክረናል ። ሰው ፡
ባለው ፡ በችሎታው ፡ በስጦታው ፡ መርዳት ፡ እንደሚገባ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥ
ሮስና ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ በሠሩት ፡ በተናገሩትም ፡ ልንረዳው ፡ እንችላለን
« . . . . ይህ ፡ ጴጥሮስና ፡ ዮሐንስ ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ሲገቡ ፡ ባየ ፡



ጊዜ ፡ ለመናቸው ፡ ምጽዋት ፡ ከርሳቸው ፡ ሊወስድ ፤ ጴጥሮስም ፡ ከዮሐ
ንስ ፡ ጋራ ፡ አድንቆ ፡ ተመለከተው ፡ አለውም ፡ ወደኛ ፡ ተመልከት ፡ እር
ሱም ፡ ወደርሳቸው ፡ አየ ፤ ተስፋ ፡ አድርጎ ፡ ከርሳቸው ፡ ምጽዋት ፡ የሚ
ወስድ ፡ መስለው ፤ ጴጥሮስም ፡ አለው ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ወደኔ፡ አይገኝም፤
ወደኔ ፡ ያለውን ፡ ግን ፡ እርሱን ፡ እሰጥሀለሁ፤ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ በናዝ
ሬቱ ፡ ስም ፡ ተነሣና ፡ ሂድ ፡ » (የሐ/ ሥራ፡፫ ፡ ፩—፯) ማንም ፡ ሰው ፡ ባለው ፡
ሀብትና ፡ በተሰጠው ፡ ዕውቀት ፡ በጠቅላላውም ፡ በተቻለው ፡ ኹሉ ፡
ከርሱ ፡ ዝቅተኛ ፡ የኾኑትን ፡ ካልረዳ ፡ የዓለም ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ የተሰ
ነካከለ ፤ ጸጥታው ፡ ያልተረጋገጠ ፡ ይሆናል ። ችግርም ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡
ላይ ፡ ይነግሣል ፤ ማለት ፡ « ዘመድ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ቢረዳ ፡ ችግርም ፡
አይጎዳ ፡ » የሚሉት ፡ የአባቶች ፡ ምሳሌ ፡ የተረጋገጠ ፡ ይኾናል ።

ከዓለማዊ ፡ ሥራ ፤ ከማኅበራዊም ፡ ሥራ ፤ ከመንፈሳዊም ፡ ሥራ ፡
ኹሉ ፡ ከምጽዋት ፡ የሚደርስና ፡ የበለጠ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ከቶ ፡ የለም፤
እንዲያውም ፡ ከመሥዋዕት ፡ ምጽዋት ፡ እንደሚበልጥ ፡ « ሂዱ ፡ ግን ፡
ምሕረት ፡ እወዳለሁ ፡ መሥዋዕትም ፡ አይ
ዕወቁ ፡ ይህ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ምሕረት ፡ እወዳለሁ ፡ መሥዋዕትም ፡ አይ
ደለም - - - ፡ » (ማቴ/ ፱ ፡ ፲፫ ፤ ሆሴዕ፡ ፯ ፡ ፯ ፤ ሉቃስ፡፫፡፲፩) ሲል ፡ ክርስቶስ ፡
አስረድቷል ። ለሰው ፡ የሚራሩ ፡ የሚያዝኑ ፡ የምሕረትን ፡ የምጽዋትን ፡
ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ የተመሰገኑ፡ ናቸው ፡ ሲል ፡ እንዲሁ ፡ በመጀመሪያው፡
ጉባኤው፡ ንግግር፡ በሰፊው፡ አስረድቷል ፡ (ማቴ/፭ ፡ ፯ ፤ ሉቃስ ፡ ፲፩፡ ፵፩) ።
ምጽዋት ፡ ከፍጹም ፡ ፍቅር ፡ የተነሣ ፡ ለኔ ፡ የማታስኘ ፡ ከልቡና ፡ የምት
መነጭ ፡ ርኅራኄ ፡ የክርስትና፡ ሃይማኖትና ፡ ፍቅር ፡ የምትገለጥባት እው
ነተኛ ፡ ትሩፋት ፡ ናት ፤ ማለት፡ ክርስቲያን፡ ሁኖ ፡ ፍቅር ፡ የሌለው ፤ ፍቅ
ርም ፡ እያለው ፡ እንደ ፡ ችሎታው ፡ ባልንጀራውን ፡ ካልረዳውና ፡ የም
ሕረት ፡ ሥራውን ፡ ካልሠራለት ፤ እምነቱም ፡ ፍቅሩም ፡ ከንቱ ፡ ዋጋ ፡
የሌለው ፡ ነው ። ይህ ፡ ትሩፋት ፡ ለክርስቲያኑ ፡ ኹሉ ፡ የሚገባ ፡ ሲሆን ፤
ለካህኑ ፡ ዕጥፍ ፡ ይሆንበታል ፤ ማለት ፡ ፩ኛ ፡ ራሱ ፡ በመፈጸም ፡ ካለው ፡
ከገንዘቡ ፤ ከቃሉ ፤ ከማንኛውም ፡ ችሎታው ፡ ማበርከት ፤ ፪ኛም ፡ ለምእ
መናን ፡ በማስተማርና ፤ በመምከር ፡ ሊፈጽመው ፡ ይችላል ።

www.ethiopianorthodox.org

## የምጽዋት ፡ ዋጋው ።

ምጽዋት ፡ በዚህም፡ ዓለም ፡ በወዲያኛውም ፡ ዓለም ፡ የምትጠቅም፡
ናት ፤ ማለት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ፩ኛ ፡ የራሱ ፡ ሀብት ፡ እየሰፋለት ፡ እየበዛ
ለት ፡ ይሄዳል ፤ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ አብርሃምን ፡ እንያዝ ፡ «እግዚአብሔር
ከሃሊ ፡ ነው ፤ ጸጋን ፡ ኹሉ፡ ያበዛላችሁ፡ ዘንድ ፡ ኹሉ ፡ የተሰጣችሁ ፡ እስ
ክትኾኑ ፡ ድረስ ፤ ትርፍም ፡ አላችሁ ፡ በመልካም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፤ እንደ ፡
ተጻፈ ፡ በተነ ፡ ለድኾችም ፡ ሰጠ ፡ ጽድቁ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል »
(፪ ቆሮ /፳፰ ፡ ፱፡ ፳) ። ሰሎሞንም ፡ ይህን ፡ ሲያስረዳ ፡ «ለድኻ ፡ የሚሰጥ ፡
አይጐልበትም ፤ ዐይኖቹን ፡ ግን ፡ የሚጨፍን ፡ እጅግ ፡ ይራብማል ፡ »
(ምሳሌ ፡ ፳፪) ፡ ይላል ።

፪ኛ/ ራሱ ፡ ሰውን ፡ እንደ ፡ ረዳ ፡ ሰውም ፡ ይረዳዋል ፤ ምጽዋት ፡
እንደ ፡ ብድር ፡ ያለ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ አንዱ፡ አንዱን፡ በመርዳቱ ፡
ችግረኛ ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ። ኦሪትም ፡ ነቢያትም ፡ ሐዲስ ፡ ኪዳንም ፡
ስጡ ፡ ይሰጣችኋል ፤ አድርጉ ፡ ያድርጉላችኋል፡ ትላለችና ፡ «ሰዎች ፡ ሊያደ ፡
ርጉላችሁ ፡ የምትወዱትን ፡ እንዲሁም ፡ እናንተም ፡ አድርጉላቸው ፤ ኦሪ
ትም ፡ ነቢያትም ፡ ይህ ፡ ነውና ፡ » (ማቴ/ ፯ ፡ ፲፪ ፡ ሮሜ/ ፲፫ ፡ ፰—፲) ።

በነፍስ ፡ ምጽዋት ፡ የሚጠቅመው ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለው ፡
የሚሰጡት ፡ ሀብት ፡ ብል ፡ ነቀዝ ፡ ከማያበላሸው ፡ መዝገብ ፡ እንደ ፡ ተቀ
መጠ ፡ ይሆናል ፤ ማለት ፡ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ ያገኙታልና ፡ «ለላንት ፡
መዝገብ ፡ አትሰብስቡ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ትል ፡ ወደሚበላው ፡ ነቀዝም ፡
ወደሚያነቅዘው ፤ ሌቦችም ፡ ነድለው ፡ ወደሚሰርቁት ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለላ
ንት ፡ መዝገብ ፡ ሰብስቡ ፡ በሰማይ ፡ ትል ፡ ወደ ፡ ማይበላው ፤ ነቀዝም ፡
ወደ ፡ ማያነቅዘው ፤ ሌቦችም ፡ ነድለው፡ ወደ፡ ማይሰርቁት፤ መዝገባቸው፡
ወዳለበት ፡ ልባቸው ፡ ከዚያው ፡ በተስፋ ፡ ይኖራልና ፡ » ማቴ / ፮ ፡ ፲፱ ፡
፳፩) ፡ ምጽዋት ፡ በየጊዜው ፡ ብዙ ፡ ትርፍ ፡ እንደሚሰጥ ፡ አክሲዮንና፡ በባ
ንክ ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ፡ የሚረባ ፡ ሀብት ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ በኋለ
ኛው፡ ዘመን ፡ ትርፉን ፡ በዕጥፍ ፡ ያገኙታልና ፡ «ነገር ፡ ግን ፡ ጠላቶቻ
ሁን ፡ ውደዱ ፡ መጽውቱም ፡ አበድሩም ፡ ምንም ፡ ተስፋ ፡ ሳታደርጉ ፡
ዋጋችሁም ፡ እጅግ ፡ ይሆናል ፤ የልዑልም ፡ ልጆች ፡ ትሆናላችሁ ፤ እርሱ



ለማያመሰግኑ ፡ ለክፎችም ፡ ቸር ፡ ነውና ፡ » (ሉቃ/፮ ፡ ፴፭) ። እንዲሁም ፡
ምጽዋት ፡ በደኅና ፡ መሬት ፡ እንደ ፡ ተዘራ ፡ ዘር ፡ ፍሬውን ፡ ዕጥፍ ፡ አድ
ርጎ ፡ እንደሚመልስ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ ዘሩን ፡ ጨብጦ ፡ አሳንሶ ፡ የዘሩት ፡
እንደ፡ ኾነ ፡ መከሩ ፡ አዝመራው ፡ በመጠኑ ፡ ይሆናል፡ ታፍኖ ፡ አብዝቶ፡
የዘሩት ፡ እንደኾን ፡ እንዲሁ ፡ መከሩ፡ የበዛ ፡ ይኾናል ፡ «በንፍገት ፡ የዘራ፡
በንፍገትም ፡ ያጭዳልና ፤ በበረከትም ፡ የዘራ ፡ በበረከትም ፡ ያጭዳል ፡ »
(፪ኛ ፡ ቆሮ / ፱ ፡ ፮—፯) ፡ ስለዚህ፡ ምጽዋት ፡ በልግሥና ፡ በደስታ ፡ የሚ
ሰጠውን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወዳል ። የምጽዋት ፡ ተቃራኒ ፡ ገንዘብ ፡ መው
ደድ ፤ ጨካኝነት ፡ ነው ።

## ፯ኛ/ ትሕትና ።

ትሕትና ፡ ማለት ፡ ዐዋቂ ፡ ሲሆን ፡ እንዳለላዋቂ ፤ ክቡር ፡ ሲሆን ፡
የተዋረደ ፤ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሲሆን ፡ እንደ ፡ ዝቅተኛ ፡ አድርጎ ፡ ራስን ፡ ለሰው፡
የሚያዋርድ ፡ በጠቅላላውም ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ ቆጥሮ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ ማድረግ ፡ ነው ። የዚህም ፡ ትሩ
ፋት ፡ መሪው ፡ አስተማሪው ፡ መድኀኒታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡
ማለት ፡ ከከፍተኛ ፡ ዙፋኑ ፡ ለኛ ፡ ሲል ፡ ልዑል ፡ ባሕርዩን ፡ ዝቅ ፡ አድ
ርጎ ፡ ሰው ፡ ኾነ ፤ ለኛ ፡ ሲል ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መከራን ፡ ተቀበለ ፤ ይህን ፡
ያህል ፡ ትሕትና ፡ ምን ፡ ትሕትና ፡ ነው ! ሌላውን ፡ ደግሞ ፡ እንዲህ ፡
ሲል ፡ ያስተምራል ። «ቀንበሬን ፡ በላያችሁ ፡ ተሸከሙ ፡ ከኔም ፡ ተማሩ፤
እኔ ፡ የዋህ ፡ ነኝና፡ ልቤም፡ ትሑት፡ ነውና፡ » (ማቴ/፲፩፡ ፳፱) ፡ እንዲሁም፡
በሌላው ፡ ምዕራፍ ፡ ከናንተ ፡ ውስጥ ፡ የሚበልጠው ፡ ሎሌ ፡ ይሁናችሁ፤
ነፍሱን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደረገ ፡ ዝቅ፡ ይላልና፤ ነፍሱንም ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ ያደ
ረገ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላልና ፡ » (ማቴ/ ፳፫፡፲፩ ፤ ሉቃስ/፲፰፡ ፲፬) ። በሚያስተ
ምርበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ፡ ትሕትና ፡ በዕድሜ ፡ በማዕርግ ፡ ዝቅተኛ ፡ ከሆነው ፡
ከሰው ፡ ወገን ፡ ሕፃን ፡ ጠርቶ ፡ በመካከላቸው ፡ አቁሞ ፡ « እንደዚህ ፡
ሕፃን ፡ ራሱን ፡ ያዋረደ ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚበ
ልጥ ፡ (ማቴ / ፲፰ ፡ ፬) ሲል ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ ራሳቸውን ፡ ያዋ
ረዱ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንደሚበልጡ ፡ አስረድቷል ።

የርሱን ፡ ትምህርት ፡ ተከትለው ፡ ሐዋርያት ፡ ለሕዝቡ፡ ራሳቸውን፡
እያዋረዱ ፡ ያስተምሩ ፡ ነበር ፤ ከነርሱም ፡ ውስጥ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡

www.ethiopianorthodox.org

«ከኹሉ ፡ ሐዋርያት ፡ አንሳለሁና ፡ የማይገባኝ ፡ ነው፡ ሐዋርያው ፡ እባል፡
ዘንድ - - - ፡ » (፩ኛ ፡ ቆሮ / ፲፭ ፡ ፱) እያለ ፡ ራሱን ፡ አዋርዶ ፡ ያስተምር፡
ነበር።ሌሎችም ፡ ሐዋርያት ፡ ራሳቸውን ፡ አዋርደው ፡ ለኹሉ ፡ አስገዛ
ተው ፡ በሚሠሩበት ፡ ጊዜ ፡ ሲዋረዱ ፡ አይከፋቸው ፤ ቢያከብሩዋቸውም ፡
ደስ ፡ አይላቸው ፡ እነርሱም ፡ ወድቀው ፡ አይቀሩም ፡ ነበር ፤ «እንሰደዳ
ለን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንጣልም ፤ እንወድቃለን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንጠፋም --»
(፪ ፡ ቆሮ / ፬፡፱) ብሎ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ በኀይል ፡ ላይ ፡
ኀይል ፡ እየተጨመረላቸው ፡ ሥራቸውን ፡ ያከናውኑ ፡ ነበር ።

ኹሉን ፡ ለማድረግ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ የመልካም ፡ ስጦታና ፡ የፍ
ጹም ፡ ጸጋ ፡ መገኛ ፡ የሚሆን ፡ አምላክ ፡ ሲመራቸው ፤ ሥራቸው ፡ እንዲ
ከናወንላቸው ፡ ሲረዳቸው ፡ ተልእኮዋቸውን ፡ በሚገባ ፡ አከናወኑ ፤ አሁ
ንም ፡ ካህን ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ ማድረግና ፡ ለኹሉ ፡ ማስ
ገዛት ፡ ተገቢው ፡ ነው ፤ ኹሉን ፡ እጅ ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻለው ፡ ራሱን ፡
ዝቅ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ነው ።

## የትሕትና ፡ ዋጋ ።

ትሕትና ፡ ከኹሉ ፡ የበለጠ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡አለው ፤ ማለት ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ የተዋረደ ፡ በወዲያኛው ፡ ከፍ ፡ ይላልና ። በመንግሥተ ፡ሰማያት፡
ከፍተኛ ፡ ተብሎ ፡ የሚገመተው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የተዋረደው ፡ ራሱን ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ዝቅ ፡ ያደረገው ፡ ነው ፡ የከፍተኞች ፡ የባለጠ
ጎች ፡ ዝናቸው ፡ ስም ፡ አጠራራቸው ፡ የጠፋ ፡ ሲሆን ፡ ትሑታኑ ፡ ከፍ ፡
ብለው ፡ ይታያሉ ፡ (ማቴ/ ፯ ፡ ፩—፲ ፤ ም/ ፲፰ ፡ ፪—፬ ፡ ም/ ፲፱ ፡
፳፮—፳፰) ። የዚህም ፡ ተቃራኒ ፡ ትዕቢት ፤ ሐኬት ፤ ኵራት ፡ ናቸው ፤ እነዚ
ህም ፡ የጥፋት ፡ ኹሉ ፡ ምንጮች ፡ ናቸው ።

## ፯ኛ/ ፡ ገርነት ።

ገርነት ፡ ማለት ፡ ሰውን ፡ ለማዳ ፡ የሚያደርግ ፤ ከኹሉ ፡ ዘንድ ፡ የሚ
ያዛምድ ፤ ለነፍስ ፡ ጸጥታን ፡ የሚሰጥ ፡ ትሩፋት ፡ ነው ። በሰው ፡ ኹሉ ፡
ላይ ፡ የአውሬነት ፡ ጠባይ ፡ የሚታይበት ፡ የገርነት ፡ መንፈስ ፡ ስለሌለ
ውና ፡ ምቀኝነትን ፤ ተንኰልን ፤ ቍጣን ፤ ራስ ፡ መውደድን ፤ ኵራትን ፡



ገንዘብ ፡ በማድረጉ ፡ ነው ። ገሮች ፡ የሚባሉ ፡ ከኹሉ ፡ ጋራ ፡ግንኙነት ፤
ዝምድናም ፤ ሰላም ፡ ያላቸው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የቍጣ ፡ መልክ ፡ የማይታይ
ባቸው ፤ ደማቸው ፡ የማይበረዝ ፤ በልቦናቸውም ፡ መጣጣ ፡ ነገር ፡ የሌለ
ባቸው ፡ የክርስቶስ ፡ ተከታዮች ፡ እውነተኞች ፡ ክርስቲያኖች ፡ ናቸው ።
እንደዚህ ፡ ያሉት ፤ ሰው ፡ ቢሰድባቸው ፡ ቢያዋርዳቸው ፡ ምንም ፡ ፍቺ ፡
አይሰጡትም ፤ እንዲያውም ፡ የጋለውን ፡ የሰውን ፡ ቍጣ ፡ በፍቅር ፡ ውኃ፡
የሚያበርዱ ፤ የለዘበ ፡ ቃል ፡ የሚናገሩ ፤ ዋጋቸውን ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ብቻ ፡ የሚጠብቁ ፡ ናቸው ። ለነዚህ ፡ ሰዎች ፤ ኹሉ ፡ ዘመዳቸው ፤ የሄዱ
በት ፡ ኹሉ ፡ አገራቸው ፡ ሁኖ ፡ በሰላም ፡ ይኖራሉ።ገሮች ፡ ከኹሉ ፡ ጋራ፡
በመፋቀራቸው ፡ የቅዱስ ፡ ጳውሎስን ፡ ትምህርት ፡ « ቢቻላችሁስ ፡
ሰላም ፡ አድርጉ ፡ በላንትና ፡ በሰው ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ » ( ሮሜ ፡ ፲፪ ፡
፲፰) ፡ ሲል ፡ ያስተማረውን ፡ ይፈጽማሉ ።

ገርነት ፡ የክርስቶስ ፡ ትምህርት ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡
«ገሮች ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ፤ እርሳቸውም፡ ምድርን፡ይወርሳሉና ፡ » (ማቴ/
፭፡፭) ሲል ፡ አስረድቷል ። እንዲሁም ፡ ይህንን ፡ የመሰለ ፡ «እንደ ፡ እባብ፡
ብልኆ ፡ እንደ ፡ ርግብም ፡ የዋሃን ፡ ኹኑ፡ » (ማቴ/፲፡፲፮) ሲል ፡ የዋህነት ፡
ለክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ እንደሚገባ ፡ አስረድቷል ። የክርስቶስንም ፡ ትምህ
ርት ፡ ይዘው ፡ ሐዋርያት ፡ ኹሉ ፡ ገርነትን ፡ ገንዘብ ፡ አድርገው ፡ ኑረዋል፤
ገርነትም፡ እንዲገባ፡ አስተምረዋል ። ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ «በትሕትናና፡በገ
ርነትም ፡ ኹሉ ፡ በትዕግሥትም ፡ እርስ ፡ በራሳችሁ ፡ ስትቻቻሉ ፡ በፍቅር»
(ኤፌ / ፬፡፪ ፤ ቆላ / ፫፡፲፪) ሲል ፡ ተናግሮአል ። በተለየ ፡ ግን ፡ ለካህን ፡ የዋህ
ነት ፡ ገርነት ፡ አስፈላጊነቱን ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ « ጠላቶችን ፡ በየዋህ
ነት፡የሚገሥጽ ፡ ምናልባት ፡ እግዚአብሔር ፡ ንስሓ ፡ ይሰጣቸው ፡ እንደ፡
ኾነ ፡ እውነትን ፡ ለማወቅ ፡ » (፪ኛ፡ጢሞ/ ፪፤ ፳፭) ሲል ፡ ገልጿል ። ገርነትና ፡
የዋህነት ፡ ይገባል ፡ ስንል ፡ ክፋውን ፡ ነገር ፡ ከመናገር ፤ ከማሰብ ፤ ከመ
ሥራት ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ለደግ፡ ነገርስ ፡ ጥበበኛ ፤ ዐዋቂ ፤ ተራቃቂ ፡ መሆን፡
ተገቢ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ «ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ በአእምሮ ፡
ሕፃናት ፡ አትሁኑ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በክፋት ፡ ሕፃናት ፡ ኹኑ ፤ በአእምሮ ፡
ግን ፡ ፍጹማን ፡ ኹኑ ፡ » (፩ ፡ ቆሮ / ፲፬ ፡ ፳ ፤ ፩ ፡ ጴጥ / ፪ ፡ ፩—፪ ) ሲል ፡
በሰፊው ፡ አስረድቶናል ።

www.ethiopianorthodox.org

## የገርነት ፡ ዋጋው ፤

በዚህ ፡ ዓለም ፡ የርስታቸው ፡ የሀብታቸው ፡ ባለቤቶች ፡ ሁነው ፡ ለልቡናቸው ፡ ሰላምን ፡ ለነፍሳቸው ፡ ዕረፍትን ፡ አግኝተው ፡ ኹሉ ፡ ዘመዳቸው ፡ ኹሉ ፡ ወዳጃቸው ፡ ሁኖ ፡ ይኖራሉ ። ገሮች ፡ የርስታቸው ፡ የሀገራቸው ፡ ባላባቶች ፡ ኾነው ፡ ወርሰው ፡ እንዲኖሩ ፡ «ገሮች ፡ ግን ፡ ምድርን ፡ ይወርሳሉ ፤ በብዙም ፡ ሰላም ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤ (መዝ/ ፴፯ ፡ ፲፩)፡ሲል፡ አስረድቷል ። በወዲያኛውም ፡ ዓለም ፡ አዲሱን ፡ ምድር ፡ አዲሲቱን ፡ ሰማይ ፡ ወርሰው ፡ ይኖራሉ» ፤ ገሮች፡ የተመሰገኑ፡ ናቸው ፡ እርሳቸውም፡ ምድርን ፡ ይወርሳሉና ፡ (ማቴ/ ፭ ፭) ፡ ምድር ፡ አልፋ፡ ምድር ፡ ትተካለች ፡ ይችንም ፡ ያለገሮች ፡ ማንም ፡ እንዳይወርስ ፡ አምላካዊ ፡ ቃል ፡ ዐውጇል ። ጻድቃን ፡ ገሮች ፡ የሚወርሷት ፡ አገር ፤ የሚገቡባት ፡ ከተማ ፤ ጥበበኛዋ ፡ ሠራተኛዋ ፡ እግዚአብሔር ፡ የኾነ ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸንታ ፡ የምትኖር ፡ የማትናወጥ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት፡ ናት ፡ ዕብ / ፲፩፡ ፲ ፤ ፪ኛ ፡ ጴጥ / ፫ ፡ ፲ ፤ ራዕይ ፡ ፳፩ ፡ ፩) ። የዚህም ፡ ተቃራኒ ፡ ያለመጠን ፡ ብልጠት ፡ ክፋት ፤ ብስጭት ፡ ነው ። ይኸም ፡ የካህን ፡ ዋና ፡ ጕድለት ፡ ተብሎ ፡ የሚገመተው ፡ ነው፡ ምክንያቱም፡ በቍጡ ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ፡ አያድርበትም ፤ ጸጋም ፡ አይሰጠውምና ።

## ፰ኛ/ ርኁቀ ፡ መዓት ።

ርኁቀ ፡ መዓት ፡ ማለት ፡ ልበ ፡ ሰፊ ፡ ነገር ፡ አላፊ ፡ ሁኖ ፡ ማንኛውንም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ቻል ፡ ማለት ፡ ማሳለፍ ፡ ቍጣውን ፡ በትዕግሥት ፡ መዓቱን ፡ በምሕረትና ፡ በሰላም፡ መልክ፡ ለውጦ፡ ሰላምን ፡ ፍቅር ፡ አንድነትን ፡ ገንዘብ፡ ማድረግ፡ ነው ። ሊቀ፡ ካህናት ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲሁ፡ «ርኁቀ ፡ መዓት ፡ ወብዙኅ ፡ ምሕረት ፡ » እየተባለ ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ይመሰገናል ። (መዝ / ፯ ፡ ፲፪) ፡ የእግዚአብሔር፡ እንደራሴ ፡ የሚሆን ፡ ካህኑም፡ እንዲሁ፡ ከቍጣ፡ የራቀ፡ በፊቱ ፡ የገርነት ፡ መንፈስ፡ ሊቀረጽበት ፤ ኹሉን በገርነት ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ። ቍጡ ፡ ብስጩ ፡ የኾነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ ምእመናንን ፡ ይበትናቸዋል ፤ ስሚታቸውንም ፡ ሊገልጡለት ፡ አይፈቅዱም ፤ ካህን ፡ ቀርቶ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሊቈጣ፡



አይገባውም ። ጊዜ ፡ አነጣሥቶት ፡ ደግሞ ፡ ቢቆጣ ፡ ሳይታረቅና ፡ ይቅር ፡ ሳይል ፡ ሊያድር ፡ አይገባውም « ተቆጡ ፡ ግን ፡ አትበድሉ ፤ ፀሐይም ፡ ሳይገባ ፡ ቍጣችሁን ፡ አብርዱ » (መዝ / ፬ ፡ ፬)፡ ሲል ፡ ያስረዳናል።ሁኖም፡ ካህኑ ፡ ሊቆጣበት ፡ የሚገባው ፡ ጊዜ ፡ አለ ፤ ሀይማኖት ፡ ሲለወጥ ፤ ትምህርቱ ፡ ሥርዐቱ፡ ሲናወጥ ፤ ሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲሻር ፡ መንፈሳዊ ፡ ተግባር ፡ ሲጓደል ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ሊያይ ፡ አይገባውም ፤ መብቱ ፡ ወደሚመለከተው ፡ ማስታወቅና ፡ ምእመናኑን ፡ ሊገሥጽ ፡ ይገባዋል ። ተግሣጽ ፡ ለካህን ፡ ዋና ፡ ተግባሩ ፡ ነው ፤ የጥፋት ፡ ሥራን ፡ ሲሠሩ ፡ እያየ ፡ ዝም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ኀላፊነቱን ፡ እንደ ፡ ዘነጋው ፡ ይቆጥሩና ፡ ይታዘቡታል ፤ ወይም ፡ ተባባሪያቸው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይገምቱታል ፤ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ምእመናኑ ፡ ጠባቂ ፡ እንደ ፡ ሌላቸው ፡ በጎች ፡ ይበተናሉ ።

## ከቍጣ ፡ መራቅ ፡ የሚሰጠው ፡ ዋጋ ።

ቍጣ ፡ የኀጢአት ፡ ኹሉ ፡ ምንጭ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ አንድ፡ ሰው ፡ በተቆጣ ፡ ጊዜ ፡ ኀይለ ፡ ቃል ? ጸያፍ ፡ ነገርን ፡ ከመናገር ፡ ያደርሰዋል ፤ ይኸም ፡ ንግግር ፡ ወይም ፡ ከመሞት ፡ ወይም ፡ ከመግደል ፡ ያደርሰዋል ። ስለዚህ ፡ ከቍጣ ፡ የራቀ ፡ ሰው ፡ ፩ኛ/ ራሱን ፡ ሕይወቱን ፡ ይጠብቃል ፤ ፪ኛም ፡ ከሌላው ፡ ወንጀል ፡ ይርቃል ። ማንኛውም ፡ ሕዝባዊ ፡ ከማኅበራዊ ፡ ኑሮው ፡ እየተለየ ፡ ሲሰነካከል ፡ የሚኖረው ፡ ቍጣን ፡ ከማዘውተሩና ፡ ገንዘብም ፡ አድርጎ ፡ ከመያዙ ፡ የተነሣ ፡ ነው ። የርኁቀ ፡ መዓት ፡ ተቃራኒ ፡ ብስጩ ፤ ነዝናዛ ፤ ቍጡ ፡ መኾን ፡ ነው ።

## ፱ኛ ፤ ኀዳጌ ፡ በቀል ።

ኀዳጌ ፡ በቀል ፡ ማለት ፡ በድሎ ፡ ማሩኝታ ፤ ተበድሎ ፡ ይቅርታ ፡ የሚያደርግ ፤ ቂምን ፡ በቀልን ፡ በደልንም ፡ በልቡናው ፡ የማያውል ፡ የማያሳድር ፡ ማለት ፡ ነው ። ይኸም ፡ ትሩፋት ፡ ከልቡና ፡ ንጽሕና ፡ ከገርነት፡ ከየዋህነት ፡ የሚመነጭ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ በልቡናው ፡ ክፋት ፡ ስለሌለበት ፤ የሚያደርጉበትን ፡ የሚናገሩትን ፡ በልቡናው ፡ ሊያውለው ፡ ሊያሳድረው ፡ አይፈቅድምና ። የይቅርታው ፡ መምህር ፤ የመጀመሪያው ይቅር ፡ ባይ ፤ የይቅርታው ፡ መዝገብ ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስ

www.ethiopianorthodox.org

ቶስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ «እርሱ ፡ በመካከላችን ፡ አስማምቷልና ፡ ኹለቱንም ፡ አንድ ፡ አደረገ ፤ በመካከልም ፡ የነበረውን ፡ ግድግዳ ፡ አፈረሰው ፤ በሥጋ ውም ፡ ጸልን ፡ ፈታው - - - - ኹለቱንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አስታረቀ ፡ በአንድ ፡ ሥጋ ፡ በመስቀሉ ፡ ጸልንም ፡ ገደለ ፡ በአካሉ ፡ » (ኤፌ / ፪ ፡ ፲፬- ፲፮) ፡ ሲል ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በሰፊው ፡ አስረድቷል ። ክርስቶስም ፡ በመ ጀመሪያ ፡ ጉባኤው ፡ ሕዝብ ፡ አብዝቶ ፤ ጉባኤ ፡ አስፍቶ ፡ በሚያስተምር በት ፡ ጊዜ ፡ «እርቅ ፡ የሚያደርጉ ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ፤ እርሳቸው ፡ የእ ግዚአብሔር ፡ ልጆች፡ ይባላሉና፡ » (ማቴ / ፭ ፡ ፱ ፡ ) ሲል ፡ ተናግሯል ። በዚ ያን ፡ ጊዜ ፡ ቅን ፡ መላሽ ፡ ቢገኝ ፡ ኑሮ ፡ ኹሉን ፡ ይቅር ፡ የምትል ፡ የይቅ ርታ ፡ መምህር ፡ አንተ ፡ እንጂ ፡ ኹል፡ ጊዜ፡ የተመሰገንክ ፡ ነህ ፤ ምስጋና፡ አሁንም ፡ ይግባህ ፡ ባለው ፡ ነበር ። በሌላም፡ ጊዜ ፡ ሲያስተምር ፡ የሰላም፡ መምህር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ «ሰላምን ፡ እተውላችኋለሁ ፡ ሰላምን ፡ እሰጣች ኋለሁ ፡ እኔ ፡ የምሰጣችሁ ፡ ዓለም ፡ እንደሚሰጠው ፡ አይደለም ፡ - - - - » (ዮሐ/፲፬ ፡ ፳፯) ፡ እያለ ፡ የሰላም ፡ የዕርቅ ፡ መዝገብ ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከርሱ ፡ ለሌላው ፡ እንደሚናኝ ፡ ያስተምራል ።

የበደለውንም ፡ ዓለም ፡ ራሱ ፡ ክሶ ፡ ለመታረቅ ፡ ፈቅዶ ፡ በተሰቀለ ጊዜ ፡ « - - - - አባቴ ፡ ሆይ ፡ ስረይላቸው ፡ የሚያደርጉትን ፡ አያውቁም ፡ ና ፡ » (ሉቃስ፡ ፳፫፡ ፴፬) ፡ ብሎ፡ ከአባቱ፡ ጋራ፡ አስታረቀ ፤ እርሱም ፡ ዓለ ምን ፡ ታረቀ ። ይቅርታ ፡ ለክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ ይገባዋል ፤ በተለየ ፡ ግን ፡ በካህኑ ፡ ላይ ፡ ጐልቶ ፡ ሰፍቶ ፡ ሊታይበት ፡ ይገባዋል ፤ ምክንያቱም ፡ የክ ርስቶስ ፡ ተከታይ ፡ ስለ ፡ ኾነ፤ ክርስቶስ፡ ሲገርፉት፡ ሲገፉት ፡ ሲያዳፉት፡ ከቶ ፡ አልተመረረም ፡ አልተቀየመም ፡ « ሲሰድቡት ፡ አልተሳደበም ፡ መከራም ፡ ሲያጸኑበት ፡ አልተቀየመም ፡ እውነተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ለሚፈ ርደው ፡ ነፍሱን ፡ ሰጠ ፡ እንጂ ፡ » (፩ኛ ፡ ጴጥ / ፪፡ ፳፫) ፡ ሲል ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥ ሮስ ፡ መስክሮለታልና ። ስለዚህ፡ ካህኑ፡ የክርስቶስ ፡ ተከታይ ፡ ለመሆኑ ፡ መታወቂያው፡ ምልክት፡ ኀዳጌ ፡ በቀል ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ኹል፡ ጊዜ፡ ይቅር ፡ ማለት ፡ በጣም ፡ ተበድሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በቀላሉ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ይቅር ፡ ማለት ፡ አይደለም ፤ ክርስቶስ ፡ ራሱ ፡ ጠላቶቹ ፡ ስንሆን ፡ ካሣ ፡ ሳይፈ ልግ ፡ ይቅር ፡ አለን ፡ «እግዚአብሔርም ፡ ጠላቶቹ ፡ ስንሆን ፡ ከታረ ቀን ፡ - - - » (ሮሜ ፡ ፭፡፲) ፡ እያለ ፡ ቅዱስ፡ ጳውሎስ ፡ ያስተምራል ። ክርስ ቶስም ፡ ከትንሣኤው ፡ በኋላ፡ «ሰላም ፡ ለናንተ ፡ ይሁን ፡ » (ዮሐ / ፳፡፲፱) ፡



ሲል ፡ ለዓለም፡ ኹሉ ፡ ይቅርታን ፡ ሰጥቷል ። ይህም ፡ የሚያስረዳው ፡ ፩ኛ ፡ በእርግጥ ፡ እርሱ ፡ ዓለምን ፡ ይቅር ፡ እንዳለ ፡ ፪ኛ፡ ሐዋርያት ፡ የይ ቅርታ ፡ መምህራን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ የሚያስረዳ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ካህን ፡ የሆነ ፡ ኹሉ ፡ ይህን፡ ትሩፋት ፡ አብልጦ፡ መያዝና፡ የፍቅርና ፡ የይቅርታ ፡ መምህር ፡ መሆን ፡ አለበት ። በተለይም፡ ሰው ፡ ከሰው ፡ ጋር ፤ እንዲሁም ፡ ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ በተጣላበት ፡ ጊዜ ፡ ክርስቶስን ፡ ተከትሎ ፤ ክርስቶስን ፡ መስሎ ፡ ኹሉን ፡ የሚያስታርቅ ፤ ኹሉን ፡ የሚያስማማ ፡ እውነተኛ ፡ ካህን ፡ ያስፈልጋል ። ካህኑ፡ ይቅር ፡ ያለውን ፡ ካህኑ ፡ ያስታረ ቀውን ፡ እግዚአብሔር፡ ይቅር፡ ይለዋልና ። «እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ በም ድር ፡ ያሰራችሁት ፡ በሰማይ ፡ የታሰረ ፡ ይኾናል ፤ በምድርም ፡ የፈታች ሁት ፡ በሰማይ ፡ የተፈታ ፡ ይኾናል» (ማቴ / ፲፰ ፡ ፲፰ ፤ ምዕ / ፲፮ ፡ ፲፱ ፤ ዮሐ / ፳ ፡ ፳፫) ።

<u>የይቅርታ ፡ ዋጋ ።</u>

ይቅር ፡ የሚል ፡ ዋጋው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ይቅርታን ፡ ከእ ግዚአብሔር ፡ ያገኛልና ፡ «ለሰዎች ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ይቅር ፡ ብትሉ ፡ የሰማዩ ፡ አባታችሁ ፡ ደግሞ ፡ ይቅር ፡ ይላችኋል ፤ ለሰዎች ፡ ግን ፡ ኀጢአ ታቸውን ፡ ይቅር ፡ ባትሉ ፡ አባታችሁም ፡ ኀጢአታችሁን ፡ ይቅር ፡ አይ ላችሁም፡ » (ማቴ / ፮ ፡ ፲፬—፲፭ ፤ ማር / ፲፩ ፡ ፳፭) ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይቅርታን ፡ የሚያገኝ ፡ በምድር ፡ ይቅር ፡ ያለ ፡ ነውና፡ ስለዚህ፡ የይቅርታ ዋጋው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ክብር ፡ አግኝተው ፡ መንግሥቱን ፡ ወርሰው ፡ የሚኖሩ ፡ ልጅነታቸው ፡ የታወቀላቸው ፡ ይቅርታን ፡ የሚያደ ርጉ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ «ዕርቅ ፡ የሚያደርጉ ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ። እርሳቸውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ይባላሉ ፡ » (ማቴ / ፭ ፡ ፱) ፡ ሲል ፡ በጉባኤ ፡ ክርስቶስ፡ መስክሯል ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ መኾን፡ ቀርቶ ፡ በሥጋም ፡ በጋብቻም ፡ በልዩ ፡ ልዩም ፡ ምክንያት ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ለመዛመድ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ድካም ፡ ያደርጋሉ ፤ ሁነውስ ፡ ቢገኙ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ኵራት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ትምክህት ፡ ይሰማቸው ! ይህም ፡ ቀርቶ ፡ የንጉሡ ፡ ባለሟል ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፤ ይህም ፡ ቀርቶ ፡ ከፍ ፡ ካሉት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በሥጋም ፡ ኾነ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያት ፡ የተዛመዱ ፡

www.ethiopianorthodox.org

የቱን ፡ ያህል ፡ ኵራት ፤ የቱን ፡ ያህል ፡ ትምክህት ፡ ይሰማቸዋል ። ደስታ ቸውስ ፡ ምን ፡ ያህል ? በእርግጥም ፡ ይህ ፡ ሊኾን ፡ የሚገባው ፡ ታላቅ ፡ ደስታና ፡ ክብር ፡ ዓለው ፤ ታላቅም ፡ ዕድል ፡ ነው ፤ ግን ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ፡ ይቅር ፡ የሚሉ ፡ ይቅርታን ፡ የሚያደርጉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ይኾ ናሉ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ፤ የቱን ፡ ያህል ፡ ኩራት ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ትምክሕት ፡ ይሰማቸው ፡ ይሆን !

ማንም ፡ ክርስቲያን ፡ በጥምቀት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ይወለዳል፤ የእ ግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ይባላል ፡ «ለተቀበሉት ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ ሥልጣን፡ሰጣ ቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ በስሙ ፡ የሚያምኑ ፡ » (ዮሐ/ ፩ ፡ ፲፪ ፤ ፫ ፡ ፬—፲) ። ክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይቅርታ ፡ የማያደርግ ፡ ሰው ፡ ስሙ ፡ ከግ ብሩ ፡ ያልተባበረ ፡ ይኾናል ፤ ምክንያቱም ፡ የቀደመ ፡ ልጅነቱ ፡ አያስ መሰግነውም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይቅር ፡ የሚሉትን ፡ ይቅርታውን ፡ የእግዚአ ብሔር ፡ ልጅነቱን ፡ ያጸድቅለታል ፤ ያስመሰክርለታል ። ልጅ ፡ የአባቱን፡ ሀብት ፡ ኹሉ፡ እንደሚወርስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ይቅርታ ፡ የሚ ያደርጉ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ እንዲሠለጥኑና ፡ ኹሉን ፡ እንደሚወርሱ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ «ያም ፡ መንፈስ ፡ ለልባችን ፡ ይመሰ ክራል ፡ እኛ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ልጆቹም ፡ ከኾነ ፡ እኛ ፡ ወራሾቹ ፡ ነነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወራሾችና ፡ የክርስቶስ ፡ ባልን ጀሮች ፡ ወራሾች ፡ ነነ ። - - - » (ሮሜ ፡ ፲፰ ፡ ፲፮—፲፯) የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ መሆን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መሾም ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ስለ ፡ ኾነ፡ ይቅ ርታን ፡ ገንዘብ ፡ አድርገን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ እንሁን ። የይቅ ርታ ፡ ተቃራኒው ፡ ቂም ፤ በቀል ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ከሰይጣን ፡ የተገኘ ፡ ነው።

## ፲ኛ/ ፡ ንጽሕና ።

ንጽሕና ፡ ማለት ፡ መጀመሪያ ፡ እግዚአብሔር ፡ በአርአያውና ፡ በምሳሌው ፡ የፈጠረውን ፡ ሰውነቱን ፡ ከመጥፎ፡ ዐሳብ፤ከመጥፎ፡ነገር፤ ከመጥፎ ፡ ሥራ ፡ መከልከል ፤ ኹል፡ጊዜ፡ ዐዲስ ፡ ኹኖ ፡ በኀጢአት ፡ ሳያ ድፍ ፡ መኖር ፡ ነው ። በሠለጠነው ፡ ዓለም ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ልብሱ ንም ፡ አካሉንም ፡ በጽዳት ፡ እንዲይዝ፡ ብዙ፡ ትምህርት፡ ብዙ፡ ድርጅት፡ ያደርጋል ፤ ይህን ፡ ትምህርት ፡ ተከታትሎ ፡ ሰውነቱንም ፡ አካሉንም



በንጽሕና ፡ የማይከባከብ ፡ ሰውን ፡ ነቢብ ፡ አእምሮ ፡ ከሌለው ፡ ጾታ ፡ ጋራ ፡ ይገምቱታል ፤ ከሰው ፡ ተራ ፡ ያወጡታል ። ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ግን፡ ውስጣዊ ፡ ሰውነቱን ፡ በኀጢአት ፡ ዘወትር፡ የሚያሳድፍ ፡ በእግዚአብ ሔር ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ወቀሳ ፡ ያገኘው ! ከሰውነት ፡ ተራም፡ ያወ ጣው ! ስለዚህም ፡ ክርስቶስ ፡ ሲያስተምር ፡ «ወዮላችሁ ፡ እናንት ፡ ጻሐ ፎች ፡ ፈሪሳውያንም ፡ ግብዞች ፡ የጽዋውንና ፡ የወጭቱን ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ታጸራላችሁና ፡ ውስጣቸው ፡ ግን ፡ ቅምያ ፤ ስስትም፡ መልቷል ። አንተ፡ ፈሪሳዊ ፡ ዕውር፡ አስቀድመህ፡ የጽዋውንና፡ የወጭቱን ፡ ውስጥ ፡ አጥራ፡ ደግሞ ፡ ላያቸውን ፡ ንጹሕ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ። ወዮላችሁ ፡ እናንት ፡ ጻሐ ፎች ፡ ፈሪሳውያንም ፡ ግብዞች ፡ የተለሰነ ፡ መቃብር ፡ ትመስላላችሁና ፡ በሜዳ፡ መልካም፡ ኹኖ፡ የሚታይ ፡ በውስጡ ፡ ግን ፡ የሙታን ፡ አጥንት ፡ ርኩስም ፡ ኹሉ ፡ መልቶበታል ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ እናንት ፡ በሜዳ ፡ ለሰው ፡ ይምሰል ፡ ጻድቃን ፡ መስላችሁ ፡ ትታያላችሁ ፡ በውስጣችሁ ፡ ግን ፡ ማድላት ፡ ኀጢአትም ፡ መልቶባችኋል » (ማቴ/ ፳፫ ፡ ፳፭—፳፰) ፡ እያለ ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ ውሳጣዊ፡ ሰውነቱን፡ ንጹሕ ፡ ማድረግና ፡ በን ጽሕና ፡ መኖር ፡ እንዲገባ፡ ያስተምራል፤ በውጭ፡ ግን፡ ንጹሕ፡ መስለው፡ የሚታዩትን ፡ ይወቅሳል ። ንጽሕና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ማዕርግ ፤ የመጨረሻው፡ ደረጃ ፤ የብቃት ፡ ምልክት ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ በዐሳቡ ፡ በንግግሩ ፡ በሥ ራው ፡ ንጹሕ፡ የኾነ ፡ ሰውነቱ፡ መላልሰው፡ ካጠቡት ፡ ከብርሌ ፡ የበለጠ፡ የጠራ ፡ ኹኖ ፣ ፈጣሪውን ፡ ያየዋልና ፡ «ልባቸው ፡ የነጻ ፣ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ፤ እርሳቸውም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያዩታልና ፡ » (ማቴ/ ፭ ፡ ፰) ።

በመጀመሪያ ፡ እግዚአብሔር፡ ሰውን፡ ተገልጦ፡ ያነጋግረው ፡ ነበረ፤ በበደል ፡ ምክንያት ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ራቀ ፤ እግዚአብሔ ርም፡ ከሰው ፡ ተሰውሮ ፡ ነበር ፡ « የእግዚአብሔርንም ፡ የአምላክን ፡ ድምፅ ፡ ሰሙ፡ በገነት፡ ሲሄድ ፡ ነፋስ፡ በሚነፍስበት፡ ጊዜ፡ ከቀትር ፡ በኋላ፡ አዳምም ፡ ተሸሸገ ፤ ምሽቱም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ፊት ፡ በገ ነት ፡ ዛፍ ፡ መካከል ፡ » (ዘፍ/ ፫ ፡ ፰—፲፩) ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ኀጢ አት ፡ ታላቅ ፡ ግድግዳ ፡ ኹና ፡ ሰውንና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጋርዳ ፡ ትኖር፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ካለ ፡ ወዲህ ፡ ንጽሕና ፣ ያላ ቸው ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያዩታል ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ይነጋ ገራሉ ። ክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ በንጽሕና ፡ መኖርና ፡ እግዚአብሔርን ፡ መም



www.ethiopianorthodox.org

ሰል ፡ ይገባዋል ። እግዚአብሔር ፡ ንጹሐ ፡ ባሕርይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ንጽሕና፡ የሚስማማው ፡ ነው ፡ « ነገር ፡ ግን ፡ እንደጸራችሁ ፡ እንደ ፡ ቅዱሱ ፡ እና ንተም ፡ ደግሞ ፡ ቅዱሳን ፡ ኹኑ ፡ በአካሄዳችሁ ፡ ኹሉ ፤ ተጽፍዋልና ፡ ቅዱሳን ፡ ኹኑ ፡ እኔ ፡ ቅዱስ ፡ እንደ ፡ ኾንኩ ፡ » (፩ኛ፡ ጴጥ/ ፩፡፲፭—፲፮ ፡ ዘሌዋ/ ፲፩ ፡ ፵፬) እያለ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ያስተምራል ።

ቅዱስ ፡ ዳዊትም ፡ የንጽሕናን ፡ ጥቅም ፡ የንጽሕናን ፡ ዋጋ ፡ ዐውቆ ፡ «አቤቱ ፡ ንጹሕ ፡ ልብ ፡ ፍጠርልኝ ፡ የጸናውንም ፡ መንፈስ ፡ በልቡናዬ ፡ አድስልኝ ፡ »(መዝ/ ፶፩ ፡ ፲) እያለ ፡ ይጸልያል። ንጽሕና ፡ ለኹሉ ፡ ተገቢ ፡ ሲሆን ፤ ካህኑ ፡ በተለይ ፡ ሌላውን ፡ የሚያነፃ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከሐልዮ ፡ ከነ ቢብ፤ ከገቢር ፡ ንጹሕ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ካህን ፡ ረከሰ ፡ የሚባል ፡ ክሴት ፡ የተገኘ ፡ ዝሙት ፡ የሥራ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ እውነቱ ፡ የኾነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከማንኛውም ፡ የሚያሳፍርና ፡ የሚያጸይፍም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ መራቅ ፡ መከልከልና ፡ ንጽሕናን ፡ መያዝ፡ ተገቢው ፡ ነው ።

## የንጽሕና ፡ ዋጋ ።

የንጽሕና ፡ ዋጋ ፡ ፩ኛ/ ከማንኛውም ፡ ሐሜት ፤ ጥርጥር ፡ ይጠብቃል ፤ ታምራት ፡ ለማድረግ ፡ የሕዝብን ፡ ኀጢአት ፡ ለማስተስረይ ፡ ይችላል ። ፪ኛ/ ከሕዝብነት ፡ ደረጃ ፡ ይለይበታል ፤ እግዚአብሔር ፡ ያድርበታል ፤ ሥራውን ፡ ኹሉ ፡ ያቃናለታል ። ንጽሕና ፡ የሌለው ፡ ካህን ፡ ክንፉ፡ እንደ ፡ ተሰበረ ፡ ወፍ ፡ ነው ። ያ ፡ ወፍ ፡ ያለ ፡ ክንፍ ፡ ለመብረር ፡ እንደ ፡ ማይችል ፡ እርሱም ፡ ምንም ፡ ለመሥራት ፡ አይችልምና ። የንጽሕና ፡ ተቃራኒው ፡ ርኩሰት ፡ ኀጢአት ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ የማይ በጅ ፡ ነው ።

## ፲፩ኛ ፤ ትዕግሥት ።

ትዕግሥት ፡ ማለት ፡ ለኹሉ ፡ አለመቸኮል ፤ አለመቅበዝበዝ ፤ የያዙትን ፡ አለመሰልቸት ፤ አለማቃለል ፤ ደስታም ፡ ኾነ ፡ ኀዘን ፡ መቻል ፡ ማለት ፡ ነው ። የትዕግሥት ፡ ጀማሪው ፡ የትዕግሥት ፡ መምህሩ ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፤ እርሱ፡ ለኛ ፡ ሲል ፡ ከልዑል፡ ዙፋኑ ፡ ወርዶ ፡ መከራ ፡ እየተቀበለ ፡ በትዕግሥት ፡ እኛን ፡ እጅ ፡ አደረገ



እርሱም ፡ ሲያስተምር ፡ « እስከ ፡ መጨረሻው ፡ የታገሠ ፡ እርሱ ፡ ይድናል ፡ »(ማቴ/ ፲፡ ፳፪፡ ፳፬ ፡ ፲፫) ፡ ብሏል። ትዕግሥት ፡ የሰው፡ የድካሙ፡ ዋጋ ፡ አስመጪና ፡ ላኪ ፡ ናት ፤ ማለት ፡ ምንም፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ትሩፋት ፡ አብዝቶ ፡ ቢሠራ ፡ ሕግጋትን ፡ ቢጠብቅ ፤ ታግሦ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ካልደረሰ ፡ በመጀመሩ ፡ አብዝቶም ፡ በመሥራቱ፡ የሚያገኘው፡ ዋጋ ፡ የለም፤ የመከራው ፡ መድኀኒት ፤ የኀዘኑ ፤ ማቅለያ ፡ የድካም ፡ ማጽናኛ ፡ ትዕግሥት ፡ ብቻ ፡ ነው። «ይህም፡ ብቻ፡ አይደለም፡ በኀዘን ፡ እንመካለን ፡ እንዲ፡ ደግሞ ፡ ኀዘን ፡ ትዕግሥት ፡ እንዲያመጣልን ፡ ዐወቅን ፤ ትዕግሥትም ፡ መፈተንን ፡ መፈተንም ፡ አለኝታን ፡ » (ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፫) ፡ ሲል ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ትልቅ ፡ ትምህርት ፡ ይሰጠናል ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የዘረዘርናቸው ፡ ትሩፋት ፡ ኹሉ ፡ ለክርስቲያን ፡ እንዲገቡ ፡ በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ « ስለዚህም ፡ ጥረትን ፡ ኹሉ ፡ አቅርባችሁ ፡ በሃይማኖታችሁ፡ በጎነትን ፡ ጨምሩ ፤ በበጎነትም ፡ ዕውቀትን ፡ በዕውቀትም ፡ መሻትን ፤ መግዛት ፡ በመሻትም ፡ መግዛት ፡ ትዕግሥትን ፤ በትዕግሥትም ፡ አምልኮን ፤ በአምልኮም ፡ ወንድሞችን ፡ መውደድን፤ ወንድሞችንም፡ በመውደድ፡ ፍቅርን፤ ይህ፡ በላንት ፡ ቢሆን ፡ ቢበዛም ፡ ታካቾችና ፡ ያለ ፡ ፍሬ ፡ አያደርጋችሁም ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በማወቅ ... » (፪ኛ ፡ ጴጥ/፩፡ ፭—፱) ፡ እያለ ፡ ዘርዝሮ ፡ ተናግሮዋል ። በተለየ ፡ ግን ፡ ካህኑ ፡ አብልጦ፡ መያዝ ፡ አብልጦም ፡ መሥራት ፡ ይገባዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

# ክፍል ፡ ፫ ፡፡

## መንፈሳዊው ፡ ጠባቂ ፡ (ካህን ፡ ) ከተሾመ ፡ በኋላ ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ካህኑ ፡ ሊፈጽማቸው ፡ የሚገባው ፡ ተግባሮች ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ሊፈጽማቸው፡ ደግሞም ፡ ሊርቃቸው ፡ የሚገቡ ፡ ነገሮች ፡ አሉ ፤ እኒህም ፡ በሕግ ፡ ጠባያዊ ፡ ይታወቃሉ ፤ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ በዐሠርቱ ፡ ቃላተ ፡ ኦሪትና ፡ በስድስቱ፡ ቃላተ ፡ ወንጌል ፡ ተረድተዋል ። ማለት ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ለባልጀራው ፡ ለራሱ ፡ ሊፈጽመው ፡ የሚገባ ፡ ተግባርና ፡ ግዴታ ፡ እንዳለው ፡ በኢቲክስ ፡ ይታወቃል ። ከዚህ ፡ ግን ፡ ካህኑ ፡ ፩ኛ/ ፡ ለራሱ፤ ፪ኛ/ ፡ ለሕዝቡ፡ ሊፈጸመው፡ የሚገባውን ፡ እንናገራለን ፤ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ የሚፈጽመው ፡ ግን ፡ ለራሱም ፡ ለሕዝቡም ፡ የሠራው ፡ ኹኖ ፡ ይገኛል ።

ስለ፡ራሱም ፡ የሚፈጽማቸው ፡ ግዴታዎችና ፡ ተግባሮች ፡ በገጽ ፡ ፩፫—፲፱ ፡ ስለ ፡ ትሩፋት ፡ የተነገረውን ፡ መመልከት ፡ ያስፈልጋል ። ከዚህም ፡ ጋራ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ለጢሞቴዎስ « ለራስህ ፡ ተጠንቀቅ ፡ ለትምህርትህም ፤ በርሱዋ ፡ ጽና፤ይህንም ፡ ያደርግህ ፡ እንደኾንክ፡ ራስህን ፡ ታድናለህ ፡ የሚሰሙህንም ፡ ደግሞ ፡ » ( ፩ኛ ፡ ጢሞ/ ፬ ፡ ፲፮) ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፤ ራስን ፡ በመመርመር ፡ በማንጻት ፡ መንፈሳዊነትን ፡ በማዘውተር ፡ ልቡናን ፡ የሚያንጹ ፡ መጻሕፍትን ፡ በማንበብ፡ ይህንም ፡ በመሰለ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥራን ፡ በማዘውተር ፡ ጸንቶ ፡ መኖር ፡ ነው ።

#### ሀ/ ስለ ፡ ራሱ ፡

#### ፩ኛ/ ፤ መንፈሳዊነት ።

መንፈሳዊነት ፡ ለካህኑ፡በጣም፡አስፈላጊው ፡ ነው ፤ ማለት፡ምንም፡ ክህነት ፡ ራሱ ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ ቢኾን ፡ የካህኑ ፡ ስሜቱ ፡ ኑሮው ፡ ሥራው ፡ መንፈሳዊ ፡ ካልኾነ ፡ እንደ ፡ ዓላማው ፡ ለመሄድና ፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ለመፈጸም ፡ አይችልም።ካህን ፡ ሰማያዊ ፡ ስጦታ፡ ያለው ፡ ከሰማያውያን፡ መላእክት ፡ ጋራ ፡ የተቈጠረ ፤ ኑሮው ፡ በምድር ፡ ይሁን፡ እንጂ ፡ ሰማያዊ፡ ማዕርግ ፡ ያለው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከምድራውያን ፡ የተለየ ፡ አኗኗር ፡ መኖርና ፡ መሥራት ፡ ይገባዋል ። የክህነትን ፡ ማዕርግ ፡ ከተቀበለባት ፡ ዕለትና ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ ኑሮው ፡ የተለወጠ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በፍጹም ፡ ልቡናው ፡ ማወቅና ፡ መረዳት ፡ አለበት ። ሰውን ፡ በየጊዜው ፡ የሚገጥሙ ፡ ፈተናዎች ፡ ስማቸው ፡ ዐይነታቸው ፡ የበዛ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ብዙ፡ ሰውን፡ ከማዕርጉ ፡ አዋርደዋል ፤ በጦርነትም ፡ ድል ፡ ነሥተዋል ፤ በተለይ ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ በካህኑ ፡ ላይ፡ ዕጥፍ፡ ድርብ ፡ ኹነው ፡ ስለሚገኙ ፡ እነዚህን፡ ድል፡ ለመንሣት ፤ የነቁ ፡ የተጉ ፡ ሁኖ ፡ መኖር ፡ የግድ ፡ ያስፈልጋል ፤ ክርስቶስ፡ «ነገር ፡ ግን ፡ ጽኑ ፡ እኔ ፡ ዓለምን ፡ አሸንፍሁ ። » (ዮሐ/ ፲፮ ፡ ፴፫ ) ሲል ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ካህኑን ፡ የሚያጽናና ፡ ራሱን ፡ ከማንኛውም ፡ ፈተና ፡ እንዲያወጣ ፡ የሚረዳው ፡ ነው ።

## ፪ኛ/ ጸሎት ።

ጸሎት ፡ ማለት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ መነጋገር ፡ መለመን ፡ ማለት፡ ስለ፡ ኾነ ፤ ፈጣሪያችንን፡ በእምነታችን ፡ እናየዋለን ፤ በጸሎታችን፡ እንነጋገረዋለን ። ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ክርስቶስ ፡ ዘወትር ፡ ይጸልይ ፡ ነበር ፡ ዘወትርም ፡ መጸለይ ፡ እንዲገባ፡ በምሳሌ ፡ ያስተምር ፡ ነበር ፤ (ሉቃስ፡ ፲፩ ፡ ፩— ፬ ) ይኸውም፡ እኛን፡ ለማስተማር፡ እንደ፡ ኾነ ፡ ግልጥ ፡ ነው። የክርስቶስን ፡ ሥራና ፡ ትምህርት፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ተከትሎ ፡ «ጸልዩ፡ ሳትታክቱ፡፡ » (፩ኛ፡ ተሰሎ/ ፭፡ ፲፯፡ ሮሜ፡ ፲፪፡ ፲፪ ፤ ቆላስ፡ ፬፡ ፪)፡ እያለ ፡ ዘወትር ፡ ያስተምር ፡ ነበር ። ካህኑም ፡ ለራሱ ፡ ለሕዝቡ ፡ ዘወትር ፡ መጸለይ ፡ በግሉም ፡ ሕዝቡንም ፡ ሰብስቦ ፡ ሰዓት ፡ ወስኖ ፡ እንዲጸልዩ ፡ ማድረግ ፡ ዋና ፡ ተግባሩ፡ ነው ። «እኔ፡ እመክርሀለሁ፡ ከኹሉ፡ በፊት፡ ልመና፡ ጸሎትም ፤ መማለድም፡ ምስጋናም፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ እንዲደረግ ፡ ስለ፡ ነገሥታት ፡ ስለ ፡ ታላላቆችም፡ ኹሉ ፡ በሕይወታችን ፡ እንኖር ፡ ዘንድ ፡ በፀጥታና ፡ በሰላም ፡ በመልካም ፡ አምልኮ፡ ኹሉ ፡ በቅንነትም ፡ - - - - » (፩ኛ ፡ ጢሞ/ ፪፡ ፩—፫) ፡ ሲል፡ ቅዱስ፡ ጳውሎስ፡ ልጁን፡ ጢሞቴዎስን ፡ ያስተምራል ።



## ፫ኛ፡ ኑዛዜ ።

ኑዛዜ ፡ ማለት ፡ በየጊዜው ፤ በየሰዓቱ ፡ ደክመው ፡ የሠሩትን ፤ የተናገሩትን ፡ ያሰቡትን ፡ ለአበ ፡ ነፍሱ ፡ መናገር ፡ ማለት ፡ ነው ። ፩ኛ፡ ሰው ፡ ደካማ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ካህኑ ፡ ደክሞ ፡ የሠራውን ፡ ኀጢአቱን ፡ ተናዞ ፡ ነጻ ፡ ይኾናል ። ፪ኛ ፡ እርሱ ፡ ሲናዘዝ ፡ እያዩ ፡ ምእመናንም፡ በየጊዜው ፡ ለመናዘዝ ፡ መንገዱ ፡ ጥርጊያ ፡ ይኾናልና ።
፺፫—፺፬ ፡ ተመልከት ።

## ፬ኛ ፡ ትሩፋት ፡

ከ፹፫—፺፱ ፤ የዘረዘርነውን ፡ መፈጸም ፡ አለበት ፡ ማለት ፡ ለሰው ፡ መልካም ፡ አርአያ ፡ የሚኾንበትን ፡ ኹሉ፡ ካህን ፡ ቸል ፡ ሳይል ፡ መሥራትና ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

## ፭ኛ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን፡ ማንበብ ።

ለካህን ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍን ፡ ማንበብ ፡ የሥራው፡ ኹሉ ፡ መጀመሪያ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የሥራውም ፡ ኹሉ ፡ መፈጸሚያ፡ ይኾናል ፤ ምክንያቱም ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ በመመልከቱ ፡ ዕውቀቱን ፡ ያድሳል ፤ ራሱን ፡ ይገሥፃል ፤ ከትሩፋት ፡ ወደ ፡ ትሩፋት ፡ ለመራመድ ፡ መንገዱ ፡ ጥርጊያ ፡ ይኾንለታል ። ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ እስትንፋሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባላሉ ፤ ማለት ፡ እግዚአብሔር ፡ ነግሮዋቸው ፡ በመንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቃኝተው ፡ ነቢያት ፡ ሐዋርያት ፡ ጽፈዋቸዋልና ። ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ በማንበብ ፡ ሰው ፡ ልቡናውን ፡ እንዲገሥጽ ፡ እምነቱን ፡ እንዲያጸና ፡ በምግባሩ ፡ እንዲቀና ፡ ክርስቶስ «መጻሕፍትን ፡ እላንት ፡ ይመስላችኋል ፡ በርሳቸው ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ የምታገኙ ፤ እርሳቸውም ፡ ስለኔ ፡ የሚመሰክሩ ፡ ናቸው ፤ » (ዮሐ/፭፡፴፱) ብሏል ። ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ «ከሕፃንነትህ ፡ ጀምረህ ፡ የተቀደሱትን ፡ መጽሐፍ ፡ ተምረሃልና ፡ ለደኅንነት ፡ ታስተምር ፡ ዘንድ፡ የምትችል ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ ሀይማኖት ፡ » ( ፪ ፡ ጢሞቴ/ ፫ ፡ ፲፭) ብሏል ። ቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፡ «ይህንንም ፡ አስቀድማችሁ ፡ ዕወቁ ፡ የመጽሐፍ ፡ ትንቢት ፡ ኹሉ ፡ ትርጓሜ

www.ethiopianorthodox.org

ውም ፡ ከራስዋ ፡ እንዳይደለ ፤ ትንቢት ፡ ከቶ ፡ በሰው ፡ ፈቃድ ፡ አልመጣ ችም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተመርተው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቅዱሳን ፡ ሰዎች ፡ ተናገሩ ፡ » (፪ኛ፡ጴጥ/፩፡፳—፳፩) እያለ ፡ አትቷል፡ስለ፡ መጻሕፍት ፡ ቅዱሳት ፡ የቤተ፡ክርስቲያን፡አባቶች ፡ ኹሉ፡ እንዲያውም ፡ ከክርስትና ፡ ሀይማኖት ፡ ውጭ ፡ የኾኑ ፡ ሊቃውንት ፡ ሳይቀሩ ፡ ጠቃሚነ ቱን ፡ በሰፊው ፡ አስረድተዋል ።

እንዲሁም ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ መስለው ፡ እርሳቸውንም ፡ አኽለው ፡ የተጻፉ ፡ ብዙ ፡ የቤተ፡ክርስቲያን ፡ መጻሕፍት ፡ ይገኛሉ ። እነ ርሱንም ፡ ማንበብ ፡ ለዕለት ፡ ሥራው ፡ በጣም ፡ ይጠቅሙታል ፤ ምክንያ ቱም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባቶች ፡ የዕለት ፡ መሣሪያ ፡ እንዲሆናቸው ፡ ለማንኛውም ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ እንዲጠቀሙባቸው ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍን ፡ ምንጭ ፡ አድርገው ከርሱ ፡ ቀድተው ፡ ከርሱ ፡ አውጥ ተው ፡ በምዕራፍ ፡ በቁጥር ፡ የተለያየውን ፡ አገናኝተው ፡ ጽፈዋቸዋልና።

## ፯ኛ/ ፤ መንፈሳዊ ፡ ትምህርትን ፡ መከታተል ።

አንድ ፡ ሰው ፡ በአንድ ፡ ትምህርት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዕውቀት ፡ ኑሮት ፡ የእስፔሻሊስትነት ፡ ዲግሪ ፡ ቢኖረው ፡ በየጊዜው ፡ የሚሰጠውን ፡ ሌክ ቸር ፡ ካልሰማ ፡ በየጊዜው ፡ የሚጻፉትን ፡ መጋዚኖች ፤ በየጊዜው ፡ የሚደረ ሱትን ፡ ድርሰቶች ፡ እየተከታተለ ፡ ካላነበበ ፡ በየጊዜው ፡ የሚለዋወጡ ትን ፡ ቲዎሪዎች ፡ ( ልዩ ፡ ልዩ ፡ አሳቦች ፡ ኹሉ ፡ ) ሊደርስባቸው ፡ አይች ልም ። እንዲያውም ፡ ቀድሞ ፡ ያውቀው ፡ የነበረውን ፡ ወደ ፡ መዘንጋት ፡ ይደርሳል ። እንዲሁም፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ካህን ፡ በመንፈሳዊ ፡ ትምህርቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደረጃ ፡ ኑሮት ፡ በየጊዜው ፡ የሚነገሩትን ፡ ሌክቸሮች ፡ ካልተ ከታተለ ፤ በየጊዜው ፡ የሚጻፉትን ፡ መጻሕፍት ፡ የሚደረሱትን ፡ ድርሰ ቶች ፡ ካልተመለከተ ፤ ቀድሞ ፡ የሚያውቀው ፡ ብቻ ፡ ከቶ ፡ የሚረባው ፡ የሚጠቅመው ፡ ነገር ፡ የለም ፤ ስለዚህ ፡ በየጊዜው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕ ፍትን ፡ ማንበብ ፡ አእምሮውን ፡ ያድስለታል ፤ ዕውቀቱን ፡ ያበዛለታል ፤ ምክንያቱም ፡ የሰው ፡ አእምሮ ፡ እንደ ፡ ብረት ፡ ነው ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሠር ተውበት ፡ ቢያስቀምጡት ፡ መልኩ ፡ ይዝጋል ፤ ስለቱ ፡ ይበርዳል ፤ አፈ ርም ፡ ይበላዋል ፤ ስለዚህ ፡ በየጊዜው ፡ ይሠሩበታል፤ ቅባትም ፡ ይቀቡ



ታል ። የሰውም ፡ አእምሮ ፡ ካልሠሩበት ፡ ዕውቀቱ፡ ይረሳል፤ አእምሮው፡ ይዝጋል ። ለአእምሮ፡ እንደ፡ቅባት ፡ የሚሆኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ፡ መጻሕፍትን፡ በተለይም ፡ መንፈሳዊ ፡ ነክ ፡ የሆኑትን ፡ አጥብቆ ፡ ማንበብ ፡ ይገባል ፤ ከዚህም ፡ ጋራ ፡ የ፳ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ሃይማኖት ፡ ሳይንስ፡ ኹኖ ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ ስለሚያመልከው ፡ ለዚህ ፡ ተቃራኒ ፡ የኾነውን ፡ ቀጥተኛ ውን ፡ አስረጂ ፡ ለመስጠት ፡ እንዲችል ፡ የፍልስፍና ፡ የሳይንስ ፡ መጻሕፍ ትን ፡ ጠቅላላ ፡ ዕውቀት ፡ (እንሳየክሎፒዲያን) ፡ ይህንም ፡ የመሳሰሉትን፡ ጊዜውን ፡ መስለው ፡ ለጊዜው ፡ ተስማሚ ፡ ሆነው ፡ የተጻፉትን ፡ መጻሕ ፍት ፡ ማንበብ ፡ አለበት ። ይህን ፡ ለማድረግ ፡ እንዲረዳው ፡ እንደ ፡ ዐቅሙ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ማቋቋም ፡ አለበት ።

## ፩—(ለ)ለምእመናን ፡ በዐደባባይ ፡ ሊፈጽማቸው፡ የሚገባው ፡ ተግባሮች ፤

ካህኑ ፡ ሕዝባዊ ፡ ሳለ ፡ ማለት፡ እስከ ፡ ተሾመበት ፡ ጊዜ፡ ድረስ ፡ ኀላ ፊነቱ ፡ የግሉ ፡ ነበር ፤ ቢያጠፋም ፡ በራሱ ፡ ኀጢአት ፡ ብቻ ፡ ስለሚፈረ ድበት ፡ ፍዳው ፡ የቀለለ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ተሹሞ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ከተቀበለ ፡ ወዲህ ፡ የሕዝቡ ፡ ኀላፊ ፡ ኹኖ ፡ የሕዝ ቡን ፡ ሸክም ፡ ራሱ ፡ ስለ ፡ ተሸከመ ፡ ራሱንም ፡ ሕዝቡንም ፡ ለማዳን ፡ እንዲችል ፡ ሊያደርገው ፡ ሊፈጽመው ፡ የሚገባው ፡ ተግባርና ፡ ግዴታ ፡ አለበት ። ይኸውም ፡ ፩ኛ ፡ በዐደባባይ ፡ መስበክ ፡ ማለት ፡ ድካም ፡ ሳይ ሰማው ፡ ምን ፡ ይሉኝ ፡ ሳይል ፤ ሳያፍር ፡ ሳይፈራ ፡ ሕዝብ ፡ በበዛበት ፤ በዓል ፡ በሚከበርበት ፤ ጉባኤ ፡ በሰፋበት ፡ እየተገኘ ፡ መስበክ ፡ ማስተማር ፡ የግዴታ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ። ክርስቶስ ፡ ሐዋርያትን ፡ ሲልካቸው ፤ በዐ ደባባይ ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ገብተው ፡ እንዲሰብኩ ፤ እንዲያስተምሩ ፡ ነው (ማቴ/ ፲ ፡ ፩—፵፪ ፤ ፳ ፡ ፲፱ ፤ ማር/ ፮ ፡ ፯—፲፫ ፤ ሉቃስ ፡ ፱ ፡ ፩— ፮ )። ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ የክርቶስን ፡ ትእዛዝ ፡ ተከትሎ ፡ አሕዝብ ፡ በበ ዙበት ፡ የክርስቶስ ፡ ስም ፡ ወደ ፡ አልተጠራበት ፡ ሳይፈራ ፡ ቸልም ፡ ሳይል፡ ያስተምር ፡ ነበር ። (ሮሜ ፡ ፲፭ ፡ ፲፱—፳፩)። እርሱም ፡ ለተከታዩ ፡ ለጢ ሞቴዎስ ፡ « በነገር ፡ አስተምር ፡ አንተ ፡ ባለህበትም ፡ ጽና ፤ እየተጋደ ልህ ፡ በጊዜው ፡ ያለጊዜውም ፡ ሰነፎችን ፡ ዝለፍ ፤ ገሥጽም ፡ በርኅራኄ ፡ ኹሉ ፡ በትምህርትም ፡ » (፪ኛ ፡ ጢሞ / ፬ ፡ ፪) እያለ ፡ ይመክራል ፡ ያስተ ምራል ።

www.ethiopianorthodox.org

ይህን ፡ ይዘው ፡ የቀደሙ ፡ አባቶች ፡ ስብከትን ፡ ያዘወትሩ ፡ ነበር ፡
እንዲያውም ፡ ስብከት ፡ ከቅዳሴ፡ ፩ኛው ፡ ክፍል፡ ኹኖ ፡ ሊታጐል፡የማ
ይገባ፡ አድርገው፡ ይሠሩት ፡ ነበር ፤ በዚህም፡ ምክንያት፡ የክርስቶስ ፤ መን
ግሥት፡ ሰፋች፡ ምዕመናን፡ በዙ ፤ ወንጌል ፡በዓለም ፡ ለመድረስ፡ ቻለች።

ካህን ፡ ተብሎ ፡ ተሹሞ ፡ በዐደባባይ ፡ አዘውትሮ ፡ የማይሰብክ ፡
ወዮለት ፡ ወዮታ ፡ ይገባዋል ። ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ « ወንጌልን ፡ በማስተ
ማሬ ፡ አልመካበትም ፡ ያው ፡ በግድ ፡ ወድቆብኛልና ፡ ባላስተምር ፡ ግን ፡
ወዮልኝ ፡ » ( ፩ኛ ፡ ቆሮ / ፱ ፡ ፲፮ ፡ ) ሲል ፡ በስፊው ፡ ያስረዳል ። አንድ ፡
ካህን ፡ ፍጹም ፡ ምግባር ፡ ጽኑ ፡ ሀይማኖት ፡ አለው ፡ ቢባል ፤ የማይሰብክ፡
የማያስተምር ፡ ከኾነ ፡ ምንም ፡ የሚረባው ፡ የሚጠቅመው ፡ የለም ፤
እንዲያውም ፡ ከንቱ ፡ መኾኑ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ አሁንም ፡ ወዮለት ፤ ካህኑ፡
ካልሰበከ ፡ ካላስተማረ ፡ እንዴት ፡ አምነው ፡ ሊጠመቁ ፤ የቀናውንም ፡
የክርስቶስን ፡ መንገድ ፡ ሊከተሉ ፡ ይችላሉ ? ስለዚህ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ፡
« የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ የሚጠራ ፡ ኹሉ ፡ ይድናል ፤ ነገር ፡ ግን ፡
እንዴት ፡ ይጠሩታል ፡ የማያምኑበት ፡ ወይስ ፡ እንዴት ፡ ያምናሉ ፡ ያል
ሰሙት ፡ ወይስ ፡ እንዴት ፡ ይሰማሉ ፡ አስተማሪ ፡ የሌላቸው ፤ እንዲትስ፡
ያስተምራሉ ፡ ሳይላኩ ፡ እንደተጻፈ ፡ በሰላም ፡ የሚያስተምሩ ፡ እግራ
ቸው ፡ መልካም ፡ ነው ። በመልካም ፡ የምሥራች ፡ የሚናገሩ ፡ ( ሮሜ ፡
፲ ፡ ፲፫— ፲፭ ) ፡ እያለ ፡ ጮሆ ፡ አሰምቶ ፡ ይናገራል ፤ ካህናት ፡ ለማስተ
ማር ፡ ለመስበክ ፡ ለማጥመቅ ፡ የተላኩ ፡ ሲኾኑ ፤ ዝም ፡ ብለው ፡ ቍልፉ፡
በነርሱ ፡ እጅ ፡ ኹኖ ፡ የእምነት ፡ ደጅ ፡ ሊዘጋ ፡ አይገባም ፤ ከክርስቶስ ፡
አስቀድሞ ፡ የሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ ለመስበክ ፡ የንስሓ ፡ ትምህርት ፡ ለማ
ስተማር ፡ የንስሓ ፡ ጥምቀት ፡ ለማጥመቅ ፡ ተላከ ( ማቴ/ ፫ ፡ ፩—፲፮ ፤
ማር / ፩ ፡ ፩—፰ ፤ ሉቃ / ፫ ፡ ፩—፳ ) ተልእኮውንም ፡ በሚገባ ፡ እንደ ፡
ፈጸመ ፡ በመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ «እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ደስታዬ ፡ የተፈጸመ፡
ነው ፡ ለዚያ ፡ ይገባዋል ፤ ያድግ ፡ ዘንድ ፡ ለኔ ፡ ግን ፡ አንስ ፡ ዘንድ ፡ »
( ዮሐ / ፫ ፡ ፳፱—፴፩) ፡ ብሎ ፡ አስረድቷል ። በዚህ ፡ መልክ ፡ የተሾሙት፡
ኹሉ ፡ በማስተማራቸው ፡ ክርስትናን ፡ ለማስፋፋት ፡ ምእመናን ፡ ለማ
ብዛት ፡ ቻሉ ። አሁንም ፡ አስተማሪ ፡ ሰባኪ ፡ በጠቅላላው ፡ ካህን ፡
የሆነ ፡ ኹሉ ፡ ዓላማውን ፡ ተከትሎ ፡ መስበክ ፡ አለበት ።



ስብከትም ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ሊኾን ፡ ይችላል ፤ አንደኛው ፡ ለአ
ማንያን ፡ የሚኾን ፡ ስብከት ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ በተማሩት ፡ ትምህርት ፡
በያዙት ፡ ሀይማኖት ፡ በሚሠሩት ፡ ምግባርና ፡ ትሩፋት ፡ ጸንተው ፡ እን
ዲኖሩ ፤ ከኀጢአት ፡ ከክፋት ፡ እንዲመለሱ ፤ ንስሓ ፡ እንዲገቡ ፤ በቀናው፡
ጐዳና ፡ እንዲራመዱ ፡ የሚያስረዳቸው ፡ ስብከት ፡ ነው ። ይኸውም ፡
የማነጽ ፡ የማንጻት ፡ የማጽናት ፡ ትምህርት ፡ ይባላል ፤ ወይም ፡ ከክብር ፡
ወደ ፡ ክብር ፡ ከትሩፋት ፡ ወደ ፡ ትሩፋት ፡ እንዲራመዱ ፡ ወኔ ፡ የሚሰጥ፡
መንፈስን ፡ የሚያነቃ ፡ የማንቃት ፡ የማትጋት ፡ ስብከት ፡ ይባላል ።
፪ኛ/ ፤ ለአሕዛብና ፡ ለአረመኔ ፡ የሚሰጥ ፡ ትምህርትና ፡ ስብከት ፡ ነው ፤
ይኸም ፡ ከክርስትና ፡ ትምህርት ፡ ለራቁ ፡ በድንቍርና ፡ በክህደት ፡ በአ
ምልኮ ፡ ጣዖት ፡ የሚኖሩትን ፡ ስቦ ፡ ጐትቶ ፡ ወደ ፡ ዕውቀት ፡ ወደ ፡ እው
ነተኛው ፡ ሀይማኖት ፡ ወደ ፡ እውነተኛው ፡ አምልኮት ፡ የሚቀርቡበትን፡
ጐዳና ፡ ጥርጊያ ፡ አድርጎ ፡ ለመመለስ ፡ የሚያደረግ ፡ ትምህርት ፡ ነው ፤
ይኸም ፡ የማዘጋጃ ፡ የመመርመሪያ ፡ የማወቂያ ፡ ትምህርት ፡ ይባላል ።
ይህን ፡ ኹሉ ፡ በትክክል ። ለመስጠት ፡ ካህኑ ፡ በቀን ፡ በሌሊት ፡ መድ
ከም ፡ አለበት ፤ ተግቶ ፡ ነቅቶ ፡ ሠርቶ ፡ ኹሉን ፡ ቢያሳምን ፤ ኹሉን ፡ ክርስ
ቲያን ፡ ቢያደርግ ፡ እርሱም ፡ የሰሙትም ፡ ይድናሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ደክሞ፡
አስተምሮ፡ ሰብኮ፡ ሳያምኑ ፤ አምነውም ፡ እንደ፡ ገና ፡ የራሳችን ፡ ይሻለናል፡
ብለው ፡ ወደቀደመ ፡ አለዐዋቂነታቸው ፡ ቢመለሱ ፡ ካህኑ ፡ ራሱን፡ ያድ
ናል ፤ «ለራስህም ፡ ተጠንቀቅ ፡ በትምህርትህም ፡ በርስዋም ፡ ይህንም፡
ያደረግህ ፡ እንደኾነ፡ ራስህን፡ ታድናለህ፡ የሚሰሙህንም፡ ደግሞ ፡ » (፩ኛ ፡
ጢሞ/ ፬ ፡ ፲፮)፡ ሲል ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ተወዳጅ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩን ፡
መክሯል ፤ አስተምሯል ።

በሁለቱም ፡ በኩል፡ መልካም፡ ውጤትን ፡ እንዲያገኝ፡ ስብከቱ ፡ ልክ ፤
መልክ ፡ ወሰን ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ፤ ማለት ፡ መነሻ ፡ መድረሻ ፡ ምክን
ያት ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ። ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ውል ፡ የሌለው ፡ ወይም ፡
ውሉ ፡ የጠፋ ፡ የኾነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ለሠሪውም ፡ ለተመልካችም፡ አስቸጋ
ሪና ፡ አታካች ፡ ይኾናል ። የስብከት ፡ ሥራ ፡ በመንፈሳዊም ፡ ነገር ፡ ቢኾን፡
በፖለቲክ ፡ ሰውን ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ዓላማ ፡ መሳቢያ ፡ ገመድ ፡ ስለኾነ ፡
መሳቢያው ፡ ክርር ፡ ሳይል ፤ ተሳቢውም ፡ ሳይጠረጥር ፤ በዝግታ ፡ በለ

www.ethiopianorthodox.org

ዘብታ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ እንደታሰበው ፡ ለመፈጸም ፡ ይችላል ። በዛሬ ፡ ጊዜ ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ነገር ፡ ቀርቶ፡ ለፖለቲኩ፡ አመራርም ፡ ቢኾን ፡ በኀይል ፡ በመሣሪያ ፡ ብዛት ፡ መኾኑ ፡ ቀርቶ ፡ በስብከት ፡ ቃልን ፡ በማሳመር ፡ የንግግር ፡ አቅድን ፡ በመለወጥ ፡ ያልያዘውን ፡ እንደያዘ ፡ የሌለውን ፡ እንዳለው፡ አድርጎ፡በአነጋገር፡ ማሳመርና፡ በቃል ፡ አመራረጡ፡ ይኹን፤ ይኹን ፤ ያሰኘዋል ። አባቶች ፡ ሲመሰሉ ፡ «ከአነጋገር ፡ ይፈረዳል ፡ ከአያያዝ ፡ ይቀደዳል» ይላሉ ፤ ይኸውም ፡ ማለት ፡ ምንም ፡ ነገሩ ፡ ሐሰት፡ ቢኾን ፡ የአነጋገሩን ፡ ስልት ፡ አይተው፡ ዳኞች ፡ ይፈርዱበታል ፡ ፤ ወይም ፡ ይፈርዱለታል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ክርስቶስም ፡ ሲያስተምር፡ «ከነገርህ፡ የተነሳ፡ ትጸድቃለህና፡ ከነገርህም፡ የተነሣ፡ ይፈረድብሀልና፡ » (ማቴ/ ፲፪ ፡ ፴፺) ፡ ብሎ ፡ አስረድቷል ። ስለዚህ፡ሰባኪዎች፡ ኹሉ ፡ እንዳገኙ፡ መናገራቸውን፡ ትተው፡ የስብከት፡ ዐቅድ ፡ እንዲማሩ ፡ ሕዝብን ፡ እጅ ፡ የሚያደርጉበትን ፡ ዐቅድና ፡ ዘዴ ፡ እንዲያጠኑ ፡ የግድ ፡ ያስፈልጋቸዋል። ቤተ፡ ክርስቲያንም ፡ ለዚህ ፡ ድርጅት ፡ በሰፊው ፡ ማሰብ ፡ አለባት ። ምንም ፡ ወደፊት ፡ በሰፊው ፡ የንግግር ፡ ዐቅድ ፡ »በሚል ፡ አርእስት ፡ የስብከትን ፡ ስልት ፡ ብጽፍ ፡ ለጊዜው፡ ለያዝነው፡ ዓላማ፡ የሚረዳ፡ ያህል ፡ ከዚህ ፡ በአጭሩ ፡ ባ፩ ፡ ክፍል፡ ከፍዬ ፡ እናገራለሁ ።

፩ ፡ በአርእስት ፡ አመራረጥ ፤ ሰባኪው ፡ መጀመሪያ ፡ ለስብከት ፡ ተስማሚ ፡ የኾነውን ፡ አርእስት ፡ መምረጥ ፡ ግዴታ ፡ አለበት ፤ ምክንያቱም ፡ በመላ ፡ ንግግሩ ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ፡ የመነጨ ፡ ስለሚኾን ፡ አርእስቱ፡ የሞተ ፡ እንደኾነ ፡ በመላ ፡ ስብከቱ ፡ ኹሉ ፡ የሞተ ፡ ይናኾል ።

አርእስቱም ፡ ለጊዜው ፡ ከተነበበው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ሊወጣ ፡ ይችላል ። ወይም ፡ ለጊዜው ፡ ለአኳኋኑ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነውንና ፡ ለሰው ፡ ልቡና ፡ የሚመጥነውን ፡ መርጦ ፡ ሊሰብክ ፡ ይችላል ፤ ይህ ፡ አርዕስት፡ ግን ፡ ሁልጊዜ ፡ የተሰቀለውን፡ የክርስቶስን ፡ ነገርና ፡ የርሱን ፡ ታላላቅ ፡ ሥራዎች ፡ የሚገልጥ፡ መኾን፡ አለበት ። ቅዱስ ፡ ጳውሎስ፡ ኹል ፡ ጊዜ፡ ሲሰበክ ፡ የተሰቀለውን ፡ ክርስቶስን ፡ በማስታወስ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ «እኛ፡ ግን ፡ በክርስቶስ ፡ እናስታመራለን ፡ በተሰቀለው ፡ ያውም ፡ በአይሁድ ፡ ዘንድ ፡ ዕንቅፋት ፡ ነው ፡ በአሕዛብም ፡ ዘንድ ፡ ስንፍና ፡ ነው ፤ በተጠ



ሩት ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኀይል ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጥበብም ፡ ነው ፡ —» (፩ኛ ፡ ቆሮ / ፩ ፡ ፳፫—፴፩ ፤ ፪ ፡ ፩—፲፮ ፡ ) ሲል ፡ ያስረዳናል፡ የትሩፋት፡ ምንጭ፡ የምግባራት ፡ መሥራችና፡ ፈጻሚ ፡ ክርስቶስ ፡ ነውና ።

፪ ፡ የቃል ፡ አመራረጥ ፡ ። ለስብከት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ በንግግሩ ፡ ኹሉ ፡ ቃል ፡ መምረጥ፡ ያስፈልገዋል ፤ በተለየ ፡ ለስብከት ፡ ጊዜ ፡ ተስማሚ ፡ የኾኑትን፡ ኀይለ፡ ቃሎች ፡ መምረጥ ፡ ፩ኛ ፡ ለያዘው ፡ ሥራ ፡ ይረዳዋል ፤ ፪ኛ ፡ ሳያውቅ ፡ ተናግሮ ፡ ሰውን ፡ ከማስቀየም ፡ ይድናል ፤ « ያምራል ፡ ብሎ ፡ ከመናገር ፡ ይከፋል ፡ ብሎ፡ መተው ፡ » እንደ ተባለው ፡ ኹሉ ፡ አመዛዝኖ ፡ መናገር፡ ያስፈልገዋል ። የአረፍተ፡ ነገሩ፡ አቀማመጥ ፡ የኀይለ ፡ ቃሉ ፡ አመራረጥ ፤ ከዓላማው፡ ጋራ ፡ የተያያዘና ፡ ኅብር ፡ ንግግር ፡ ያለው ፡ ኾኖ ፡ ምስጢሩ ፡ ጕልቶ ፡ የተገኘ ፡ እንደኾነ ፡ ሕዝቡ ፡ ሳይወድ ፡ በንግግሩ ፡ ተስቦ ፡ ሊገባለት ፡ ይችላል ።

፫ ፡ ስብከቱን ፡ ማጥናት ። ማንኛውም፡ ሰባኪ፡ ካህን፡ ወደ ፡ ስብከት፡ ከመሔዱ ፡ በፊት ፡ አስቀድሞ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ረዳቶች ፡ መጻሕፍት ፡ አንብቦ ፡ ሊናገራቸው፡ የፈቀዳቸውን፡ ጽፎ ፡ አርሞ ፤ በቃሉ ፡ አጥንቶ ፡ መናገር ፡ አለበት ፡ ምክንያቱም፡ መልካም፡ ውጤት፡ የሚያገኘው፡ ተስማሚ፡ ጥቅሶች ፡ የጠቀሰ ፤ ብዙ ፡ ምሳሌዎች ፡ የመሰለ ፤ የታሪኮችን ፡ አስረጂ ፡ የሰጠ ፡ እንደኾንና ፡ ከዓለም ፡ የዕለት ፡ ኹኔታ ፡ ያለፈውን ፡ በመጥቀስ ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ሰሚውን፡ ሙሉ ፡ በሙሉ፡እጅ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ። የምን ፡ ግዴ ፡ ተነሥቶ ፡ አገኝ ፡ ባጣውን ፡ ልናገር ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በጀመረበት፡ አርእስት፡ ለመዝለቅ፡ አቅቶት፡ ቆላና ፡ ደጋ ፡ ሲወጣ፡ ሲወርድ ፡ ሰው ፡ ሊረዳው ፡ ቀርቶ ፡ በኋላ ፡ ራሱን ፡ ስለምን ፡ ተናገርክ ፡ ያሉት ፡ እንደ ፡ ኾን ፡ ስለዚህ ፡ ብሎ ፡ የሚሰጠው ፡ መልስ ፡ አያገኝም ። ሰውን ፡ በከንቱ ፡ ማድከም ፡ በሌላ፡ ጊዜ ፡ አትምጣ ፡ ብሎ ፡ እንደ፡ ማባረርና ፡ እንደማሰናበት ፡ ዐዋጅም ፡ እንደማወጅ ፡ ይቈጠራል ፡ ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የተናገረው ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተጠብቆ፡ በአእምሮ ፡ ተቀርጾ፡ እንዲኖር፡ ሰሚውም ፡ በአንክሮ ፡ እንዲቀበለው ፡ ሰባኪዎች፡እንዲጠነቀቁ፡ ያስፈልጋል ፤ «ከልብ ፡ ካለቀሱ ፡ እንባ ፡ አይገድም ፡ » እንደተባለው ፡ ማንኛውም ፡ ሥራ ፡ ከልብ ፡ ከተሠራ፡ መልካም ፡ ውጤት ን ፡ ይሰጣል ።

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ማሰብ ፡ ከልብ ፡ የተሠራ ፡ ስለሚሆን ፡ አስቀድሞ፡ ጽፎ ፡ አርሞ ፡ አጥንቶ ፡ እንዲናገር ፡ ያስፈልጋልዋል ።

፬ ፡ የንግግር፡ ስልት ። ስብከት፡ የሚያደርግ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ መጮህ ፡ በጣምም፡ ማሾክሾክ፡ የለበትም ፤ ሰሚዎቹን ፡ ለማርካት ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ በለዘበ ፡ ድምፅ ፡ በጣም ፡ ሳይሮጥ ፡ በጣም ፡ ዝግ ፡ ሳይል፡ ልክ ፡ ወዳጅ፡ ከወዳጁ ፡ ጋር ፡ እንደሚነጋገር፡ በሚያስደስት ፡ ድምጽ ፡ በሚረዳ ፡ ቃል ፡ መናገር ፡ አለበት ። ክርስቶስ ፡ እንዲሁ ፡ ሲያስተምር ፡ ከቃሉ ፡ ልዝብነት ፡ ከእግሩ ፡ ጭምትነት ፡ የተነሣ ፡ ኹሉ ፡ ያደንቁት ፡ ያመሰግኑት ፡ ነበር ። «ኹሉም ፡ ይመሰክሩለት ፡ ነበሩ ፤ ከአፉ ፡ ከሚወጣውም፡ ከጸጋው ፡ ነገር ፡ የተነሣ ፤ ያደንቁ ፡ ነበር ፡ » ( ሉቃስ ፡ ፬ ፡ ፳፪ ፤ ፪ ፡ ፵፯ ፤ መዝ / ፵፬ ፡ ፪ ) በቁጣ ፡ ቃል ፡ በጩኸት ፡ ንግግር ፡ እሰብካለሁ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ድምፁን ፡ ብቻ ፡ እየሰሙ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ሳይረዱት ፡ ይቀራሉ ፡ ስለዚህ ፡ የስብከት ፡ ዋናው ፡ ዓላማ ፡ ለማስረዳትና ፡ ለያዙት ፡ ሥራ ፡ መሳቢያ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ቃሉ ፡ ሳይከር ፤ የደም ፡ ሥሩ ፡ ሳይነባበር ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባዩን ፡ ሳይለውጥ ፤ በለዘብታ ፤ በዝግታ ፡ መስበክ ፡ ያስፈልገዋል ። ከዚህም ፡ ጋራ ፡ አቋቋሙ ፡ የተካከለ ፤ ንቅናቄው ፡ ከንግግሩ ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ እጅ ፡ አጠቃቀሱ ፡ ከአስረጂ ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ መኾን ፡ አለበት ፤ ስብከቱም ፡ በጣም ፡ ሳይበዛ ፡ በጣምም ፡ ሳያንስ ፡ መጠነኛ ፡ ኹኖ ፡ መካከለኛው ፡ ሰዓት ፡ ፲፭ ፡ ደቂቃ ፡ የኾነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለሰሚው ፡ ኹሉ ፡ ተስማሚ ፡ ኩኖ ፡ ምነው ፡ ባላለቀብን ፡ በሌላ ፡ ቀን ፡ መቼ ፡ ይናገር ፡ ይኾን ፡ ሲሉ ፡ ሲጠባበቁት ፡ ይኖራሉ ። በንግግሩ ፡ መጨረሻ ፡ ግን ፡ የዘረዘረውን ፡ ኹሉ ፡ አጠቃሎ ፡ በአጭር ፡ መግለጫ ፡ እንሥራው ፡ እና ድርገው ፡ በሚል ፡ ቃል ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አጋዥነትን ፡ ለምኖ ፡ በጸሎት ፡ ይፈጽም ።

## ፪ ፤ ለምእመናን ፡ በግል ፡ የሚፈጽማቸው ፡ ተግባሮች ።

ሕዝብ ፡ በበዛበት ፡ በዐደባባይ ፡ መስበክ ፡ ለካህኑ ፡ ዋና ፡ ተግባሩ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ አትተን ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ አይሆንም ፤ እንዲሁ ፡ ለያንዳንዱ ፡ የተለየ ፡ ርዳታ ፡ የተለየ ፡ ጥበቃ ፡ ሊያደርግና ፡ በግል ፡ ሊጐበኝ ፡ ይገባል ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ክርስቶስ ፡ እንዲሁ ፡



በዐደባባይ ፡ ብቻ ፡ አያስተምርም ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ዕድሜያቸው ፡ እንደ ፡ ፍላጎታቸው ፡ ለያንዳንዱ ፡ የተለየ ፡ ርዳታ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፤ ለምሳሌ ፤ የሞቱትን ፡ ሲያስነሣ ፡ የታመሙትን ፡ ሲፈውስ ፤ ጋኔን ፡ የያዛቸውን ፡ ሲያስወጣላቸው ፤ ለምጽ ፡ የያዛቸውን ፡ ሲያነጻ ፡ ይህንም ፡ የመሰለውን ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ፍላጎቱ ፡ ይፈጽምለት ፡ ነበር ፤ ከሱም ፡ በኋላ ፡ የተነሡ ፡ መምህራን ፡ እንዲሁ ፡ ሥራቸውን ፡ በማኅበር ፡ በዐደባባይ ፡ በግልም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ያደርጉ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ካህኑ ፡ በታማኝነቱ ፡ አስፈላጊውን ፡ ዕርዳታ ፡ አስፈላጊውን ፡ ጥበቃ ፡ በማድረጉ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ክርስቶስን ፡ ይመስለዋል ፤ ማለት ፡ ከሰው ፡ ወገን ፡ ብዙው ፡ ድኖ ፡ አንደኛው ፡ ሊጠፋ ፡ አይፈቅድምና ፡ «ማነው ፡ ከላንተ ፡ መቶ ፡ በግ ፡ ያለው ፡ ከርሳቸው ፡ አንዱ ፡ ቢጠፋ ፡ ዘጠና ፡ ዘጠኙን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ትቶ ፡ ይሄድ ፡ የለምን ፡ ወደ ፡ ጠፋው ፡ እስኪያገኘው ፡ ድረስ ፤ በአገኘውም ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ በጫንቃው ፡ ላይ ፡ ይሸከመዋል ። ወደ ፡ ቤትም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ወዳጆቹንና ፡ ጎረቤቶቹን ፡ ይጠራል ፤ እንዲህ ፡ ሲላቸው ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡ የጠፋውን ፡ በጌን ፡ ስላገኘሁ ። እላችኋለሁ ፡ እንዲሁ ፡ ደስታ ፡ በሰማይ ፡ እንዲኾን ፡ ንስሐ ፡ በሚገባ ፡ በአንድ ፡ ኀጢአተኛ ፡ ከዘጠና፡ ዘጠኙ፡ ጻድቃን ፡ ይልቅ ፡ ንስሐ ፡ ከማይሹ ፡ » (ሉቃ/ ፲፭ ፡ ፬—፲ ፤ ማቴ/ ፲፰ ፡ ፲፪—፲፭)

ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ የክርስቶስ ፡ ተከታይ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ የክርስቶስን ፡ ትምህርት ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ያስተምር ፡ ነበር ። «እላንተ ፡ ትመሰክራላችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመሰክራል ፡ በንጽሕና ፡ በጽድቅም ፡ ያለ ፡ ነውርም ፡ እንደ ፡ ነበርን ፡ በላንት ፡ በአመናችሁት ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ እንድታውቁ ፡ አባት ፡ ልጁን ፡ እንዲመክር ፤ እንዲሁ ፡ ከላንት ፡ እያንዳንዱን ፡ እንመክር ፡ እንደ ፡ ነበር ፤ ልባችሁንም ፡ እናጽናና ፡ ነበር ። እንመሰክርም ፡ ነበርን ፡ እንድትሄዱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዲገባ ፡ ወደ ፡ መንግሥቱ ፡ ወደ ፡ ክብሩም ፡ ለጸራቸው » (፩ ተሰሎ/ ፪ ፡ ፲—፲፪ ) ። ይህ ፡ የተለየ ፡ ርዳታ ፡ የተለየ ፡ ጥበቃ ፡ የተለየ ፡ መከባከብ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥም ፡ በመኖሪያ ፡ ቤታቸውም ፡ እየሄደ ፡ ሊያደርገው ፡ ሊፈጽመውም ፡ ለካህኑ ፡ ይገባዋል ። አንድ ፡ አባት ፡ የልጁን ፡ ችግር ፡ ዐውቆ ፡ ቦታ ፡ ሳይለይ ፡ ሰዓት ፡ ሳይወስን ፡ እንዲከባከበው ፡ እንዲጠይቀው ፡ እንዲመ

www.ethiopianorthodox.org

ክረው ፣ መንፈሳዊ ፡ አባትም ፡ ሰዓት ፡ ሳይወስን ፡ ቦታ ፡ ሳይለይ ፡ ምእመናን ፡ በሚገኙበት ፡ እየተዘዋወረ ፡ እንደ ፡ ብስጭታቸው ፡ ማጽናናት ፡ እንደ ፡ ችግራቸው ፡ መርዳት ፡ ይገባዋል ።

ጸሎት ፡ እንዲያደርግ ፣ ቡራኬ ፡ እንዲሰጥ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ በተጠራ ፡ ጊዜ ፡ ሂዶ ፡ መንፈሳዊ ፡ ፍላጎታቸውን ፡ አርክቶ ፡ ላለፈው ፡ ጥፋታቸው ፡ ስርየት ፡ ሰጥቶ ፡ ለሚመጣው ፡ መክሮ ፡ አጽናንቶ ፡ መውጣት ፡ አለበት ፣ ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ሐኪም ፡ ሰው ፡ ታምዋል ፡ ብለው ፡ በጠሩት ፡ ጊዜ ፡ እንደማይል ፡ እንደ ፡ በሽታውም ፡ ዐይነት ፡ ለአለፈው ፡ መድኀኒቱን ፡ ሰጥቶ ፡ ለሚመጣውም ፡ መከላከያውን ፡ ክትባቱን ፡ እንዲያዘጋጅለት ፡ መንፈሳዊ ፡ ሐኪም ፡ ካህኑ ፡ ከዚህ ፡ በበለጠ ፡ ለመሥራት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ መኖር ፡ አለበት ። ካህኑም ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ቢሄድ ፣ ምእመናኑም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቢመጡ ፣ በዘር ፡ በመልክ ፡ በዕድሜ ፡ በዕውቀት ፡ በጾታ ፡ የተለያየው ፡ ሕዝብ ፡ በባሕርይም ፡ የበለጠ ፡ ስለሚለያይና ፡ የሚያስበው ፡ የሚሠራው ፣ በጠቅላላም ፡ ኑሮው ፡ ኹሉ ፡ የተለያየ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ለኹሉም ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ትምህርት ፣ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ሥርዐት ፡ ሊሰጥ ፡ አይገባውም ። አንድ ፡ ሐኪም ፡ በሐኪም ፡ ቤት ፡ ለተኙት ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ መድኀኒት ፡ እንደማይሰጥ ፣ ለቊስለኛው ፡ ልዩ ፡ መድኀኒት ፣ ሌላም ፡ ይህን ፡ ለመሰለ ፡ በሽታ ፡ ኹሉ ፡ የተለየ ፡ ምርመራ ፡ የተለየ ፡ መድኀኒት ፡ እንደሚያደርግ ፡ ኹሉ ፣ ካህኑም ፡ ለያንዳንዱ ፡ የተለየ ፡ ትምህርት ፡ የተለየ ፡ አስተያየት ፡ እያደረገ ፡ መቀበል ፡ ይገባል ። የተለየ ፡ ምርመራ ፡ የተለየ ፡ ጥበቃ ፡ ለማድረግ ፡ እንዲመቸው ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ የዕድሜ ፡ የጾታ ፡ የዕውቀት ፡ የማዕርግ ፡ ደረጃን ፡ ከዚህ ፡ እዘረዝራለሁ ።

## ፩ ፣ የዕድሜ ፡ ደረጃ ።

በአንድ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ስለሚገኝ ፡ በተለይም ፡ ትልቅም ፡ ትንሽም ፡ ስለሚገኝ ፡ «ብዙ ፡ ፈላጊ ፡ አንዱን ፡ ያጣል ፡ » እንደ ፡ ተባለው ፣ ለኹሉ ፡ ተብሎ ፡ የሚሰጠው ፡ ትምህርት ፡ ለ፩ኛው ፡ እንኳን ፡ ተሳይኾን ፡ ይቀርና ፡ ሁሉንም ፡ ሊያጣ ፡ ይችላል ። ለ፩ኛው ፡ በተለየ ፡ የተሰጠ ፡ እንደኾን ፡ እኔን ፡ እንጂ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባል ፡ ባይቈጥረኝ ፡ ነው ፡ ይላል ፣ ስለዚህ ፡ ለያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ዕድሜው ፡ ደረጃ ፡ የተለየ ፡ ትምህርት ፡ የሰጡት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ውጤቱ ፡ ብዙ ፡ ይኾናል ። ለሽ



ማግሌዎች ፡ ማሰብና ፡ መድከም ፡ እስከሚችሉበት ፡ ደረጃ ፡ ድረስ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ ያለው ፡ ትምህርት ፡ የሰጡዋቸው ፡ እንደ ፡ ኾን ፡ ለባሕርያቸው ፡ መጥኗቸው ፡ በደስታ ፡ ይቀበሉታል ። ለሕፃናቱም ፡ እንዲሁ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ዕውቀታቸው ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፣ ለባሕርያቸው ፡ ተስማሚ ፡ የኾነ ፡ ሊደርሱበት ፡ ሊመረምሩት ፡ በሚችሉት ፡ መንፈስ ፡ ያስተማሩዋቸው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በደስታ ፡ ይቀበሉታል ።

ስለዚህ ፡ ሽማግሌዎችን ፡ በሚገባ ፡ መያዝ ፡ በተለይም ፡ የቀድሞ ፡ ሥርዐታቸውን ፡ የተከተለ ፡ አስተያየት ፡ መስጠት ፡ ማስተማር ፡ ይገባል ። ለአለፈው ፡ ምስክር ፡ ለሚመጣው ፡ መምህር ፡ የሚኾኑት ፡ ሕፃናት ፡ አብነት ፡ የሚያደርጓቸው ፡ ሥዕላቸውን ፡ ተመልክተው ፡ የሚከተሉት ፡ በእግራቸው ፡ የሚተኩት ፣ ሽማግሌዎች ፡ በሚገባው ፡ በዕውነተኛው ፡ ትምህርት ፡ ተጠብቀው ፡ የኖሩ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ነው ። ይህን ፡ ስንል ፡ ግን ፡ ሕፃናቱን ፡ ዘንግተን ፡ ወይም ፡ ከቊጥር ፡ አይገቡም ፡ ብለን ፡ አይደለም ፣ ነገር ፡ ግን ፡ አባቶችን ፡ መስለው ፡ አባቶችን ፡ አህለው ፡ ልጆች ፡ የሚተኩ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፣ አባቶች ፡ በቀናው ፡ ጐዳና ፡ ያልሄዱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፣ ወጣቶችም ፡ አባቶች ፡ በሄዱበት ፡ ጐዳና ፡ ይራመዱና ፡ ውጤቱ ፡ መለያየት ፡ መፈጸሚያው ፡ ጥፋት ፡ ይኾናል ። በተለይ ፡ አሁን ፡ በያዝነው ፡ ጊዜ አባቶችም ፡ አባቶች ፡ ሊሄዱበት ፡ በማይገባው ፡ መንገድ ፡ በመሄዳቸው ፡ ልጆች ፡ እነርሱን ፡ ተከትለው ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ጐዳና ፡ ይጓሠግሣሉ ። መጀመሪያ ፡ አባቶች ፡ የዛሬ ፡ ዘመን ፡ ልጅ ፡ እያሉ ፡ ወጣቶችን ፡ ይዘልፋሉ ፣ ወጣቶች ፡ ደግሞ ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ የሚመለከቷቸው ፡ አባቶች ፡ ተሳስተው ፡ በመገኘታቸው ፡ እነርሱን ፡ ሲዘልፉ ፡ እነርሱን ፡ ሲገሥጹ ፡ ይገኛሉ ፣ «ርጉም ፡ ተረጋግሞ ፡ ያልቃል ፡ » እንደ ፡ ተባለው ፡ ኹሉም ፡ ሲረጋገሙና ፡ ሲዘባበቱ ፡ ይገኛሉ ። ለዚህ ፡ አስታራቂው ፡ ዳኛው ፡ እውነተኛው ፡ ካህን ፡ ነበር ፣ ማለት ፡ አባቶች ፡ በቀናው ፡ እምነት ፡ ጸንተው ፡ በጎውን ፡ ምግባር ፡ እንዲፈጽሙ ፣ ወጣቶች ፡ ደግሞ ፡ በዚሁ ፡ ጐዳና ፡ አባቶችን ፡ ተከትለው ፡ እንዲራመዱ ፣ ለአባቶች ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ በዓልና ፡ በትልልቅ ፡ ስብሰባ ፣ በማኅበር ፡ ይህንም ፡ በመሰለ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ እየተገኙ ፡ ለማስተማር ፡ ይቻላል ።

ለወጣቶች ፡ ደግሞ ፡ በበለጠ ፡ ማሰብና ፡ መጠንቀቅ ፡ የካህኑ ፡ ዋና ፡



www.ethiopianorthodox.org

ተግባር ፡ ነው ፤ ማለት ፡ አንድ ፡ አባት ፡ ለልጁ ፡ ጤና ፡ ልብስ ፡ ምግብ ፡
ይህንም ፡ በመሰለ ፡ ሥጋዊ ፡ ፈቃድ ፡ ኹሉ ፡ እንዲያስብና ፡ እንዲጠነቀቅ
ለት ፡ ካህኑ ፡ ከዚህ ፡ በበለጠ ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ኑሮው ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ምግቡ ፡
አስተዳደጉ ፡ ማሰብና ፡ መጠንቀቅ ፡ አለበት ፤ ምክንያቱም ፡ ሰው ፡
እንደ ፡ ሌላው ፡ ፍጥረት ፡ በሥጋ ፡ ብቻ ፡ ሊኖር ፡ የማይገባው ፡ ፍጥረት ፡
ነው ፡ ወይም ፡ በሥጋ ፡ ብቻ ፡ ሊኖር ፡ የማይችል ፡ ነው ፤ ከሥጋ ፡ የተወ
ለደ ፡ ሥጋ ፤ ከመንፈስ ፡ የተወለደ ፡ መንፈስ ፡ ሲኾን ፤ (ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፮) ሰው ፡
ከሥጋም ፡ ከመንፈስም ፡ የተወለደ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፤ መንፈሳዊም ፡ ሥጋ
ዊም ፡ ምግብ ፡ ያስፈልገዋል « ተጽፎዋል ፡ ሰው ፡ በዕንጀራ ፡ ብቻ ፡ እን
ዳይድን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ በምትወጣው ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ እንጂ »
(ማቴ/፬ ፡ ፬ ፤ ሉቃ/፩ ፡ ፹ ፤ ፪ ፡ ፶፪) ፡ ሲል ፡ ክርስቶስ ፡ መስክሮዋል ። ካህኑ ፡
የሕፃናት ፡ ፍቅር ፡ ኑሮት ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ በባሕርይ ፡ ተስማምቶ ፡ መስሎ ፡
ለማስተማር ፡ እንዲችል ፤ ቢቻል ፡ አስቀድሞ ፡ ካህኑ ፡ ኹሉ ፡ ፔዳጎ ግን ፡
(የሕፃናት ፡ አስተዳደግ ፡ ትምህርት ፡ ) ማጥናት ፡ ያስፈልጋል ። ሕፃናቶ
ችን ፡ ማስተማር ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታላቅ ፡ ጥቅም ፡ ነው ። ፩ኛ በሕ
ፃንነታቸው ፡ የተማሩት ፡ በሕሊናቸው ፡ ተቀርጾ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሳይገደፍ ፡
ይኖራልና ። ፪ኛ ፤ አድገው ፡ እነርሱ ፡ ስለሚተኩ ፡ ከጥንት ፡ ከሕፃንነት ፡
ጀምሮ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባል ፡ መኾናቸውን ፡ ያወቁ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤
ባደጉና ፡ መብት ፡ ባገኙ ፡ ጊዜ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዐምድ ፡ ኹነው ፡
ይደግፋሉ ። የዚህን ፡ ጠቃሚነት ፡ ለማስረዳትና ፡ ሕፃናትን ፡ በበለጠ ፡ መከ
ባከብ ፡ ማስተማር ፡ ተገቢ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ለማስረዳት ፡ ክርስቶስ ፡ ኹል
ጊዜ ፡ ሕፃናቱን ፡ ከፊቱ ፡ ሳይለይ ፡ ያስተምር ፡ ነበር ። እንዲያውም ፡
ሰዎች ፡ ቢከለክሉዋቸው ፡ «ሕፃናትን ፡ ተው ፡ አትከልክሏቸው ፡ ወደኔ ፡
ይመጡ ፡ ዘንድ ፤ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንደ ፡ ነዚህ ፡ ላሉት ፡ ናትና »
(ማቴ/ ፲፱ ፡ ፲፬) ፤ እያለ ፡ ይከራከርላቸው ፡ ነበር ። ኹል ፡ ጊዜም ፡ ምሳሌ ፡
የሚመስልባቸው ፡ በሕፃናት ፡ ነበር ፡ (ማቴ/ ፲፰ ፡ ፪—፲፬) ። ይህን ፡ ተግ
ባር ፡ ካህኑ ፡ ለመፈጸም ፡ የሚችለው ፤ ፩ኛ ፤ በእሑድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፤
፪ኛ ፤ በመንግሥትና ፡ በልዩ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ነው ።



## ፩ኛ ፤ የእሑድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ።

ለታላላቁ ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ ጠቅላላው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎት ፡
ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ እሑድ ፡ እሑድ ፡ ሕፃናትን ፡ ሰብስቦ ፡ እንደ ፡
ግጥም ፡ እንደ ፡ መዝሙር ፡ እንደ ፡ ተች ፡ እንደ ፡ ምሳሌ ፡ ያለ ፤ ወይም ፡
የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባቶችን ፡ ታሪክ ፡ ባጭሩ ፡ እያወጡ ፡ ማስተማር ፡
ቢቻል ፡ ከዚያም ፡ የዕድሜን ፡ የክፍልን ፡ ደረጃ ፡ በመለየት ፡ ልጃገረዶ
ችን ፡ ወንዶችን ፡ በመለየት ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ማስተማር ፡ መልካም ፡ ውጤትን ፡
ይሰጣል ። የዚህን ፡ ዐይነት ፡ ትምህርት ፡ የጥንት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትጠ
ቀምበት ፡ ነበር ፤ አሁንም ፡ ብዙው ፡ ዓለም ፡ የሕፃናት ፡ ማሳደጊያ ፡ የሕዝብ ፡
ማጥመጃ ፡ አድርጎ ፡ ይጠቀምበታል ። ይህም ፡ ነገር ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ቢቻል ፡
በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ መኾን ፡ አለበት ፤ ምክንያቱም ፡ ፩ኛ ፤ በቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ የሚሠራው ፡ ኹሉ ፡ መንፈሳዊ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ሕፃናቱ ፡ አክብ
ረው ፡ ይቀበሉታልና ። ፪ኛ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ እንደ ፡ ቤት ፡ ቈጥረው ፡
ኹል ፡ ጊዜ ፡ ለመገኘት ፡ ፈቃደኛ ፡ ይኾናሉና ፡ ባይቻል ፡ ግን ፡ ምቹ ፡ ከኾ
ነው ፡ ከማንኛውም ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሊኾን ፡ ይችላል ፤ ማለት ፡ ለሕፃናቱ ፡
አማካይ ፡ በኾነ ፡ ጨኸት ፡ ዋካታ ፡ በሌለበት ፡ ለጊዜውም ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡
ቦታ ፡ የሚቆጠር ፡ መኾን ፡ አለበት ፤ ወደዚህ ፡ ቦታ ፡ ሲሄዱ ፡ ወላጆች ፡
ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ልብስ ፡ ማልበስ ፡ ያስፈልጋቸዋል ፤ ምክንያቱም ፡ ያ ፡ ቀን ፡
ደርሶላቸው ፡ ያን ፡ ልብስ ፡ ለመልበስ ፡ ሲጓጉ ፡ ቆይተው ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡
በደስታ ፡ ስለሚሄዱ ።

፪ኛ ፤ በመንግሥት ፡ ወይም ፡ በልዩ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሲገቡ ፤ ሕፃ
ናት ፡ የትም ፡ ቢሄዱ ፡ ካህኑ ፡ መከተል ፡ ስለሚገባው ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡
ሲገቡ ፡ ከሥራም ፡ ቢኾን ፡ እየተከተሉ ፡ ማስተማር ፡ አለበት ፡ በትምህ
ርት ፡ ቤት ፡ የመንግሥትም ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ የራስ ፡ (የግል) ፡ ትምህርት ፡
ቤት ፡ ካህኑ ፡ ፕሮግራም ፡ አውጥቶ ፡ ሰዓት ፡ ለይቶ ፡ ማስተማር ፡ ዋና ፡ ተግ
ባሩ ፡ ነው ። በተለይም ፡ አሁን ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በዘነጋበት ፡ ተፈ
ጥሮውን ፡ በረሳበት ፡ ሳይንስን ፡ በሚያመለክበት ፡ ጊዜ ፡ ሕፃናትን ፡ በት
ምህርት ፡ በሀይማኖት ፡ በግብረ ፡ ገብነት ፡ መከታተል ፡ ለካህኑ ፡ የግ
ዴታው ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ በየጊዜው ፡ የሚሰጣቸው ፡ የሳይንስ ፡ አስ
ረጂ ፡ የሀይማኖት ፡ ተቃዋሚ ፡ ስለሆነ ፡ የሀይማኖት ፡ ሕንፃ ፡ እንዳይፈ

www.ethiopianorthodox.org

ርስ ፡ በትምህርት ፡ መደገፍ ፡ የግድ ፡ ያስፈልጋል ። ትምህርት ፡ ቤት ፡ በሚዘጋበት ፡ ጊዜ ፡ በተለየ ፡ ለወጣቶች ፡ በዓል ፡ አድርጎ ፡ የምሥጢራት ፡ ኹሉ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆኑ ፡ ቅዱስ ፡ ቍርባንን ፡ መስጠት ፡ ሌሎችንም ፡ ምሥጢራት ፡ እንደ ፡ አስፈላጊነታቸው ፡ መስጠት ፤ አብሮ ፡ መጸለይን ፡ ማስለመድ ፡ ማንኛውንም ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ እንዳለባቸው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባል ፡ የሚሠራውን ፡ ኹሉ ፡ ዐቅማቸው ፡ በፈቀደላቸው ፡ ልክ ፡ እንዲሠሩ ፡ ማስተማር ።

## ፫ኛ ፤ ጾታን ፡ በመለየት ፡ መስበክ ።

ምንም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ለወንድ ፡ የተነገረው ፡ ለሴት ፤ ለሴት ፡ የተነገረው ፡ ለወንድ ፡ ቢኾንና ፡ ካህኑም ፡ በወል ፡ ስም ፡ መናገር ፡ ቢችል ፤ ወንዶች ፡ ሲያጠፉ ፡ በተለይ ፡ ወንዶችን ፤ ሴቶች ፡ ሲያጠፉ ፡ በተለይ ፡ ሴቶችን ፡ ማስተማር ፡ ዋና ፡ ተግባሩ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ የወንድ ፡ ሳይኮሎጂ ፡ ከሴት ፤ የሴትም ፡ ከወንድ ፡ የተለየ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ለየራሳቸው ፡ በግል ፡ እንደ ፡ ስሚታቸው ፡ በነርሱ ፡ ጠባይ ፡ ገብቶ ፡ ማስተማር ፤ መምከር ፤ መገሠጽ ፡ ለካህኑ ፡ የተለየ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ።

፩ ፡ ወንድ ፤ ማንኛውም ፡ ወንድ ፡ የቤቱ ፡ መሠረት ፡ እርሱ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ቤቱ ፡ እንዳይዛባ ፡ ጸንቶ ፡ መሥራት ፡ ጋብቻውን ፡ አክብሮ ፡ ለሚስቱ ፡ የሚገባትን ፡ ፍቅር ፡ እየፈጸመ ፤ ልጆች ፡ በሚገባ ፡ እንዲያግ ፡ እየመከረ ፡ እያስተማረ ፡ ወጥቶ ፡ ወርዶ ፡ ደክሞ ፡ ቤቱን ፡ እንዲያደረጅ ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ በትክክል ፡ እንዲያስተዳድር ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ከባድ ፡ ኀላፊነቱን ፡ ቸል ፡ እንዳይል ፡ መምከር ፡ ማስተማር ፡ የካህኑ ፡ ተግባር ፡ ነው ። ወንድ ፡ ሚስቱን ፡ መውደድ ፤ ጋብቻውን ፡ ማክበር ፡ እንዲገባ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ወንዶችን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ለብቻ ፡ ይመክራል ፡ «እላንት ፡ ወንዶች ፡ ሚስቶቻችሁን ፡ ውደዱ ፡ ክርስቶስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ ስለርስዋም ፡ ራሱን ፡ እንደለወጠ ፡ እንዲሁም ፡ ይገባል ፡ ለወንዶች ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ እንደ ፡ ሥጋቸው ፡ ይወዱ ፡ ዘንድ ፡ ሚስቱን ፡ የሚወድ ፡ ራሱን ፡ ይወዳልና ፤ ማንም ፡ ሥጋውን ፡ የሚጠላ ፡ ከቶ ፡ የለምና ፡ ይመገበዋል ፡ እንጂ ፤ ያቅፈዋልም ፡ እንጂ ፤ ክርስቶስ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ እንዳደረገ ፡ ስለዚስህ ፡ ሰው ፡ አባቱንና ፡



እናቱን ፡ ይተዋል ፡ ከሚስቱም ፡ ይጣበቃል ፡ ኹለቱም ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ይኾናሉ ፡ » ኤፌ/ ፭ ፡ ፳፫—፴፫ ፤ ፩ኛ ፡ ቆሮ/ ፯ ፡ ፫—፲፯ ፤ ቆላስ / ፫ ፡ ፲፱ ) ። ወንድ ፡ ሚስቱን ፡ ከወደደ ፡ ጋብቻንም ፡ ካከበረ ፡ በዓለም ፡ በሽታ ፡ አይገኝም ፤ ዘር ፡ አይቀነሰስም ፤ ጸጥታው ፡ አይበላሽም ፤ ዛሬ ፡ በዓለም ፡ ያስቸገረው ፡ ጋብቻ ፡ ከመርከሱ ፡ የተነሣ ፡ ልጆች ፡ ቢወለዱም ፡ እናቶቻቸው ፡ እንጂ ፤ አባቶቻቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አይታወቁም ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ መካኑ ፡ ይበዛል ። ይህን ፡ ርኩስ ፡ መንፈስ ፡ ሊለውጠው ፡ የሚችል ፡ የካህኑ ፡ ትምህርት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ካህኑ ፡ በወንዶች ፡ ሳይኮሎጂ ፡ ገብቶ ፡ በሚስቶታቸው ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ፍጹም ፡ ፍቅር ፡ ሙሉ ፡ እምነት ፡ እንዲያድርባቸው ፡ ማስተማር ፡ ይገባዋል ።

## ፪ ፤ ሴ ት ።

ሴት ፡ ለቤቷ ፡ ጕልላት ፤ ለባልዋ ፡ ጌጥ ፡ ዕንቍ ፡ ፈርጥ ፡ ናት ፡ የቤትን ፡ ጸጥታ ፡ የምታስከብር ፡ የውስጥ ፡ ድርጅትን ፡ የምታሳምር ፡ ርሷ ፡ ናት ፤ ስለዚህ ፡ በሕግ ፡ ጸንጥታ ፡ ጋብቻዋን ፡ አስከብራ ፡ ባሏን ፡ አፍቅራ ፡ መኖር ፡ እንዲገባት ፡ ሴትን ፡ ለብቻ ፡ አድርጎ ፡ ማስተማር ፡ የካህኑ ፡ ልዩ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ፤ ሴቶችን ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ለይቶ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ይመክራቸዋል ፡ «እንዲሁም ፡ እላንት ፡ ሴቶች ፡ ለባሎቻችሁ ፡ ተገዙ ፡ ርሳቸው ፡ ስዎች ፡ ቢኖሩ ፡ ለነገር ፡ የማይገዙ ፡ ያጌጡ ፡ ዘንድ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ በሴቶቻቸው ፡ አካሄድ ፡ የነጻችውን ፡ አካሄዳቸውን ፡ በመመልከት ፡ በፍርሀት ፤ እሊያ ፡ ጌጣቸው ፡ ከአፍአ ፡ ያይደለ ፡ የራስ ፡ ጠጕር ፡ በመሠራት ፤ በወርቅም ፡ ዝርግፍ ፡ በጌጥም ፡ ልብስ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በማይጠፋ ፡ በተሰወረች ፡ በልብ ፡ ሰውነት ፡ በየዋህ ፡ ነፍስ ፡ ጸጥ ፡ ባለ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ገናንነቱ ፡ የከበረ ፤ ቀድሞ ፡ እንዲህ ፡ ነፍሳቸውን ፡ ያስጌጡ ፡ ነበሩና ፡ የተቀደሱት ፡ በእግዚአብሔር ፡ የታመኑ ፡ ሴቶች ፡ ለባሎቻቸውም ፡ የተገዙ ፡ ለአብርሃም ፡ እንደ ፡ ተገዛች ፡ እንደሣራ ፡ ጌታየም ፡ ትለው ፡ ነበረች ፤ እላንት ፡ ልጆችዋ ፡ የኾናችሁ ፡ መልካም ፡ ብታደርጉ ፡ ከፍርሀትም ፡ ኹሉ ፡ አንዳች ፡ ሳትፈሩ ፡ » (፩ኛ ፡ ጴጥ / ፫ ፡ ፯—፯ ።

ምንም ፡ ሴቶችን ፡ ወንዶች ፡ ቢበድሏቸው ፡ ልበኛ ፡ ሴት ፡ ነገር ፡ አላፊ ፤ ልበ ፡ ሰፊ ፡ ከኾኑ ፡ በእሳት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ፈሰሰ ፡ ውኃ ፡ ነገሩን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሊያበርዱት ፡ ይችላሉ ፤ ከሞቀ ፡ ቤት ፡ ከደረጀ ፡ ሀብት ፡ ወጥቼ ፡ ብቸኝነ
ትን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጌ ፡ ልኑር ፡ አይሉም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ብዙዎቹ ፡ «ሲሻኝ፡
ጢስ ፡ ወጋኝ ፡ » እንደ ፡ ተባለው ፡ ለመለያየት ፡ ምክንያት ፡ ሲሹ ፡
ይኖሩና ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሲናገሩዋቸው ፡ እነርሱም ፡ ተቀይመው ፡ ሰውም ፡
አስቀይመው ፡ ሊሄዱ ፡ ይችላሉ ። ይህ ፡ ኹሉ ፡ እንዳይኾን ፡ ካህኑ ፡ በሴ
ቶች ፡ ሳይኮሎጂ ፡ ገብቶ ፡ ነገሩ ፡ የሚበርድበትን ፤ ቤቱ ፡ የሚደረጅበትን፡
ልጆች ፡ የሚያድጉበትን ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚጠበቅበትን ፤ ፍቅ
ራቸው ፡ የሚጸናበትን ፡ በጠቅላላም ፡ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ እንደ፡ት ፡ ባለ ፡
ዘደ ፡ ሕይወታቸውን ፡ በሰላም ፡ ለማሳለፍ ፡ እንዲችሉ ፡ መምከር ፡ ማስ
ተማር ፡ አለበት ።

ሴቶችን ፡ የልጅነት ፡ ጠባይ ፡ ስለሚያቸንፋቸው ፡ ሥጋዊ ፡ ጌጥ ፡
ስለሚያምራቸው ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የሥጋ ፡ ደካማነት ፡ አግኝቷ
ቸው ፡ ለቤታቸው ፡ ዕንቅፋት ፡ እንዳያገኛቸው ፡ ሴቶች ፡ በምግባር ፡ በሀይ
ማኖት ፡ በትሩፋት ፡ የቤት ፡ ድርጅትን ፡ በማሳመር ፡ እንዲያጌጡ ፡ ካህኑ፡
ሳያፍር ፡ ሳይፈራ ፡ መምከር ፡ ማስተማር ፡ አለበት ። ይህን ፡ የመሰለውን፡
ትምህርት ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ « እንዲሁም ፡ ሴቶች ፡ በማያስነውር ፡
ልብስ ፡ በነፍረትና ፡ በጥበብ ፡ ራሳቸውን ፡ ያጊጡ ፤ ራስ ፡ በመሠራትም ፡
አይደለም ፡ በወርቅም ፡ አይደለም ፡ በዕንቍም ፡ በውድ ፡ ልብስም ፡ አይ
ደለም ፤ እግዚአብሔርን ፡ ለሚፈሩት ፡ ሴቶች ፡ እንደሚገባ ፡ እንጂ ፤ መል
ካም ፡ በመሥራት ፡ » (፩ኛ ፡ ጢሞ / ፪ ፡ ፱—፲) ፡ እያለ ፡ ያስተምራል ። ሴት፡
የባሏ ፡ ፍቅር ፡ ከጸና ፡ ቤት ፡ ለመያዝ ፡ ልጅ ፡ ለማሳደግ ፡ ከፈለገች ፡ የም
ንዝር ፡ ጌጥን ፡ ኹሉ ፡ አትሻውም ፤ ይኸውም ፡ በአንዳንድ ፡ ደጋጎች ፡
ቤተ ፡ ሰብ ፡ ይታወቃል ።

በተለየ ፡ ካህኑ ፡ ሴቶች ፡ በምግባር ፡ በሃይማኖት ፡ የጸኑ ፤ ሕግን ፡
ያከበሩ ፡ እንዲኾኑ ፡ መድከም ፡ አለበት ፤ ምክንያቱም ፡ ሴቶች ፡ ለማንኛ
ውም ፡ ነገር ፡ ተስማሚዎች ፡ ናቸው ፤ ጽድቁ ፡ በነርሱ ፡ ይበዛል ፤ ግን ፡
ስሕተቱም ፡ በነርሱ ፡ ይጸናል ፤ በነርሱም ፡ ይበዛል ፤ ኹሉን ፡ በፍጥነት ፡
ይቀበሉታል ፤ በፍጥነትም ፡ ይዘነጉታል ፤ ለምሳሌ ፡ የሴት ፡ ጻድቅ ፡ በበ
ዛበት ፡ አገር ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ጻድቅ ፡ ይኾናል ፤ የመንግሥቱም ፡ አስተ
ዳደር ፡ ጸጥታ ፡ ያለው ፡ ይኾናል ። የሴት ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በበዛበት ፡ አገር ፡
ደግሞ ፡ ኹሉ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ይኾንና ፡ ለአስተዳደሩም ፡ ልክ ፡ መልክ ፡ እያሳጣ፡



የኑሮ ፡ ዕንቅፋትን ፡ በራሱ ፡ ሲያዘጋጅ ፡ ይገኛል ። ይኹን ፡ እንጂ ፤ ጽድ
ቁም ፡ የሚበዛው ፡ ካህኑ ፡ በሚያስተምርበት ፡ በሚሠራበት ፡ አገር ፡ በሚ
ሠራበትም ፡ ጊዜ ፡ ነው ፤ ሕገ ፡ ወጡም ፡ የሚበዛ ፡ ካህኑ ፡ ቸል ፡ ባለበት፡
አገርና ፡ ካህኑ ፡ በማይሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

## ፬ኛ ፤ የዕውቀት ፡ ደረጃን ፡ በመለየት ።

ካህኑ ፡ በሚያስተምርበት ፡ ጊዜ ፡ የእያንዳንዱን ፡ የዕውቀት ፡ ደረጃ፡
መመጠን ፡ አለበት ፤ ከሥራውም ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ሊኾን ፡ ይገባል ፡ ማለት፡
ለእያንዳንዱ ፡ ስም ፡ መልክ ፡ ዕውቀት ፤ ሥራ ፡ የለየ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤
እንደ ፡ ፍላጎታቸው ፡ ለማስተማር ፡ ይችላል ። ዐዋቂውንና ፡ አላዋቂውን፡
ባንድ ፡ ላይ ፡ አስተምራለሁ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ጥሬና ፡ ብስል ፡ የኾነ
ውን ፡ ለምግብ ፡ አቅርቦ ፡ ኹሉም ፡ እንዳይበላ ፡ እንደ ፡ ማድረግ ፡ ይኾን
በታል ፤ ማለት ፡ ዐዋቂውም ፡ እንደ ፡ ዕውቀቱ ፡ ደረጃ ፡ ስላላገኘው ፡ ነቅ
ፎት ፡ ይሄዳል ፤ አላዋቂውም ፡ ምንም ፡ ሳይረዳውና ፡ ከቀድሞ ፡ ዕውቀቱ ፡
የተሻለ ፡ ስላላገኘበት ፡ ድካም ፡ ትርፍ ፡ መኾኑን ፡ ዐውቆ ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡
ሊገኝለት ፡ አይፈቅድም ። ይኸም ፡ ከኾነ ፡ ካህኑ ፡ ድካምን ፡ ብቻ ፡ አተ
ረፈ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ አስተዋይ ፡ ገበሬ ፡ ምርቱንና ፡ ገለባውን ፡ ለይቶ ፡
ኹሉንም ፡ በየተወሰነላቸው ፡ ቦታ ፡ እንዲያስቀምጥ ፡ ዐዋቂ ፡ የኾነው ፡
የትምህርት ፡ ገበሬ ፡ ካህኑ ፡ ለዐዋቂዎች ፡ የሚሰጠውን ፡ ትምህርት ፡
ጊዜና ፡ ቦታ ፡ ወስኖ ፡ ያስተምራል ። ላላዋቂዎችም ፡ እንዲሁ ፡ ያደርጋል ፤
ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንደ ፡ ደረጃው ፡ ማስተማር ፡ እንደሚገባ ፡ «እኔ ፡
ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ እንደ ፡ መንፈሳውያን ፡ እነግራችሁ ፡ ዘንድ ፡ አልቻል
ሁም ፡ እንደ ፡ ሥጋውያን ፡ እንጂ ፤ እንደ ፡ ትናንሽ ፡ ሕፃናት ፡ በክርስቶስ፡
ወተት ፡ ጋትኋችሁ ፡ መብልም ፡ አይደለም ፡ ያን ፡ አልቻላችሁትምና ፡
እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ አልቻላችሁትም ፡ » (፩ኛ ፡ ቆሮ / ፫ ፡ ፩—፪) ፡ ሲል ፡
የቆሮንቶስን ፡ ሰዎች ፡ ያስተምራል ። ለሕፃናት ፡ የሚሰጠው ፡ ምግብና ፡
ለዐዋቂ ፡ የሚሰጠው ፡ የተለየ ፡ እንደ ፡ ዕድሜው ፡ እንደ ፡ ችሎታው ፡ ነው ።
መንፈሳዊው ፡ ምግብ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃልም ፡ እንደዚሁ ፡ የኾነ ፡
ንደ ፡ ኾነ ፡ መረዳትን ፡ ገንዘብ ፡ ማድረግ ፡ ከሰሚዎች ፡ ስለሚገኝ ፡ ሰሚ
ውም ፡ አሰሚውም ፡ መልካም ፡ ውጤትን ፡ ያገኛሉ ። ዕብራውያን ፡ ወጣ

www.ethiopianorthodox.org

ንያን ፡ ሲኾኑ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ትምህርት ፡ ተምረው ፡ ሳይረዱ ፡ እንደ ፡ ቀሩ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ወቀሳን ፡ የተመረከዘ ፡ ምክር፡ «መምህራን ፡ ትኾኑ፡ ዘንድ ፡ ይገባ ፡ ነበርና ፡ ረጅም ፡ ዘመን ፡ ስለ፡ ኾናችሁ ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ ትሻ ላችሁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የነገሩን ፡ መጀመሪያ ፡ ትማሩ ፡ ዘንድ ፡ ወተ ትም ፡ የምትሹ ፡ ኾናችሁ ፡ ጽኑ ፡ መብልም፡ አይደለም ። ምግቡ ፡ ወተት፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ የእውነት፡ ነገር ፡ አያውቅምና ፡ ገና ፡ ሕፃን ፡ ነውና ፤ ጽኑ፡ መብል ፡ ግን ፡ ለፍጹማን ፡ ነው፤ ልቡናቸው ፡ መልካሙንና ፡ ክፉውን ፡ ለመለየት ፡ የለመዱ ፡ » (ዕብ / ፭ ፣ ፲፪—፲፬) ፡ ሲል ፡ ሰጥቷቸዋል ።

፫ኛ ፡ የማዕርግ ፡ ደረጃን ፡ በመለየት ።

የሰው ፡ የፍጥረት ፡ ምንጭ ፡ ማለት ፡ ፈጣሪው ፡ አንድ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ሲኾን ፤ ዘሩም ፡ ኹሉ ፡ ከአዳምና ፡ ከሔዋን፡ ሲገኝ ፡ እንዲሁ፡ ለአ ንዳንድ ፡ ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ ስለሚሰ ጠው ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰጠው ፡ ስጦታ ፡ ሊከበር ፡ የሚገባው ፡ አለ ፤ በዘርም ፡ የሚከበር ፡ አለ ፤ ለምሳሌ ፡ የከፍተኞች፡ ባለሥልጣኖች ፡ ዘር ፡ የኾኑትን ፡ ኹሉ፡ ቀን፡ ጣላቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነሣቸው ፡ ብሎ ፡ ማዋ ረድ ፡ አይገባም ፤ እንዲሁም ፡ ንጉሥ፡ የሾመው ፡ ኹሉ ፡ የእርሱ ፡ እንደ ራሴ ፡ ስለ ፡ ኾነ፤ ማክበር ፡ ይገባል ። እግዚአብሔር ፡ በሰጠው ፡ ሀብት ፡ ኹሉን ፡ ማክበር ፡ እንዲገባ፡ «ለኹሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ የሚገባውን ፡ ስጡ ግብር ፡ ለሚገባው ፡ ግብሩን ፤ ከዐሥር ፡ አንድ ፡ ለሚገባው ፡ ከዐሥር ፡ አንዱን ፤ ፍርሀት፡ ለሚገባው ፡ ፍርሀቱን ፤ ክብር ፡ ለሚገባው ፡ ክብሩን፡ (ሮሜ፡ ፲፫፡ ፯፡ ፩ኛ፡ ጴጥ/ ፪፡ ፲፫—፲፯)፡ ሲል ፡ቅዱስ፡ ጳውሎስ፡ ያስተምራል»

ስለዚህ ፡ ካህኑ፡ ክብር ፡ የሚገባቸውን ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ክብራቸው፡ ማስተማር ፡ መጀመሪያ ፡ እርሱ ፡ አክብሮ ፡ ሌላም ፡ እንዲያከብራቸው ፡ ማስተማር ፡ አለበት ። ቅዱስ ፡ ሉቃስ ፡ የመቄዶንያውን ፡ መኰንን ፡ ሲያ ከብር ፡ «የከበርክ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ሆይ ፤ » ሲል ፡ በአክብሮት ፡ ቃል ፡ ይጽ ፍለታል ። ቅዱስ ፡ ዮሐንስም ፡ «ከሽማግሌው ፡ ወደ ፡ ተመረጠች ፡ እመ ቤትና ፡ ልጆቿ ፡ » ሲል ፡ የአክብሮት ፡ ደረጃን ፡ በመለየት ፡ ጽፎዋል ። ካህኑ ፡ የደግ ፡ ነገር፡ ኹሉ ፡ አብነት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ እርሱ ፡ ያከበራቸውን ፡ ሕዝቡ ፡ ስለሚያከብራቸው ፡ ክብር ፡ የሚገባቸውን ፡ በደንብ ፡ አክብሮ ፡



ማስተማር ፡ ለባሕርያቸው ፡ ለክብራቸው ፡ ተስማሚ ፡ የኾነውን ፡ ትምህ ርት ፡ አዘጋጅቶ ፡ ማስተማር ፡ አለበት ።

ነገር ፡ ግን ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔር፡ ሲፈርስ ፡ ሀይማኖት ፡ ሲለወጥ ፡ ሥርዐተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲፋለስ፡ መገሠጽ ፡ ይገባዋል ፤ መፍራት፡ ማፈር ፡ ለየበትም ፤ ከዚህም ፡ ሌላ፡ ክብር፡ የሚገባቸውን ፡ ማክበር ፡ ይገ ባል ፤ ስንል ፡ ሌላውን ፡ ያዋርድ ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ካህን ፡ ትሑት ፡ ኾኖ ፡ ኹሉን ፡ ማክበር፡ አለበት፤ ይህ፡ የኾነ ፡ እንደ፡ ኾነ ፡ ኹሉ ፡ ይከባበ ራል ፤ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ለበሽተኞች ፡ ልክ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ እንደሚሠቃይ፡ የበሽታቸውም፡ ተካፋይ ፡ ኹኖ ፡ ከሚያዝኑት ፡ ከሚተክዙት ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ያዘነ ፡ የተከዘ ፡ ኹኖ ፡ ማስተማር ፡ አለበት ።

«የታሰሩትን ፡ ዐስቡ ፡ እላንተ ፡ ከርሳቸው ፡ ታሥራችሁ ፡ እንደ ፡ ነበራችሁ ፡ መከራ ፡ የጸናባቸውንም ፡ እላንት ፡ ደግሞ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ » (ዕብ / ፲፫ ፡ ፫) ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ «ደስ ፡ ካላቸው ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡ ከሚያለቅሱ ፡ ጋራም ፡ አልቅሱ ፡ » (ሮሜ ፡ ፲፪፡ ፲፭ ፡ ፩ኛ ፡ ጴጥ / ፫ ፡ ፰) ፡ ሲል ፡ ማንኛውንም ፡ ሰው ፡ መስሎ ፡ በበ ሽታ ፡ በእስራት ፡ በኀዘን ፡ ያሉትን፡ ኹሉ ፡ በማጽናናት ፡ በመምከር ፡ የሚያክ ማቸው ፡ ካህኑ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ እውነተኛ ፡ ሐኪም ፡ መኾን ፡ አለበት ። በአ ንድ ፡ መንጋ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ እንስሳት ፡ እንዲገኙ ፡ ጠባቂው ፡ ኹሉን ፡ በትክክል ፡ እንዲያሰማራ ፡ ለዐመለኛውም ፡ አስፈላጊውን ፡ መከ ላከያ ፡ አድርጎ ፡ ኹሉን ፡ እንዲጠብቅ ፤ አንዱን ፡ ቢያጠፋ ፡ ከባለቤቱ ፡ ዘንድ ፡ ወቀሳ ፡ መቀጫ ፡ እንደሚያገኘው ፡ ኹሉ ፡ ንባብ ፡ አእምሮ ፡ ያለ ውን ፡ መንጋ ፡ ለሚጠብቅ ፡ ለካህኑ ፡ ኹሉን ፡ እንደ ፡ ዐመሉ ፡ እንደ ፡ ማዕርጉ ፡ እንደ ፡ በሽታው ፡ እንደ ፡ ስሜቱ ፡ እየተከታተሉ ፡ መጠበቅ ፡ አለ በት ። በቸልተኝነት ፡ አንዱን ፡ ያጠፋ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ከባለቤቱ ፡ ከእግዚ አብሔር ፡ ዘንድ ፡ የዘለዓለም ፡ ቅጣት ፡ ይቆየዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

# ክፍል ፡ ፪ ።

# የካህኑ ፡ የማንጻት ፡ ሥራው ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ምሥጢራተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

የካህኑን ፡ ሥራ ፡ ስንዘረዝር ፡ ስብከት ፡ ጉብኝት ፡ ይህንንም ፡ የመሰለ ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ መፈጸም ፡ እንደሚገባው ፡ በሰፊው ፡ አትተናል ። ይህን ፡ ኹሉ ፡ የሚሠራበት ፡ ዋናው ፡ ዓላማ ፡ ሕዝብን ፡ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ የንጉሥ ፡ ማደሪያ ፡ የተመረጠ ፡ ወገን ፡ (፩ኛ ፡ ጴጥ / ፪ ፡ ፱ ፡ ) ለማድረግ ፡ ነው ። እንደ ፡ ታሰበው ፡ ግን ፡ ለማድረግ ፡ አስቀድሞ ፡ ማንጻት ፡ ማጽናት ፡ የቅዱስ ፡ ምሥጢርና ፡ የማናኛውም ፡ ቅዱስ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ተሳታፊ ፡ የምሥጢራት ፡ ኹሉ ፡ ተካፋይ ፡ መኾን ፡ አለበት ፤ « ስለዚህም ፡ ሰዎች ፡ እኛን ፡ ይቈጠሩን ፡ ለክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ምናገለግል ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምስጢር ፡ እንደምንጠብቅ ፤ ከዚህም ፡ ጋራ ፡ ከመጋቦች ፡ ይፈልጋል ፡ ከርሳቸው ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ የታመነ ፡ ኹኖ ፡ ይገኝ ፡ ዘንድ » (፩ኛ ፡ ቆሮ / ፬ ፡ ፩—፪)፡ እያለ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ለመምህራን ፡ ይገልጣል። ካህኑ ፡ የማንጻት ፡ ተግባሩን ፡ የሚፈጽምባቸው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ ሀብት ፡ ልጅነት ፡ የሚያስተላልፍባቸው ፡ ፯ት ፡ ምሥጢራተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሉ ። እነዚህም ፡ ምሥጢራት ፤ ምሥጢረ ፡ ጥምቀት ፡ ምሥጢረ ፡ ሜሮን ፡ ምሥጢረ ፡ ቍርባን ፡ ምሥጢረ ፡ ንስሓ ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ አራቱ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ የግድ ፡ የሚያስፈልጉ ፡ ያለነዚህ ፡ ድኅነት ፡ ልጅነት ፡ ሕይወት ፡ የማይገኝ ፡ ታላላቅ ፡ ምሥጢራት ፡ ናቸው ። ደግሞም ፡ ክህነት ፡ ተክሊል ፡ ቀንዲል ፡ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ለፈለገው ፡ ሰውና ፡ እግዚአብሔር ፡ ላደለው ፡ ለተለዩ ፡ ሰዎች ፡ እንጂ ፤ ለሁሉ ፡ የማያስፈልጉ ፡ ምሥጢራት ፡ ናቸው ።

ምክንያቱም ፡ ኹሉ ፡ ክህነት ፡ አይቀበልም ፤ የክህነት ፡ ሀብት ፡ ከተሰጠው ፡ እግዚአብሔር ፡ ከጠራው ፡ በቀር ፤ ሁሉም ፡ አያገባም ፤ የጋብቻ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሀብት ፡ ከተሰጠው ፡ ዘር ፡ ለማብዛት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለመኖር ፡ ከተወሰነ
ለት ፡ በቀር ፡ ሁሉ ፡ አይታመምም ፤ ለታመሙና ፡ ለፈለጉ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ።
ከነዚህ ፡ ከ፯ቱ ፡ ምሥጢራት ፡ የሚደገሙ ፡ የሚከለሱ ፡ እንዲሁም ፡
የማይደገሙም ፡ አሉ ፤ ለምሳሌ ፡ ክህነት ፡ ጥምቀት ፡ እነዚህ ፡ ምንም ፡
ቢኾን ፡ አይደገሙም ፤ ጥምቀት ፡ አንዲት ፡ ናት ፤ «ወነአምን ፡ በአሐቲ ፡
ጥምቀት ፡ ለስርየተ ፡ ኀጢአት ፡ » (የሀይ / ጸሎት ፡ ) ብለው ፡ የሃይማኖት ፡
አባቶች ፡ እንደ ፡ ተናገሩ ። ክህነትም ፡ ከዲቁና ፡ ወደ ፡ ቅስና ፡ ከቅስና ፡
ወደ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ይሄዳል ፡ እንጂ ፤ በዚያው ፡ ባ፩ኛው ፡ ደረጃ ፡
መደገም ፡ የለበትም ። «እመበ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ አው ፡
ዲያቆን ፡ ዘተሰይመ ፡ ፪ተ ፡ ጊዜ ፡ ይትመተር ፡ ውእቱኒ ፡ ወዘሤሞ ፡ - -»
(ፍትሐ ፡ ነገ / አንቀጽ ፡ ኀምስ ፡ በእንተ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፤ ሳምን ፡ ወታ
ስዕ ፡ ረስጠብ ፡ ዘ፴፯) ።

ጋብቻም ፡ በመሠረቱ ፡ እንዲሁ ፡ ሊደገም ፡ የማይቻል ፡ ምሥጢር ፡
ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የሞተችበትና ፡ በታወቀ ፡ በልዩ ፡ ምክንያት ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ፈቅዳ ፡ እስከ ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ ለማግባት ፡ ይችላል ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡
ግን ፡ ዝሙት ፡ እንጂ ፤ ጋብቻ ፡ አይባልም ። «ወለእመ ፡ ተሀበለ ፡ ከመ ፡
ይግበር ፡ ላዕለ ፡ አውስቦ ፡ ራብዕ ፡ ዘኢኮነ ፡ አውሰቦ ፡ ውእቱ ፡ ኢይትኌ
ለቍ ፡ ውስተ ፡ ሕገ ፡ ተዋስቦ ፡ ዝንቱሰ»(ፍትሐ ፡ ነገ / አንቀጽ ፡ ፳፬ ፡ በእ
ንተ ፡ ፍሕርት ፡ ወሕጼ ፡ - - - - ጠስ ፬) ። እነዚህ ፡ ምሥጢራት ፡ ክርስቶስ ፡
ዓለምን ፡ ለማዳን ፡ ከአዘጋጀው ፡ ቸርነት ፤ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ ከፈጸመው ፡
ምሕረት ፡ የሚመነጩ ፡ ኹልጊዜም ፡ ያለማቋረጥ ፡ ለሰው ፡ ጸጋን ፡
ሲያሰጡት ፡ የሚኖሩ ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ምሥጢራት ፡ ናቸው ። እነዚህንም ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያለ ፡ ማቋረጥ ፡ ለመጪው ፡ ትውልድ ፡ ኹሉ ፡ ስታስ
ተላልፋቸው ፡ ትኖራለች ።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

## ምሥጢረ ፡ ጥምቀት ።

ጥምቀት ፡ ማለት ፡ ሌላውን ፡ ምሥጢራት ፡ ለመሳተፍ ፡ የቤተ ፡ ክር
ስቲያን ፡ አባል ፡ ለመኾን ፡ የመጀመሪያው ፡ መግቢያ ፡ በር ፡ ክርስቶስ ፡
የመሠረተው ፡ ከውሃው ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ በማለት ፡ ከመንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ የሚወለዱት ፡ ልደት ፡ ነው ። ራሱ ፡ ክርስቶስ ፡ የመሠረተው ፡



ምሥጢር ፡ ለመኾኑ ፡ «እንግዲህ ፡ ሂዱና ፡ አሕዛብን ፡ ኹሉ ፡ አስተምሩ ፡
አጥምቋቸውም ፡ በአብና ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ስም ፡ » (ማቴ /
፳፰ ፡ ፲፱ ፡ ) ሲል ፡ ያስረዳናል ።

ማንም ፡ ቢኾን ፡ በነገዱ ፡ በዘሩ ፡ በኀይሉ ፡ ተመክቶ ፡ የእግዚአሔ
ርን ፡ መንግሥት ፡ ለማየት ፡ የሚችል ፡ የለም ፤ ከአብራከ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ከማሕጸነ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ካልተወለደ ፡ በቀር ፡ «ኢየሱስም ፡ መለሰ ፡ እው
ነት ፡ እልሀለሁ ፡ ማንም ፡ ከውሀና ፡ ከመንፈስ ፡ ካልተወለደ ፡ ወደ ፡ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ መንግሥት ፡ ይገባ ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፡ » (ዮሐ / ፫ ፡ ፫—፯ ፡ ) ሲል ፡
ክርስቶስ ፡ አስረድቷል ። ክርስቶስ ፡ በቃል ፡ ብቻ ፡ አላስተማረም ፤ ነገር ፡
ግን ፡ በሥራም ፡ ፈጸመው ፡ እንጂ ፤ ማለት ፡ በባሕረ ፡ ዮርዳኖስ ፡ በእደ ፡
ዮሐንስ ፡ ተጠመቀ ፡ (ማቴ/ ፫ ፡ ፲፫—፲፯ ፤ ማር/ ፩ ፡ ፱—፲፩ ፤ ሉቃስ /
፫ ፡ ፩ ፤ ዮሐ/ ፩ ፡ ፴፫) ።

፩ኛ ፤ ለጥምቀት ፡ የሚያስፈልጉ ። እውነተኛ ፡ ጥምቀትን ፡ ለመጠ
መቅ ፡ የተፈለገ ፡ እንደኾን ፡ ሊቀሩ ፡ የማይገባቸው ፡ አንቀጾች ፡ አሉ ፤
እነርሱም ፡ ፩ኛው ፡ እምነት ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ሰውየው ፡ በዕድሜ ፡ ከፍ ፡
ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የክርስትናን ፡ ትምህርት ፡ የተማረ ፤ በክርስቶስ ፡ ያመነ ፡
መኾን ፡ አለበት ። እምነት ፡ መሠረት ፡ ነው ፤ ሌሎች ፡ ምግባራት ፡ ግን ፡
ሕንፃዎች ፡ ይኾናሉ ። በዕድሜ ፡ ዝቅተኛ ፡ ስሜቱን ፡ እምነቱን ፡ ለመግ
ለጥ ፡ የማይችል ፡ ሲሆን ፡ ግን ፡ በወላጆችና ፡ በክርስትና ፡ አባቱ ፡
ወይም ፡ እናቱ ፡ አማካይነትና ፡ ኀላፊነት ፡ ሊጠመቅ ፡ ይገባል ። ለጊ
ዜው ፡ የነርሱ ፡ እምነት ፡ ለርሱ ፡ እንኳን ፡ ባይኾን ፡ በኀላፊነታቸው ፡
ይመክሩታል ፤ ያስተምሩታል ።

፪ኛ ፤ ጥምቀት ፡ በሥላሴ ፡ ስም ፡ መኾን ፡ አለበት ። የሥላሴ ፡ ስም ፡
ሳይጠራ ፡ የተጠመቁት ፡ ጥምቀት ፡ ከውሃ ፡ እንደ ፡ ተነከረ ፡ ቆዳ ፡ ያለ ፡
ነው ፡ እንጂ ፤ የሚሰጠው ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ ጥቅም ፡ የለውም ። በሥላሴ ፡
ስም ፡ ጥምቀት ፡ እንዲገባ ፡ «እንግዲህ ፡ ሂዱና ፡ አሕዛብን ፡ ኹሉ ፡ አስተ
ምሩዋቸው ፤ አጥምቋቸውም ፡ በአብና ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡
ስም ፡ » (ማቴ/ ፳፰ ፡ ፲፱) ፡ ሲል ፡ ራሱ ፡ ክርስቶስ ፡ አስረድቷል ።

www.ethiopianorthodox.org

፫ኛ ፤ በውሃ ፡ ማጥመቅ ። ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ እያደረጉ ፡ የሥላሴን ፡ ስም ፡ እየጠሩ ፡ አጠምቀከ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ አጠምቀከ፡ በስመ ፡ ወልድ ፡ አጠምቀከ ፡ በስመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ፡እያሉ፡በውሃ፡ማጥመቅ፡ ይገባል ። ውሃውም ፡ በተፈጥሮ ፡ ንጹሕ ፡ የኾነ ፡ ምንም ፡ ያልተቀላቀ ለበት ፡ መኾን ፡ አለበት ። ምክንያቱም ፡ ራሱ ፡ ክርስቶስ ፡ በውሃ ፡ ተጠ ምቋል ፡ ሐዋርያትንም ፡ በውሃ ፡ እንዲያጠምቁ ፡ አዟልና ። ከውሃው፡፫፡ ጊዜ ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ እያደረገ ፡ ያጠምቀዋል ፤ ፫ ፡ ጊዜ፡መኾኑ፡የሥላሴ፡ አምሳል ፡ ሥራው ፡ አንድ ፡ መኾኑ ፡ የአንድነት ፡ ምሳሌ፡ከውሃው፡መጥ ለቁና ፡ መውጣቱ ፡ እንዲሁ ፡ ክርስቶስ ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ ፫ ፡ መዓ ልት ፡ ፫ ፡ ሌሊት ፡ አድሮ ፡ የመነሣቱ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። «ወይስ ፡ አታው ቁምን ፡ እኛ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተጠመቅን ፡ በሞቱ ፡ እንደ ፡ ተጠ መቅን ፡ እንግዲህ ፡ በጥምቀት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተቀበርን ፡ ለሞት ፤ ክር ስቶስ ፡ ከሙታን ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ በአብ ፡ ክብር ፡ እንዲሁ ፡ እኛም ፡ ደግሞ ፡ በአዲስ ፡ ሕይወት ፡ እንሄድ ፡ ዘንድ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የተተከ ልን ፡ ከኾን ፡ በሞቱ ፡ ለሞቱ ፡ ምሳሌ ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ እንኾናለን፡ በትንሣኤው ፡ - - » (ሮሜ/ ፮ ፡ ፫—፭) ።

ከዚህም ፡ ጋራ ፡ አጥማቂው ፡ ደንበኛ ፡ ካህን ፡ ከደንበኛው፡ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ የተሾመ ፡ መኾን ፡ አለበት ፡ ማንኛውም ፡ አገልግሎት ፡ በትክ ክል፡እንዲፈጸም ፡ የግድ ፡ ያስፈልጋል ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ የተጠመቁትም ፡ ጥምቀት ፡ በምንም ፡ ምክንያት ፡ አይመለስም ፡ አይከለስም ፤ ጥምቀት ፡ የማያረጅ ፡ የማያፈጅ ፡ የማይለወጥ ፡ ምስጢር ፡ ነውና ፡ ምንም ፡ ቢኾን፡ ጥምቀት ፡ አንዲት ፡ ናት ፡ « ወነአምን ፡ በአሐቲ ፡ ጥምቀት ፡ ለስርየተ ፡ ኃጢአት ፡ » (የሀይማኖት ፡ ጸሎት ፤ ፍትሐ ፡ ነገ/አንቀጽ ፡ ሠላሳ ፡ ) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘረው ፡ በሚገባ ፡ እንዲፈጸም ፡ የካህኑን ፡ ኀላፊነት ፡ ይመ ለከታል ።

## ፬ኛ ፤ ለጥምቀት ፡ የተወሰነ ፡ ዕድሜ ።

ለጥምቀት ፡ የተወሰነ ፡ ዕድሜ፡የለም ፤ ትንሽም፡ትልቅም፡ቢኾን ፡ ወይም ፡ የጌታም ፡ የእመቤትም ፡ ልጅ ፡ የገረድም ፡ የአሽከርም ፡ ልጅ ፡ ቢኾን ፤ ወንድም ፡ ሴትም ፡ በጠቅላላ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ መጠመቅ ፡ እንዲገባው ፡ « እንግዲህ ፡ ሂዱና ፡ አሕ



ዛብን ፡ ኹሉ ፡ አስተምሩ ፡ አጥምቋቸውም ፡ - - - - »(ማቴ/ ፳፰ ፡ ፲፱)፡ እያለ ፡ ክርስቶስ ፡ አዟል ። የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሊቃውንት፡« ጥምቀ ትሰ ፡ - - - - ለዕደው ፡ ወለአንስት ፡ ንኡሶሙ ፡ ወዐቢዮሙ ፡ - - - - - » (ፍትሐ፡ነገ/ አንቀጽ ፫)፡ ሲሉ ፡ ያስረዳሉ።ሐዋርያት፡የክርስቶስን፡ቃል፡ ሰምተው ፤ ትምህርቱን ፡ ተከትለው ፤ ማንኛውንም ፡ ዕድሜ ፡ ያለውን ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ያጠምቁ ፡ ነበር ። በጠቅላላውም ፡ በአንድ ፡ ቤት ፡ የሚገ ኙትን ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ኹሉ፡ያጠምቁ፡ነበር ። ለምሳሌ፡ቅዱስ፡ጴጥሮስ፡ ቆርነሌዎስን ፡ ከነቤተ ፡ ሰቡ ፡ አጥምቋል። ( የሐ/ ሥራ ፡ ፲ ፡ ፵፰ ) ቅዱስ ፡ ጳውሎስም፡የእስጢፋኖስን፡ቤተ፡ሰብ፡አጥምቋል ። (፩ኛ፡ ቆሮ/ ፩፡ ፲፮፡ ) ሌሎችም ፡ ሐዋርያት ፡ እንዲሁ ፡ አጥምቀዋል ። የቀደሙ ፡ አባቶች ፡ ይህን ፡ ይዘው ፡ ሞት ፡ የሚያሠጋው ፡ ከኾነ ፡ ዕለት ፡ የተወለደውን ፡ ሳይ ቀር ፡ ያጠምቁ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታሪክና ፡ ሕግ (ፍት/ ነገ/ ፡ አንቀጽ ፡ ሣልስ)፡ ያስረዳናል ። ሞት ፡ የማያሠጋው ፡ ከኾነ ፡ ግን፡ ወንድ ፡ በ፵ ፡ ሴት ፡ በ፹ ፡ ቀን ፡ መጠመቅ ፡ እንዲገባው ፡ ኦርቶዶክሳ ዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ወስናለች ።

## ፭ኛ ፤ የጥምቀት ፡ ጥቅም ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በዘር ፡ ቁራኝነት ፡ የነበረበትን፡ኀጢአት ፤ ተፈ ርዶበት ፡ የነበረውን ፡ ሞት ፤ መጽሐፈ ፡ ዕዳውንም ፡ ኹሉ ፡ በጥምቀት ፡ ያጠፋል ፤ ይደመስሳል ፤ ነፍስን ፡ የጸራች ፡ አድርጎ ፡ የቀደመ ፡ ክብሩን ፡ ማዕርጉን ፡ ልጅነቱን ፡ ያገኛል ፤ በእግዚአብሔር፡ያለው ፡ ተስፋ ፡ ፍቅር ፤ ሀይማኖት ፡ የጸና ፡ ይኾናል ፤ ክርስቶስ ፡ ለሠራው ፡ ምሥጢር ፡ ኹሉ ፡ ተካፋይ ፤ የዘለዓለም ፡ ሕይወትም ፡ ወራሽ፡ ይሆናል ። በመላ፡ኀጢአቱ፡ ፈጽሞ ፡ እንዲደመሰስ ፡ ያደርጋል ። «ጴጥሮስም ፡ አላቸው ፡ ንስሓ፡ግቡ፡ ከላንት ፡ ኹሉ ፡ ለእያንዳንዳችሁ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም፡ይጠመቅ፡ ኀጢአት ፡ ለማስተስረይ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ ጸጋ ፡ ትወስዳላችሁ ፡ ተስፋው ፡ ለላንት ፡ ነውና ፤ ለልጆቻችሁም ፡ በሩቅ ፡ ላሉ ፡ ኹሉ ፡ እግዚ አብሔር ፡ አምላካችን፡ለጸራችውም፡ ኹሉ ፡ » (የሐ/ ሥራ፡፪፡፴፰ ፤ ፩ኛ፡ ቆሮ/ ፮፤፲፩) እያለ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ፡እንዳስረዳ።ማንኛውም፡የእግዚአብ ሔር ፡ ጸጋ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ የሚሰጠው ፡ በጥምቀት ፡ ከሥላሴ፡ከተወለደ፡ በኋላ ፡ እንደሆነ ፡ ቅዱሳት፡መጻሕፍት ፡ ተስማምተውበታል ፡ (ዮሐ/ ፫ ፡

www.ethiopianorthodox.org

፭ ፤ ኤፌ/ ፭ ፡ ፳፮ ፤ ገላ/ ፡ ፫ ፡ ፳፯ ፡ ቲቶ ፡ ፫ ፡ ፭ ፤ ፩ኛ ፡ ቆሮ/ ፲፪ ፡ ፲፫ ) ። በጠቅላላውም ፡ አሮጌው ፡ ሰውነት ፡ የሚታደሰው ፤ የጠፋው ፡ ልጅነት ፡ የሚመለሰው ፡ በ፪ኛው ፡ ልደታችን ፡ በጥምቀት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ « ጽድቅ ፡ በማድረግ ፡ ያደረግናት ፡ አይደለም ፤ በምሕረቱ ፡ አዳነን ፡ እንጂ ፤ ከ፪ኛ ፡ ልደቱ ፡ ጥምቀት ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መታደስ ፡ » (ቲቶ ፡ ፫ ፡ ፭ ) ፤ ሲል ፡ አስረድቷል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ምስጢረ ፡ ሜሮን ።

ሜሮን ፡ ማለት ፤ ከጥምቀት ፡ በኋላ ፡ የሚደረግ ፡ በርሱም ፡ አፈጻጸም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ለምእመናን ፡ የሚሰጥበት ፡ ምስጢር ፡ ነው ። መንፈሳዊ ፡ ሕይወት ፡ በጥምቀት ፡ ይጀመራል ፤ ማለት ፡ ሰው ፡ ፪ኛ ፡ ይወለዳል ፤ በሜሮን ፡ ይጸናል ፡ ማለት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይሰጠዋል ።

### ፩ ፤ የሜሮን ፡ አገልግሎት ፡ አፈጻጸም ፤

ሜሮን ፡ ማለት ፡ ቅባት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ ሽቱ ፡ ከሚሰጡ ፡ ዘይትነት ፡ ካላቸው ፡ ዕፀዋት ፡ ተዋሕደው ፡ የሚገኝ ፡ ቅባት ፡ ነው ። ይህም ፡ መጀመሪያ ፡ ሲሠራ ፡ በፓትርያርክና ፡ በጳጳሳት ፡ ጸሎት ፡ ይባረካል ፤ ይከብራል ፤ ከብዙ ፡ ዐይነት ፡ መደባለቁና ፡ አንድ ፡ መኾኑ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንድ ፡ ሲኾን፡ሀብቱ ፡ ብዙ ፡ ነውና ። ይህም ፡ ምሥጢር ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ምስጢራት ፡ በጽሑፍ ፡ ባይገለጥ ፡ ጌታ ፡ እንደ ፡ መሠረተው ፡ « ከርሱ ፡ የወሰዳችሁት ፡ መቀባት ፡ እላንት ፡ ትጸናበታላችሁ ፡ ማንም ፡ ያስተምራችሁ ፡ ዘንድ ፡ አትሹም ፤ እንዲሁ ፡ መቅባት ፡ ያስተምራችኋል ፡ እንጂ ፤ - - - » (፩ኛ ፡ ዮሐ/ ፪ ፡ ፳፯) እላንተም ፡ መቅባት ፡ አላችሁ ፡ ከቅዱሱ ፡ ኹሉንም ፡ ዐውቃችኋል ፡ - - - ቍጥር፳ ፤ ፩ኛ ቆሮ/ ፩ ፡ ፳፩ ) ሲል ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ያስተምራል ። ይህን ፡ የመሰለ ፡ የሐዋርያት ፡ የሊቃውንትም ፡ አገላለጥ ፡ ያስረዳል ። ይህም ፡ ቅባት ፡ የቅዱስ ፡ መንፈስ ፡ መሰጠትን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ ሐዋርያት ፡ ካጠመቁ ፡ በኋላ ፡ እጃቸውን ፡ ሲጭኑባቸው ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡ ወርዶ ፡ በተጠማቂዎቹ ፡ ላይ ፡ ያድር ፡ ነበር « በዚያን ፡ ጊዜም ፡ እጃቸውን ፡



ጫኑባቸው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ ተቀበሉ » (የሐ/ ሥራ ፡ ፰ ፡ ፲፬—፲፯ ) ሲል ፡ ሉቃስ ፡ ያስረዳል ።

ከዚያም ፡ አያይዘው ፡ እጅ ፡ በመጫን ፡ ፈንታ ፡ ቅዱስ ፡ ሜሮንን ፡ አዘጋጅተው ፡ ሲቀቧቸው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይሰጣቸው ፡ ጸጋ ፡ በረከትን ፡ ያገኙ ፡ ነበር ።

### ፪ ፤ የሜሮን ፡ ጥቅም ፡

ጥምቀት ፡ መወለድ ፡ ሲኾን ፡ ሜሮን ፡ ማደግ ፡ መጽናት ፡ ቅዱ ፡ መንፈስን ፡ ማግኘት ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ መወለዱ ፡ ብቻ ፡ ጠቃሚ ፡ አይደለም ፤ ቅዱስ ፡ መንፈስን ፡ አግኝቶ ፡ መጽናትም ፡ ያስፈልጋል ፡ እንጂ ። በጥምቀት ፡ የሚሰጡትን ፡ ሀብት ፡ ጸጋ ፡ የሚያረጋግጥ ፡ የሚያጸና ፡ ማኅተም ፡ ሜሮን ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ ምንም ፡ ጥምቀትም ፡ ሜሮንም ፡ ራሳቸውን ፡ የቻሉ ፡ ምስጢራት ፡ ቢኾኑ ፡ ተራ ፡ በተራም ፡ ቢሰጡ ፡ ሜሮን ፡ ከጥምቀት ፡ አይለይም ፤ ዕለቱን ፡ ተጠምቆ ፡ ዕለቱን ፡ መሰጠት፡ አለበት ። ይህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎትና ፡ የማንጻት ፡ ሥራ ፡ በትክክል ፡ የሚፈጽመው ፡ ካህኑ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ፩ኛው ፡ ሳይጎል ፡ በትክክል ፡ መፈጸም ፡ የግዴታ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## ምሥጢረ ፡ ቍርባን ።

የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ ለማግኘት ፡ ክርስቶስን ፡ መስለን ፤ ክርስቶስን ፡ ተዋሕደን ፤ ለዘለዓለም ፡ ሕያዋን ፡ ኹነን ፡ ለመኖር ፡ የሚያስችለን፡ ታላቁ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ክርስቶስ ፡ የመሠረተው ፡ እርሱም ፡ የፈጸመው ፡ ታላቁ ፡ ምሥጢር ፡ ምሥጢረ ፡ ቍርባን ፡ ነው።ይህን ፡ ምሥጢር ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ መሠረተው ፡ ፬ቱ ፡ ወንጌላውያን ፡ በመላም ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ በትክክል ፡ ይመሰክራሉ ( ማቴ/ ፡ ፳፮ ፡ ፳—፳፱ ፤ ማር/፲፬ ፡ ፲፯—፳፭ ፤ ሉቃስ/ ፡ ፳፪ ፡ ፲፬—፴፰ ፤ ዮሐ/ ፡ ፲፫ ፡ ፳፮—፴፩ ፤ ፮ ፡ ፶፮—፷፱ ፤ ፩ኛ ቆሮ/ ፲፩/ ፡ ፳፫-፳፰ ) ። አስቀድሞ ፡ በትምህርት ፡ « እኔ ፡ ነኝ ፡ የሕይወት ፡ ዕንጀራ ፡ ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ ማንም ፡ ከዚህ ፡ እንጀራ ፡ የበላ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ፤ እኔም ፡ የምሰጠው ፡ እንጀራ ፡ ሥጋዬ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ነው ። ስለ ፡ ዓለም ፡ ሕይወት ፡ እሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ያለኝ ---- ኢየሱስ ሰም ፡ መለሰ ፡ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ሥጋ ፡ ካልበላችሁ ፡ ደሙንም ፡ ካልጠጣችሁ ፡ እላንት ፡ ሕይወት ፡ የላችሁም ። ሥጋዬን ፡ የበላ ፡ ደሜን ፡ የጠጣ ፡ ለርሱ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ አለው ፤ እኔም ፡ አስነሣዋለሁ ፡ በኋላኛው ፡ ቀን » ሲል ፡ የዘረዘረውን ፡ በጸሎተ ፡ ኀሙስ ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ግብር ፡ አግብቶ ፡ ሲያበላቸው ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ « ---- ንሡ ፡ ብሉ ፡ ይህ ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ፤ ጽዋም ፡ ተቀብሎ ፡ አመሰገነም ፡ እንዲህ ፡ ሲልም ፡ ሰጣቸው ፤ ከዚህ ፡ ጠጡ ፤ ኹላችሁ ። ይህ ፡ ደሜ ፡ ነውና ፡ ለአዲስ ፡ ሥርዐት ፡ ስለ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሚፈስ ፡ ኀጢአት ፡ ለማስተስረያ ፡ » (ማቴ/ ፳፮ ፡ ፳፮—፴) ፡ ብሎ ፡ ፈጸመው ።

## ፰ኛ ፡ የቅዱስ ፡ ቍርባን ፡ አገልግሎት ።

በምሥጢረ፡ ቍርባንም ፡ የሚታይ ፡ አገልግሎት ፡ የማይታይ፡ጸጋ፡ ለሰው ፤ ወይኑ ፡ በጽዋዕ ፡ ኅብስቱ ፡ በፃሕል ፡ ሁኖ ፡ ካህኑ ፡ ሲጸልይበት ፡ ሲባርከው ፡ ሲያከብረው ፡ ሕዝቡም ፡ በአፍኣ ፡ ኹነው ፡ አሜን፡ ይኹን ፣ ይደረግ ፡ እያሉ ፡ ደጅ ፡ ሲጠኑ ፡ ይታያልና ። ኅብስቱ ፡ ሲለወጥና ፡ ሥጋ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡ ሲኾን ፤ ወይኑ ፡ ተለውጦ ፡ ደመ ፡ መለኮት ፡ ሲኾን ፤ ለሚቀበሉትም ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ ሲሰጥ ፡ አይታይም፡አይታወቅ ምም ፤ የኾነው ፡ ኹኖ ፡ ኅብስቱ ፡ ንጹሕ ፡ ምንም ፡ ያልተቀላቀለበት ፣ በንጹሕ ፤ የተሠራ ፡ ወይኑም ፡ ከንጹሕ ፡ ዘቢብ ፡ የተሠራ ፡ ምንም፡ ያል ተቀላቀለበት ፡ ኹኖ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፤ ካህኑ ፡ በሚገባ ፡ ጸሎቱን ፡ ማድረስ ፡ አለበት ፤ ይህ ፡ አፍኣዊ ፡ ጥንቃቄ ፡ ከውስጣዊ ፡ ጥንቃቄ፡ ጋራ፡ የተስማማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ኅብስቱ ፡ ወደ ፡ ሥጋ ፡ አምላክ ፡ ወይኑ ፡ ወደ ፡ ደመ ፡ አምላክ ፡ ተለውጦ ፡ የታሰበውን ፡ ዓላማ ፡ ፈጽሞ ፡ የሰው፡ልጅ፡ ኹሉ ፡ እርሱን ፡ ተቀብሎ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ አግኝቶ፡ ይኖራል ። ከወይኑ ፡ ግን ፡ ውሃ ፡ መጨመር ፡ ያስፈልጋል ፤ ምክንያቱም፡ክርስቶስ፡ በተሰቀለ ፡ ጊዜ ፡ ደም ፡ ብቻ ፡ አልፈሰሰም ፡ ውሃም ፡ ፈሷልና (ዮሐ/ ፲፱ ፴፬) ፪ኛም «ቶስሐ ፡ ማየ ፡ ምስለ ፡ ወይን» ፡ እንዲል ፡ ሊቃውንት ፡ ተስማምተውበታልና ። አገልጋዮችም ፡ ደንበኛ ፡ ምርጫ፣ ደንበኛ፡ሹመት፡ ያላቸው ፡ ካህናት ፡ ሊኾኑ ፡ ይገባል ፤ ማለት ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ቄስ ፤



ናቸው ። ዲያቆን ፡ ግን ፡ በረዳትነት ፡ ይቀድሳል ፡ እንጂ ፤ ዲያቆን ፡ ብቻውን ፡ ሊቀድስ ፡ አይችልም ።

## ፱ኛ ፤ የኅብስቱና ፡ የወይኑ ፡ መለወጥ ።

ሌሎች ፡ ምሥጢራት ፡ ሲደረጉ ፣ ምሳሌ ፡ ወይም ፡ እግዚአብሔር ፣ ለሚሰጠው ፡ ጸጋ ፡ ምክንያት ፡ እየሆኑ ፡ ነው፤ በምሥጢረ፡ቍርባን፡ግን፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፤ የምናቀርበው ፡ ኅብስትና ፡ ወይን ፡ ተለውጦ፡ራሱ፣ ሥጋ ፡ አምላክ ፡ ደመ ፡ አምላክ ፡ ይኾናልና ፤ ይህንም ፡ ራሱ ፡ ክርስቶስ ፡ ይህ ፡ ኅብስት ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ወይን ፡ ደሜ ፡ ነው ፡ እያለ ፡ በግልጥ ፡ አስተምሮዋልና ። ስለዚህም ፡ በእርግጥ ፡ የክርስቶስን ፡ ሥጋ ፡ የክርስቶስን ፡ ደም ፡ አምነን ፡ እንቀበላለን ። ሥጋውን ፡ ተቀብሎ ፡ ደሙን ፡ ሊተውት ፡ አይገባም ፤ ምክንያቱም ፡ ክርስቶስ ፡ ሲሰጥ ፡ ደሙን ፡ ለይቶ፣ አልተወውምና ፤ ደግሞም ፡ ሲያስተምር ፡ ሥጋዬን፡የበላ ፡ ደሜን፡የጠጣ፡ ሕይወት ፡ አለው ፡ ሲል ፡ ከኹለቱም ፡ መቀበል ፡ እንደሚገባ ፡ አረጋግጧል ፤ ሥጋውን ፡ ብቻ ፡ የተቀበለ ፡ ግማሽ ፡ ሕይወት ፡ እንዳለው ፡ እንጂ ፤ ፍጹም ፡ ሕይወት ፡ አለው ፡ ተብሎ ፡ አይቆጠርም ። ኅብስቱ ፡ ተለውጦ ፡ ሥጋ ፡ አምላክ ፡ ወይኑ ፡ ተለውጦ ፡ ደመ ፡ አምላክ ፡ ይኾናል ፡ ስንል ፤ በዐይነ ፡ ሥጋ ፡ ስንዳስሰው ፤ ስንቀምሰውም ፡ በአምሳለ፡ ኅብስትና ፡ ወይን ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በቄሱ ፡ ሥልጣን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ተለውጦ ፡ ሥጋ ፡ አምላክ ፡ ደመ ፡ አምላክ ፡ እንደሚኾን፣ እናምናለን ።

## ፲ኛ ፤ መቼ ፡ መቍረብ ፡ እንደሚገባ ።

ቅዱስ ፡ ቍርባን፡መንፈሳዊ ፡ ምግብ ፡ ነው ፤ ሥጋዊ ፡ ምግብ ፡ በየዕለቱ ፡ እንደሚያስፈልግ ፤ ይህም ፡ የሕይወት ፡ ምግብ ፡ በየዕለቱ፡ ያስፈልጋል ፤ ይህም ፡ ባይቻል ፡ በየሳምንቱ ፡ በተመቸ ፡ ጊዜ ፡ መቀበል፡ ያሻል። ምንም ፡ ሰው ፡ ኹኖ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ዐሳብ ፡ የተዋጠ ፡ ቢኾንና፡ ለመንፈሳዊ ፡ ነገር ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ቢያጣለት ፡ በየሳምንቱ ፡ ለመቀበል፡ባይችል፡ በወር ፡ በወሩ ፡ የግድ ፡ መቍረብ ፡ አለበት ። ይህም ፡ ባይኾን ፡ በ፫ ፡ ወር፣ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መቍረብ ፡ አለበት፤ማለት ፡ በዓመት ፡ ፫ ፡ ጊዜ፡ያልቈረበ፡

www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያን ፡ ተብሎ ፡ ሊጠራ ፡ አይገባውምና ። ይህንም፡ ሳይነግር ፡ ሳያ ስተምር ፡ በስም ፡ ካህን ፡ ነኝ ፤ አበ ፡ ነፍስ ፡ ነኝ ፤ የንስሐ ፡ ልጆች፡አሉኝ፡ የሚል ፡ ካህን ፡ ወዮለት ፡ እነርሱ ፡ አይገቡ ፡ የሚገቡትንም ፡ምእመናን፡ ይከለክላል ፡ ብሎ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ኹሉም ፡ ከእግዚአ ሔር ፡ መንግሥት ፡ ውጭ ፡ ይኾናሉ ። ለቊርባንም ፡ የተወሰነ ፡ ዕድሜ፡ ሊኖር ፡ አይገባውም ፤ ማለት ፡ በኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናችን፡ ሥርዐት ፡ ያመነ ፡ የተጠመቀ ፡ ኹሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባል ፡ የምሥጢር ፡ ኹሉ ፡ ተካፋይ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ ካመ ነበት ፡ ከተጠመቀበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስከሚሞትበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የምሥጢረ ፡ ቊርባንና፡ እንዲሁም ፡ የሌሎች ፡ ምሥጢራት ፡ ኹሉ፡ ተካ ፋይ ፡ መኾን ፡ አለበት ፤ ያለዚያ ፡ ግን ፡ አለሁ ፡ አለሁ ፡ ሲል ፡ የሞተ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ተዋሕዶት ፡ የሚኖር ፡ ሕይወት ፡ የለውም ። ስለ ዚህ ፡ በዕድሜ ፤ በዘር ፤ በሰዓት ፤ በዕለት ፡ እያመካኘ ፤ ምሥጢረ፡ ቊርባ ንን ፡ የሚከለክል ፡ የተሾመ ፡ አጋፋሪ ፡ ስለሌለ ፡ ክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ ይህ ፡ ዕድል ፡ አያምልጠው ።

## ፬ኛ ፤ የምሥጢረ ፡ ቊርባን ፡ ጥቅም ።

ቅዱስ ፡ ቊርባን ፡ ሰውንና ፡ እግዚአብሔርን ፡ አንድ ፡ ያደርጋል ፤ ያዋሕዳል፡ማለት ፡ የምንቀበለው ፡ ሥጋ ፡ የርሱ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ከርሱ ፡ ጋራ አንድነትን ፡ ይሰጣል ። የምእመናን ፡ ነፍስ ፡ በጣዕመ ፡ ጸጋ ፡ የተመላ ፡ ደስታን ፡ ሕይወትን ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገ ፡ ይኾናል ። ሥጋዊ ፡ ምግብ ፡ ለቁ መተ ፡ ሥጋ ፡ ለአጽንኦተ ፡ ሥጋ ፡ ምክንያት ፡ እንደሚኾነውና ፡ ደግፎ፡ ሰውን ፡ እንደሚኖር ፤ መንፈሳዊ ፡ ምግብ ፡ ምሥጢረ፡ ቊርባንም ፡በመ ንፈሳዊ ፡ ነገርና ፡ በመንፈስ ፡ ለመጽናት ፡ የበለጠ ፡ ይረዳናልና ። ጥም ቀት ፡ መወለድ ፡ ሜሮን ፡ መጽናት ፡ ሥጋና፡ ደሙን ፡ መቀበል ፡ ግን ፡ ተስማሚውን ፡ ምግብ ፡ መመገብ ፡ ነው።ሰውነት ፡ የሚጸናው ፡ አካልም ፡ የሚገዛው ፡ በምግብ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ ይህን፡በመመገቡ፡ አካለ ፡ ነፍስን ፡ ይገዛል ፤ ሕይወትን ፡ ገንዘብ ፡ ያደርጋል ፤ በጠቅላላ ውም ፡ ቊርባን ፡ የተፈተነ ፡ የሞት ፡ መድኀኒት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ እርሱን ፡ የበሉ ፡ የሞት ፡ ሞት ፡ አያገኛቸውም ።



# ምዕራፍ፲ ፡ ፮ ።

## ምስጢረ ፡ ንስሐ ።

ንስሐ ፡ ማለት ፤ ከጥምቀት ፡ በኋላ ፡ የተሠራውን ፡ ኀጢአት ፡ ማስ ተስረያ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታዘዘ ፡ በክርስቶስ ፡ የተመሠረተ ፡ ታላቅ ፡ ምስጢር ፡ ነው ። ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ በክርስቶስ ፡ እንዲያምን ፡ እን ዲጠመቅ ፡ የግዴታ ፡ ነው ። የጥምቀቱም ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ ኀጢአትን ፡ ለማስተሥረይ፡ ሲኾን፡ በየጊዜው ፡ በሚሠራው፡ከባድ፡ኀጢአት ፡ ሰው፡ ኹሉ ፡ እንዳይወድቅና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ልጅነት ፡ እንዳይለይ፤ በየጊዜ ውም ፡ የሚሰጠው ፡ ጸጋ፡እንዳይጓደልበት፡ ከልብ፡ መመለስ ፡ መጸጸት ፡ ንስሐ ፡ መግባት ፡ ለክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ ዋና ፡ ተግባሩ ፡ ነው ። ይህም ፡ ምስጢር ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ ምስጢራት ፡ የሚታይ ፡ አገልግሎት ፡ የማይ ታይ ፡ ጸጋ ፡ አለው ፤ ማለት ፡ ተነሳሒው ፡ ሲጸጸት ፡ ሲያለቅስ ፡ ሲናዘዝ፡ ቄሱ ፡ ለርሱ ፡ የተለየ ፡ የሥርየት ፡ጸሎት ፡ ሲጸልይ ፡ ይታያል ፤ ነገር ፡ግን፡ ተነሳሒው ፡ የኀጢአትን ፡ ሲያይ ፡ ስርየት፡ ልጅነቱ ፡ ሲመለስ ፤ ሀብተ ፡ ጸጋ ፡ ሲሰጠው ፡ አይታይምና ። እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ ከመውደዱ ፡ የተነሣ ፡ አንዱ ፡ እንኳ ፡ እንዳይጠፋ ፡ የበደለውን ፡ ኹሉ ፡ ይቅር ፡ ለማለት ፡ ታላቁን ፡ የምሕረት ፡ አዳራሽ ፡ ንስሐን ፡ ከፈተ ። ይህም ፡ ምስ ጢር ፡ ያለ ፡ ማቋረጥ ፡ እንዲሠራ ፡ ሥልጣኑን ፡ ለሐዋርያት ፡ «የመንግ ሥተ ፡ ሰማያትን ፡ መክፈቻ ፡ እሰጥኻለሁ ፡ በምድር ፡ ያሰርከው ፡በሰማይ፡ የታሰረ ፡ ይኾናል ፤ በምድርም ፡ የፈታኸው ፡ በሰማይ ፡ የተፈታ ፡ ይኾና ል ፡» (ማቴ/ ፳፮/፲፱ ፤ ፲፰፡ ፲፰)፡ ሲል ፡ ሰጠ ። ማንም ፡ ሰው ፡ ከሚመጣበት፡ የኀጢአት ፡ ቁራኘነትና ፡ ፍዳ ፡ ኹሉ ፡ ለመዳን ፡ የሚችለው ፡ ኀጢአ ቱን ፡ ለካህኑ ፡ የተናዘዘ ፤ ከልቡም ፡ የተመለሰ ፡ እንደ ፡ ኾነና ፡ ካህኑም ፡ የሚገባ ፡ ጸሎት ፡ ያደረገለትና፡ የበደለውን፡ ኹሉ ፡ ይቅር ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ነው ። «ለሰዎች ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ይቅር ፡ ብትሉ ፡ የሰማዩ ፡ አባ ታችሁም ፡ ይቅር ፡ ይላችኋል ፤ ለሰዎች ፡ ግን ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ይትር ፡ ባትሉ ፡ አባታችሁም ፡ ኀጢአታችሁን ፡ ይቅር ፡ አይላችሁም» (ማቴ/ ፮ ፡ ፲፬) ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፩ኛ ፤ የምሥጢረ ፡ ንስሓ ፡ አገልግሎት ።

ንስሓ ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ምስጢር ፡ ኹሉ ፡ በክርስቶስ ፡ እንደራሴ
ዎች ፤ በሐዋርያት ፡ ተከታዮች ፡ በኤጴስ ፡ ቆጶሱና ፡ በቄሱ ፡ አገልጋይ
ነት ፡ የሚፈጸም ፡ ምስጢር ፡ ነው ። ካህኑ ፡ ተነሳሒውን ፡ በክብር ፡ ተቀ
ብሎ ፡ ካነጋገረው ፡ በኋላ ፤ የተለየ ፡ የኀጢአት ፡ ስርየትን ፡ ሰጥቶ ፡
« እግዚአብሔር ፡ ይፍታህ ፡ » የሚል ፡ የምሕረት ፡ ቃልን ፡ ያሰማዋል ፤
በዚህ ፡ ጊዜ ፡ «ኀጢአቱን ፡ የተዋችሁለት ፡ ቀረችለት ፤ የያዛችሁበትም ፡
ሰው ፡ ተያዘችበት ፡ » (ዮሐ/ ፳ ፡ ፳፫) ፡ ብሎ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ተና
ገረው ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ኀጢአቱን ፡ ያስወግድለታል ።
ካህናት ፡ የሕይወት ፡ መሰላል ፡ ወይም ፡ ድልድይ ፡ ኹነው ፡ የእግዚአ
ሔርን ፡ ምሕረት ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፤ የሕዝቡን ፡ ንስሓና ፡ ልመና ፡ ወደ ፡
እግዚአብሔር ፡ የሚያደርሱ ፡ ናቸው ።

## ፪ኛ ፤ ንስሓና ፡ ኑዛዜ ።

ንስሓ ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በሠራው ፡ ጥፋት ፤ ባደረገው ፡ ስሕተት ፡
መፀፀት ፤ መቈርቈር ፤ ኹለተኛም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ እንደማያደርግ ፡ ሐሳ
ቡን ፡ ቆርጦ ፡ መጣል ፡ ማለት ፡ ነው ። ኑዛዜ ፡ ማለት ፡ ግን ፤ ሲሠራ ፡ ያላፈረ
ውን ፡ ኀጢአት ፡ ሲናገር ፡ ሳያፍር ፡ ለካህን ፡ መናገር ፤ መዘርዘር ፡ ልቡና
ውን ፡ ታዛቢ ፡ ምስክር ፤ አንደበቱን ፡ ከሳሽ ፤ እግዚአብሔርን ፡ ዳኛ ፡ አድ
ርጎ ፡ ራሱን ፡ መክሰስ ፡ መናገር ፡ ማለት ፡ ነው ። ምሥጢረ ፡ ንስሓ ፡
ሲባል ፡ ኑዛዜም ፡ የግድ ፡ ያስፈልገዋል ፤ ሁለቱም ፡ አይለያዩም ፤ ኹለቱ
የተያያዙና ፡ የተገናኙ ፡ ናቸው ፤ ያለ ፡ ኑዛዜ ፡ ንስሓ ፡ ከሐኪም ፡ ቤት ፡
ሂዶ ፡ በሽታውን ፡ እንደ ፡ ማይናገር ፡ ሰው ፡ ነው ። ኑዛዜም ፡ ያለ ፡ ንስሐ
ራስን ፡ ማታለል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ፍጹም ፡ ዋጋን ፤ ፍጹም ፡ ድኅነትን ፡ ለማግ
ኘት ፡ ኹለቱም ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ መገናኘት ፡ አለባቸው ። ሐኪም ፡ በሽ
ታውን ፡ ሰምቶ ፡ እርሱም ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ መርምሮ ፡ ለበሽታው ፡
ተቃዋሚ ፤ ለጤናው ፡ ጠበቃ ፡ የሚኾን ፡ መድኃኒት ፡ እንደሚሰጥ ፡ ኹሉ ፡
ወደ ፡ ካህንም ፡ የሄደ ፡ ተነሳሒ ፡ ሲታወቀው ፡ በድፍረት ፡ ሳይታወቀው ፡
በስሕተት ፡ የሠራውን ፡ ገልጦ ፡ መናገር ፡ አለበት ፤ የሠራውን ፡ ኀጢአት ፤
ያለውን ፡ ቊራኝነት ፡ ካልተናዘዘና ፡ ካልተፀፀተ ፡ «በሽታውን ፡ የሰወረ ፡



መድኀኒቱን ፡ አያገኝም ፡ » እንደ ፡ ተባለው ፡ ፍጹም ፡ ድኅነትን ፡ ሊያ
ገኝ ፡ አይችልም ።

ስለዚህ ፡ ፩ኛ ከልቡ ፡ መመለስ ፡ ባለፈው ፡ ኀጢአት ፡ መፀፀትና ፡
ኹለተኛም ፡ ይህን ፡ ከመሰለው ፡ ስሕተት ፡ እንዲጠበቅ ፡ ቊርጥ ፡ ሐሳብ ፡
ያደርጋል ። ይህ ፡ ንስሓ ፡ ይባላል ። ፪ኛ ፤ ይህን ፡ የሠራው ፡ ወዶ ፤ ለምዶ
ወይስ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ሥራውን ፡ ከነምክንያቱ ፡ ለካህኑ ፡ መዘርዘር ፡
መናዘዝ ፡ ይገባል ፤ ይህ ፡ ደግሞ ፡ ኑዛዜ ፡ ይባላል ። ካህኑ ፡ ንስሓውን ፡
ተመልክቶ ፡ ኑዛዜውን ፡ ሰምቶ ፡ በሰፊሕ ፡ እድ ፤ በሰቂለ ፡ አዕይንት ፤
በአንቃዕድዎ ፡ ሕሊና ፡ የንስሓን ፡ ጸሎት ፡ ሲያደርግለት ፡ የታመመውን ፡
ቃባም ፡ የያዘውን ፡ በግ ፡ ለይተው ፡ ሲያክሙ ፡ ሰንብተው ፡ በዳኝ ፡ ጊዜ ፡
ወደ ፡ መንጋው ፡ እንዲመልሱት ፤ ካህኑም ፡ ተነሳሒውን ፡ ፍጹም ፡ ጻድቅ ፡
ጤነኛ ፡ አድርጎ ፡ ከምእመናን ፡ ጋራ ፡ ይቀላቅለዋል ፡ ተከልክሎት ፡
ከነበረው ፡ ቅዱስ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እንዲሳተፍ ፡ ያደርገዋል ፤ ይህ ፡ የኀጢ
አት ፡ ስርየት ፡ ይባላል ። ንስሓ ፡ ዘማዊውን ፡ እንደ ፡ ድንግል ፤ ኀጢአ
ተኛውን ፡ እንደ ፡ ጻድቅ ፡ ያደርገዋል ፤ በዕንባ ፡ መታጠብ ፡ በባኛ ፡ እንደ ፡
መታጠብ ፡ ፍጹም ፡ ንጹሕ ፡ ያደርጋል ።

## ፫ኛ ፤ ለንስሓ ፡ የሚሰጡ ፡ ቅጣቶች ።

ለንስሓ ፡ የሚሰጠው ፡ ቅጣት ፡ «ቀኖና» ይባላል ። ይህም ፡ እንደ ፡
ካህኑ ፡ ተመልካችነት ፤ እንደ ፡ ኀጢአቱ ፡ ብዛት ፤ እንደ ፡ ተነሳሒው ፡
ብርታት ፡ ይሰጠዋል ። የጥንት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዳቈየችው ፡ ቀኖና ፡
የሚባለው ፡ ለተነሳሒው ፡ የሚሰጠው ጸሎት ፤ መጽሐፍ ፡ ቅዱስና ፤ ሌሎ
ችንም ፡ የጸሎት ፡ መጻሕፍት ፡ ማንበብ ፤ ቅዱሳት ፡ መካናትን ፡ እጅ ፡ መን
ሣት ፤ አስተብርኮ ፡ መያዝ ፤ ከንብረቱ ፡ ምጽዋት ፡ መስጠት ፤ ትህርም
ትንም ፡ መያዝ ፤ ይህንም ፡ የመሳሰሉ ፡ ትሩፋት ፡ በመሥራት ፡ ቅጣቱን ፡
በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ይፈጽማል ። ለተነሳሒው ፡ ቀኖና ፡ መስጠት ፡ እንዲገ
ባ ፤ «እላንትም ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ትጓደደላችሁ ፡ አላለቀሳችሁምም ፡ እንደሚ
ገባችሁ ፡ መጠን ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ ከላንት ፡ ይርቅ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡
ግን ፡ ከላንተ ፡ በሥጋ ፡ ብርቅ ፡ በመንፈስ ፡ ከላንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝ ፤ አሁንም ፡
ፈርጃለሁ ፤ ከላንተ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ነበርሁ ፡ ይህንን ፡ እንዲሁ ፡ በሥራ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ላይ ፡ - - - »(፩ኛ ፤ ቆሮ/፫ ፡ ፪—፫ ፤ ፪ኛ ፡ ቆሮ/፪ ፡ ፯—፰ ፤ ማቴ/፲፰ ፡ ፲፯ - - ) ሲል፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ይመሰክራል ።

ከዚህም ፡ ጋራ ፡ የጥንት ፡ አባቶች ፡ የሠሩት ፡ ሥርዐት ፤ ያስተማሩት ፡ ትምህርት ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ሲሠራበት ፡ ቈይቷልና ። ይህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘረውን ፡ በሚገባ ፡ መፈጸም ፡ ሰውም ፡ ወደ ፡ ንስሓ ፡ እንዲገሠግሥ ፡ መድከም ፡ የካህኑ ፡ ፈንታ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ካህን ፡ የኾነው ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ ምሥጢር ፡ ባይፈጽም ፡ ወዮለት ።

## ፬ኛ ፤ የንስሓ ፡ ጥቅሙ ።

ውሃ ፡ ያደፈውን ፡ ልብስና ፡ የሰውን ፡ አካል ፡ እንደሚያነጻ ፤ ያረጀውን ፡ ልብስ ፡ እንደሚያድስ ፤ ንስሓም ፤ የጐሰቈለውን ፡ ሰውነት ፡ ያረጀውን ፡ አካል ፡ ያድሳልና ። ንስሓ ፡ ፪ኛ ፡ እንደ ፡ መወለድ ፡ ወይም ፡ በየጊዜው ፡ እንደ ፡ መታደስ ፡ ነው ፤ ማለት ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ በየጊዜው ፡ ኀጢአት ፡ የሚሠራ ፡ በእርጅና ፡ ላይ ፡ እርጅና ፤ በበሽታ ፡ ላይ ፡ በሽታ ፡ ይጨምራል ፤ ንስሓ ፡ የማይገባ ፡ ሰው ፡ ክርስትናው ፡ ከንቱ ፡ ነው ፤ እንዲሁ ፡ በደሉ ፡ የበዛ ፡ ይሆናል ። ንስሓ ፡ የሚገባ ፡ ራሱንም ፡ ለአበ ፡ ነፍሱ ፡ የሚያስመረምር ፡ ሰው ፡ ኹልጊዜ ፡ የሐኪምን ፡ ርዳታ ፡ ከመጠየቁ ፡ የተነሣ በጤና ፡ በሰላም ፡ የሚኖር ፡ ሰውን ፡ ይመስላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፮

## ምሥጢረ ፡ ክህነት ።

ምሥጢረ ፡ ክህነት ፤ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምሥጢር ፡ የማሰር ፤ የመፍታት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሌላውንም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምሥጢራት ፡ ለመቀደስ ፤ ለማክበር ፤ ለመፈጸም ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፤ ክርስቶስ ፡ የሠራው ፤ የመሠረተው ፤ ከርሱም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ያለ ፡ ማቋረጥ ፡ የሚሰጥ ፡ ጸጋ ፡ ነው ። ይህንም ፡ ሥልጣን ፡ ክርስቶስ ፡ ለሐዋርያት ፡ በንፍሐተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰጥቷቸዋል ። ሐዋርያትም ፡ ለተከታዮቻቸው ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ እያስተላለፉ ፡ እስከኛ ፡ ድረስ ፡ ደርሷል ፤ ከኛም ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ እንዲሁ ፡ ያለ ፡ ማቋረጥ ፡ እንደሚሰጥ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ፤ ይህ



ንም ፡ ምሥጢር ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ መሠረተው ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ፡ (ማቴ/ ፲፩ ፤ ማቴ/፲፰ ፡ ፲፰ ፤ ም/ ፲፯፡ ፲፱ ፤ ዮሐ/፳ ፡ ፳፫) ስለ ፡ ምስጢረ ፡ ክህነት ፡ በገጽ ፡ ፷፪—፷፫ ፡ ተመልከት ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ፡

## ምሥጢረ ፡ ተክሊል ።

ተክሊል ፡ ማለት ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ተስማምተው ፡ በሚያደርጉት ፡ ጋብቻ ፡ ካህኑ ፡ የሚሠራው ፡ ጸጋን ፡ በረከትን ፡ የሚሰጥ ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ ነው ። ይህም ፡ ምሥጢር ፡ በሥጋዊ ፡ ጠባይ ፡ አስፈላጊነት ፡ ብቻ ፡ የተመሠረተ ፡ ሳይኾን ፤ መንፈሳዊ ፡ ዓላማ ፡ ያለው ፡ ለዘር ፡ መብዛት ፤ ለኑሮ ፡ ሕይወት ፡ እንዲገኝ ፤ ቅዱስ፡እግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ፡ ኹኖ፡ ያዘዘው ፡ የሠራው ፡ ምስጢር ፡ ነው ፡ ማለት፡ በመጀመሪያው ፡ በጥንተ ፡ ፍጥረት ፡ ሴትና ፡ ወንድ ፡ በጋብቻ ፡ ሥርዐት ፡ አንድ ፡ ኹነው ፡ መኖር ፡ እንዲገባቸው ፡ አዳምና፡ ሔዋንን፡ በመፍጠሩ፡ ይታወቃል ። (ዘፍ/፪፡፳፡ ፳፭) ። እንዲሁም ፡ ከ፫ቱ ፡ አካል ፡ አንዱ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ መጥቶ ፡ በመጀመሪያ ፡ ታምራቱን ፡ የገለጠበት ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ በአንዲት ሴት ፡ ኹነው ፡ በሚጋቡት ፡ በቅዱሱ፡ ጋብቻ ፡ ነው፡ (ዮሐ/፪፡፩—፲፩) ። እንዲሁም ፡ ሲያስተምር ፡ ፈሪሳውያን ፡ ሊፈታተኑት ፡ ጋብቻን ፡ እያቃለሉ ፡ ቢጠይቁት ፡ ጋብቻ ፡ ቅዱስ ፡ ሥራ ፡ እግዚአብሔር ፡ የባረከው ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈቀደው ፡ እንደ ፡ ኾነና ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ያደረገውን ፡ ማንም ፡ ለመለየት ፡ እንደማይችል ፡ በሰፊው ፡ አስረድቷል ። ኹሉ ፡ ማግባት ፡ እንደሚገባው ፤ ጋብቻም ፡ ክቡር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ሐዋርያት ፡ ለጠየቁት ፡ ጥያቄ ፡ « - - - ይህ ፡ ነገር ፡ ለሰዎች ፡ ኹሉ ፡ አይቻላቸውም ፡ ለተሰጣቸው ፡ በቀር ፤ ጃንደረባ፡ ሁነው ፡ ከናቶቻቸው ፡ የተወለዱ፡ ሰዎች ፡ አሉና ፡ ሌሎችም ፡ ሰዎች ፡ ሰልበው ፡ ጃንደረባ ፡ ያደረጓቸው ፤ ስለ ፡ መንግሥት ፡ ሰማያትም ፡ ሰውነታቸውን ፡ ጃንደረባ ፡ ያደረጉ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ። ማስተዋል ፡ የሚችል ፡ ግን ፡ ያስተውል» (ማቴ/ ፲፱ ፡ ፲፩) ፡ ሲል ፡ የሰጠው ፡ መልስ ፡ ያስረዳናል ፤ ማለት ፡ በንጽሕና ፤ በድንግልና ፡ ሊኖሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፈቀደላቸው ፡ ሰዎች ፡ በቀር ፡ ኹሉ ፡ በጋብቻ ፡ እንዲኖሩ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ያስረዳል ።

www.ethiopianorthodox.org

ምሥጢረ ፡ ተክሊልም ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ ምሥጢራት፥ የሚታይ ፡ አገልግሎት ፡ የማይታይ ፡ ጸጋ ፡ አለው። ሙሽራውና ፡ ሙሽራዪቱ ፡ ነጭ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፤ አክሊል ፡ ተቀዳጅተው ፡ ወደውም ፡ ለመጋባታቸው፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሲገቡ ፤ ካህኑም ፡ ስለ ፡ አንድነታቸው ፡ ሲጸልይባቸው ፥ ሲባርካቸው ፡ ቅዱስ ፡ ዘይትን ፡ ሲቀባቸው ፡ ይታያል ። እንዲሁም ፡ የተፈጥሮው ፡ ጋብቻ ፡ ሲቀደስ፡ ኹለት፡ የነበሩ ፡ በመንፈስ ፥ ቅዱስ፡ አንድ፥ ሲኾኑ ፡ በኹለቱ ፡ ላይ ፡ ፍጹም ፡ ፍቅር ፡ ሲያድርባቸው ፤ መለያየት ፥ ሲጠፋላቸው ፡ አይታይምና ።

## ፩ኛ ፤ የምሥጢረ ፡ ተክሊል ፡ አገልግሎት ።

ማንኛውንም ፡ ምሥጢር ፡ ካህናት ፡ እንደሚፈጽሙት ፡ ይህም ፡ እንዲሁ ፡ በካህናት፡ ሊፈጸም ፡ ይገባዋል። ካህኑ ፡ በበለጠ ፡ ሊያስብበት፡ ሊጠነቀቅበት ፡ የሚገባ ፡ በምሥጢረ ፡ ተክሊል ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፥ ለሌላው ፡ ምስጢር፡ ኹሉ ፡ ሕዝብ ፡ ተሳታፊ ፡ የሚኾን ፡ ጋብቻ ፡ የከበረ፡ እንደኾን ፡ ነው ። ጋብቻ ፡ ሲረክስ ፤ ዘር ፡ ሲቀነስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አብራ ፡ ትረክሳለች ፤ አባሎቿም ፡ ይቀነሳሉ ፤ ለመንግሥትም ፥ ጸጥታው ፡ ሊረጋገጥ ፡ ሰላም ፡ ጤንነት ፡ ሊገኝ ፡ አይችልም።ሰው ፡ ሕግ፡ የተላለፈውን ፡ ያህል ፡ ችግር ፥ መከራ፡ ፈተና ፡ ያገኘዋል ፤ ስለዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ኹሉ ፡ በሕግ ፡ እንዲጋባ ፤ በጋብቻውም ፡ ጊዜ ፡ ልዩ ፡ ጸሎት ፥ እንዲደረግለት ፡ መለያየታቸው ፡ እንዲጠፋ ፡ መድከም ፡ የካህኑ ፡ ዋና ፥ ተግባር ፡ ነው ።

## ፪ኛ ፤ ጋብቻ ፡ የማይፈታ ፡ ምሥጢር ፡ ስለ ፡ መኾኑ ።

የመጀመሪያው ፡ ሰው ፡ አዳም ፡ ሔዋንን ፡ ብቻ ፡ አግብቶ ፡ በደስታ ጊዜ ፡ በገነት ፤ በመከራም ፡ ጊዜ ፡ በምድረ ፡ ፋይድ ፡ አብረው ፡ ይኖሩ ፥ ነበር ። በምኞት ፡ ሚስት ፡ መፍታት ፡ የሚገባ ፡ ቢሆን ፡ አዳም ፡ በገነት፡ ሳለ ፡ ሔዋንን ፡ በፈታትና ፡ ባባረራት ፡ ነበር ፤ ወይም ፡ በመከራ ፡ ጊዜ ፡ መፍታት ፡ የሚገባ ፡ ቢኾን ፡ ምድረ ፡ ፋይድ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ባባረራት ፡ ነበር ፥ ወይም ፡ ብዙ ፡ ሴት ፡ ማግባት ፡ የሚገባ ፡ ቢኾን ፡ ሥላሴ ፡ ለአዳም ፡ ብዙ፡ ሴት ፥ መፍጠር ፡ በቻሉ ፡ ነበር ፤ ብዙ ፡ ወንድ ፡ ማግባት ፡ የሚገባም ፡



ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ለሔዋን ፡ ሥላሴ ፡ ብዙ ፡ ወንድ ፡ በፈጠሩላት ፡ ነበር ፤ ነገር፡ ግን ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ በአንድ ፡ ሴት ፤ አንዲት ፡ ሴትም ፡ በአንድ ፡ ወንድ፡ መኖር ፡ በደስታም ፡ በመከራም ፡ አብረው ፡ መኖር ፡ እንዲገባቸው ፡ ለሔዋን ፡ አዳምን ፡ ብቻ ፡ ለአዳምም ፡ ሔዋንን ፡ ብቻ ፡ ፈጠሩ ፡ (ዘፍ/፪፡፳—፳፫)። በኋላም ፡ ክርስቶስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሲያስተምር ፡ ይህኑ ፡ አጽንቶ ፡ «ኣላነበባችሁምን ፡ እግዚአብሔር ፡ አስቀድሞ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አድርጎ፡ አለም ፡ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ይተዋል ፡ ምሽቱንም ፡ ይከተላል ፤ ኹለቱም ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ይኾናሉ ። ኹለትም ፡ አይደሉም ፤ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ያደረገውን ፡ ሰው ፡ አይለየውም » (ማቴ/ ፲፱ ፡ ፫—፮) ። ሲል ፡ ከቶ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ እንደኾኑ ፡ ማንም ፡ ሊለያቸው ፡ እንደማይችልና ፡ እንደማይገባ ፡ በሰፊው ፡ ክርስቶስ ፡ አስረድቷል ። እንግዲያ ፡ ለምን ፡ ሙሴ ፡ አዘዘ ፡ የነውር ፡ ደብዳቤ ፡ እየሰጠ ፡ ሚስቱን ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ እንዲፈታ ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁት ፡ «ሙሴስ ፡ ስለ፡ ልባችሁ ፡ ደንዳናነት ፡ ሚስቶቻችሁን ፡ ትፈቱ ፡ ዘንድ ፡ አዘዛችሁ ፤ ከጥንት ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አልነበረም ። እኔም ፡ እላችሁኋለሁ ፡ ምሽቱን ፡ ያለ ዝሙት ፡ ነውር ፡ የፈታ ፡ ኹሉ ፡ ሌላይቱንም ፥ ያገባ ፡ ፈጽሞ ፡ አመነዘረ፤ የተፈታችውንም ፡ ያገባ ፡ ፈጽሞ ፡ አመነዘረ ። (ማቴ/ ፲፱ ፡ ፯—፱) ፡ ሲል፡ በሰፊው ፡ አስረድቷል ።

እግዚአብሔር ፡ በጥንተ ፡ ፍጥረት ፡ አንድ ፡ ያደረገውን ፡ ጋብቻ ፡ በበደል ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ማግባት ፤ ብዙ ፡ መፍታት ፡ መጣ ። ይህም ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ካመጣው ፡ ፍዳ ፡ ፩ኛው ፡ ነበር ፤ በኋላ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ኹኖ ፡ ሥጋ ፡ ለብሶ ፤ የረገመውን ፡ ማሕፀን ፡ ቀድሶ ፡ ያረጀውን ፡ አካል ፡ አድሶ ፡ የአዳምን ፡ ልጅነት ፡ መልሶ ፡ ጋብቻም ፡ እንዲሁ ፡ የጸና እንዲኾን ፡ አውጀአል ። ሐዋርያትም ፡ ይህን ፡ ተከታትለው ፡ ጋብቻ ፡ ቅዱስ ፡ ምሥጢር ፡ ሲኾን ፡ መፋታት ፡ እንደማይገባና ፡ የተፈታችውንም ፡ ማግባት ፡ እንደማይገባ ፡ በየምዕራፉ ፡ አስረድተዋል ። ባልና ፡ ሚስት ፡ ሊለያዩ ፡ የሚችሉበት ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ ሞት ፡ ብቻ፡ ነው ። ይህን ፡ የመሰለ ፡ የነፍስ ፡ ሞት ፡ ፩ኛው ፡ ወገን ፡ ዝሙት ፡ በሠራና ፥ እምነትን ፡ ባጕደለ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

### ፫ኛ ፤ የምሥጢረ ፡ ተክሊል ፡ ጥቅሙ ።

ዘርን ፡ ለማብዛት ፡ ጸጋን ፡ ለመስጠት ፡ የኹለቱን ፡ አንድነት ፡ ለማ ጽናት ፡ እምነትን ፡ ፍቅርን ፡ ለማሳደር ፡ ነው ። መጀመሪያ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አድርጎ ፡ ሲፈጥራቸው ፡ አንድ ፡ ኹነው ፤ ተረ ዳድተው ፤ ተደስተው ፡ እንዲኖሩ ፡ የኹሉም ፡ ገዥ ፤ የኹሉም ፡ አዛዥ ፤ ኹነው ፡ እንዲኖሩ ፤ ዘራቸው ፡ በዝቶ ፤ ምድርን ፡ መልተዋት ፡ እንዲኖሩ ፡ ነውና ፡ «እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ ፈጠረ ፤ በመልኩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መልክ ፡ ፈጠረው ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አድርጎ ፡ ፈጠራቸው ። እግዚአብሔ ርም ፡ ባረካቸው ፡ እግዚአብሔርም ፡ አላቸው ፤ ብዙ ፤ ተባዙም ፡ ምድ ንም ፡ ምሏት ፡ ግዟትም ፤ - - - - » (ዘፍ/፩፡ ፳፯—፳፰) ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለሚደረገው ፡ ጋብቻ ፡ የሚጸለየው ፡ ጸሎት ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነው ፤ ዋጋው ፡ ግን ፡ ሁለትነት ፡ ጠፍቶ ፡ አንድነት ፡ እንዲመሠረት ፤ ፍቅራ ቸው ፡ ፍጹም ፡ እንዲኾን ፤ የባልና ፡ ሚስትነታቸው ፡ እምነት ፡ እንዲ ከበር ፡ ነው ።

### ምዕራፍ ፡ ፯ ።

### ምሥጢረ ፡ ቀንዲል ።

ቀንዲል ፡ ወይም ፡ ቅብዐ ፡ ቅዱስ ፡ የተባለው ፡ ምሥጢር ፡ ከንጹሕ ፤ ወይራ ፤ ዘይት ፡ የተሠራ ፡ የሥጋንም ፡ የነፍስንም ፡ በሽታ ፡ የሚያርቅ ፡ የማዳን ፡ ኀይል ፡ ያለው ፡ ክርስቶስ ፡ የመሠረተው ፤ ሐዋርያት ፡ ያስተማ ሩት ፡ ምሥጢር ፡ ነው ። ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ መሠረተው ፡ ምንም ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ ምሥጢራት ፡ ግልጽ ፡ የኾነ ፡ ጽሑፍ ፡ እንኳን ፡ ባይገኝ ፡ ሐዋር ያትን ፡ እንዳዘዛቸው ፤ እነርሱም ፡ ዘይት ፡ እየቀቡ ፡ ብዙ ፡ ድውያንን ፡ እን ዳዳኑ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለው ፡ ጽሑፍ ፡ ያስረዳል ፤ «በወጡም ፡ ጊዜ ፡ አስ ተማሩ ፤ ንስሓ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ እጅግም ፡ ሰይጣናትን ፡ አወጡ ፤ በዘይ ትም ፡ ብዙ ፡ ድውያንን ፡ ቀቡ ፤ አዳኗቸውም » (ማር/፮፡ ፲፫) ። ሐዋርያት ፡ ግን ፡ ይጠቀሙበት ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ከላይ ፡ የዘረዘርነው ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ቅዱስ ፡ ያዕቆብ ፡ «ማንም ፡ ከላንተ ፡ ቢታመም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቀሳ ውስትን ፡ ይጥራ ፤ ይጸልዩበትም ፤ በዘይትም ፡ ይቅቡት ፤ በጌታ ፡ ስም ፡



የሃይማኖትም ፡ ጸሎት ፡ ድውዩን ፡ ትፈውሰዋለች ፤ ጌታም ፡ ያስነሣዋል ፤ ኃጢአትም ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ትሰረይለታለች - - - » (ያዕ/፭፡ ፲፬-፲፮) ሲል ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ሊጠቀሙበት ፡ አስፈላጊና ፡ ተገቢ ፡ መኾኑን ፡ በሰፊው ፡ ያስረዳል ።

የማዳን ፡ ኀይል ፡ አለው ፡ ስንል ፡ ከዘይቱ ፡ የተገኘ ፡ ኀይል ፡ አይደ ለም ፤ በእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፤ በቄሱ ፡ ሥልጣንና ፡ በጸሎቱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ኀጢአትን ፡ ቅሉ ፡ በማስተስረዩ ፡ ይታወቃል ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ቅዱስ ፡ ያዕቆብ ፡ «የእምነት ፡ ጸሎት ፡ በሽተኛውን ፡ ያድናል ፤ ኃጢአቱንም ፡ ያስ ተሰርያል ፡ » ሲል ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ በትሑት ፡ ሰብእና ፡ ኹነው ፡ አም ነው ፡ በጸለዩበት ፡ ዘይት ፡ ታምራት ፡ እንዲሠራ ፤ ኀይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደሚገለጥ ፡ ያስረዳል ።

### ፩ኛ የምሥጢረ ፡ ቀንዲል ፡ አገልግሎት ።

እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ምሥጢራት ፡ በካህን ፡ ብቻ ፡ የሚሠራ ፡ ምሥጢር ፡ ነው ። የተወሰነውን ፡ ጸሎት ፡ ካህኑ ፡ በሚገባ ፡ አድርሶ ፡ የበሽተኛውን ፡ አካል ፡ በመስቀል ፡ ምልክት ፡ ግንባሩን ፡ ፪ ፡ ፊቱን ፤ ሽንኅበቱን ፤ ቀኝና ፡ ግራ ፡ እጁን ፡ በውጭም ፡ በውስጥም ፤ ፪ ፡ እግሩን ፡ ቢቻል ፡ ታላላቅ ፡ ሕዋ ሳቱን ፡ ያለዚያም ፡ ለጊዜው ፡ ከሚያመው ፡ አካሉ ፡ ላይ ፡ ይቀባዋል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በሽታውም ፡ ይለቀዋል ፤ ኀጢአቱም ፡ ይሰረይለታል ። ደዌ ፡ ሥጋ ፡ ለደዌ ፡ ነፍስ ፤ ደዌ ፡ ነፍስም ፡ ለደዌ ፡ ሥጋ ፡ ይተርፋልና ፡ ማለት ፡ ንጽሕናቸውን ፡ ባለመጠበቃቸው ፡ ሰውነታቸውን ፡ በማጐስቈ ላቸው ፤ ነፍሳቸውንም ፡ አብረው ፡ ያጐስቍላሉ ፤ ሥጋቸው ፡ በታመመ ፡ ጊዜ ፡ ነፍሳቸው ፡ አብራ ፡ ትታመማለች ፤ ግን ፡ ንስሓ ፡ ገብተው ፤ ተመ ልሰው ፡ ምሥጢረ ፡ ቀንዲልን ፡ የተቀበሉ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ድኅነተ ፡ ሥጋ ንም ፡ ድኅነተ ፡ ነፍስንም ፡ ያገኛሉ ። የምሥጢረ ፡ ቀንዲልም ፡ የሚታይ አገልግሎትና ፡ የማይታይ ፡ ጸጋ ፡ አለው ፡ ማለት ፡ በሽተኛው ፡ ወድቆ ፡ ድኅነትን ፡ ደጅ ፡ ሲጠና ፡ በንጹሕ ፡ ዘይት ፡ ላይ ፡ የሀይማኖት ፡ ጸሎት ፡ ሲጸለይ ፡ ቄሱ ፡ ሲባርከው ፡ ከጸሎቱም ፡ በኋላ ፡ አካሉን ፡ ሲቀባው ፡ ይ ታያል ፤ ይህ ፡ የሚታይ ፡ አገልግሎት ፡ ይባላል ። ደዌ ፡ ሥጋውም ፡ ደዌ ፡ ነፍሱም ፡ ሲለቀውና ፡ ሲፈወስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ሲሰጠው ፡ አይ ታይምና ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ከደዌ ፡ ሥጋው ፡ ሲፈወስ ፡ ይታያል ፤ ይታ

www.ethiopianorthodox.org

ወቃል ። ኹኖም ፡ በሽታው ፡ ሲለቀው ፡ እንጂ ፤ እንዴት ፡ እንደ ፡ ዳነ ፡ ራሱ ፡ ቅሉ ፡ አያውቀውም ።

## ፪ኛ/ የምሥጢረ ፡ ቀንዲል ፡ ጥቅም ።

በምሥጢረ ፡ ቀንዲል ፤ የሥጋንና ፡ የነፍስን ፡ ድኅነት ፡ የኀጢአትን ፡ ስርየት ፡ የነፍስን ፡ መጽናናት ፡ እናገኛለን ። ምሥጢረ ፡ ቀንዲል ፡ ከጥምቀት ፡ በኋላ ፡ ለተሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ማስተስረያ ፡ ሲኾን ፡ ከምሥጢረ ፡ ጥምቀትና ፡ ከምሥጢረ ፡ንስሓ ፡ ጋራ ፡ ኀጢአት ፡ በማስተስረይ ፡ ድኅነትን ፡ በመስጠት ፤ ጸጋን ፡ በረከትን ፡ በማስገኘት ፡ ይገናኛሉ ። ኹኖም ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ምሥጢር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ካህኑ ፡ ይህንና ፡ ሌላውንም ፡ ምሥጢር ፡ በሚገባ ፡ መሥራት ፤ ምእመናንን ፡ ማንጻት ፤ ማጽናትም ፡ ዋና ፡ ተግባሩ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ቅዱስ ፡ ያዕቆብ ፡ በምዕራፍ ፡ ፭ ፡ በቍጥር ፡ ፲፩ ፡ የጻፈውን ፡ ጥብቅ ፡ ትእዛዝ ፡ መመልከትና ፡ መረዳት ፤ ተረድቶም ፡ መሥራት ፡ አለበት ።

# ምዕራፍ ፡ ፱ ።

## የወታደር ፡ ቄስ ።

ክህነት ፡ ቅዱስ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ የክህነት ፡ አገልግሎትም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዓላማ ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባለፉት ፡ ምዕራፎች ፡ አስረድተናል ። የካህኑ ፡ ሥራም ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ በትክክል ፡ እንዲያምንና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ እንዲኾን ፡ ማንጻት ፡ ማጽናት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንዲሁ ፡ አትተናል ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ የካህኑ ፡ ሥራ ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ነው ፤ ማለት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ በዘር ፡ በቀለም ፡ በነገድ ፡ በዕድሜ ፡ በሥራ ፡ ሲለያይ ፡ በእምነት ፤ በእግዚአብሔር ፡ ልጅነት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ሰብነት ፡ አንድ ፡ እንዲኾንና ፡ ኹሉም ፡ በርሱ ፡ እንዲያምን ፡ እርሱንም ፡ እንዲያመልክ ፡ ማስተማር ፡ የካህኑን ፡ ኀላፊነት ፡ የሚመለከት ፡ ነው ። በማንኛውም ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ድርጅት ፡ ብዙም ፡ ሥራ ፡ እንዳለ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ወታደርነትም ፡ ከሥራው ፡ ኹሉ ፡ ከድርጅቱም ፡ ከመንግሥቱም ፡ አቋም ፡ ኹሉ ፡ አንደኛው ፡ መኾኑ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ የፈቀደው ፡ ሕዝብ ፡ የወደደው ፡ በኤቲክሰም ፡ መንገድ ፡ የተፈ



ቀደ ፡ ነው ፤ ማለት ፡ ሕዝብ ፡ በሰላም ፡ እንዲኖር ፤ የሀገሩ ፡ ነጻነት ፡ እንዲጠበቅ ፤ መንግሥትም ፡ በሥልጣኑ ፡ ለመሥራት ፡ እንዲችልና ፡ መብቱ ፡ እንዲከበር ፤ ሕጉ ፡ እንዲታፈር ፡ የግድ ፡ ወታደር ፡ ያስፈልጋል ። ወደ ፡ ወታደርነትም ፡ የሚገቡ ፡ ሰዎች ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባሎች ፡ ስለ ፡ ኾኑና ፡ ሊኾኑም ፡ ስለሚገባቸው ፡ እነሱም ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትምህርት ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ልጅነት ፡ ሊለዩ ፡ አይገባቸውም ፤ ካህኑም ፡ ቸል ፡ ሊላቸው ፡ አይገባውም ፤ ስለዚህ ፡ ለነርሱ ፡ የተለየ ፡ ካህን ፡ አስፈለገ ።

ከእግዚአብሔር ፡ ልጅነት ፡ እንዳይወጡ ፤ ከሀይማኖት ፡ እንዲይናወጡ ፤ እንዲሁም ፡ በሥራቸው ፡ በኀላፊነታቸው ፡ የተጉና ፡ የነቁ ፡ እንዲኾኑ ፡ የወታደርነት ፡ ተግባርን ፡ የሚያስተምር ፡ የተለየ ፡ የወታደር ፡ ካህን ፡ የግድ ፡ ያስፈልጋል ፤ ስለዚህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ካህን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስተምራና ፡ አሠልጥና ፡ ኀላፊነቱን ፡ ገልጣ ፡ ከርሷም ፡ ጋራ ፡ በየጊዜው ፡ የሚያደርገውን ፡ ግንኙነት ፡ የማያቋርጥ ፡ አድርጋ ፡ መላክ ፡ አለባት ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከቤተ ፡ ሰቦቿ ፡ አንደኛውም ፡ እንኳን ፡ እንዲጐዳ ፡ የማትፈቅድ ፡ ስለ ፡ ኾነች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥበቃ ፡ መጠበቅና ፡ መከታተል ፤ እንደ ፡ የመፍቅዳቸውም ፡ መፈጸም ፡ ልዩ ፡ ተግባሯ ፡ ነው ።

## ፩ኛ ፤ የወታደር ፡ ቄስ ፡ ኑሮው ።

ይህ ፡ ካህን ፡ ከመንፈሳዊ ፡ ዕውቀቱ ፡ ሌላ ፡ የነባቢት ፡ ነፍስ ፡ ዕውቀትና ፡ (ሳይኮሎጂና ፡ ) ታሪክ ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልገዋል ። ምክንያቱም ፡ እነርሱን ፡ መስሎ ፡ እጅ ፡ እንዲያደርጋቸው ፡ ነው ። ኹሉን ፡ መስሎ ፡ ማስተማር ፡ እንዲገባ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ « ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ከሰው ፡ ኹሉ ፡ አርነት ፡ የወጣሁ ፡ ስኾን ፡ ራሴን ፡ ለኹሉ ፡ አስገዛሁ ፤ ኹሉን ፡ ረባ ፡ ዘንድ ። ከአይሁድም ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ አይሁዳዊ ፡ ኾንሁ ፤ አይሁድን ፡ ረባ ፡ ዘንድ ። ከኦሪት ፡ በታች ፡ ካሉት ፡ ጋራ ፡ ከኦሪት ፡ በታች ፡ እንዳለ ፡ ኾንሁ ፤ ከኦሪት ፡ በታች ፡ ያሉትን ፡ ረባ ፡ ዘንድ ። ሕግ ፡ ከሌላቸው ፡ ጋራ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ሌለኝ ፡ ኾንሁ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ አይደለሁም ፤ በክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ አለሁ ፡ እንጂ ፤ ሕግ ፡ የሌላቸውን ፡ ረባ ፡ ዘንድ ። ከደካሞች ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ደካማ ፡ ኾንሁ ፤ ደካሞችን ፡ ረባ ፡ ዘንድ ። ከኹሉ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ርሳቸው ፡ ኾንሁ ፤ ከርሳቸው ፡ ሰዎች ፡ ፈጽሜ ፡ አድን ፡ ዘንድ» (፩ኛ ቆሮ/ ፱ ፡ ፲፱—፳፪) ፡ ሲል ፡ ያስረዳል ። እን

www.ethiopianorthodox.org

ደዚሁም ፡ ሙሉ ፡ ጤንነት ፡ ሙሉ ፡ አካል ፡ የኾነ ፡ ሥራን ፡ የሚወድ ፡ ይህን ፡ ተግባሩን ፡ በሚገባ ፡ ለመፈጸም ፡ ቍርጥ ፡ አሳብ ፡ ያለውና ፡ በጣም ፡ ልጅ ፡ ያልኾነ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በጣምም ፡ ያልሸመገለ ፡ መኾን ፡ አለበት ። መኖሪያው ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ከወታደር ፡ ጋራ ፡ በካምፕ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚኾን ፡ እንደቡቱ ፡ የታረመና ፡ ቀልድ ፡ ጨዋታ ፡ ዋዛ ፡ ፈዛዛ ፡ የማያበዛ፤ ክብሩን ፡ የጠበቀ ፤ ልበ ፡ ሙሉ ፤ በሰላም ፡ ጊዜም ፡ ኾነ ፡ በጦርነት ፡ ልቡናን ፡ የሚያጽናና ፡ የሚያረጋጋ ፡ ሊኾን ፡ ይገባዋል ።

## ፬ኛ ፤ የወታደር ፡ ቄስ ፡ ሥራው ።

የወታደር ፡ ቄስ ፡ ሥራው ፡ ልክ ፡ እንደሌሎች ፡ ቀሳውስት ፡ ነው ። እርሱ ፡ ግን ፡ በተለይ ፡ በሥጋዊም ፡ በኩል ፡ ተግቶና ፡ ነቅቶ ፡ የሚኖር ፡ እነርሱ ፡ ካረፉበት ፡ ለማረፍ ፤ ከሄዱበት ፡ ለመሄድ ፡ ዝግጁ ፡ የኾነና ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ በጧት ፡ በማታ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ አንዳንድ ፡ ምዕራፍ ፡ እያነበበ ፡ ሰውነታቸውን ፡ ለንጉሥ ፡ ነገሥቱ ፤ በነፍሳቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ማገልገል ፡ እንዳለባቸው ፡ መንፈሳዊ ፡ ተግባርንም ፡ እንደ ፡ ችሎታቸው ፤ እንደ ፡ ቦታው ፡ አቀማመጥ ፤ እንደ ፡ ጊዜው ፡ አኳኋን ፡ መፈጸም ፡ እንለዳባቸው ፡ የሚነግርና ፡ የሚያስተምር ፡ መኾን ፡ አለበት ። በአካሉ ፡ (በሥጋው ፡ ) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የንጉሡ ፤ የሀገሩ ፤ የወገኑ ፡ እንደኾንና ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥቱን ፡ ማክበርና ፡ ትእዛዙን ፡ መፈጸም ፤ በነፍሱ ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማምለክ ፡ ለርሱም ፡ የሚገባውን ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ለማንኛውም ፡ ሰው ፡ እንዲገባ ፡ «የቄሣርን ፡ ለቄሣር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስጡ» ያለውን ፡ አምላካዊ ፡ ቃል ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ። ማለት ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ወታደር ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ከመንፈሳዊ ፡ ቢወጣ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ከወቀሳ ፡ የማይድን ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ አለበት ። መንፈሳዊም ፡ ሥራ ፡ ቢሠራ ፡ ፍላጎት ፡ ካለው ፡ ምንም ፡ የሚቸግረው ፡ እንደ ፡ ሌሊ ፡ የቆርኔሌዎስን ፡ ምሳሌ ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ማስረዳት ፤ «በቂሳርያ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ ስሙን ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ የሚሉት ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ኢጣሊቂ ፡ ለሚሏት ፡ ጭፍራ ፡ የኾነ ፡ መልካም ፡ የሚሠራና ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ከቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ ጋራ ፡ እጅግ ፡ ምጽዋት ፡ ለድኾች ፡ ያደረገ ፤ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚጸልይ ፡



ነበረ ፤ እርሱም ፡ ከቀኑ ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ገብቶ ፡ በግልጽ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ሆይ ፡ ሲል ፡ ጠራው ፤ እርሱም ፡ በተመለከተ ፡ ጊዜ ፡ ፈራ ፤ አለም ፡ ምንድር ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፤ መልአኩም ፡ አለው ፡ ጸሎትህ ፡ ምጽዋትህም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመታሰቢያ ፡ ወጣ» (የሐ/ ሥራ ፡ ፲ ፡ ፫—፴፬) ፡ ቀጥሎም ፡ ሥጋዊ ፡ ኀይልን ፡ ከመንፈሳዊ ፡ ጋራ ፡ አስተባብረው ፡ እየተዋጉ ፡ ጠላታቸውን ፡ ድል ፡ የነሡትን ፡ ነገሥታት ፡ መሳፍንት ፡ እንዲሁም ፡ ወታደሮችን ፡ ምሳሌ ፡ እያደረገ ፡ ማስተማር ፡ አለበት ።

ኢያሱ ፡ በሀይማኖት ፡ ጸንቶ ፡ የኢያሪኮን ፡ ምሽግ ፡ ቢከበው ፡ ምሽፈረሰ ፤ እንደ ፡ ሠምም ፡ ቀለጠ ፤ ሕዝቡም ፡ አለቁ ። (ኢያሱ ፡ ፮ ፡ ፳ ፤ ዕብ/ ፲፩ ፡ ፴)። ይህም ፡ ማለት ፡ ከሥጋዊ ፡ መሣሪያ ፡ ይልቅ ፡ መንፈሳዊ ፡ መሣሪያ ፡ የበለጠ ፡ ግዳጅ ፡ የሚፈጽም ፡ መኾኑን ፡ የሚስረዳ ፡ ነው። ሃይማኖት ፡ ተራራ ፡ ታፈልሳለች ፤ ዛፍ ፡ ታደርቃለች ፤ ሀይማኖታዊ ፡ ወታደርም ፡ ኹሉን ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል። እንዲሁም ፡ በሀይማኖት ፡ ጸንተው ፡ የሀገርንና ፡ የወገንን ፡ ፍቅር ፡ በሰፊው ፡ ይዘው ፤ ሕይወታቸውን ፡ ለሀገርና ፡ ለወገን ፡ ለውጠው ፡ ከጠላት ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ የነሡትን ፤ የጌዴዎንን ፤ የባርቅን ፤ የሶምሶንን ፤ የዮፍታሄን ፤ የዳዊትንና ፡ የሳሙኤልን ፡ እንዲሁም ፡ የሌሎችን ፡ መሳፍንትና ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ በሰፊው ፡ ማተትና ፡ ማስተማር ፡ (ማስረዳት) ፡ ይገባል። (መሣ/ ፯ ፡ ፲፩ ፡ ፱ ፡ ፯ ፡ ፲፫ ፡ ፳ ፤ ፲፪ ፡ ፯ ፤ ፪ኛ ፡ ሳሙ/ ፪ ፡ ፱ ) ።

በነፍስም ፡ በሥጋም ፡ ቈርጦ ፡ መዋጋት ፡ የሾመውን ፡ የሸለመውን ፡ ለማስደሰት ፡ ብቻ ፡ የሚጋደሉ ፡ እንዲኾኑ ፡ የተጋደለ ፡ ብቻ ፡ ዋጋውን ፡ ሽልማቱን ፡ እንደሚያገኝ ፡ አስፋፍቶ ፡ መንገርና ፡ ማስተማር ፡ ይገባል ። ስለዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ «ማንም ፡ ጭፍራ ፡ ኹኖ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ነገር ፡ የሚያስብ ፡ የለምና ፡ ጭፍራ ፡ ያደረገውን ፡ ደስ ፡ ያሰኝ ፡ ዘንድ ፤ የሚጋደልም ፡ ቢኾን ፡ አክሊል ፡ አይወስድም ፤ እንደሚገባው ፡ ካልተጋደለ ፡ - - - - » (፪ኛ ፡ ጢሞ/ ፪ ፡ ፬—፯ ፤ ፩ኛ ፡ ቆሮ/ ፱ ፡ ፳፯ ፡ ፩ኛ ፡ ጴጥ ፡ ፯ ፡ ፬)ይህን ፡ የተፈለገውን ፡ መልካሙን ፡ የበረከት ፡ ቃል ፡ ለማሰማትና ፡ መልካም ፡ ውጤትን ፡ ለመስጠት ፡ ካህኑ ፡ የነቃና ፡ የተጋ ፡ እንደቡቱም ፡ የረታ ፡ መኾን ፡ አለበት ፤ የወታደር ፡ ካህን ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ አለበት ። ስለዚህ ፡ ቤተ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያን ፡ ለርሱ ፡ ተስማሚ ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ እስክታወጣለት፡ እርሱ ፡ በዚህ ፡ እየተመራ ፡ ሊሠራ ፡ ስለሚችል ፡ የወታደር ፡ ቄስ ፡ ይህን፡ ይመልከት ። በዕረፍቱ ፡ ጊዜ ፡ ኹሉን ፡ መጐብኘትና ፡ የታመሙትን ፡ የቈሰሉትን ፡ ማጽናናት ፤ ቅዱስ ፡ ቊርባንን ፡ መስጠት ፤ ቅዱስ ፡ ቀንዲልን፡ መቀባት ፤ ንስሓውንም ፡ ተቀብሎ ፡ ሥርየት ፡ መስጠት ፤ የተጣሉም ፡ ቢኖሩ ፡ ማስታረቅና፡ በዕረፍትና ፡ በምቹ ፡ ጊዜ ፡ ኹሉም ፡ በሚሰበሰቡበት ፡ ጸሎተ ፡ ቅዳሴ ፡ ማድረግ ፤ የካህኑ ፡ የግዴታ ፡ ሥራው ፡ ነው ።

የወታደርነት ፡ ኑሮ ፡ ከሌላው ፡ ኑሮ ፡ በጣም ፡ የተለየ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ካህኑም ፡ እንደ ፡ ባሕርያቸውና ፡ እንደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዐት ፡ ለማስተዳደር ፡ እንዲችል ፡ በመካከለኛው ፡ መንገድ ፡ መምራትና ፡ አስታራቂ ፡ ሽማግሌ ፡ መኾን ፡ አለበት ። የወታደር ፡ ቄስ ፡ ልብስ ፡ እንደ ፡ ካፖርት ፡ ኾኖ ፡ የክፍለ ፡ ጦሩ ፡ ምልክት ፡ (መለዮ ፡ ) ሊኖረው ፡ ይገባል የልብሱ ፡ ቀለም ፡ ግን ፡ ጥቁር ፡ መኾን ፡ አለበት ፤ ኹኖም ፡ ቤተ ፡ ክህነቱና ፡ የጦር ፡ መሪዎች ፡ ሊወስኑት ፡ ይችላሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲ ፡

## የደብር ፡ መምህር ፡ (አለቃ ። )

በጥንት ፡ ክርስትና ፡ ጊዜ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሱ ፡ የሚቀድስበትና ፡ ሕዝቡ ፡ የሚሰበሰብበት፡ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካቴድራል ፡ ይባል ፡ ነበር ። ፍችውም፡ የኤጲስ፡ ቆጶሱ ፡ መንበር፡ ማለት፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነገሥታቱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መዓርግና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቃል፤ ኪዳን ፡ እየሰጡ ፡ ያከብሩት ፡ ነበር ። እየዋለና ፡ እያደረ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሲበዛና ፡ ቦታው ፡ ሲራራቅ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሱ ፡ እየዞረ ፡ መቀደስ ፤ መወደስ፡ ሥራው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ በየሄደበት ፡ አገር ፡ ሕዝቡ ፡ የሚሰበሰብበት ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ ታላላቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ እንዲሁ ፡ ካቴድራል ፡ (ደብር)፡ እየተባለ ፡ በብዛት ፡ ይከበር ፡ ጀመር ። እየቈየ ፡ ግን ፡ በየዘመኑ ፡ የተነሡ ፡ ነገሥታትና ፡ መኳንንት ፡ ጳጳሳትም ፡ ለስማቸው ፡ መታሰቢያ ፡ እንዲኾን ፡ ያሠሩት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲከበርላቸው ፡ በነገሥታቱ ፡ ፈቃድ ፡ ሕግ ፡ ወጥቶለትና ፡ ሥርዐት ፡ ተሠርቶለት ፡ ደብር ፡ ወይም ፡ ገዳም ፡ እየተባለ ፡ ተከብሮ ፡ ይኖራል። የዚህም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ በመ



ዓርግና ፡ በትምህርት ፡ በሌላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ከፍ ፡ ያሉ፡ካህናት ፡ እየተሾሙ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐቅድ ፡ ያስተዳድራሉ ። እንደነዚህ ፡ ያሉት፡መምህራን ፡ የኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ እንደራሴዎች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ኤጲስ፡ ቆጶሱ ፡ ለተሾመበት ፡ አገር ፡ በጠቅላላው ፡ እንደሚያስብ ፡ ኹሉ ፡ መምህራኑም ፤ ለደብሩ ፡ ስፋትና ፡ ለምእመናን ፡ ብዛት ፡ ለልቡናቸውም፡ መጽናናት ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መደርጀት ፡ ለወንጌል ፡ ስብከት ፡ ጊዜ ፡ ሳይወስኑ ፡ ተግተውና ፡ ነቅተው ፡ ይሠራሉ ።

ለተሾሙበት ፡ ቦታ ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ አገናኝ ፡ መሰላልና ፡ አስታራቂ ፡ ሽማግሌ ፡ እየኾኑ ፡ የማንጻትና ፡ የማጽናት፡ ሥራቸውን ፡ በትክክል ፡ መሥራት ፡ ቅዱስ ፡ ተግባራቸው ፡ ነው ፤ ለማንጻትና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ ለምእመናን ፡ ለመስጠት ፡ ክርስቶስ ፡ የመሠረታቸውን ፡ ምሥጢራተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሚገባ ፡ መፈጸምና ፡ የተለየ ፡ ጥበቃ ፤ የተለየ ፡ ጉብኝት ፡ እያደረጉ ፡ ምእመናንን፡ መከታተልም ፡ የነርሱ ፡ ኀላፊነት ፡ ነው ። የማይሰብክና ፡ የማያስተምር ፡ አስተዳዳሪ ፡ (ካህን ፡ ) ለሹመት ፡ አይገባም ፤ ምክንያቱም ፡ የክርስቶስ ፡ የምሕረቱና ፡ የድኅነቱ ፡ ሥራ ፡ በሰው ፡ ልቡና ፡ የሚመሠረተው ፡ በስብከትና ፡ ምሥጢራተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በትጋት ፡ በማደል ፡ ነው ። ስለ ዚህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃልም ፡ (ስብከት ፡ ) ከምሥጢራት ፡ አንዳንዱ ፡ ኹኖ ፡ የሚቈጠር ፡ በተለይም ፡ ከምሥጢረ ፡ ቊርባን ፡ ኹለተኛውን፡ ክፍል፡ ይዞ ፡ ይገኛል ፡ ማለት ፡ ስብከት ፡ ከቅዳሴ ፡ አንደኛው ፡ ክፍል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ሊታጐል ፡ የማይገባው ፡ ኹኖ ፡ እናገኛለን። በአካባቢው ፡ የሚገኙትን ፡ ሕዝቦች ፡ ደረጃቸውን፡ በመዓርግ፡ በጾታ ፡ እየለየ ፡ ተስማሚውን፡ ስብከት ፡ ማድረግ ፡ የካህኑ ፡ የግዴታ ፡ ተግባር ፡ ነው። ሌላም፡ መንፈሳዊ፡ ድርጅትና ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ማኅበር ፡ እንዲቋቋምና ፡ መልካም ፡ የሥራ ፡ ፍሬንም ፡ እንዲያስገኝ ፡ ምእመናንን ፡ ማነቃቃትና ፡ መምከር ፡ የመምህሩን ፡ ኃላፊነት ፡ የሚመለከት፡ ነው ። በውስጡ ፡ የሚገኙት ፡ ካህናት ፡ በሥራና ፡ በአሳብ ፡ እርሱን ፡ የሚመስሉና ፡ እርሱን ፡ የሚከተሉ ፡ መኾን ፡ አለባቸው ። አስተዳዳሪው ፡ እነርሱን ፡ መምከርና ፡ ማስተማር፡ እንዲሁም ፡ ለበጎ ፡ ሥራ ፡ ማነሣሣት ፡ ኹለተኛው ፡ ሥራው ፡ ይኾናል፡ ማለት ፡ ካህናት ፡ (መምህራን ፡ ) መንፈሳዊ ፡ አገልግሎታቸውን ፡ በሚ

www.ethiopianorthodox.org

ገባ ፡ ካልሰጡና ፡ ግዴታቸውን ፡ ካልፈጸሙ ፡ በሰበካው ፡ ያለውን ፡ ወይም፡ የያንዳንዳቸውን ፡ የንስሓ ፡ ልጆች ፡ ስም ፡ ከመልክ ፤ እንዲሁም ፡ ከሥራ ፡ ጋራ ፡ አጣርተው ፡ ካላወቁና ፡ ካልረዱት ፡ በቀር ፡ አስተዳዳሪው ፡ ብቻውን ፡ እሠራለሁ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ድምፁን ፡ ብቻ ፡ እንደሚሰጥ ፡ ከበሮ ፡ ኹኖ ፡ ይቀራል ።

ስለዚህ ፡ አስተዳዳሪውም ፡ ካህናቱም ፡ ምእመናንም ፡ በየተቻላቸው ፡ መጠን ፡ በተግባራቸው ፡ ጸንተው ፡ የኖሩ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ የሥራው ፡ ውጤት ፡ የተቃና ፡ ይኾናል ። ከኹሉም ፡ አስቀድሞ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጽዳት ፤ በአልባሳቱና ፡ በንዋየ ፡ ቅድሳቱ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ጉድለት ፡ ሁሉ ፡ እንዲዘጋጅና ፡ ሙሉ ፡ እንዲኾን ፡ ማሰቡ ፤ ማሠራቱ ፡ የርሱ ፡ ኀላፊነት ፡ ነው ። የጧት ፡ የማታው ፡ ጸሎት ፡ እንዲደረግ ፡ ሕዝቡ ፡ በጧት ፡ በማታ ፡ የመንፈሳዊ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ተካፋይ ፡ ለመኾን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲገሠግሡ ፡ ማስተማር ፡ ወደ ፡ ክርስትና ፡ የገቡትን ፡ በልዩ ፡ ጥበቃ ፡ ይዞ ፡ ሊገቡም ፡ የሚፈቅዱትን ፡ በልዩ ፡ ዘዴና ፡ ፀቅድ ፡ በመቀበል ፡ ስንቱ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ ኾኑና ፡ ስንት ፡ ክርስቲያንም ፡ በሞት ፡ እንደ ፡ ተለየ ፡ ለማወቅ ፡ መዝገበ ፡ ሕያዋን ፡ ወሙታን ፡ መዝገበ ፡ ክርስቲያን ፡ ወተክሊል ፡ አዘጋጋቶ ፡ ኹሉን ፡ እየመዘገበ ፡ በዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ለበላዩ ፡ ያቀርባል ። የሚቻለውን ፡ እየሠራ ፡ የማይቻለውን ፡ ለበላዩ ፡ ማስታወቅ ፤ ኑሮው ፡ የታወቀና ፡ በመንፈሳዊ ፡ ዓለም ፡ የተዋጠ ፤ ፍቅርን ፡ ሰላምን ፡ የተመላ ፡ ኹኖ ፡ ለላላው ፡ አብነት ፡ እንዲኾን ፡ ማስማተር ፡ ይገባል ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

## የምእመናን ፡ መንፈሳዊ ፡ ግዴታ ።

### ፩ኛ ፡ ኑሮዋቸው ።

ምእመን ፡ ማለት ፡ አምነ ፡ አመነ ፡ ካለው ፡ የወጣ ቃል ፡ ነው ። ምእመንም ፡ ማለት ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ በቃሉ ፡ የሚውል ፤ ተናግሮ ፡ የማይበድል ፤ ሀይማኖቱ ፡ የጸና ፤ ጐዳናው ፡ የቀና ፤ የተናገሩት ፡ ከሚጠፋ ፡ የወለዱት ፡ ይጥፋ ፤ ያመኑትን ፡ እምነት ፡ ከመለወጥ ፡ ሕይወት ፡ በሞት ፡ ይለወጥ ፡ ብሎ ፡ በተማረው ፡ ትምህርትና ፡ በተሠራለት ፡ ሥር



ዐት ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማመንና ፡ በማምለክ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልጋይና ፡ በችግሯ ፡ የሚረዳት ፡ የሚደግፋት ፡ ነው ። በዚህም ፡ ወንድና ፡ ሴት ፤ ትንሽና ፡ ትልቅ ፡ ሳይል ፡ አእምሮ ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ለድኅነተ ፡ ነፍስ ፡ የሚያበቃ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በአባልነት ፡ መደገፍ ፡ እንዳለባቸው ፡ ዐውቀው ፡ ኀይላቸውንና ፡ ገንዘባቸውን ፡ ጊዜያቸውንም ፡ ለዚህ ፡ ለበጎ ፡ ነገር ፡ የሚያውሉ ፡ ናቸው ።

### ፪ኛ ፡ መንፈሳዊ ፡ ግዴታቸው ።

ባንድ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ወይም ፡ ቄስ ፡ ውስጥ ፡ የሚተዳደሩ ፤ አንድ ፡ ዕምነት ፡ አንድ ፡ ሥርዓት ፡ አንድ ፡ ትምህርት ፡ ያላቸው ፡ ምእመናን ፡ አንድ ፡ ጠባቂ ፡ እንዳላቸው ፡ መንጋዎች ፡ ኹነው ፡ ፀሳባቸውና ፡ ኑሮዋቸው ፡ አንድ ፡ መኾን ፡ አለባቸው ። ወይም ፡ አንድ ፡ አባት ፡ እንዳላቸው ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ኹነው ፡ አንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አባታቸውን ፡ አስተዳዳሪያቸውን ፡ በሚገባ ፡ እንዲያከብሩና ፡ በትእዛዙም ፡ በምክሩም ፡ ጸንተው ፡ እንዲኖሩ ፤ ምእመናንም ፡ በካህኑ ፡ መሪነትና ፡ በካህኑ ፡ አስተዳዳሪነት ፡ እንዲኖሩ ፤ የርሱንም ፡ ፈቃድ ፡ እንዲፈጽሙ ፡ መንፈሳዊ ፡ ግዴታ ፡ አለባቸው ። ምእመናን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባል ፡ ናቸው ፡ ብለናል ፤ አንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ የኾነ ፤ ግማሹ ፡ ቆላ ፡ ግማሹ ፡ ደጋ ፡ ብሎ ፡ ቤቱ ፡ የሚደረጅበትን ፡ ተባብረው ፡ እንዲሠሩ ፡ በቆላም ፡ በደጋም ፡ የተሠራው ፡ ቤቱን ፡ እንዲያደረጀው ፤ የቤቱም ፡ ሸክም ፡ እንዲቀል ፡ ምእመናንም ፡ በአፍአ ፡ ያለውን ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ በሚገባ ፡ ሲፈጽሙ ፤ ካህናትም ፡ በአባልነታቸው ፡ ውስጣዊውን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎት ፡ በሚገባ ፡ ሲፈጽሙ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትደረጃለች ፤ ሸክሚም ፡ ይቀልላታል ።

አፍአዊ ፡ የምእመናን ፡ አገልግሎት ፡ የተባለው ፡ አስተዋጽኦ ፡ ማውጣትና ፡ ዐሥራቱን ፤ በኵራቱን ፡ መስጠት ፤ የካህናት ፡ ኑሮ ፡ የሚሻሻልበትን ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምትደረጅበትን ፤ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚቋቋምበትንና ፡ የተቋቋመውም ፡ ሥራውን ፡ በመልካም ፡ ፀቅድ ፡ የሚያከናውንበትን ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ በካህኑ ፡ ላይ ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ አለመናገርና ፡ የእግዚአብሔር ፡ እንደራሴ ፡ ኹኖ ፡ በነሱ

www.ethiopianorthodox.org

ላይ ፡ እንደ ፡ ተሾመ ፡ ዐውቆ ፡ ማክበር ፤ የሚናገረውም ፡ ቃልም ፡ ቅዱስ መጽሐፍን ፡ የተመረኰዘ ፡ ስለ ፤ ኾነ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አድርጎ ፡ መቀበል ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡ የሚነገረውንም ፡ የሐሰት ፡ ቃለ ፡ ክስ ፡ አለመቀበል ፤ የታመመ ፡ ሰው ፡ መድኀኒትን ፡ ሽቶ ፡ ወደ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ እንደሚሄድ ፤ ደዌ ፡ ሥጋም ፡ ደዌ ፡ ነፍስም ፡ በታመሙ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ካህን ፡ ሂዶ ፡ መናዘዝና ፡ ንስሓ ፡ መግባት ፤ ጸበል ፡ እንዲረጫቸው ፡ እንዲባርካቸው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መገሥገሥ ፡ «ኢየሱስም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ አላቸው ፤ ባለጤኖች ፡ ባለመድኀኒትን ፡ አይሹትም ፤ ድውዮች ፡ እንጂ ፡» (ማቴ / ፱ ፡ ፲፪) ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ።

ይህን ፡ ኹሉ ፡ ለመፈጸም ፡ እንኳ ፡ ባይቻል ፡ ጊዜ ፡ ወስኖና ፡ ቀን ፡ ለይቶ ፡ መጠየቅ ፤ ክርስቲያን ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባል ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፡ የማንኛውም ፡ ቅዱስ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ተሳታፊ ፡ መኾን ፡ አለበት ። በዓል ፡ በሚያከብርበትና ፡ ግብር ፡ በሚያበላበት ፡ ቤተ ፡ ሰቡንም ፡ ሰብስቦ ፡ በሚደሰትበት ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ተለዋዋጭ ፡ ኹኖ ፡ በሚያዝንበት ፡ ጊዜ ፡ በመካከሉ ፡ ካህኑ ፡ እንዲገኝ ፡ አስቀድሞ ፡ መጥራት ፤ ካህን ፡ ያልባረከውና ፡ ያልቀደ ሰው ፤ መንፈሳዊ ነገርም ፡ ያልተቀላቀለበት ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ለጊዜው ፡ ደስታ ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ ቢመስል ፡ ፈጥኖ ፡ ኀዘንን ፡ ያስከትላልና ። የክርስቲያን ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ፋና ፡ ጕልቶ ፡ የሚታይና ፡ የሚያበራ ፡ መኾን ፡ አለበትን ፤ ስለ ፡ ክርስቶስም ፡ እንደ ፡ መለከት ፡ በሚሰማ ፡ ድምፅ ፡ መጮህ ፤ ለኹሉ ፡ የተገለጠና ፡ የታወቀ ፡ ሥራን ፡ መሥራት ፡ ይገባል ። ኹልጊዜም ፡ በፈቃደ ፡ ካህን ፡ በምክረ ፡ ካህን ፤ ጸንቶ ፡ መኖር ፡ እንደሚገባ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘረ ፡ ቢኾንም ፡ ቅሉ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕፍት ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎት ፡ ያለባቸውን ፡ ግዴታ ፡ ምእመናን ፡ በሚገባ ፡ እንዲፈጽሙ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትጠይቃቸዋለች ።

# ማ ጠ ቃ ለ ያ

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መንፈሳውያን ፡ ጠባቂዎች ፡ የእግዚአብሔር ፡ እንደራሴዎች ፤ የሐዋርያት ፡ ተከታዮች ፤ የዓለም ፡ ብርሃናትና ፤ የምድር ፡ ጨው ፡ የተባሉ ፡ ካህናት ፤ ንባበ ፡ አእምሮ ፡ ያለውን ፡ በግ ፡ እንዲጠብቁ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተሾሙ ፡ ናቸው ። ይህንም ፡ ሥልጣን ፡ መጀመሪያ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሐዋርያት ፡ ሰጥቷል ፡ (ማቴ/፳፰ ፡ ፲፱—፳ ፤ ፱ ፡ ፴፯-፴፰ ፡ ፲ ፡ ፩—፵፪ ፤ ማር/፮ ፡ ፯—፲፫ ፤ ዮሐ/፲ ፡ ፩-፲፰) ፡ ሐዋርያትም ፡ ለተከታዮቻቸው ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ አስተላልፈዋል ። እነርሱም ፡ እንዲሁ ፡ እንዲያደርጉ ፡ አዘዋቸዋል ፤ ሥርዐትም ፡ ሠርተውላቸዋል ። ሐዋርያትም ፡ የጌታን ፡ ዓላማ ፡ ተከትለው ፡ እንደ ፡ ሠሩ ፡ ካህናትም ፡ የሊቀ ፡ ካህናታቸውን ፡ የክርስቶስን ፤ የአባቶቻቸውን ፡ የሐዋርያትን ፡ ፍለጋ ፡ እየተከተሉ ፡ መሥራት ፡ እንዳለባቸው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ለጢሞቴዎስና ፡ ለቲቶ ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ ያስረዳል ። (፩ኛ ፡ ጢሞ / ፩ ፡ ፲ ፤ ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፯) ። ካህናትም ፡ ይህን ፡ ሥልጣን ፡ በከንቱ ፡ ስላልተቀበሉና ፡ የሰጣቸውም ፡ ቀላል ፡ ሰው ፡ ስላይደለ ፤ እንዲሁ ፡ መብራት ፡ አብርተው ፡ ዕንቅብ ፡ እንዳይደፋበት ፡ ለኹሉ ፡ ይታይ ፡ ዘንድ ፡ በመቅረዝ ፡ እንዲሰቅሉት ፤ ካህናትም ፡ በሥልጣናቸው ፡ ተገልጸው ፡ እንዲሠሩበት ፤ በብርሃናቸው ፡ ዓለም ፡ እንዲጠቀምባቸው ፡ ክርስቶስ ፡ «እላንተ ፡ የዓለሙ ፡ ብርሃን ፡ ናችሁ ፤ አገር ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ተሠርታ ፡ መሰወር ፡ አይቻላትም ፤ መብራት ፡ አያበሩም ፡ በዕንቅብ ፡ ውስጥ ፡ ሊያኖሩት ፡ በመቅረዝ ፡ ላይ ፡ በቤት ፡ ላሉት ፡ ኹሉ ፡ እንዲያበራ ፤ እንዲሁም ፡ ብርሃናችሁ ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ይብራ ፤ ሥራችሁን ፡ አይተው ፡ የሰማዩን ፡ አባታችሁን ፡ ያመሰግኑት ፡ ዘንድ ፡ »እያለ ፡ አዟል ።

ይህንም ፡ ቃል ፡ ለመፈጸም ፤ ከኀላፊነትም ፡ ለመወጣት ፤ ሐዋርያትም ፡ የነርሱም ፡ ተከታዮች ፡ የብሱን ፡ በእግር ፡ ባሕሩን ፡ በመርከብ ፡ እየዞሩ ፡ አስተምረው ፡ ውጤታቸው ፡ አምሮላቸው ፡ ዋጋቸውን ፡ እንዳገኙ ፡ «መልካሙን ፡ ገድል ፡ ተጋደልኩ ፤ ሩጫዬንም ፡ ጨረስኩ ፤ ሀይማኖትንም ፡ ጠበቅሁ ፤ እንግዲህም ፡ የጽድቅ ፡ አክሊል ፡ ተዘጋጅቶልኛል ፤ እግዚአብሔር ፡ የሚሰጠኝ ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ ያ ፡ ጻድቅ ፡ ፈራጅ ፡ ለኔ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ መገለጡን ፡ ለሚወዱ ፡ ኹሉ ፡ እንጂ ፡ » (፪ኛ ፡ ጢሞ / ፬

www.ethiopianorthodox.org

፯—፰)፡ እያለ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ መስክሯል ። ማንኛውም ፡ ካህን ፡ ኹሉ ይህ ፡ ከባድ ፡ ኀላፊነት ፡ እንዳለበት ፡ ፀውቆ ፡ መሥራት ፡ ግዴታው ፡ ነው ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ለመወጣት ፡ ፩ኛ ፡ ሳያቋርጥ ፡ መስበክ ፡ ማስተማር ፡ ፪ኛ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምስጢራትን ፡ ለበቁት ፡ መስጠት ፡ ያልበቁ ትን ፡ ደግሞ ፡ እንዲበቁ፡ መሳብ ፡ ማለት ፡ መመለሻውን ፡ መንገድ ፡ ማሳ የትና ፡ መምራት ፡ ፫ኛ ፡ የተሰጣቸው ፡ መዓርግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ኹሉን ፡ በሚገባ ፡ ማስተዳደር ፡ ማለት ፡ ለያንዳንዱ ፡ ያለበትን ፡ ግዴታ፡ ገልጦ ፡ መንገር ፡ እንደ ፡ ዕውቀቱ ፡ እንደ ፡ ጤንነቱ ፡ ለርሱ ፡ የሚስማማ ውን ፡ ሥራ ፡ በመስጠት ፡ በለዘበ ፡ ቃል ፡ ማረጋገት ፡ እንዲሁም ፡ መም ከር ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ ሌላ ፡ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ ትምህርቱንና ፡ ሥርዐቱን ፡ አስ ተያየቱን ፡ ሁሉ ፡ በጽሑፍ ፡ እያደረገ፡ ለሕዝቡ ፡ ማዳረስ ፡ ከሌሎች፡ ሐዋ ርያት ፡ ይልቅ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ደከመ ፡ ሠራ ፤ ውጤቱም ፡ ከሌሎች ፡ ይልቅ ፡ የርሱ ፡ አማረ ፡ እርሱ ፡ ከሌሎቹ ፡ ሐዋርያት ፡ ይልቅ ፡ ፲፬ ፡ መል እክቶችን ፡ ጻፈ ፡ እነሆ ፡ የዓለም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምትጠቀምበት ፡ እርሱ ፡ በጻፈው ፡ ነው ። ይነስ ፡ እንጂ ፡ ሌሎች ፡ ሐዋርያትም ፡ መልእክ ቶች ፡ በመጻፋቸው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሠሩ ፡ ልንረዳበት ፡ ምን ፡ እንዳሉ፡ ልን ማርበት ፡ ቻልን ። ስለዚህ ፡ ካህን ፡ በድርሰቱ ፡ በተግሣጹ ፡ ጐልቶ ፡ ስለ ሚታወቅ ፡ ካህኑ ፡ ኹሉ ፡ የሚናገረውንና ፡ የሚሠራውን ፡ በጽሑፍ ፡ መግለጥ ፡ አለበት ። ካህን ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ ከቶ ፡ ለራሱ ፡ ብቻ ፡ ማሰብ ፡ የለበትም።የእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንዲጠበቁ ፡ ፕሮ ግራም ፡ አውጥቶና ፡ ሥርዐት ፡ ሠርቶ ፡ ማስተዳደር ፡ አለበት ፡ እንጂ ፤ እውነተኛ ፡ ጠባቂ ፡ ለበጎቹ፡ተላልፎ፡መሞትና ፡ ራሱን ፡ ንጹሕ፡ መሥ ዋዕት ፡ አድርጎ ፡ መስጠት ፡ ይገባዋል ። « ክርስቶስ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ቸር ፡ ጠባቂ ፡ ቸር ፡ ጠባቂ፡ ራሱን ፡ ስለ ፡ በጎቹ ፡ ይለውጣል » (ዮሐ / ፲ ፡ ፲፩፡) ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ በሥራም ፡ እንደ ፡ ፈጸመ ፤ ካህኑም ፡ ተላ ልፎ ፡ ስለ ፡ ምእመናን ፡ ቤዛ ፡ ኹኖ ፡ መሞት ፡ አለበት ።

ይህን ፡ ቅዱስ ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ካህኑ ፡ መጀመሪያ፡ በሃይማ ኖት ፡ የጸና ፡ በምግባር ፡ የቀና ፡ ሙሉ ፡ ጤንነት ፡ ሙሉ ፡ አካል ፡ ያለውና ፡ በሚገባ ፡ ተመርጦ ፡ በሚገባ ፡ የተሾመ ፡ ከመልካምና ፡ እውነ



ተኛ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ የተሾመ ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅንአ ትና ፡ ፍቅረ፡እግዚአብሔር፡እንዲሁም ፡ ፍቅረ ፡ ቢጽ ፡ ያለው ፡ መኾን ፡ አለበት ። ቢያዘው ፡ ሥራም ፡ የማይሰለች ፡ የማይመረር ፡ የራሱን ፡ አደራ ፡ በምእመናን ፡ ያለውን ፡ ከባድ ፡ ኀላፊነት ፡ ለመወጣት ፡ በአሳቡም ፡ በሥራ ውም ፡ የታመነና ፡ የነቃ ፡ የተጋ ፡ ሀብተ ፡ ክህነትም ፡ ገንዘቡ ፡ የኾነ ፡ ማለት ፡ መንፈሳዊ ፡ ስጦታና ፡ ፍጹም ፡ ጥሪ ፡ ያለው ፡ በበጎ ፡ አርአያነቱ፡ መልካም ፡ አብነትነትን ፡ የያዘ ፡ መኾን ፡ አለበት ። በተለይም ፡ ዛሬ፡ ኹሉ፡ ራሱን ፡ የቀበረበትና ፡ አንገቱን ፡ ያዘነበለበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ሕዝቡ ፡ ከልጓሚ ፡ እንደ ፡ ተፈታች ፡ በቅሎ ፡ በሚፋንንበት ፡ ወቅት ፡ በሃይማኖ ትና ፡ በምግባር ፡ ልጓምነት ፡ ገትቶ ፡ የሚይዝ ፡ ልበ ፡ ሙሉ ፡ የኾነ ፡ ካህን ፡ ያስፈልጋል ።

ዛሬ ፡ በኢሳይያስ ፡ ዘመን ፡ « ወደ ፡ ሕዝቤ ፡ ማንን ፡ እልካለሁ ? ማንስ ፡ ይሻለኛል » ? ብሎ ፡ እንደ ፡ ጠየቀበት ፡ አሁንም ፡ የሚጠይቅበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ በዚያን ፡ ጊዜስ ፡ ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ አቤቱ ፡ እኔ ፡ አለሁ ፡ የሚል፡ ድምጽ ፡ አሰምቶ ፡ መልስም ፡ ሰጥቶ ፡ ነበር ። ዛሬስ ፡ ማነው ፡ ለዚህ ፡ መልስ ፡ የሚሰጥ ፡ እንደ ፡ መልሱም ፡ የሚሠራ? (ኢሳይያስ፡ ፮ ፡ ፰)፡ አሁንም፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ያነበብንና ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተማርን ፡ ኹሉ ፡ ኢሳ ይያስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ አለሁና ፡ ላከኝ ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ መለሰ ፡ እውነተኛ ፡ አበ ፡ ነፍስ ፡ ለመኾን ፡ በዚህ ፡ ውስጥ ፡ የተዘረዘረ ውን ፡ ኹሉ ፡ ፈጽመን ፡ ዛሬም ፡ ኾነ ፡ ነገ ፡ ይህ ፡ ጥያቄ ፡ ሲቀርብልን ፡ እኔ ፡ አለሁ ፡ ብለን ፡ የቀና ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ያብቃን ።

አነሣሥቶ ፡ ላስጀመረን ፡ አስጀምሮም ፡ ላስፈጸመን ፡ ለእግዚአብ ሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ። አሜን ።



www.ethiopianorthodox.org

# በውስጡ ፡ የሚገኙ ።


ገጽ ።

መግለጫ .... .... .... .... .... .... .... .. ፲፫—፲፬

መቅድም .... .... .... .... .... .... .... ... ፲፭—፲፰

መግቢያ .... .... .... .... ........ .... .... ፲፱—፳፩

ክፍል ፡ ፩ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፍች ፡ .... .... .... ፳፫—፴፫

ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ .... .... .... .... .... ፳፫—፳፯

፩/ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሠረት ፡ .... .... .... .... ፳፬

፪/ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባሎች ፤ .... .... .... ፳፭—፳፮

፫/ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዓላማ ፤ .... .... .... .... ፳፮—፳፯

ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ መንግሥት ፤ .... .... .... .... .... ፳፯—፳፱

፩/ የመንግሥት ፡ ዓላማ ፡ .... .... .... .... . ፳፯—፳፰

፪/ የመንግሥት ፡ ሥራ ፤ .... .... .... .... .... ፳፰—፳፱

ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ የመንግሥት ግንኙነት ፤ ፳፱—፴፫

፩/ መሠረታቸው ፡ .... .... .... .... .... .... ፳፱—፴፩

፪/ ግንኙነታቸው፡ .... .... .... .... .... .... ፴፩—፴፫

ክፍል ፡ ፪ ፡ አበነፍስ ፡ (የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጠባቂ ፡) ወደክህነት ፡

ከመግባቱ ፡ በፊት ፤ .... .... .... .... .... ፴፭—፶፱

ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ የክህነት ፡ ፍች ፤ .... .... .... .... ፴፭—፵፩

፩/ የክህነት፡ ጅማሪ፡ .... .... .... .... .... ... ፴፮—፴፯

፪/ ክህነት ፡ ቅዱስ ፡ አገልግሎት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ .... .... ፴፯

፫/ ክህነት ፡ ከፍተኛ ፡ መዐርግ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ .... .... ፴፰


www.ethiopianorthodox.org

፬/ የክህነት፡ ችግር ፡ ........ ፴፰—፵፩
ሀ/ ውስጣዊ ፡ ችግር ፡ ........ ፴፱—፵
ለ/ አፍአዊ ፡ ችግር ፡ ........ ፵—፵፩
ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ለክህነት፡ መጠራት፡ ........ ፵፩—፵፯
ሀ/ ውስጣዊ ፡ ጥሪ ፡ ........ ፵፪—፵፬
ለ/ አፍአዊ ፡ ጥሪ ፡ ........ ፵፬—፵፯
ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ የካህኑ ፡ ትውልድ ፡ ........ ፵፯—፵፰
፩/ ከአዲስ ፡ አማኒ ፡ ውስጥ ፡ እንዳይሆን ፡ ........ ፵፯
፪/ ግብረ ፡ ገብነት፡ ከሌላቸው፡ ሰዎች፡ ውስጥ፡እንዳይሆን፡ ፵፯—፵፰
ምዕራፍ ፡ ፬፡ ክህነት፡ ከመቀበሉ፡ በፊት፡ ሊኖሩት ፡ የሚገባው ፡ ፵፰—፶፱
ሀ/ በመንፈሳዊነት ፡ (በሀይማኖት) ፡ በኩል ፡ ........ ፵፰—፶፪
፩/ ጽኑ ፡ እምነት ፡ ........ ፵፱
፪/ ፍጹም ፡ ፍቅር፡ ........ ፵፱—፶
፫/ ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ........ —፶
፬/ መንፈሳዊ ፡ ቅንዓት ፡ ........ ፶፩—፶፪
ለ/ በፍጹም ፡ ምግባር ፡ (በሞራል) ፡ በኩል ፡ ........ ፶፪—፶፯
፩/ ቅድስና ፡ ........ ፶፪—፶፫
፪/ አስተዋይነት ፡ ........ ፶፫—፶፬
፫/ በቂ ፡ ዕውቀት ፡ ........ ፶፬—፶፯
ሐ/ በስብአዊ ፡ ሁኔታው ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ መድን ፡ ፶፯—፶፱
፪/ ፩/ ሙሉ ፡ አካል ፡ ........ ፶፯—፶፰
፪/ ሙሉ ጤንነት ፡ ........ ፶፰
፫/ ልከኛ ፡ ዕድሜ ፡ ........ ፶፰—፶፱
ክፍል ፡ ፫ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጠባቂ ፡ ወደ ፡ ክህነት ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ፷፩—፸፩
ምዕራፍ ፡ ፩/ ክህነታዊ፡ ዝግጅት፡ ........ ፷፩—፷፪

ምዕራፍ ፡ ፪/ ፡ ሥልጣነ ፡ ክህነት ፡ ምሥጢር ፡ እንደሆነ ፡ ፷፪—፷፮
፩/ የምሥጢር ፡ አገልግሎት ፡ ........ ፷፫
፪/ ሀብተ ፡ ክህነት ፡ እንዴት ፡ እንደሚሰጥ ፡ ........ ፷፬—፷፮
ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ካህን ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በሹመት ፡ ቦታው ፡ ሲታይ ፡ ........ ፷፮—፷፯
ምዕራፍ ፡ ፬ ፡ የካህኑ ፡ ሥራ ፡ ........ ፷፯—፸፩
ክፍል ፡ ፬/ ፡ የካህኑ ፡ ጠባይና፡ ትሩፋት ፡ ........ ፸፫—፺፱
ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ የካህኑ ፡ ጠባይ ፡ ........ ፸፫—፸፯
፩/ መዐርጉን ፡ መጠበቅ ፡ ........ ፸፮
፪/ የመውጫውና ፡ የመግቢያው ፡ ጊዜ ፡ እንዲወሰን ፡ ........ ፸፯
፫/ ንግግሩ ፡ እንዲወሰን ፡ ........ ፸፯
፬/ ልብሱ ፡ የተለየ ፡ እንዲሆን ፡ ........ ፸፯
ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ የካህኑ ፡ ትሩፋት ፡ ........ ፸፯—፺፱
፩/ ንቃት ፡ ........ ፸፯—፸፱
፪/ ተጋድሎ ፡ ........ ፹—፹፪
፫/ ትህርምት ፡ ........ ፹፪—፹፬
፬/ ገንዘብ ፡ አለመውደድ ፡ ........ ፹፬—፹፯
፭/ ምጽዋት ፡ ........ ፹፯—፹፱
፮/ ትሕትና ........ ፹፱—፺
፯/ ገርነት ፡ ........ ፺—፺፪
፰/ ርኅቀ ፡ መዓት ፡ ........ ፺፪—፺፫
፱/ ኅዳጌ ፡ በቀል ፡ መሆን ፡ ........ ፺፫—፺፯
፲/ ንጽሕና ፡ ........ ፺፯—፺፰
፲፩/ ትዕግሥት ፡ ........ ፺፰—፺፱

www.ethiopianorthodox.org

ክፍል፡ ፭፡ መንፈሳዊው፡ጠባቂ፡(ካህኑ)፡ከተሾመ፡በኋላ፡ ፻፩—፻፳፩

ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ካህን ፡ ሊፈጽማቸው ፡ የሚገባው ፡ ተግባሮች ፡ ፻፩—፻፳፩

ሀ/ ስለ ፡ ራሱ፡ የሚፈጽማቸው፡ ........ ፻፩—፻፭

፩/ መንፈሳዊነት ፡ ........ ፻፩—፻፪

፪/ ጸሎት ፡ ........ ፻፪

፫/ ኑዛዜ ፡ ........ ፻፫

፬/ ትሩፋት ፡ ........ ፻፫

፭/ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ማንበብ ፡ ........ ፻፫—፻፬

መንፈሳዊ ፡ ትምህርትን ፡ መከታተል ፡ ........ ፻፬—፻፭

ለ/ ለምዕመናን ፡ ባደባባይ ፡ ሊፈጽማቸው ፡ የሚገባው ፡ ተግባሮች ፡ ........ ፻፭—፻፳፩

፩/ ባደባባይ ፡ ለሁሉ ፡ መስበክ ፡ ........ ፻፭—፻፳፩

፪/ ለምዕመናን፡ በግል፡ የሚፈጽማቸው፡ ........ ፻፲—፻፳፩

፫/ የድዕሜን ፡ ደረጃ ፡ በመለየት ፡ ........ ፻፲፪—፻፲፮

፬/ ጸታን፡ በመለየት፡ ........ ፻፲፮—፻፲፱

፭/ የዕውቀት ፡ ደረጃን ፡ በመለየት ፡ ........ ፻፲፱—፻፳

፮/ የመዐርግ ፡ ደረጃን ፡ በመለየት ፡ ........ ፻፳—፻፳፩

ክፍል ፡ ፮ ፡ የካህኑ ፡ የማንጸት ፡ ሥራ፡ ........ ፻፳፫—፻፺፫

ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ምሥጢራተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ........ ፻፳፫—፻፳፬

ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ምሥጢረ ፡ ጥምቀትን ፡ መስጠት፡ ........ ፻፳፬—፻፳፰

፩/ ለጥምቀት፡የሚያስፈልጉ፡ ........ ፻፳፭—፻፳፮

፪/ ለጥምቀት ፡ የተወሰነ ፡ ዕድሜ ፡ ........ ፻፳፮—፻፳፯

፫/ የጥምቀት ፡ ጥቅም ፡ ........ ፻፳፯—፻፳፰

ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ምሥጢረ ፡ ሜሮንን ፡ መስጠት ፡ ........ ፻፳፰—፻፳፱

፩/ የሜሮን ፡ አገልግሎት ፡ ........ ፻፳፰—፻፳፱

፪/ የሜሮን ፡ ጥቅም ፡ ........ ፻፳፱

ምዕራፍ ፡ ፬ ፡ ምሥጢረ ፡ ቁርባንን ፡ መስጠት ፡ ........ ፻፳፱—፻፴፪

፩/ የቅዱስ ፡ ቁርባን ፡ አገልግሎት ፡ ........ ፻፴

፪/ የኅብስቱና ፡ የወይኑ ፡ መለጥ ፡ ........ ፻፴፩

፫/ መቼ ፡ መቁረብ ፡ እንደሚገባ፡ ........ ፻፴፩—፻፴፪

፬/ የምሥጢረ፡ ቁርባን ፡ ጥቅም፡ ........ ፻፴፪

ምዕራፍ ፡ ፭ ፡ ምሥጢረ ፡ ንስሐን ፡ መስጠት ፡ ........ ፻፴፫—፻፴፮

፩/ የምሥጢረ ፡ ንስሐ ፡ አገልግሎት ፡ ........ ፻፴፬

፪/ ንስሐና ፡ ኑዛዜ ፡ ........ ፻፴፬—፻፴፭

፫/ ለንስሐ ፡ የሚሰጡ ፡ ቅጣቶች ፡ ........ ፻፴፭—፻፴፮

፬/ የንስሐ ፡ ጥቅም ፡ ........ ፻፴፮

ምዕራፍ ፡ ፮ ፡ ምሥጢረ ፡ ክህነትን ፡ መስጠት ፡ ........ ፻፴፮—፻፴፯

ምዕራፍ ፡ ፯ ፡ ምሥጢረ ፡ ተክሊልን ፡ መስጠት ፡ ........ ፻፴፯—፻፵

፩/ የምሥጢረ ፡ ተክሊል ፡ አገልግሎት ፡ ........ ፻፴፰

፪/ ጋብቻ ፡ የማይፈታ ፡ ምሥጢር ፡ ስለመሆኑ ፡ ፻፴፰—፻፴፱

፫/ የምሥጢረ ፡ ተክሊል ፡ ጥቅሙ ፡ ........ ፻፵

ምዕራፍ ፡ ፰ ፡ ምሥጢረ ፡ ቀንዲልን ፡ መስጠት ፡ ........ ፻፵—፻፵፪

፩/ የምሥጢረ ፡ ቀንዲል ፡ አገልግሎት ፡ ........ ፻፵፩

፪/ የምሥጢረ ፡ ቀንዲል ፡ ጥቅም ፡ ........ ፻፵፪

ምዕራፍ ፡ ፱ ፡ የወታደር፡ ቄስ ፡ ........ ፻፵፪—፻፵፮

፩/ ኑሮው ፡ ........ ፻፵፫

፪/ ሥራው ፡ ........ ፻፵፬—፻፵፮

ምዕራፍ ፡ ፲ ፡ የደብር ፡ መምህር ፡ (አለቃ) ........ ፻፵፮—፻፵፰

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ፡ የምዕመናን ፡ መንፈሳዊ ፡ ግዴታ ፡ ........ ፻፵፰—፻፶

ማጠቃለያ ፡ ........ ፻፶፩—፻፶፫


www.ethiopianorthodox.org

# ማረሚያ

| ገጽ ፡ | መሥመር ፡ | ስሕተቱ ፡ | ዕርማቱ ፡ |
|---|---|---|---|
| ፲፰ | ፴፪ | ፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ | ፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ |
| ፳፫ | ፫ | ከኸሉ ፡ | ከኹሉ ፡ |
| ፴፫ | ፳ | የሚቸገረው ፡ | የሚቸግረው ፡ |
| ፴፭ | ፪ | ምዕራፍ ፡ ፬ ፡ | ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ |
| ፴፱ | » | አቅሞን ፡ | አቅሞውን ፡ |
| ፵፪ | ፲፭ | በገጽ ፡ ፴፱ ፡ | በገጽ ፡ ፵፩ ፡ |
| ፵፯ | ፲፭ | ለኸሁም ፡ | ለኹሉም ፡ |
| ፵፯ | ፳፪ | ከመመልካሙ ፡ | ከመልካሙ ፡ |
| ፵፱ | ፲፫ | ማንኛው ፡ | ማንኛውም ፡ |
| ፵፱ | ፲፬ | ሊጀመር ፡ | ሊጀምር ፡ |
| ፵፱ | ፳፭ | ሰጥቶታልና ፡ | ሰጥቷልና ፡ |
| ፵፱ | ፴ | ባልጀራህን ፡ | ባልንጀራህን ፡ |
| ፶፩ | ፯ | ሕወቱን ፡ | ሕይወቱን ፡ |
| ፶፩ | ፳፬ | ከሌዋውንያን ፡ | ከሌዋውያን ፡ |
| ፶፪ | ፫ | በባልጀራው ፡ | በባልንጀራው ፡ |
| ፶፫ | ፩ | የሚሆንበቅን ፡ | የሚሆንበትን ፡ |
| ፶፫ | ፲፯ | ከካሽም ፡ | ከሳሽም ፡ |
| ፷፩ | ፲፫ | ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፵፭ ፡ | (፩ ፡ ጢሞ/ ፫ ፡ ፬—፭) |
| ፷፫ | ፩ | የሚጠሰው ፡ | የሚሰጠው ፡ |
| ፷፫ | ፲ | ብዕልና ፡ | ብልና ፡ |
| ፷፱ | ፲፰ | ሄዱ ፡ | ሂዱ ፡ |
| ፸፱ | ፲ | እንዳላለዋቂ ፡ | እንዳላዋቂ ፡ |
| ፺፩ | ፲፫ | ለባልጀራው ፡ | ለባልንጀራው ፡ |
| ፺፩ | ፲፬ | ግዲታ ፡ | ግዴታ ፡ |
| ፺፭ | ፳፭ | አሕዝብ ፡ | አሕዛብ ፡ |

www.ethiopianorthodox.org

# ማ ረ ሚ ያ

| ገጽ | መሥመር ፡ | ስሕተቱ ፡ | ዕርማቱ ፡ |
|---|---|---|---|
| ፻፮ | ፲፮ | እንዲትስ ፡ | እንዴትስ ፡ |
| ፻፰ | ፳፪ | ይናኸል ፡ | ይሆናል ፡ |
| ፻፰ | ፳፮ | ሁልጊዚ ፡ | ሁልጊዜ ፡ |
| ፻፰ | ፳፰ | ሲሰበክ ፡ | ሲሰብክ ፡ |
| ፻፰ | ፳፱ | እናስታምራለን ፡ | እናስተምራለን ፡ |
| ፻፲ | ፲ | ከእግሩ ፡ | ከንግግሩ ፡ |
| ፻፲ | ፲፰ | ኩኖ ፡ | ኹኖ ፡ |
| ፻፲፫ | ፬ | ትች ፡ | ትችት ፡ |
| ፻፲፮ | ፳ | እንዲያግጉ ፡ | እንዲያድጉ ፡ |
| ፻፲፯ | ፬ | አይቀነሰስም ፡ | አይቀነስም ፡ |
| ፻፳፩ | ፫ | ለየበትም ፡ | የለበትም ፡ |
| ፻፳፬ | ፲፯ | አውሰቦ ፡ | አውስቦ ፡ |
| ፻፳፯ | ፳፬ | ለእያንዳንዳችሁ ፡ | እያንዳንዳችሁ ፡ |
| ፻፴፪ | ፳፪ | እንደሚኖር ፡ | እንደሚያኖር ፡ |
| ፻፵፫ | ፱ | ምኽ ፡ | ምኽጉ ፡ |
| ፻፵፫ | ፲፪ | የሚስረዳ ፡ | የሚያስረዳ ፡ |
| ፻፵፯ | ፲፰ | አንዳንዱ ፡ | እንዳንዱ ፡ |
| ፻፵፰ | ፲፯ | አዘጋጋቶ ፡ | አዘጋጅቶ ፡ |
| ፻፵፰ | ፳ | ለላላው ፡ | ለሌላው ፡ |
| ፻፵፱ | ፳፪ | ይቀልለታታል ፡ | ይቀልለታል ፡ |
| ፻፶ | ፳ | አለበትን ፡ | አለበት ፡ |

www.ethiopianorthodox.org